አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሙዩኒኬሽን ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የድኅረ ምረቃ ትምህርት መርሐ ግብር

# የዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራት ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ጥናት

በ

ፍፁም ኩራባቸው

በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለአርት ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ

ታህሣስ 2006 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሙዩኒኬሽን ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የድኅረ ምረቃ ትምህርት መርሐ ግብር

# የዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራት ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ጥናት

በ

ፍፁም ኩራባቸው

በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለአርት ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ

አማካሪ

ሰላማዊት መካ (ረዳት ፕሮፌሰር)

ታህሣስ 2006 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሙዩኒኬሽን ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የድኅረ ምረቃ ትምህርት መርሐ ግብር

# የዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራት ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ጥናት

በ

ፍፁም ኩራባቸው

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

[illegible]

አማካሪ ፊርማ

ዘሪሁን አስፋው

የውስጥ ፈታኝ ፊርማ

ሥርጋው ገላው

የውጭ ፈታኝ ፊርማ

ILS LIBRARY
ADDIS ABABA

# ማውጫ

ይዘት ገጽ

ምስጋና ....................................................................................................................................i
የፎቶ መግለጫ ............................................................................................................................ii
የዝዋይ ሐይቅና ደስያት ካርታ ..........................................................................................iii
አጠቃሎ ..................................................................................................................................iv

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ

1.1. የጥናቱ ዳራ ...................................................................................................................1
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ...............................................................................................5
1.3. የጥናቱ አላማ .................................................................................................................5
1.4. የምርምር ጥያቄዎች .......................................................................................................6
1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ ..............................................................................................................7
1.6. የጥናቱ ወሰን ...................................................................................................................7
1.7. የጥናቱ ዘዴ .....................................................................................................................8
1.7.1. የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ..................................................................................................8
1.7.2. የመረጃ አተናተን ዘዴ ................................................................................................11
1.8. ለጥናቱ የተደረገ ቅድመ ዝግጅትና የመስክ ክንውን ........................................................15
1.9. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ አቅጣጫዎች ...............................................16
1.9.1. ያጋጠሙ ችግሮች ......................................................................................................16
1.9.2. የተወሰዱ የመፍትሄ አቅጣጫዎች ...............................................................................16

ምዕራፍ ሁለት

ክለሳ ድርሳናት

2.1. ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ .........................................................................................................17
2.1.1. የተረክ ንድፈ ሀሳብ ....................................................................................................17
2.1.1.1. የተረክ ዓይነት ........................................................................................................20
2.1.1.2. ተረክን የማጥናት ጠቀሜታና የአጠናን ሂደት ............................................................22

2.1.2. የቁሳዊ ባህል ጥናት ....................................................................................25
2.1.2.1. የቁሳዊ ባህል ዓይነት ....................................................................................26
2.1.2.2. ቁሳዊ ባህልን የማጥናት ተግባርና የአጠናን ስልቱ ....................................................................................26
2.1.3. የዝርው ቃላዊ ተረክና የቁሳዊ ባህል ዝምድና ....................................................................................28
2.2. የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ....................................................................................30
2.2.1. በትምህርት ክፍሉ የተሰሩ ጥናቶች ....................................................................................30
2.2.2. ከክፍለ ትምህርቱ ውጪ የተሰሩ ጥናቶች ....................................................................................35
ምዕራፍ ሶስት
የዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራት አጠቃላይ ገለጻ
3.1. የደስያቱ መልክዓ ምድራዊ ሁኔታና ስያሜ ....................................................................................42
3.1.1. የደብረ ጽዮን ደሴት....................................................................................43
3.1.2. የደብረ አብርሃም ደሴት....................................................................................44
3.1.3. የጌቴሴማኒ ደሴት....................................................................................45
3.1.4. የገሊላ ደሴት....................................................................................45
3.1.5. የደብረ ሲና ደሴት....................................................................................46
3.2. የደስያቱ የቅርሶች ማዕከልነት ....................................................................................46
3.3. የገዳምና አድባራቱ መመስረት ....................................................................................48
ምዕራፍ አራት
የዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራት ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ትንተና
4.1. ከዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራት የተሰበሰቡ ተረኮች ትንተና ....................................................................................55
4.1.1. የገዳምና አድባራቱን ጥንታዊነትና ታሪካዊነት የሚዘክሩ ተረኮች ....................................................................................57
4.1.2. የዝዋይ ሐይቅን ገዳምና አድባራት ቅድስና የሚሰብኩ ተረኮች ....................................................................................72
4.1.2.1. የስፍራው ሥያሜዎች የፈለቁባቸው ተረኮች ....................................................................................73
4.1.2.2. በደስያቱ የተለያዩ ገቢረ ተአምራት መፈጸም ....................................................................................79
4.1.2.3. የሐይቁ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም መባረክ ....................................................................................81
4.1.2.4. የዝዋይ ደስያት በሃይማኖቱ ተጋዳሊያን መትበኘት ....................................................................................82
4.1.3. ለመልክዓ ምድራዊ አፈጣጠር ምክንያት የሚሰጡ ተረኮች ....................................................................................84

4.1.4. የቦታውን ክብር ከፍ የሚያደርጉ ተረኮች ....................................................................86

4.1.5. የስፍራውን ሉዓላዊነት የሚያስከብሩ ተረኮች ..........................................................87

4.2. በዝዋይ ደሴት ገዳምና አድባራት የተገኙ ቁሳዊ ባህሎች ትንተና ..........................................91

4.2.1. ሃይማኖታዊ አስተምህሮን ለማቆየትና ለማጽናት የሚያገለግሉ ቁሶች...................................91

4.2.2. ስርዓተ አምልኮን ለመፈጸም የሚያገለግሉ ቁሶች............................................................102

4.3. ከዝዋይ ደሴት ገዳምና አድባራት የተገኙ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ተዛምዶ .............................113

ምዕራፍ አምስት

መደምደሚያ

5.1. ማጠቃለያ ...............................................................................................117

5.2. የይሁንታ ሃሳብ ..........................................................................................118

ዋቢ ጽሑፎች .................................................................................................119

አባሪዎች

ከስፍራው የተሰበሰቡ ተረኮች

ለመረጃ ሰጪዎች የቀረቡ ጥያቄዎች

የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር መግለጫ

ከስፍራው የተወሰዱ ፎቶዎች

የተለያዩ ደብዳቤዎች

# ምስጋና

የዚህ ጥናት ስኬት የብዙ ባለውለታዎቼ እጅ ያለበት ቢሆንም ከሁሉም በፊት ግን ውድ ጊዜያቸውን ሰውተው ጠቃሚ ምክሮችን በመለገስ፣ አስተያየቶችን በመስጠትና መረጃዎችን በመጠቆም ለስራው መሳካት ከፍተኛውን አስተዋጽኦ ያደረጉልኝ አማካሪና መምህሬ የሆኑት የሰላማዊት መካ የላቀ ነውና ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ በዚህ የሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት መስከ የማስተርስ ዲግሪዬን እንድማር ድጋፍ የሆነኝን የሰመራ ዩኒቨርሲቲን እና ትምህርቱን በማስተማርና ለጥናቱ የገንዘብ ድጎማ በማድረግ የረዳኝን አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን አመሰግናለሁ፡፡

ጥናቱን ተግባራዊ ለማድረግ ስንቀሳቀስ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የቤተክህነት ሀላፊዎች፣ የምስራቅ ሸዋና አርሲ ሀገረ ስብከት ሃላፊዎች፣ የዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራት አገልጋዮች እንዲሁም ነዋሪዎች በሙሉ ትብብራቸው አልተለየኝምና ከፍ ያለ ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡ በተለይም በቃለ መጠይቅ መረጃ በመስጠትና ታሪካዊ ስፍራዎችን በማሳየት የተባበሩኝን (በአባሪ ክፍል ስማቸው የተጠቀሱትን) የደስያቱን ነዋሪዎች ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

የጥናቴን ረቂቅ ጽሑፍ በማየት ወንድማዊ አስተያየታቸውን የለገሱኝ የክፍል ጓደኞቼ (ሰራዊት፣ ዳዊት፣ አዲስና ውቤ)፣ የከምን አደረስከው ጥያቄያቸውና አይዞህ ባይነት ድጋፋቸው ያልተለየኝ ወዳጆቼ (ነብይ፣ ገብሬ፣ ምንውዬ፣ ሳሚ፣ ዘላለም፣ የሽዋስ፣ ማናዬ፣ ጌች፣ ዝናሽ፣ ወርቅዬ፣ የሚ፣ ጸዲና ጺዮን) ባለውለታዎቼ ናቸውና አመሰግናለሁ፡፡ በመጨረሻም የሁልጊዜ ድጋፋችሁ የማይነጥፍብኝ ውዷ እናቴ እመቤት ሁሪሳ፣ አባቴ ኩራባቸው ባልቻ፣ ወንድሞቼ (ደጀኔ፣ ሙሌ፣ አድዬና ጌች) እንዲሁም እህቶቼ (ገንዘብና ዮድ) በሀሳብ ከእኔ ጋር ነበሩና ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡

# የፎቶ መግለጫ

ርዕስ ጉዳይ                                                                 ገጽ


ፎቶ 1 በደብረ ጽዮን ገዳም ሙዚየም ውስጥ የሚገኙ መጻሕፍት ...............................93

ፎቶ 2 ከደብረ ሲና ማርያም ከተገኙ ሁለት አርባዕቱ ወንጌል የተወሰዱ ስዕሎች ...............................96

ፎቶ 3 የማውጫ ስንጠረዥ፣ ምዕራፍና ቁጥር መለያና የሀረግ አጣጣል ማሳያ ስዕሎች ...............................97

ፎቶ 4 በደብረ ሲና ደሴት መጻፉን የሚያሳይ የአርባዕቱ ወንጌል ክፍል ...............................98

ፎቶ 5 የማህበረሰቡ የወንጀለኛ መቅጫ እግረ ሙቅ ...............................101

ፎቶ 6 አምስቱ የዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራት ...............................104

ፎቶ 7 ታቦተ ጽዮን አርፋበታለች የሚባለው ቦታና የደብረ አብርሃም ቤተክርስቲያን ...............................106

ፎቶ 8 ከዝዋይ ደሴት ቤተክርስቲያን ጋር የዛዮች መኖሪያ ቤት ሲነጻጸር ...............................106

ፎቶ 9 በደብረ ጽዮን ገዳምና በቦጨሳ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ ስዕሎች ...............................107


ፎቶ 10 በደብረ ጽዮን ገዳም የአቡነ በጸሎተ ሚካኤልና ሙሴ ጽላትን ሲረከብ የሚያሳይ ስዕል ...............................107

ፎቶ 11 ዝዋይ ደስያት ውስጥ የሚገኙ ዋሻዎችን ለማሳየት የቀረበ ...............................108

ፎቶ 12 የደስያቱን ጥንታዊ መስቀሎች የሚያሳዩ ...............................109

ፎቶ 13 የደስያቱን እርከን ስራ የሚያሳይ ...............................112

ፎቶ 14 የዛይ ማህበረሰብን የሽመና ስራ የሚያሳይ ...............................112




የዝዋይ ሐይቅና ደሴቶች ካርታ

( Source, Google earth and Ethio_GIS)

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት በዝዋይ ሐይቅ ውስጥ በሚገኙ ገዳምና አድባራት ላይ የተካሄደ ሲሆን ተረክና ቁሳዊ ባህል የሚባሉትን የፎክሎር ዘውጎች የሚመለከት ነው፡፡ ጥናቱ ይዞት የተነሳው ዋና ዓለማም ተረኮቹን በመተንተንና ቁሳዊ ባህሎቹን በመመርመር ያላቸውን ተምሳሌት ማሳየት ነው፡፡ ለርዕሰ ጉዳዩ መመረጥ እንደ ዓብይ ምክንያት የሚጠቀሱት የዝዋይ ሐይቅ ደሴያት በታሪክ አጋጣሚ የታቦተ ጽዮን መሸሸጊያ መሆናቸውን የሚናገሩ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች በመኖራቸውና እንደ ገዳማውያን ሕይወታቸው ከገዳምና አድባራቱ ጋር ያቆራኙ ማህበረሰቦች በመገኘታቸው ሲሆን በአጠቃላይ አብያተ ክርስቲያናቱ የሀገራችን የታሪክ መዛግብት ሆነው የቆዩ መሆናቸውን የሚያስረግጡ መረጃዎች በስፍራው መታየታቸው ነው፡፡ የጥናቱ ዓላማ ግብ እንዲመታና የምርምር ጥያቄዎች ምላሽ እንዲያገኙ ከቤተ መጻህፍት፣ ከመረጃ መረብና ከመስክ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ መረጃዎቹም የተሰበሰቡት በቃለመጠይቅና በምልከታ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ነው፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎች በመቅረጸ ድምጽ፣ በፎቶና ቪዲዮ ካሜራ እንዲሁም ማስታወሻ ደብተር ተይዘዋል፡፡

በመስኑ መሳሪያዎቹ አማካይነት የተሰበሰቡት ቃላዊ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች በተረክ ንድፈ ሀሳብ፣ በቁሳዊ ባህል ጽንሰ ሀሳብ ሞዴሎችና ተረክንም ሆነ ቁሳዊ ባህልን ለመፈከር በሚያስችለው የተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ተተንትነው በገለጻና ትንተና ስልት ተብራርተው ቀርበዋል፡፡ በውጤቱም ተረኮቹ የገዳምና አድባራቱን ጥንታዊነት የመዘከር፣ ታሪካዊነትን የመናገር፣ ቅድስናን የመሰበክ፣ የስፍራውን ክብር ከፍ የማድረግ፣ ሉዓላዊነትን የማስከበር ተግባር እንዳላቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡ ቁሳዊ ባህሎቹ በአገልግሎታቸው ለስርዓተ አምልኮ መፈጸሚያ፣ ሃይማኖታዊ አስተምሮን ለማጽኛ የሚያገለግሉና ከአሪት አምልኮ ጋር የተያያዙ ሲሆኑ የተረኮቹን እውነትነት ለማረጋገጥ በማስረጃነት የቆሙ መሆናቸውም ታይቷል፡፡ የቃላዊ ተረኮቹና ቁሳዊ ባህሎቹ መረጃዎች አጠቃላይ አንድምታ የዝዋይ ደሴያት ገዳምና አድባራትን የጥባባዊ እሴት መገለጫ፣ የመንፈሳዊ እሴት ነጸብራቅ፣ የታሪካዊ ድርጊት ዘጋቢ፣ ባህላዊ ገጽታን ማሳያና የዘመንን መንፈስ መፈተሻ መሆንም በጥናቱ ተመልክቷል፡፡ የዛይ ማህበረሰብን የፈጠረ የማንነት ስንስለትም ተንጸባርቆባቸዋል፡፡ በአጠቀላይ ተረኮቹና ቁሳዊ ባህሎቹ የሃይማኖት ማጽኛና የማንነት መገንቢያ መሳሪያ መሆናቸው በጥናቱ ተመልክቷል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

የእምነት ርዕዮት በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ትልቅ ስፍራ እንደሚሰጠው የሚያጠያይቅ ጉዳይ አይደለም፡፡ እምነት የሰው ልጅ ህልውና የተመሰረተበት፣ ልዕለ ተፈጥሮ ኃይላትን የያዘ የሃይማኖት መገለጫ ነው፡፡ የአንድን ማህበረሰብ እምነት በሚታዊ ተረኩና ቁሳዊ ባህሉ ላይ ተመስርቶ ማጥናት ደግሞ ለዓለም ያለውን አስተሳሰብ (ርዕዮተ ዓለም)፣ የእምነት ስርዓቱን፣ ከየት መጣነቱን፣ ከልዕለ ተፈጥሮ ጋር ያለውን ሕብረትና ሥነ-ልቦናዊ ማንነት በጥልቀት ለመረዳት ያስችላል፡፡ ከዝዋይ ደሴያት ገዳምና አድባራት ጋር የተያያዙ ተረኮችንና ቁሳዊ ባህሎችን ማጥናት ያስፈለገውም ከዚህ የተነሳ ነው፡፡

ጥናቱ በአምስት ምዕራፎች ተደራጅቶ የቀረበ ነው፡፡ ምዕራፍ አንድ መግቢያ፣ የጥናቱን ዳራ፣ አነሳሽ ምክንያት፣ ዓላማ፣ የምርምር ጥያቄ፣ ጠቀሜታ፣ የመረጃ መሰብሰቢያና መተንተኛ ዘዴ እንዲሁም የጥናቱን ወሰን ያካተተ ነው፡፡ ምዕራፍ ሁለት ንድፈ ሀሳባዊ ጉዳዮችና ተዛማጅ ጥናቶች የተዳሰሱበት ክፍል ሲሆን ምዕራፍ ሶስት የዝዋይ ደሴያት ገዳምና አድባራት አጠቃላይ ገለጻ በሚል ርዕስ የዝዋይ ደሴያት ገዳምና አድባራትን ስያሜ፣ ታሪክ፣ ቅርስና መልክዓ ምድራዊ ሁኔታ የሚያስቀኝ ትንተና የቀረበበት ነው፡፡ ምዕራፍ አራት በቃለመጠይቅና ምልከታ ዘዴ ከአምስቱ ደሴያት የተሰበሰቡት ትረካዎችና ቁሳዊ ባህሎች ተተንትነው የቀረቡበት ክፍል ነው፡፡ የመጨረሻው ምዕራፍ ማጠቃለያና የይሁንታ ሃሳቦችን ይዟል፡፡ ዋቢ ጽሑፎችና አባሪዎች ምዕራፍ አምስትን ተከትለው ቀርበዋል፡፡

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

የፎክሎር የጥናት መስክ ሰፊ በመሆኑ በስሩ ተከፋፍለው የሚጠኑ በርካታ ጉዳዮች ይነሳሉ፡፡ ሚት፣ አፈታሪክ፣ ተረት፣ ቀልድ፣ ድግምት፣ ምርቃት፣ ምህላ፣ ሰላምታ፣ ዳንስና ተውኔት፣ ጥበብና እምነት ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ እነዚህን ፎክሎራዊ ጉዳዮች በዘውግ ከፋፍሎ ማቅረብ ለአጠናን የሚመች ነው፡፡ ሆኖም በዘውጎቹ መካከል ድንበር ማስመር ይቻላል ወይ? የሚለውን ጥያቄ መመለስ ከባድ እንደሚሆን ላሪ ዳኒኤልሰን ሲያስረዱ ሃይማኖታዊ ፎክሎርን ሀገረሰባዊ

ተረክ፣ መዝሙር፣ እምነት፣ ስርዓት፣ ንዋየ ቅድሳት፣ መድኃኒት፣ ጥበብ፣ ሥነ ምግባርና አለባበስን በመሳሰሉ ዘውጎች ልንከፍላቸው እንችላለን። ነገር ግን ሃይማኖታዊ ፎክሎር ሃይማኖታዊና ከዚያ ውጪ የሆኑ ባህላዊና ልማዳዊ የሆኑ ጉዳዮችን የምንመረምርበት መነጽር በመሆኑና እንደ እምነትና ሌሎች ትውፊታዊ ጉዳዮች ያሉት በሁሉም ዘውጎች ሊንጸባረቁ ስለሚችሉ ክፍፍሉን አስቸጋሪ ያደርገዋል (Danielson, 52-53) ይላሉ።

ሪቻርድ ዶርሰን "Folklore and Folk Life" በሚለው መጽሐፋቸው ይሄንን ጉዳይ ሲያጠናክሩ ፎክሎርን በዘውግ ከፋፍሎ ማጥናት አስቸጋሪ ነው። ሃይማኖታዊ ፎክሎርን በዘውግ ስንከፋፍል የሃይማኖት ማዕከላዊ ጉዳይ የሆነው እምነት እንቅፋት ይፈጥራል። ሆኖም ሃይማኖታዊ ፎክሎርን ጉዳያችን አድርገን ስንነሳ የትኩረት አቅጣጫ መሆን የሚገባው የሃይማኖት ማዕከላዊ ጉዳይ የሆነው እምነት ሳይሆን ተረክ ነው (Dorson, 219)።

ሃይማኖታዊ ፎክሎርን በተለያዩ ዘውጎች ከፋፍሎ ማጥናት ከባድ ቢሆንም የሰው ልጅ ተረኮች ላይ ተመርኩዞ እምነትን ስለሚመሰርት (መጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ቅዱስ ቁርዓኑ እንዲሁም የአይሁዳኑ ቅዱስ መጽሐፍ ቶራ የተረኮች ስብስብ ነውና) ተረኮቹን በማጥናት በዚያ ውስጥ የታዩ ጥበባዊ ድርጊቶቹን ማሳየት ይቻላል። የአንድን ማህበረሰብ አስተሳሰብና የህይወት ፍልስፍና ብሎም የእምነት ስርዓት፣ ከፈጣሪ ጋር ያለውን ሕብረት፣ ከየት መጣነቱንና ሥነ-ልቦናዊ ማንነቱን በጥልቀት ለመረዳት ሃይማኖታዊ ትውፊቱን (ተረክና ቁሳዊ ባህልን) እንደ አማራጭ መውሰድ ይቻላል። የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫም በገዳምና አድባራት መመስረት ምክንያት በተገኙ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ላይ የሆነው ከዚሁ በመነጨ ሀሳብ ነው።

የኢትዮጵያ አድባራትና ገዳማት ከመንፈሳዊ አገልግሎታቸው ባሻገር ለኅብረተሰቡ የቀለም፣ የዜማ፣ የትርጓሜ መጻህፍት፣ የቅርጻ ቅርጽና የሥዕላ ሥዕል ትምህርት ቤት፣ ቤተመዘክርና ቤተመጽሐፍት በመሆን ሲያገለግሉ ኑረዋል (የኢ. ኦ. ተ. ቤ.፣8)። በአጠቃላይ እስከ 20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መግቢያ ድረስ የሀገሪቱ የትምህርት፣ የሥነ-ህንጻ፣ የሥነ-ጽሑፍ ተቋማት በመሆን ማገልገላቸው ለጥናት ያስመርጣቸዋል። ለዚህም ይመስላል ስርግው "The Church of Ethiopia A Panaroma of History and Spritual Life" መጽሐፍ "The Establishment of Ethiopian church" በሚለው መጣጥፋቸው ገዳምና አድባራቱ በኢትዮጵያ የሃይማኖት መገለጫ ስፍራ ብቻ ሳይሆኑ ለዘመናት የማህበረሰቡ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ህይወት ማዕከል ነበሩ (Sergew, 5)

የሚሉት፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የዕደ ጥበብና ሥነ ጥበብ ስራዎችን በመስራት እፁብ ድንቅ የሚባሉ ሃይማኖታዊ ቁሳዊ ባህሎች ባለቤት መሆኗም ይነገራል (ብርሃኑና ሌሎች፣58)፡፡ ከዚህ የተነሳ ነው የአብያተ ክርስቲያናቱን ታሪክ፣ ሥነ ህንጻ፣ ታቦታት፣ ከመንግስት ጋር የነበረው ግንኙነት፣ የአጋጠማቸው ተግዳሮትና ለሀገራችን ኢትዮጵያ ያበረከቱት አስተዋጽኦ ወዘተ. የሚጠናው፡፡ በየገዳማቱ የሚገኙ ቅርሶችን በተለያዩ ጽንሰ ሀሳቦች የፈከሩ ጥናቶችም አሉ፡፡ እነዚህ ጥናቶች በአብዛኛው የታሪክና የሥነ ሰብዕ ተመራማሪዎችና የሥነ ጽሑፍ ሊሂቃን ስራዎች ናቸው፡፡

በፎክሎር መስክ ገዳማትና አድባራትን መሰረት አድርገው የተጠኑ ጥናቶችን ስንመለከት የፎክሎር ተመራማሪን የሚስቡ በርካታ ነገሮች የመኖራቸውን ያህል ጥናቶች አልተደረጉም፡፡ ይህ ሲባል ግን በፎክሎሪስቶች የተጠኑ ጥናቶች ፈጽሞ የሉም ማለት አይደለም፡፡ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ከተከፈተ ወዲህ እንኳ የተጠኑ ምርምሮችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ የቅኔ ቆጠራና ነገራ፣ በስብከቶች ላይ የሚስተዋሉ ቃላዊ ዝርው ተረኮች፣ የስልጣነ ክህነት ስርዓት፣ የምንኩስና ስርዓት፣ የማህሌት ስርዓተ ክዋኔ፣ የጽዋ ማህበራት ስርዓት ሥነ ቃላዊና ሃይማኖታዊ ገጽታ፣ የንዋያተ ቅድሳት ጥናት እንዲሁም የገዳማዊያንና የቆሎ ተማሪዎችን ህይወት መሰረት አድርገው የተጠኑት ይጠቀሳሉ፡፡

ገዳማትን ከተለያዩ ጉዳዮች አንጻር በመጠኑ ያጠኑ ቢኖሩም ቃላዊ ተረኮችንና ቁሳዊ ባህሎችን አያይዘው ያጠኑ ጥናቶችን ብንፈልግ ግን በምህረት ተስፋዬ "ከጣና ቂርቆስ የአንድነት ገዳም አመሰራረት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ጥናት" በሚል በ2003 ዓ.ም የተደረገውን ብቻ ነው መጥቀስ የምንችለው፡፡ እንደ ታሪካዊ ገዳማትና አድባራት የቁጥር ብዛት፣ በአንዱ ገዳም የሚተረከው ተረክ ከሌላው መለየትና ታሪካዊ ንዋየ ቅድሳት መለያየት ገዳማቱንና አድባራቱን ከተረኮችና ከቁሳዊ ባህል አንጻር የሚመረምሩ ጥናቶች በብዛት መደረግ ነበረባቸው፡፡ እስከ አሁን የተተገበሩት ጥናቶች ግን ጥቂቶች ናቸው፡፡ በዚህ መስክ ያለውን ክፍተት በማየቱም ጥናቱን "በዝዋይ **ደስያት ገዳም ወአድባራት**[1] መመስረት የተገኙ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች" በሚል

[1] የዝዋይ ደስያት ያልኩት ደሴት "ሲበዛ ደስያት - በቁሙ በባሕር ውስጥ ያለ ባሕር የከበበው የብስ፣ ሀገር፣ ምድር፣ ተራራ፤ እንደ ደቅ፣ እንደ ሀይቅ፣ እንደ ዝዋይ ያለ" (ኪዳነወልድ፣363) ስለሚባል ነው፡፡ የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት በሦስት ምድቦች ይከፈላሉ፡፡ እነሱም ገዳም፣ ደብርና ገጠር ናቸው፡፡ ገዳም የንፍሮ ወይም የህግ ገዳም ነው፡፡ ዓለሙን ንቀው ወደ ገዳም የሄዱ መናንያን መነኮሳት በጾም በጸሎት ተጠምደው የሚኖሩበት ቦታ

ርዕሰ ጉዳይ ላይ አድርጌ በዝዋይ ሐይቅ በየደሴቱ ከሚገኙት ገዳምና አድባራት ጋር በተያየዘ የተፈጠሩ ተረኮችንና በውስጣቸው የሚገኙ ቁሳዊ ባህሎችን በመመርመር ዝንቅ ምሳሌዎችና ትዕምርቶችን በማብራራት ተምሳሌታዊ ገጽታቸውን ለማሳያት ሞክሪያለሁ።

የዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራት ረጅም ዕድሜ ያላቸውና ታሪካዊ ቅርሶች የሚገኙባቸው ናቸው። የገዳምና አድባራቱ ጥንታዊነት በርካታ የሃይማኖቱ መንፈሳዊ ተጓገሮችንና ሌሎች የውጪ ጎብኚዎች ወደ ስፍራው እንዲጓዙ ማድረግ ችለዋል። የጎብኝዎችን የትኩረት አቅጣጫ የማግኘታቸውን ያህል ግን የባህል ወይም የፎክሎር ተማራማሪዎችን ትኩረት አግኝተዋል ብሎ ለመናገር የሚያስደፍሩ መረጃዎች የሉም። ለዚህም ነው እንደ ፎክሎር ተማሪነቴ አንዳች መነሻ ነገር ለማስቀመጥ የገዳምና አድባራቱን ተረኮች ከቁሳዊ ባህሉ ጋር በማዛመድ ለማጥናት የወሰንኩት።

የዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራት በዚህ መንገድ ተጠንተው አያውቁም። እነ ዘላለም አስፋው፣ ቴማ ናዶማ፣ ደስታ ፍጹምብርሃኔና እንዳሻው ወ/ሚካኤል የደስያቱን ሕዝቦችና ገዳማት አጥንተዋል። እነሱም ከታሪክ፣ ከሥነ ልሳን፣ ከሥነ መለኮትና ፊሎሎጂ አንጻር ሕዝቦቹንና ቅርሶቹን በሚመለከት እነሱ አንጂ የገዳምና አድባራትን ተረኮቹና ቁሳዊ ባህሎች አላጠኑም። በቃላዊ ተረኮቹና ቁሳዊ ባህሎቹ አንጻር ገዳምና አድባራቱን ማጥናት የሃይማኖቱን የእምነት ሥርዓት፣ የአማኒያኑን አስተሳሰብና የህይወት ፍልስፍና ብሎም ከልዕለ ተፈጥሮ ሀይላት ጋር ያላቸውን ህብረት ለማወቅ ያስችላል። በቁሳዊ ባህሉና ቃላዊ ተረኩ አማካይነት ሃይማኖታዊ ሥርዓት ይሰራልና። የምርምሩን አነሳሽ ምክንያት፣ የምርምር ጥያቄዎችና ዓላማዎች እንዲሁም የንድፈ ሀሳብና የሥነ ዘዴ አቅጣጫዎች እንደሚከተለው በማንሳት የጥናቱን አጠቃላይ ገጽታ አብራራለሁ።

---

ነው። የሚያስተዳድራቸው መምህርም አበምኔት ይባላል። ደብር ብዙ ጊዜ በከተማና በታሪክ ቦታዎች የታሪክ ቦታዎችም ባይሆኑ በዘመኑ ባለ ሥልጣኖች ትዕዛዝ ደብር እየተባሉ የሚተከሉ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው። የእነዚህ አስተዳደር በርስትና በጉልት ነበር። አስተዳዳሪዎች ንቡረ ዕድ፣ ሊቀ ሥልጣናት፣ ሊቀ ሊቃውንት፣ መልአከ ሰላም፣ መልአከ ገነት፣ መልአከ ፀሐይ ወዘተ. በተባሉ ስሞች ይጠራሉ። ገጠር ርስት ጉልት የሌለው ገበሬው በሃይማኖት ስሜት የሚሰራው ቤተክርስቲያን ነው። በገበዝ ወይም መርጌታ የሚተዳደር ነው (ጎርጎርዮስ፣ 186)። ከዚህ ሀሳብ እንደምንረዳው በዝዋይ ደስያት ያሉት አብያተ ክርስቲያናት በተለምዶ ገዳማት የሚባሉ ቢሆንም አንዱ ገዳም ሆኖ የተቀሩት አራቱ አድባራት ናቸው። ስለዚህ በቤተክረስቲያኑ አጠራር የሁለቱንም ክብር በአንድነት የሚይዝ ገዳም ወአድባር የሚል ስያሜ ስለሚሰጠው እኔም ገዳም ወአድባራት በሚል መጠቀምን መረጥኩ። አክሱም ጽዮን ርዕሰ ገዳማት ወአድባራት እንዲሉ።

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በ2001 ዓ.ም ወደ ዝዋይ በመጓዝ በሐይቁ ውስጥ ከሚገኙት አምስት ደስያት ሶስቱን (ደብረ ሲና፣ ገሊላና ደብረ ጽዮንን) የማየት እድል ገጥሞኝ ነበር፡፡ በዚህም የሐይቁ ደስያት የዛይማኖት ማዕከል ከመሆናቸው ባሻገር የሀገራችን የታሪክ፣ የሥነ ጽሑፍ መዛግብትና የተለያዩ ቅርሶች መገኛ ሆነው ማገልገላቸውን ለመረዳት ችያለሁ፡፡ በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ተማሪ ከሆንኩኝ በኋላ የዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራትን መሰረት አድርገው የተሰሩ የፎክሎር ጥናቶች ካሉ በሚል ዳሰሳ ሳደርግ ያገኘሁት ነገር የለም፡፡ በደስያቱ አብያተ ክርስቲያናት አመሰራረት ዙሪያ የሚነገሩ ቃላዊ ትውፊቶችን፣ ቁሳዊ ባህልን፣ በገዳምና አድባራቱ የሚፈጸሙትን አምልኳዊ ስርዓተ ክዋኔ እንዲሁም ህልውናቸው በሙሉ ከዝዋይ ሐይቅ ጋር የተቆራኘውን የዛይ ማህበረሰብን መሰረት ያደረጉ ፎክሎራዊ ጉዳዮች መጠናት ይችሉ ነበር፡፡ ነገር ግን በሥነ መለኮት ትምህርት ቤት፣ በሥነ ልሳን፣ በፊሎሎጂና የታሪክ ትምህርት ክፍል ከተሰሩት ሌላ በፎክሎር ተማሪዎች የተሰራ ጥናት ባለማግኘቴ በገዳምና አድባራቱ መመስረት የተገኙ ተረኮችንና ቁሳዊ ባህሎችን በመሰብሰብ ለማጥናት ወሰንኩ፡፡

የአንድን ማህበረሰብ የህይወት ፍልስፍናና የእምነት ስርዓት፣ ከፈጣሪ ጋር ያለውን ሕብረትና ከየት መጣነት፣ እንዲሁም ሥነ ልቦናዊ ማንነት ለመረዳት ከፎክሎራዊ ዘውጎች ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ይጠቀሳሉ፡፡ ቃላዊ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች የአንድን ማህበረሰብ የማንነት አሻራ የሚገነቡ ናቸውና፡፡ የገዳማትና አድባራትን ቃላዊ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ማጥናት ደግሞ ገዳማውያኑንና አማኒያኑን ለመረዳት ያስችላል፡፡ ሁለቱን የፎክሎር ዘውጎችን በማቀናጀት ያጠኑ የሀገራችን ምርምሮች ደግሞ ብዙም አይደሉም፡፡ ስለዚህ የፎክሎር ተመራማሪዎች የተለያዩ ዘርፎችን በተለያዩ ንድፈ ሀሳቦች በማጣመር በስፋት እንዲያጠኑ ምክንያት የመሆን ፍላጎትም ሌላው አነሳሽ ምክንያት ነው፡፡

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራት መመስረት የተገኙ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎችን ምሳሌ፣ ዘይቤና ትዕምርት አንድምታ መርምሮ በማብራራት እንዲሁም ተምሳሌታዊ ፍቺያቸውን በመፈከር የተረኮቹንና ቁሳዊ ባህሎቹን ፋይዳ ማብራራት ነው፡፡

ይሄንን አቢይ ዓላማ ተከትለው ግብ እንዲመቱ የሚጠበቁት ዝርዝር ዓላማዎች ደግሞ፡-

- ✓ ስለ ሐይቁ አፈጣጠርና ለደስያቱ ገዳምና አድባራት መመስረት በምክንያትነት የሚጠቀሱትን ተረኮች መመርመር፣
- ✓ የቁሳዊ ባህሎቹን ምንነት መግለጽና ትውፊታዊ አመጣጣቸውን በማብራራት ከአገልግሎት በተጨማሪ የሚኖራቸውን ትዕምርት መተርጎም፣
- ✓ የደስያቱ ማህበረሰቦች ከትውፊታዊ ተረኮቹና ከቁሳዊ ባህሉ ጋር ያላቸውን ዝምድና መተንተን፣
- ✓ ተረኮቹና ቁሳዊ ባህሎቹ በሃይማኖቱ ባለቤቶች ዘንድ እምነትን በመትከልና በማጠናከር ረገድ ያላቸውን ሚና ማስረዳት፣

## 1.4. የምርምር ጥያቄዎች

ይህ ምርምር የተደረገው ለሚከተሉት መሰረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ ላማስገኘት ሲባል ነው፡፡ እነሱም፡-

- ❖ የዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራት መመስረት ምክንያት ምንድን ነው?
- ❖ ተረኮቹና ቁሳዊ ባህሎቹ ከገዳምና አድባራቱ መመስረት ጋር ያላቸው ቁርኝት ምን ይመስላል?
- ❖ በገዳምና አድባራቱ የምስረታ ሂደት የተስተዋሉ ድርጊቶችና ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች ለደስያቱ ማህበረሰብ፣ ለሃይማኖቱ ተከታዮችና ለአካባቢው ነዋሪዎች ያላቸው ፋይዳ ምንድን ነው?
- ❖ ተረኮቹና ቁሳዊ ባህሎቹ የማህበረሰቡን ማንነት በመገንባት ሂደት ያላቸው ሃይማኖታዊና ባህላዊ ተምሳሌት እንዴት ይገለጻል?

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

የዚህ ጥናት ተግባራዊ መሆን በዝዋይ ደሴቶች ላይ ከታሪክ፣ ከሥነ ሰብ፣ ከቋንቋና ከሌላ ዘርፍ አንጻር ምርምር ለማድረግ ለሚነሱ ተመራማሪዎች ተጨማሪ መረጃን በመስጠት ያገለግላል፡፡ በሌሎች ገዳማት የሚነገሩ ተረኮችንና ቁሳዊ ባህሎችን መሰረት አድርገው የፎክሎር ተመራማሪዎች እንዲያጠኑም ምክንያት ይሆናል፡፡ በተጨማሪም በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ከሃይማኖታዊ ተቋማቸው ጋር በተያያዘ የሚተረኩ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ምን ያህል የአንድን ማህበረሰብ ማንነት እንደሚገነቡና ቁሳዊ ባህላቸውም የህይወታቸው አሻራ ነጸብራቅ እንደሆነ ልንመለከትበት እንችላለን፡፡ የዝዋይ ደሴቶች ገዳምና አድባራት ሚታዊ ተረኮች እና ቁሳዊ ባህሎች መጠናት የገዳምና አድባራቱ ተገልጋዮች ስለ ህልዎተ ፈጣሪ፣ ስለ ሰው ልጅ አመጣጥና በተፈጥሮ ልዩ ልዩ ክስተቶች ዙሪያ ያላቸውን እውቀት፣ እምነትና ስርዓት ለማወቅ ያስችላል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ በዝዋይ ሐይቅ ውስጥ የሚገኙትን ገዳምና አድባራት መሰረት አድርገው የሚተረኩ ተረኮችንና ቁሳዊ ባህሎችን በመሰብሰብ ተምሳሌታዊ ፍቺያቸውን ማሳየት ላይ ብቻ የተወሰነ ነው፡፡ መረጃዎቹም በሐይቁ ላይ ከሚገኙት አምስቱ ደሴቶች ተሰብስበዋል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት አብያተ ክርስቲያናቱ ተቀራራቢ ታሪክ ያላቸው እንደመሆናቸው መጠን በአንዱ ላይ የተፈጠረውን ክፍተት ከሌላው ለመሸፈን ተፈልጎ ነው፡፡ በእነዚህ ገዳምና አድባራት የአምልኳዊ ስርዓቶቹ ክዋኔ፣ የዛይ ማህበረሰብ የአኗኗር ስርዓት (ልደት፣ ማህበር፣ ጋብቻ፣ ሞት ወዘተ.) መሰረት ያደረጉ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ሊጠኑ ይችላሉ፡፡ ለእኔ ግን ዋና የትኩረት አቅጣጫ አይደሉም፡፡ ከቁሳዊ ባህሎቹም ለተረኮች ግብዓት የሚሆኑትን፣ ወደ ደሴቶቱ ለጉብኝት ሲኬድ ታሪካዊ ተብለው ለዕይታ የሚቀርቡትንና ከአገልግሎታቸው ባሻገር የተለየ አንድምታዊ ትንታኔ ይቀርብባቸዋል ያልኳቸው ብቻ እንጂ የደሴቶቹ ንዋየ ቅድሳት በሙሉ የተዳሰሱበት አይደለም፡፡

## 1.7. የጥናቱ ዘዴ

### 1.7.1. የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ

የመረጃ አሰባሰብ ዘዴው ተግባራዊ የሆነው በካልዓይና ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች ነው። የቤተ መጻሕፍትና መዛግብት ምንጮች ከእኔ ጥናት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የተለያዩ ጥናቶች፣ መጽሔቶችና መጻህፍትን መረጃ ለመሰብሰብ አገልግለዋል። የአንድ ጥናት ተግባር ከቤተ መጻሕፍት ስራ መጀመር እንዳለበት የመስኩ ምሁራን ይስማማሉ። በፎክሎር ጥናት ውስጥ የመስክ መረጃዎች በምልከታ፣ ቃለመጠይቅ፣ በተተኳሪ ቡድን ውይይት፣ በተፈጥሯዊ እና አርተፊሻል መቼት ቅንብር ሊሰበሰቡ ይችላሉ። Kenneth, Goldstein "ፎክሎራዊ ጉዳዮች ላይ ምርምሩን ለመስራት የሚነሳ አካል ከሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ምልከታና የቃለመጠይቅ ዘዴን ቢጠቀም ተመራጭነት እንዳለው ያስረዳሉ" (Goldstein, 77)።

ምልከታ መረጃ ሰብሳቢው ሰው በመስክ ስፍራው በአካል ተገኝቶ የሚደረገውንና የሚነገረውን በቅርበት ሆኖ በማየትና በመስማት፣ የተመለከተውን ነገር በመመዝገብ በስፍራው ለሌለና የማየት አጋጣሚውን ላላገኘ ሰው በብዕሩ አማካይነት የሚያስቃኝበት ዘዴ ነው። ዘዴውን አጥኚው በብልኃት ከያዘው ከሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በተሻለ መረጃን ለመሰብሰብና ብዙ እውነታዎችን በተጨባጭ ለማግኘት የሚያስችል ነው። ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ከዓይን እይታ በተጨማሪ የስሜት ህዋሳቶቻችንን በሙሉ በማገናኘት ስለ ተሰራው ነገርና ስለ ሰሪው ወይም ስለ ክወና አውዱም ሆነ ስለ ከዋኙ ሁኔታ የተሟላ መረጃ ለማግኘትም የሚያስችል እንደሆነ ይነገርለታል (Jackson,63, Goldstein, 77)።

የምልከታ ዘዴ የባህል ገጽታዎችን ጭምር ለመገንዘብ የሚያስችል ተመራጭ ዘዴ ነው። ፊ.ቃደ አዘዘ ደግሞ ሥነ ቃሎች በተለይም አፈ.ታሪኮችና ቃል ግጥሞች ሲሰበሰቡ ትረካው ተአማኒነት እንዳለው ሊያረጋግጥልን የሚችል የቁስ አካላት ምልከታ መኖር እንዳለበት ያስረዳሉ (ፊ.ቃደ፣ 91-94)። የምልከታ ዘዴ በውስጣችን የሚፈጠሩ ጥያቄዎችን ያለመመለስ ደካማ ባህሪ አለበት። በዚህ ዘዴ የሚፈጠረው ደክመት የሚቀረፈው ደግሞ ጥያቄ በመፍጠር ብቻ ነው። ስለዚህ የምልከታን ድክመት ለመሸፈን ከሚያስችሉን ዘዴዎች አንዱ ቃለመጠይቅ ነው።

የቃለመጠይቅ ዘዴ ከአውድ ውጪ መረጃ ይሰጠናል ብለን ካመንበት ወይም ከምናቀው መረጃ አቀባይ በጥያቄና መልስ ስለ ድርጊትና ሁነት የምንጠይቅበት ነው፡፡ የሁለቱ ዘዴዎች ውህደት ደግሞ ሰፊ መረጃን ለመሰብሰብ ያስችለናል፡፡ ሆኖም የመረጃ ሰብሳቢውን የሁለቱን ዘዴዎች አጣጥሞ የመጠቀምን ብቃት ይጠይቃል (Goldstein, 77-78)፡፡

በቃለመጠይቅ ዘዴ ጥያቄዎች የምናቀርብበት የተለያዩ ቴክኒኮች አሉ፡፡ ገደብ የሌላቸውና ውስን ጥያቄዎች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ገደብ የሌላቸው የሚባሉት ጥያቄዎች ተጠያቂዎች ነጻ ሆነው መረጃ የሚሰጡባቸው ቀድመው ያልተዘጋጁ ነገር ግን ሁነት የሚጠራቸው ጥያቄዎች ሲሆኑ ውስን ጥያቄዎች አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለማግኘት ሲባል ቀድሞ በተዘጋጁ ጥያቄዎች አማካይነት የሚፈጸም ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ ወደ መስክ ከማቅናቴ በፊት ባዘጋጀኋቸው ጥያቄዎች ቃለመጠይቅ አድርጊያለሁ፡፡ በተጨማሪም በመስክ ስራ ላይ በአውዱ ውስጥ ከሚታዩትና ከሚያጋጥሙኝ ነገሮች ተነስቼ በቦታው ያገኘኋቸውን ሰዎች ጠይቂያለሁ፡፡ "የቃለመጠይቅ ዘዴ በሚካሄድበት ወቅት እንደ ሁኔታው ሊለወጥ፣ እንደ መላሹ ዓይነት ሊሻሻል፣ እንደ ጠያቂው ችሎታ ሊቀያየር ይችላልና" (ያለው እንዳወቀ፣ 176-177)፡፡ ከተመረጡት ዘዴዎች አንጻር መረጃ ለመሰብሰብ በሄድኩበት የዝዋይ ደስያት የሚታዩትን ሃይማኖታዊና ሀገረሰባዊ ቁሶች፣ የደስያቱን ነዋሪዎች ከጾታና ከሃይማኖታዊ ድርጊት እንዲሁም ከስራ ድርሻቸው አንጻር ለመቃኘት የምልከታ ዘዴን የተገለገልኩ ሲሆን የቃለ መጠይቅ ዘዴን ደግሞ ከገዳምና አድባራቱ አመሰራረት ጋር ተያይዘው የሚተረኩትን ተረኮች፣ የቁሳዊ ባህሎችን ምንነትና አገልግሎት ከተገልጋዮቹ ለመረዳት ተጠቅሜበታለሁ፡፡

ከፎክሎር የመስክ መረጃ የመሰብሰቢያ ዘዴዎች በተጨማሪነት የሚነሳው የተተኳሪ ቡድን ውይይት ነው፡፡ የቡድን ውይይት ዘዴ በምልከታ ያልተመለሱ ጥያቄዎችና በቃለመጠይቅ ያልተዳሰሱትን ነገሮች ለመቅረፍ የሚያገለግል ነው፡፡ ከየደስያቱ ወሳኝ የሆኑ አካላትን በመምረጥ አንድ ላይ በማገናኘት የቡድን ውይይት ለማድረግ አልቻልኩም፡፡ ነገር ግን በምልከታና በቃለመጠይቅ ያልተዳሰሱ ነገሮችንና ያልተረዳኋቸው የተለያዩ ትዕምርታዊ ትርጉሞች፣ ዘይቢያዊ ገለጻዎች ግልጽ እንዲሆኑልኝ በመስክ ስራ ላይ በተለያየ ጊዜ ስመላለስ ያገኘኋቸው መረጃ ሰጪዎቼን በማነጋገር መረጃዎችን ለማጠናከር ችያለሁ፡፡

በቃለመጠይቅና ምልከታ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የሚሰበሰቡ የመስክ መረጃዎች በቪዲዮና ፎቶ ካሜራ እንዲሁም መቅረጸ ድምጽን በመሳሰሉ መሳሪያዎች መታገዝ እንዳለባቸውም (Goldstein, 97-99) ይገልጻሉ፡፡ ስለዚህ እኔም መረጃዎችን ስሰበስብ እነዚህን መርጃ መሳሪያዎች ተገልግያለሁ፡፡ አንድ ተመራማሪ የተሻለ መረጃን ከማንና እንዴት ባለሁኔታ ማግኘት እንዳለበት ቀድሞ በማቀድ ዓላማውን ማሳከት እንዳለበት ምሁራን ይናገራሉ፡፡ ለዚህም ማስረጃ የሚሆነን ፎክሎር በሰው ልጆች የእለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ ያለውን አስተዋጽኦ ከፍተኛነት ካልዘነጋ በስተቀር ማንኛውንም ሰው በፎክሎር ጉዳዮች ዙሪያ ለማነጋገር በመረጃ አቀባይነት ሊያጭ ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ አንድ ሰው በፎክሎር ከሚካተቱት ጉዳዮች መካከል በአንደኛው ወይም በተወሰኑት የተለየ የህይወት አገላለጽ ብቃት ባለቤት የሚሆንበት አጋጣሚ ብዙ ነውና አንዱን ከአንዱ በማበላለጥ መረጃ ሰጪዎችን መምረጥ ግድ ይላል (Jackson, 42)፡፡

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ እንደምንረዳው ለፎክሎር መረጃ ለመሰብሰብ ታሪኩን በሚገባ የሚያስታውሱትንና የተለየ የአገላለጽ ብቃት ያላቸውን መምረጥ ያስፈልጋል፡፡ እኔም በዚህ መርህ በመንዝ ከአካባቢው ማህበረሰቦች መካከል በቁልፍ መረጃ ሰጪነት በዋናነት ያሳተፍኩት በዕድሜ የገፉትን ነው፡፡ ምክንያቱም ፎክሎር በየትኛውም እድሜ ክልል ውስጥ ያለ ቢሆንም የበለጠ የፎክሎር መረጃ ያላቸው አረጋዊያን ናቸው ስለሚባል ነው፡፡ በዚህ ሂደት በመረጃ ሰጪነት ከተሳተፉት አስሩ ቁልፍ የመረጃ ሰጪዎች ነበሩ፡፡

መረጃዎቹ የተሰበሰቡበት ቋንቋም ከተወሰኑ ባህላዊ ጉዳዮች በስተቀር አማርኛ ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ማህበረሰቡ አማርኛን እንደ አፍ መፍቻ ተናጋሪዎች ስለሚገለገልበት ነው፡፡ የሥነ ልሳን ተመራማሪ የሆኑት እንዳሻው ወ/ሚካኤል በሁለተኛ ዲግሪ ጽሑፋቸው ይሄንን ጉዳይ ሲገልጹ የዛይኛ ቋንቋ በመሞት ሂደት ላይ ያለ መሆኑንና ማህበረሰቡ በአሁኑ ጊዜ የአማርኛና ኦሮምኛ ተናጋሪ መሆኑን ያስረዳሉ (እንዳሻው፣39-40)፡፡ እኔም በመስክ ያስተዋልኩት ነገር ይሄ በመሆኑ መረጃዎችን በአማርኛ ቋንቋ ሰብስቢያለሁ፡፡ በዛይኛ ቋንቋ የተሰበሰቡት ባህላዊ

ከተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ አቀንቃኞች መካከል ተጠቃሽ የነበሩት ዊሊያም ባስኮም የፎክሎርን ተግባር የማምለጥ፣ የመትከል፣ የማስተማርና የመቆጣጠር በማለት በአራት እንደከፈሉትና ለጥንታዊው ጥናት መንገድ እንደ ከፈቱ ይነገራል። ጥንታውያኑ ተግባራዊያን (Classical functionalist) የፎክሎር ጉዳዮችን መርምረው ተግባራቸውን ከመግለጽ ይልቅ ባስኮም በከፈሏቸው የፎክሎር ተግባራት ላይ መመደብ ላይ ያተኩሩ ነበር። ምንም እንኳ ባስኮም ፎክሎርን በአራት ተግባሮች በመክፈል ለማሳየት ቢሞክሩም አራቱ ጉዳዮች ግን ተነጣጥለው የሚታዩ አለመሆናቸውን ባስኮም እራሳቸው ሲገልጹ ወደ አንድ ተግባር በማጠቃለል ባህል ተጠብቆ እንዲኖር ፎክሎር አይነተኛ ሚና ይጫወታል ይላሉ።

የፎክሎር ተግባራት በአራት መከፈላቸውና ጥንታውያን ተግባራውያን በዚህ አከፋፈል ተመርተው ፎክሎራዊ ጉዳዮችን ሲተነትኑ በመቆየታቸው ተቃውሞ ገጥሟቸዋል። Sims and Stephens (176) "Mullen"ንን በመጥቀስ በባስኮም አከፋፈል መሰረት አዳዲስ የሚፈጠሩ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ቦታ እንደሌላቸው ያስረዳሉ። የሰው ልጅ እስካለ ድረስ ፎክሎር ይፈጠራል ወይም ደግሞ ይበልጥ ሲዳብር ይችላል። እነዚህ ጉዳዩች በተፈጠሩ መጠን ደግሞ ተግባራቸው ባስኮም ከከፈላቸው ተግባራት ውጪ ሊሆኑ ይችላሉ። በዚህም የጥንታውያን ፎክሎሪስቶች መርህ ማለትም ፎክሎራዊ ጉዳዩ ለፎክ ቡድኑ የትም ቢከሰትም አንድ ወጥ የሆነ ጉዳይና ሁሉም የፎክሎር ዘውጎች በተመሳሳይ መንገድ ከባህል ጋር የተያያዙ ናቸው የሚለውን የቆየ አስተሳሰብ ያፈርሳል።

ሲምስና እስቴፈንስ ከላይ የተነሳውን ሀሳብ ሲያስረዱ ጥንታውያኑ የፎክሎር ተንታኞች ሀገር በቀል እምነቶች ሁልጊዜ የሚያመለክቱት የማህበረሰቡን እምነት ነው። ሀገረሰባዊ ተረቶች (Folk Tales) ደግሞ በአድማጭና በከዋኙ ምክንያት ዘወትራዊና አሰልቺ ከሆነው ህይወት ማምለጥን ያስገነዝቡናል በማለት ጠቅላይ የሆነ ድምዳሜ ይሰጡ ነበር። ሀገር በቀል እምነቶች ሁልጊዜ የሚያሳዩን እምነትን ብቻ ሳይሆን የማህበረሰቡን የወደ ፊት ህይወት ለመተንበይና መጭውን ጊዜ በማሰብ ጥንቃቄ ለማድረግም ጭምር ነው። አያይዘውም ማንኛውም መተንተን ያለበት ፎክሎራዊ ጉዳይ በሚገኝበት አውድ (ቦታ፣ ባህል፣ ጊዜ) ተወስኖ መሆን እንዳለበት ይገልፃሉ (Sims and Stephens, 177)።

ቀደምት የፎክሎር ተንታኞች ከሚተቹበት አንዱ ፎክሎራዊ ጉዳዩ በሚከወንበት አውድ ላይ ተመስርተው ትንታኔ አለመስጠታቸውና የፎክሎር ተለዋዋጭነትን (Dynamic) መርሳታቸው ነው፡፡ የእምነትን ባህርይ ውስብስብነት በመዘንጋታቸው የተነሳ ፎክሎርን በአንድ ነጠላ ተግባር ለመመደብ መቻላቸውና በአንድ ፎክ ቡድን ላይ ብቻ በመመስረት ሁሉን ለመጠቅለል መሞከራቸውም ድክመታቸው ነው፡፡ በተጨማሪም ፎክሎር አንድ ተግባር አለው ካልን ማንም ሰው የፎክሎር ተግባር ይህ ነው እያለ በቀላሉ ድምዳሜ ይሰጣል፡፡ ይህ የሚያስረዳን ፎክሎርን ለማጥናት ወይም ለመመርመር ሌላ ንድፈ ሀሳብ እንደማያስፈልግ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ፎክሎርን በአንድ አቅጣጫ ብቻ እንድናስብ ያደርጋል በማለት ትችት ያቀርቡባቸዋል (Oring, 74)፡፡ ለፎክሎር ዘርፈ ብዙ ተግባር ተጠቃሽ ምክንያት የፎክሎር ዘውጎች መብዛት እንደሆነም ያስረዳሉ (Finnegan, 126)፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ የሚገለጸው አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ በተለያዩ መቼቶችና ከዋኞች ቢከወን የሚገኘው ውጤት የተለያየ እንደሚሆን ነው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረቡት ጉዳዮች የምንረዳው ፎክሎራዊ ጉዳይን መርምረን ለመረዳት ጉዳዩ የሚገኝበትን አውድ፣ ማህበረሰብ፣ ታሪካዊ ሁኔታና ባህል እንዲሁም ጉዳዩ በተናጥል መጠናት እንዳለበት የዘርፉ አጥኚዎች መስማማታቸውን ነው፡፡ ስለዚህ ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ቃላዊ፣ ልማዳዊና ቁሳዊ ስብስቦችን የያዙ ፎክሎሮች ለተተኳሪው ማህበረሰብ ምን እንደሚጠቅምና ጠቀሜታው እንዴት እንደሚከናወን የሚያጠና ነው (Sims, and Stephens, 175)፡፡ በተጨማሪም የአንድ ማህበረሰብ እምነት፣ ስርዓትና ትውፊት ያለውን ፍቺ መሰረት በማድረግ ለማህበረሰቡ የሚያበረክተውን አገልግሎት ተንትኖ የሚያቀርብ ነው (Oring, 68) የሚለውን ጽንሰ ሀሳብ ይዞ መደምደም ይቻላል፡፡

የቁሳዊ ባህል ጥናት ሰዎች የሚገለገሉባቸው ቁሶች ከሚሰጡት ግልጋሎት ባሻገር ያላቸውን ትርጉም በመፈተሽ የሰዎቹን እሴቶች፣ አመለካከትና ፍላጎት እንዲሁም የዘመንን መንፈስና የማህበረሰቡን የህይወት ልምድ ለማንጸባረቅ የሚያስችል ነው (Jones, 9)፡፡ ይሄንን ለማድረግ ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብን በመጠቀምና ሌሎች ዘዴዎችን በመከተል ለቁሳዊ ባህሉ ትንታኔ ለመስጠት ተሞክሯል፡፡ ከተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ጋር ተዛንቀው እንደ መፈክሪያ ስልት

ያገለገሉት የቁሳዊ ባህል መተንተኛ ሞዴሎች "Models of Material Culture Interpretation"[3] በመባል የሚጠቀሱትንና ዴቪድ ፕሮውን የቁሳዊ ባህል የመተንተኛ ስልት ብለው የሚጠቅሷቸውን ነው፡፡ እንደ ሞዴልነት የሚጠቀሱት የጥበብ ነጸብራቅነት፣ ተምሳሌታዊነት፣ ባህላዊነት፣ አገልግሎት ሰጭነት፣ መዋቅራዊነት፣ አካባቢያዊነት፣ ባህሪ ገላጭነትና ማህበረሰባዊ ታሪካዊነት የሚባሉት ናቸው፡፡

የቁሳዊ ባህል መተንተኛ ሞዴሎቹ ከቁሱ ውጫዊ ገጽታ እስከ ተምሳሌታዊ ትርጓሚያቸውና አንድምታዊ ትንታኔ ድረስ የሚዘልቁ ናቸው፡፡ በእነዚህ ሞዴሎች በኩል ስንጓዝ የቁሶቹን ቀለም፣ ለስላሳነትና ሻካራነት በመመልከት ጥባባዊ መስህብነታቸውን መግለጽ፤ ቁሶቹ በውክልና የቆሙለትን ነገር ማሳየት፤ የተገለጋዩን ማህበረሰብ ባህል በመግለጽ ረገድ ያላቸውን ድርሻ መፈተሽ፤ ሲሰሩ የታቀደላቸውን ተግባር መለየት፤ ቁሱ እንዴት ተሰራ፣ ከምን ተሰራ ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት፤ አከባቢው በቁሱ ላይ ያሳደረውን ተጽዕኖ መፈተሽ፤ በቁሶቹና በማህበረሰቡ መካከል ያለው መስተጋብርና ቁሶቹ በሕዝቡ ላይ አንዳች ያመጡት የተለየ ባህሪ ካለ መፈተሽ እንዲሁም ቁሱ ከየትኛው ዘመን ማህበረሰብ እንደፈለቀና ዘመኑን መፈተሽ የሚሉት ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ ሞዴሎች ለተሰበሰቡት ቁሳዊ ባህሎች እንደ መተንተኛ ዘዴ አገልግለዋል፡፡

የቁሳዊ ባህል አተናተን ስልት ተብለው የሚጠቀሱት ሶስት መሰረታዊ ደረጃዎች ናቸው፡፡ ከእነዚህም ቀዳሚው የእቃውን ውጫዊ እይታ የምናስረዳበት ገለጻ (description) የሚባለው ነው፡፡ ሁለተኛው በሕዝቡና በቁሱ መካከል ያለውን ግንኙነት የምናሳይበት ትርጓሜ (deduction) የሚባለው ደረጃ ሲሆን ጥቆምታዊ (specultion) የምንለው የመጨረሻው ደረጃ ደግሞ በሁለቱ ደረጃዎች ካገኘነው ግብዓት ተነስተን አዲስና ነጻ የሆነ ምርምራዊ ሀሳብ የምንሰነዝርበት ነው (Prown, 7-10)፡፡

---

[3] Schlereth, J. Thomas. "Understanding the Nine Models of Material Culture interpretation." Online Available at URL;http;//www.btnep.org.

## 1.8. ለጥናቱ የተደረገ ቅድመ ዝግጅትና የመስክ ክንውን

በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የጥናቱ ርዕስ ታይቶ ከጸደቀልኝ በኋላ እስከ ጥናቱ ማብቂያ ድረስ ያለፍኩባቸው ሂደቶች በዚህ ንዑስ ርዕስ ይቀርባሉ፡፡ የመስክ ስራዬን ከመጀመሬ በፊት ስለ ዝዋይ ደስያት የሚዘክሩ መጻህፍትን፣ የምርመር ስራዎችን፣ የዚጋቢ. ምስል ወድምጽ መረጃዎችንና የኢንተርኔት ምንጮችን ፈትሻለሁ፡፡ በህጋዊነት መረጃዎችን በጥሩ ሁኔታ ለመሰብሰብ ያስችለኝ ዘንድ የትብብር ደብዳቤዎችን ከተለያዩ አካላትና ክፍላት አጽፌያለሁ፡፡ ይኸውም ከትምህርት ክፍሌ ወደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ጠቅላይ ቤተክህነት፣ ከቤተክህነት ወደ አርሲና ምስራቅ ሸዋ ሀገረ ስብከት ከዚያ በኋላ ወደ ደስያቱ ገዳምና አድበራት ነው፡፡ ደብዳቤ የማጻፉ ሂደት በራሱ ከአንድ ወር በላይ ወስዷል፡፡

የመስክ ስራውን ያከናወንኩት ወደ ደስያቱ ሶስት ጊዜ በመመላለስ ነው፡፡ የመጀመሪያው ጉዞ በስፍራው ላይ አጠቃላይ ጉብኝት በማድረግ ተተኳሪ ቦታዎችን ለመለየትና መረጃ ሰጪዎችን ለመተዋወቅ የተገለገልኩበት ነው፡፡ ለቃለመጠይቅ የሚሆኑና በሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ሊረዱኝ የሚችሉትን አካላት ለመተዋወቅ የቻልኩትም በተለምዶ አስተርዮ ማርያም በሚል ጥር 21 በደብረ ጽዮን ደሴት በደመቀ ሁኔታ የሚከበረው በዓል ላይ በመገኘት ነው፡፡ በዚህ ጊዜ በስልክ ቀደም ብዬ የተዋወኳቸውን የደብረ ጽዮን አገልጋይ በሆኑት መርጌታ ስምረ ግደይ አማካይነት በመረጃ አቀባይነት ሊያገለግሉኝ የሚችሉ አካላትን፣ ከየደስያቱ ሀገር ሽማግሌዎች ጋር ሊያገናኙኝ የሚችሉ ሰዎችንና ታሪካዊ ቦታዎችን በማሳየት ሊረዱኝ የሚችሉትን ግለሰቦችን ለመተዋወቅ ቻልኩኝ፡፡ ይኸውም ከጥር 19-25/2005 ዓ.ም ባሉት ቀናት የተከናወነ ነው፡፡ ሁለተኛው የመስክ ጉዞ ዋናውን የመስክ ስራዬን ያከናወንኩበት ሲሆን ከተገናኘኋቸው መረጃ አቀባዮቹም መካከል አስሩን ቁልፍ መረጃ ሰጪዎች አድርጌ የተገለገልኩባቸው ናቸው፡፡ ይሄ ጊዜ በምርምር ዘዴዎችና የመርጃ መሳሪያዎች አማካይነት መረጃዎች የተሰበሰቡበትም ወቅት ነው፡፡ በዚህ ጊዜ በደስያቱ ላይ ለ23 ቀናት ቆይታ አድርጊያለሁ፡፡ ይኸውም ከመጋቢት 24 እስከ ሚያዝያ 16/2005 ዓ.ም ያለው ቆይታ ነው፡፡ የመጨረሻው ጉዞ በቃለመጠይቅና ምልከታ ወቅት ሳይጠየቁ የተረሱ፣ ደጋግሜ ሳዳምጥ ግልጽ ያልሆኑልኝና በዛይኛ ቋንቋ ተሰብስበው ሳይተረጎሙ የቀሩ መረጃዎችን ለማስተካከል ወደ ዝዋይ የሄድኩበት ወቅት ነው፡፡ ይኸውም ከግንቦት 6-11/2005 ዓ.ም ባሉት ቀናት የተፈጸመ ነው፡፡

## 1.9. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ አቅጣጫዎች

### 1.9.1. ያጋጠሙ ችግሮች

በዚህ የምርምር ስራ ላይ ካጋጠመኝ ችግር የመጀመሪያው የዩኒቨርሲቲው የመስክ በጀት አነስተኛ መሆንና በጊዜ አለመስጠት ነው፡፡ ሁለተኛው ችግር በመስክ ከመረጃ ሰጪዎች ጋር በተያያዘ ያጋጠመኝ ነው፡፡ ይኸውም ታሪክ አዋቂ የሆኑት የሀገር ሽማግሌዎች ከዚህ በፊት የተለያዩ ምስጢራዊ ጉዳዮችን ታውቃላችሁ በሚል የደረሰባቸውን መጉላላት እያሰቡ መረጃ ለመስጠት ፍቃደኛ ያለመሆናቸው ነው፡፡ ከጥናቱ ስፍራ ጋር በተያያዘ ደግሞ በደስያቱ ላይ የመጠጥና የምግብ አቅርቦት አለመኖር፣ የማደሪያ አጦት፣ የመብራት አለመኖርና ወደ አምስቱም ደስያት እንደ ልብ ለመመላለስ የጀልባ ትራንስፖርት ችግር አበይት እንቅፋቶች ነበሩ፡፡ የትብብር ደብዳቤ በወቅቱ አለመሰጠትም ሌላው ተጠቃሽ ችግር ነው፡፡ የድጋፍ ደብዳቤ ካገኘሁም በኋላ በ2000 ዓ.ም ባህልና ቱሪዝም ካወጣው ህግ ጋር በተያያዘ በደብረ ጽዮን ገዳም በሙዚየም የተቀመጡትን ቅርሶች ለምርምር በሚመች መልኩ ፎቶ የማንሳት እድሉን አለማግኘት በምርምር ወቅት ያጋጠመኝ ችግር ነው፡፡

### 1.9.2. የተወሰዱ የመፍትሄ አቅጣጫዎች

የምርምር በጀቱ ጋር በተያያዘ ለተፈጠረው ችግር ዋና መፍትሄ የሆነው የመስክ ትግበራውን የዓሣ ምርት በሰፊው ከደስያቱ የሚወጣበትን ወቅት በመጠበቅ ዓሣ ለሚያመላልሱ ጀልባዎች አነስተኛ ዋጋ በመክፈል ችግሩን ማቃለል ነው፡፡ ከመሰረታዊ የሰው ልጅ ፍላጎት ጋር ለተያያዙት ነገሮች ስንቅ በመያዝ፣ የገዳምና አድባራቱን አባቶች በመቅረብ ማረፊያ እንዲሰጡኝ በማድረግና ወደ ዝዋይ ከተማ በመመላለስ ችግሮቹን መቅረፍ ችያለሁ፡፡ መረጃ ሰጪዎች የሆኑት የሀገር ሽማግሌዎች ፈቃደኛና ነጻ ሆነው መረጃ በመስጠት ሊተባበሩኝ የቻሉት ቀድሞ ሰው በሰው በተዋወኳቸውና በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ባላቸው ሰዎች እንዲሁም ህጋዊነቴን ባረጋገጡት የአብያተ ክርስቲያናቱ አባቶች በኩል ተአማኒነትን በማግኘት ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ መረጃ ለመስጠት ፍቃደኛ ያልሆኑ አካላት ጋር ጥሩ ወዳጅነትን ለመፍጠር ተችሏል፡፡ ፎቶ ማንሳት ያልቻልኳቸውን ቅርሶች ገለጻ በመቅረጸ ድምጽ በመቅዳት መረጃዎችን ለማስቀረት ጥረት አድርጊያለሁ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

ይህ ምዕራፍ ሁለት ክፍሎች አሉት። ቀዳማዩ ክፍል ለጥናቴ መታገጊያ በመሆን የሚያገለግሉት የፎክሎር ጉዳዮች የሚዳሰሱበት የንድፈ ሀሳባዊ ዳራ ክፍል ሲሆን ካልዓዩ ደግሞ ከእኔ ጥናት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ምርምሮች የሚዳሰሱበት የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ነው።

## 2.1. ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ

ጥናታዊ ስራው ከግብ ይደርስ ዘንድ ከጥናት መስኩ የመረጥኳቸው የተረክ (Narrative)[4] እና ቁሳዊ ባህል (Material Culture) ንድፈ ሀሳቦች ስለ ሆኑ በዚህ ዙሪያ የፎክሎር ምሁራን የዳሰሷቸውን ሀሳቦች አነሳለሁ።

### 2.1.1. የተረክ ንድፈ ሀሳብ

ከተረክ ንድፈ ሀሳብ ጋር በተያያዘ የሚነሱትን የተለያዩ ሀሳቦች ከማንሳቴ በፊት ስለ ቃሉ ፍቺ የተወሰነ ነገር ማስቀደም ተገቢ ነውና ከቃሉ ምንነት እጀምራለሁ። ተረክ[5] የሚለው ቃል "Narrative" የሚለውን የእንግሊዘኛ ቃል የሚተካ ነው። ተረክ እንደ ኢሊዮት ኦሪንግ ገለጻ "Relate" ከሚል የላቲን ቃል የመጣና ታሪክ መንገር ለሚለው ሀሳብ እንደ መጠሪያ ያገለግል የነበረ ነው። ከጊዜ በኋላ ግን ተረክ የላቀ አስተሳሰብና የስሜት መግለጫ የሆኑ ጉዳዮችን ወደ ማቀፍ ደረጃ ተሸጋግሮ ራሱን የቻለ ንድፈ ሀሳብ እንደሆነ ያስረዳሉ (Oring, 122)። የተረክን ምንነት በተመለከተም ከጉዳዩ፣ ከሂደቱና ከማስተላለፊያ መንገዱ ጋር አያይዘው በሚከተለው መልኩ ገልጸውታል።

---

[4] ፎክሎር በአራት ዋና ክፍሎች ይከፈላል። ከእነዚህ መካከል አንዱ ቃላዊ ጥበብ ነው። በቃላዊ ጥበብ ስር ከሚነሱት ዘውጎች መካከል ትልቁን ቦታ የሚይዘው ደግሞ ቡድናዊ ተረክ (Folk Narrative) ነው (Dorson, 2)።

[5] በግስ ስሮች (ት-ር-ክ) ውስጥ /ኧ/ የተባለውን አናባቢ በመጨመር የተፈጠረ ውልድ ስም ነው። ተረክ የሚለውን ግስ ታሪክን ተረክ ለማለት እንደምናውል ሁሉ ተረክ የሚለውን ስም ደግሞ ለሚተረከው ነገር መጠሪያ አድርገን መጠቀም እንችላለን። በቃሉ ውስጥም ጠብቆ የሚነበብ አንዳችም ድምጽ የለም። ተረክን "Narrative" ለሚለው ቃል አቻ አድርገው ተጠቅመውበት ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁት ዮናስ አድማሱ "አስረኛንኩዋ?" በሚለው መጣጥፋቸው ውስጥ ነው (የኢትዮጵያ የቋንቋዎችና የሥነ ጽሑፍ መጽሔት፣ ቁጥር 10፣ ገጽ 84፣ ልዩ እትም)። ቃሉን ተስማሚ ሆኖ ስላገኘሁት ተጠቅሜበታለሁ።

> Narrative is another word for story. Narrating is amethod by which an Exprience is transformed into averbal account. Experience is recapitulazed by matching averbal sequence astatements to some sequence of events which is purpoted to have occured (Oring, 121).

ተረክ የታሪክ ሌላ ስም ሆኖ የሰው ልጅ እውቀት በቃላዊ ጥበብ አማካይነት የሚታላለፍበት ዘዴ ነው። ይህም እውቀት አንድ የተፈጸመ ድርጊት በቃላዊ ቅደም ተከተል ተቀናጅቶ በሆነ አጋጣሚ ላይ ሲተረክ ነው። ተረክ ከታሪክ ጋር አያይዘው የሚያነሱበት ምክንያት ህልውናው የተመሰረተው በታሪክ ላይ እንደሆነ ለማስረዳት ነው። ይህ ደግሞ ሌሎች ምሁራንም የሚጋሩት ጉዳይ ነው። ለዚህም ሮቤርቶ ፍራንዞሲ "It is the strong the chronological succession of events that provides the basic building blocks of narrative without story there is no narrative" (Franzosi, 522) የሚለውን ማንሳት ይቻላል። ድርጊትና ሁነት ተሰናስለው የሚፈጥሩት ተረክ ካለ ታሪክ ህልውና እንደሌለው የሚያስገነዝበን ነው። የድርጊትና ሁነት መቀናጀት የድርጊትና ሁነት ባለቤት የሆኑት ገጸባህሪያት እንዲሁም ድርጊቱና ሁነቱ የሚከወኑበት መቼት አብሮ እንዳለ ያስረዳናል። የእነዚህ ሁሉ መሰረት ግን ታሪክ ነው። ስለዚህም ታሪክ ከሌለ ተረክ የለም ማለት ነው።

ተረክ የሥነ ተረክ እድገትና በአሁኑ ሰዓት ራሱን የቻለ ንድፈ ሀሳብ ነው (Brockmeier and Carbaugh. 4)። የሥነ ተረክ እድገት ነው ሲባል ሥነ ተረክ በራሱ ምንድን ነው የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ሚኪ ባል ሥነ ተረክ (Narratology) የተረክ ንድፈ ሀሳብ እንደሆነና በተረክ ውስጥ ያለውን ታሪክ፣ ድርጊት፣ ምስል፣ ባህላዊ እሴት በማየት ተረክን ለመረዳትና ለመገምገም እንዲሁም በተረክ ላይ ትንታኔ ለመስጠት የሚያስችል ትወራ እንደሆነ ያስረዳሉ (Bal, 10)። የሥነ ተረክ[6] ጥናት በቀዳሚነት የተዋወቀው የሥነ ልሳን ጥናት ላይ በተሰማሩ ምሁራን ቢሆንም ቀስበቀስ ግን የፎክሎር ባለሞያዎችም ጉዳይ መሆን ችሏል። ሥነ-ተረክ በሚተረክ ተረክ ላይ ያለውን ብቃትና ተረኩ ከሌላ ተረክ ጋር ያለውን ተመሳስሎም የምንፈትሽበት ነው።

---

[6] ከ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ራሱን የቻለ መስክ ቢሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በአንትሮፖሎጂ፣ በሥነ ጽሑፍና በሌሎች መስኮች እየተለመደ መጥቷል። አሁን ደግሞ በፎክሎሪስቶቹ እየተፈለገ ነው። በተለይ በ1963 The Journal of the Folklore Intstitute or the folktales of the world series, ከተዋወቀ በኋላ የሥነ-ተረክ ጥናት በአስደናቂ የአዕምሮ ሁኔታ እያደገ ነው (Dorson, Mythology and Folklore, P. 107)።

የተረክን ምንነት ከህልውናውና ተስተላልፎው ጋር አያይዘው Linda, Degh (54) ሲገልጹ ተረኮች በማንኛውም ማህበረሰብ እንደሚነገሩት ሁሉ በየትኛውም አካባቢና ማህበራዊ ሁኔታ ሊቀርቡ ይችላሉ። ከእድሜ አንጻር የማያረጁ፣ ከሰው ልጅ የስልጣኔ ታሪክ ጋር አብሮ የሚጓዙና ራሳቸውን እንደ ዘመኑ ሁኔታ የሚቀያይሩ ናቸው። ሲተረኩ ደግሞ ስሜትን የመግዛት አቅም ያላቸው እንደ ሆኑ ያስረዳሉ። ስለዚህም ተረክ የጽሑፍ ጥበብ ከመጀመሩ በፊት የነበረ፣ የነገሮች አመጣጥ፣ እምነት፣ ባህል፣ ማንነት ወዘተ. የሚገለጽበት፣ ሁነትና ድርጊት ተቀናጅተው የሚያስገኙት፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ በሚደረገው ቃላዊ ተስተላልፎ ህልውናው የሚጠበቅ፣ የአንድን ቡድን ወይም ማህበረሰብ ልማድ ለማስተላለፍ የሚጠቅም መሳሪያ ነው ሊባል ይችላል። የተረክ ምንነት የበለጠ ግልጽ ይሆን ዘንድ ውድወርድ ተረክ ከግለሰብ፣ ከቡድንና ከቁሳዊ ባህል ጋር አያይዘው ያነሱት በመግለጥ አበቃለሁ።

> ተረክ በግለሰባዊነትና በማህበራዊ ደረጃ የሚነገር የታሪክ ማሳያ ነው። በግለሰባዊነት ደረጃ የሚባለው ተረክ ሰዎች ስለ ራሳቸው የሚተርኩት ታሪክ ነው። ተረክ አንድ የተፈጸመ ድርጊት ነጸብራቅና ዘጋቢ ነው። ተረክ ግለሰባዊ ተናጋሪነትን የሚፈጥር፣ እሴትና እምነትን የሚያሳይ፣ ሀብትን የሚመዘግብና የሰውን ልጅ የወደፊት ህይወት አቅጣጫ መስመር የሚያሲዝ ነው።---ይህም ሲባል ግን ተረክ የግለሰብን አስተሳሰብ የሚያንጸባርቅ ብቻ ሳይሆን የባህል መሰረታዊ አካል ነው። ይኸውም ተረክ በግለሰብ ስለ ሌላ ግለሰብ ወይም ስለ ራስ የሚነገር ብቻ ሳይሆን በባህል ውስጥ የሚመሳሰስ፣ ስለ ቡዱኑ አባላት ቃላዊ ጥበብና ስለ ቁሳዊ ባህላቸው የሚተርክ ነው (Dorson, 153)።

ከተረክ ንድፈ ሀሳብ የመግቢያ ገለጻ እንደ ተገነዘብነው ተረክ ህብረተሰቡ ሰናይና እኩይ ብሎ የተቀበላቸውን ነገሮች ለተከታዩ ትውልድ ለማስተላለፍና በቀደመው ላይ ተመስርቶ አዲስ ማንነትን ለመፍጠር የሚያስችለው እንደሆነ ነው። ይሄ ደግሞ የተረክን የዘንቅነት ወይም የተምሳሌታዊነት ባህሪ ያሳየናል። ተምሳሌታዊ ሲባል ተምሳሌት እራሱ ምንድን ነው? የሚል ጥያቄን ሊያጭር ስለሚችል እግረ መንገድ መልስ ሰጥቶ ማለፉ ተገቢ ይሆናል። ተምሳሌት ከራሱ ባሻገር ያለን ነገር የሚወክል ነው። ይኸውም በቀጥተኛ ተመሳስሎ ሳይሆን በቅንያዊ አገላለጽ፣ በአጋጣሚ ወይም በስምምነት በሚፈጠር ግንኙነት የሚመጣ ነው። ተምሳሌት ከሃይማኖት ጋር ባለው ዝምድና ደግሞ የአንድን ቁሳዊ አካል ሞራላዊ ወይም መንፈሳዊ እውነት ወክሎ የሚቆም ነው (Ballenger, 169)።

#### 2.1.1.1. የተረክ ዓይነት

በተረኮቹ አይነት ዙሪያ የተለያዩ ምሁራን የራሳቸውን ዘውጎች ሰርተዋል፡፡ በማንኛውም ቦታና ጊዜ እንዲሁም ማህበረሰብ ውስጥ ሊቀርቡ የሚችሉት ተረኮች ከቅርጽ አኳያ ሲታዩ እጅግ በጣም ብዙ እንደሆኑ ይገልጻል፡፡ በቃልም ቀረቡ በጽሑፍ እንዲሁም በስዕል ወይም በግጥም በአሁኑ ጊዜ የተረክ ዓይነት ተብለው የሚጠቀሱት ሚት፣ አፈታሪክ፣ ተረት፣ አጭር ልቦለድ፣ ውዳሴ ግጥም፣ ቀልድ፣ እንቆቅልሽ፣ የሰው ልጅ ገጠመኝ፣ ታሪክና የህይወት ታሪክ ተውኔትና ስዕልን የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ (Finnegan, 36፤ Franzosi, 517, Oring, 123)፡፡ ሆኖም ግን እንደ ዊሊያም ባስኮም ገለጻ ከሆነ በዋናነት ቃላዊ ዝርው ተረኮች[7] በመባል የሚታወቁት የፎክሎር ቅርጾች ሶስት ዓይነት ናቸው፡፡ እነሱም ሚት፣ አፈታሪክና ተረት ናቸው (Bascom, 5, Oring, 124)፡፡ የእነዚህን ቃላዊ ዝርው ተረኮች ባህሪ ግልጽ ለማድረግ ባስኮም በስዕላዊ መግለጫ ያቀረቡትን መመልከቱ የተሻለ ይሆናል፡፡

| ሶስቱ የዝርው ተረክ ቅርጾች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ቅርጽ | እምነት | ጊዜ | ቦታ | አመለካከት | ገጸ ባህርይ |
| ሚት | እውነት | የሩቅ ኃላፊ | የተለያዩ ዓለማት፡- ሌላነት ወይም ጥንታዊነት | የተቀደሰ | ሰው ያልሆነ |
| አፈታሪክ | እውነት | የቅርብ ኃላፊ | የአሁኑ ዓለም | ስጋዊ ወይም መንፈሳዊ | ሰው |
| ተረት | ፈጠራ | በማንኛውም ጊዜ | በማንኛውም ቦታ | ስጋዊ | ሰውና ሰው ያልሆነ |

[7] ቃላዊ ዝርው ተረክ (Prose narrative) "Märchen" የሚለውን የጀርመንኛ ቃል ተክቶ ያገለግል የነበረውን Folktaleን ግልጽ ለማድረግ ሲባል በመስኩ ምሁራን የተፈጠረ ቃል ነው (Dorson, 3)፡፡

ከስዕላዊ መግለጫው እንደምንረዳው ሶስቱም ቃላዊ ዝርው ተረኮች ራሳቸውን የቻለ መለያ ባህሪ አላቸው፡፡ ተረት ሰውና ሰዋዊ ያልሆኑ ገጸባህሪያት ያሉት፣ ዓለማዊ የሆነ፣ በየትኛውም ጊዜና ቦታ የሚኖር፣ መቼቱ የማይታወቅ፣ ራሱን የቻለ የመክፈቻና የመዝጊያ ስርዓት ያለውና ፈጠራዊ የሆነ ነገርን የሚይዝ ነው (Bascom, 6, Oring, 126)፡፡

አፈ-ታሪክ በእውነት ላይ የሚመሰረት፣ ልማዳዊ የሆኑ ነገሮች የሚጨመሩበት፣ ገጸባህሪያቱ ሰዎች የሆኑ (ለራሳቸው የሚቆሙ ሳይሆኑ እራሳቸውን አሳልፈው ሰዎችን ነጻ የማውጣት ባህሪ ያላቸው ገጸባህሪያት የሚተውኑበት)፣ መንፈሳዊም ስጋዊ ጉዳይም የሚያነሳ፣ በዚህኛው ዓለም የተፈጸመ፣ የቅርብ ሀላፊ ጊዜ ያለው፣ መቼቱ አንዳንዴ የሚታወቅ፣ እውነትነት ያለው (የሚታመን)፣ የመክፈቻና የመዝጊያ ስርዓት ያሌለው ወይም ያልተወሰነ፣ ስለ ሰዎች ቦታዎች እና የተለያዩ ክስተቶች የሚተርክ ማለት ነው (Bascom, 6, Oring, 125)፡፡

ሚት እውነትነቱ መረጋገጥ የማይችል፣ ዓለምን ማን ፈጠረው ለሚለው ምላሽ የሚሰጥ፣ ስለ ፍጥረታትና ፈጣሪ የሚያወጋ፣ የተቀደሰ፣ ገጸባህሪያቱ ልዕለሰብ የሆኑ፣ ፍጹም መንፈሳዊነት የሚንጸባረቅበት፣ የሚታመን፣ የመክፈቻና የመዝጊያ ስርዓት የሌለው ወይም ያልተወሰነ ነው (Oring, 124)፡፡ ዊሊያም ባስኮም ይሄንን ጉዳይ ሲያጠናክሩት ሚት “ስለ አማልክትና ስለ ነገሮች አፈጣጠር የሚተርክ፣ በአማኞቹ ዘንድ ተቀደሰ ተብሎ የሚታመንበት ሰነድ ነው” (Bascom, 4) ይላሉ፡፡ ቴዎድሮስ ገብሬ ደግሞ “ሚት የሰው ልጅ የነገረ ፍጥረትና የነገረ ህላዌ እንቆቅልሾችን ለመመለስ የሞከረበት፣ እየተመሰቃቀለ ለሚያስቸግረው ዓለም ህልው ሥርዓት ለማበጀት የባተለበት እምነታዊና ፍልስፍናዊ ጥበብ ነው፡፡ ሚት የየማኀበረሰቡ የእሴት ሥርዓትም ነው፡፡” (ቴዎድሮስ፣ xii) በሚል ይገልጹታል፡፡

ከጥቅሶቹ መረዳት እንደሚቻለው ሚት አማልክትና አምላክ አከል የሆኑ ልዕለ ተፈጥሮ ኃይላትን የያዘ፣ ስለ ፍጥረት አመጣጥና ስለ ተፈጥሯዊ ልዩ ልዩ ክስተቶች የሚያትት የሰው ልጅ ህልውና የተመሰረተበት ሃይማኖታዊ ታሪክ እንደሆነ ነው፡፡ David, Leeming የሚትን ምንነት ሚትን ከማጥናት ጋር በተያያዘ ያሰፈሩት ገለጻ የሚያስረዳንም ሚት የሰው ልጅ ህልውና የታሰረበት፣ ስነ ልቦናውን በጥልቀት ለማጥናት የሚያግዝ የማህበረሰቡ የታሪክ ሰነድ እንደሆነ ነው (Leeming, 7)፡፡

የቃላዊ ዝርው ተረክ ቅርጽ ጋር በተያያዘ የተነሳውን የማጠቃልለው እኔም የምጋራውን ጉዳይ ባስኮም Jacottet የተባለውን ሰው ጠቅሰው ተረኮችን በሁለት ክፍል አጠቃለው ያስቀመጡበትን በማብራራት ነው፡፡ እነዚህም ተረት (Folktale) እና ሚታዊ አፈታሪክ (Myth-legend) የሚባሉት ናቸው፡፡ እንደ ምክንያትነት የተነሳው ነገር ሚትም ሆነ አፈታሪክ ስለ ሰው ልጅ አመጣጥና ስለ ልዕለ ተፈጥሮ ይተርካሉ፤ ሁለቱም የሚያነሱት ተመሳሳይ ድርጊትን ነው፡፡ በተራኪዎቻቸው አዕምሮ የሚታመነውም ባለፈ ጊዜ የተፈጸመ ተብሎ ነው፡፡ ስለዚህ ዝርው ተረኮች በሁለት ክፍል መጠቃለል ይቻላል፡፡ አንደኛው እውነትነት ያለው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ፈጠራዊ የሆነው ነው፡፡ ፈጠራዊ የሆነው ተረት ሲባል እውነታዊነትን የሚንጸባረቅበት ደግሞ ሚታዊ አፈታሪክ ነው (Bascom, 10)፡፡

ከላይ የተነሳውን ጉዳይ የሚያጠናክርልን ባስኮም "Four Functions of Folklore" በሚለው ጽሑፋቸው "Myth and Legend are detailed discriptions of sacred ritual, the codified belief or dogma of religies system, accounts of tribal or clan orgins, movement and conflicts." ብለው ያስፈሩት ነው (Bascom, 345)፡፡ ይህም ሚትና አፈታሪክን አንድ ላይ በማጣመር ሚትና አፈታሪክ ስለ ተቀደሰ አምልኳዊ ስርዓት፣ ቀኖናዊ እምነት ወይም ዶግማዊ የሃይማኖት ስርዓት የአንድ ጎሳ የትመጣነት እንቅስቃሴና ግጭት ላይ ጠለቅ ያለ ገለጻ የሚሰጡ መሆናቸውን የሚያስረዳ ነው፡፡ ይሄ ደግሞ ሚትና አፈታሪክን እንደ አንድ ዘውግ ከማየት የመጣ ይመስላል፡፡

### 2.1.1.2. ተረክን የማጥናት ጠቀሜታና የአጠናን ሂደት

ተረክ አንድ የተፈጸመን ድርጊት የሚገልጽ ቢሆንም የአንድን ግለሰብም ሆነ ማህበረሰብ የወደፊት እሴትና እምነት ለመፍጠር እንደ ማዕቀፍ ሆኖ የሚያገለግል ነው፡፡ ተረክ ከግለሰብ ለግለሰብ ብቻ የሚነገር አይደለም፡፡ ባህል ውስጥ የሚመላለስ፣ የማህበረሰቡ የቡድን አበላት ስለ ራሳቸው ባህልና ቁስ የሚገልጹበትም ነው (Woodword, 53)፡፡ ከዚህ የምንረዳው ተረክ ተደምጦ ብቻ የሚታለፍ ሳይሆን የአንድ ማህበረሰብ ልማዳዊ ስርዓቶቹ በነበሩበት ተጠብቀው እንዲቆዩ፣ የሰዎችን ቁጣና ንዴት ጭምር ለማብረድ፣ የተፈጥሮንና የፍጥረታትን ምንነት በመግለጽ ረገድ ሰፊ አገልግሎት እንዳለው ነው፡፡ ህብረተሰቡ ሰናይ ብሎ የተቀበላቸውን ምግባራት ወደ ተከታዩ ትውልድ እንዲዘልቁ ማድረጊያ ስልትም መሆኑን ነው፡፡

የተረክን የማጥናትን አስፈላጊነት እንደ Brockmeier and Carbaugh (1) ገለጻ ተረክ የሰው ልጅ የህይወት ዓርዓያነት ለሌላው የሚነገርበት፣ እንደ መግባቢያ የሚያገለግል (የአሁኑ ትውልድ ከአባቶቹ ትውፊት ጋር የሚገናኝበት)፣ ዓለምን የምንረዳበትና በዚያ ውስጥ የራሳችንን ማንነት የምናይበት መስታወት ነው። በዘመናውያኑ የተለያየ ዲሲፕሊን ሊሂቃን የሰው ልጅ ማንነቱን የሚሰራበትን መንገድ ለማጥናት የተረክ ንድፈ ሀሳብ ያስፈልጋል፤ ይባላል።

ከላይ ከተነሱት ጠቀሜታቸው አንጻር ተረክን ለማጥናት የሚነሳ ሰው ትኩረት አድርጎ ሊመልሳቸው የሚገቡ ጥያቄዎች አሉ። እነሱም በተረኮቹ አማካይነት የሚተላለፈው መልዕክት ምንድን ነው? ለተረኩ መፈጠር ምክንያት የሆነው ጉዳይስ? ተረኮቹን ተራኪዎቻቸውና ታዳሚዎቻቸው እንዴት አድርገው ይመለከቷቸዋል? የሚሉት ናቸው (Degh, 54)። እንደ Elliott, Oring, (135-142) ገለጻ ደግሞ በተረክ ላይ ጥናት ለማድረግ የሚነሳ አጥኚ ስለ ተረኩ አጠቃላይ ግንዛቤ ለማግኘት፣ በተረኮቹ ላይ ትርጓሜን ለመስጠትና ፍካሬን ለማምጣት አራት አውዶችን መረዳት ይጠበቅበታል። እነዚህም ባህላዊ አውድ (Cultural context)፣ ማህበራዊ አውድ (Social context)፣ ግላዊ አውድ (Individual context)ና ንጽጽራዊ አውድ (comparative context) ናቸው።

ባህላዊ አውድ የሚባለው በትረካው ውስጥ ያሉ ሀሳቦችን፣ ትዕምርቶችንና የቡድኖቹን ባህሪ የምንለይበት ነው። ውስጣዊውን የተረኩን ትርጓሜ ለማውጣት የሚያስችለን ግን አይደለም። ይሄንን ማድረግ የሚቻለው ደግሞ ማህበረሰቡ እንዴት አገልግሎት ላይ እንደሚያውለውና በተረኩና ሕዝቡ መካከል ያለውን ዝምድና ማየት ስንችል ነው። ይሄንን አጠቃላይ ድባብ ሊያስገነዝበን የሚችለው ደግሞ ማህበራዊ አውድ ነው። ሌላው አውድ ተራኪው ግለሰብ ላይ የሚያተኩር ግላዊ አውድ ነው። አንድ ተረክ የአንድን ሰው ነጠላ ታሪክም የሚያቀርብ ስለ ሆነ የተራኪውን ግላዊ ብቃትና የህይወት ተሞክሮ ልንገመግምበት እንችላለን። ይሄንን የምናደርገው ደግሞ ተራኪው ከሌሎቹ ተረኮች መርጦ የሚተርክልንን ተረክ ለምን እንደ መረጠ፣ ከሌሎቹ ለምን እንደ ወደደውና እራሱን ከተረኩ ጋር በምን መልኩ እንዳገናኘ በመገምገም ነው። በዚህ ሂደት ተረክን የሚተነትን ግላዊ አውድ ይባላል።

የመጨረሻው ንጽጽራዊ አውድ የሚባለው ነው። ይሄኛው የዓለምን የፎክሎር ተረክ የሚያነሳ ስለ ሆነ ከሌሎቹ አውዶች ፈጽሞ የተለየ ነው። ምክንያቱም በትረካው ላይ ከሚታየው ሁኔታ ውጪ በመውጣት ትረካው ሌላ ተረክን የሚጠራ መሆኑን የምንቃኝበት ነውና። በርግጥ

ይሄኛው አውድ በሁሉም ተረክ ላይ ትንታኔ ለመስጠትና ትርጓሜን ለማምጣት ይረዳል ማለት አይደለም፡፡ ፎክሎሪስቶቹ የትረካውን ታሪክ፣ መዋቅርና ተምሳሌት በማየት ከሌላ ተረክ ጋር የሚዛመድላቸው ከሆነ ሊጠቀሙበት የሚችሉት ነው፡፡ ኦሪንግ ይሄንን ጉዳይ ሲያስረዱ ከንጽጽራዊ አውድ አንጻር ትንታኔ ለመስጠት የተለያየ መንገድ ይኖራል፡፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ ተረኮች ጋር በማያያዝ ትንታኔ ለመስጠት መሞከር አንደኛው ሊሆን ይችላል፣ ይሉና ለዚህ ምሳሌ ሊሆን ይችላል በሚል እንግሊዛዊው ፎክሎረኛ ጀምስ ጆርጅ ፍሬዘር "Tree of Life and Tree of the knowledge of Good" የሚልን የሁለት ዛፎች ተረት "Tree of Life and Tree of Death" በሚል ትንታኔ ሲሰጡ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን የአዳምና የሄዋንን ታሪክ በማምጣት እንደሆነ ይገልጻሉ (Oring, 141)፡፡ ይህም የሆነው አንዱን ተረክ ከሌላው ተረክ ጋር በማነጻጸር ነው፡፡ ስለዚህ ለተረኮች ትንታኔ ለመስጠት የሚነሳ ማንኛውም አጥኚ አራቱን አውዶች አያይዞ መጠቀምን ዓላማ አድርጎ ቢነሳ ውጤታማ እንደሚሆን ያስገነዝበናል፡፡

ሩት ፊኔጋንም የሥነ ተረክ ንድፈ ሀሳብን ተጠቅመን በተረኮች ላይ የትርጎማና የአንድምታ ትንታኔ ለመስጠት ስንነሳ ከግንዛቤ ማስገባት ያለብንን ነገሮች የሚያስረዱት፡- የተረኩን ሚና መረዳት፣ ሴራውን ወይም ደግሞ ትልሙን መለየት፣ የተረኩን የአወቃቀር ቅደም ተከተል መለየትና ድምጸቱን መገንዘብ፣ የትረካውን የትኩረት አቅጣጫ መለየት እንዲሁም የድርጊቶቹን ተዛምዶ ማሳየት የሚሉ ነጥቦችን በመግለጽ ነው (Finnegan, 37-38)፡፡

በተጨማሪም ተረኮች ሲጠኑ የትኩረት አቅጣጫ መሆን የሚገባው ስለ ድርጊቶቹና ሁነቶቹ እውነትነት ወይም ሀሰት መሆን መመርመር ሳይሆን በድርጊቱ ውስጥ የተራኪውንና የአድማጩን እምነት መመርመር መሆን እንደሚገባው ሌሎች የመስኩ ምሁራን ይገልጻሉ (Dorson, 55, Sims and Stephens, 62)፡፡ የእኔም ጥናት ይሄንን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ረቂቅ የሆነውን የእምነት ጉዳይ ተጨባጭ አድርገው የሚያንጸባርቁት ተረኮች የተሰሩበትን ትዕምርት፣ ዘይቤና ምሳሌ መመርመር ነው፡፡

የተረክን ንድፈ ሀሳብ ግልጽ ለማድረግ ምንነቱን፣ ዓይነቱን፣ ጠቀሜታውንና ተረክን ማጥናት ያስፈለገበትን ጉዳይ ለማስረዳት ሞክሪያለሁ፡፡ ከዚህ አንጻር እኔም ተረክን ለማጥናት ለምን እንደፈለግሁ አያይዤ ከማነሳው ሀሳብ አንጻር ግልጽ የሚሆን ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም ተረክ የሰው ልጅ የህይወቱን ዓርዓያነት ለሌሎች የሚነግርበትና አዲስ ማንነቱንም የሚገነባበት መንገድ

እንደሆነ ተገልጿል። እነዚህን ጥበባዊ መንገዶችና ተምሳሌቶች በማጥናት የተጠኘውን ማህበረሰብ ማንነት ማሳየት ያስፈልጋል። ከቤተ እምነቶች ጋር በተያያዘ የሚተረኩትን ስለማጠና በፎክሎር ጥናት ተረክ ከየት ሊሰበሰብ ይገባል የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችል ይሆናል። ሆኖም ግን ከላይ እንዳነሳሁት የመስኩ ምሁራን የሚሉት ተረክ በማህበረሰብ፣ በቦታ፣ በጊዜ፣ በዘመን በቤተ መቅደስና ምኩራቦች ሊከፋፈልና ሊወሰን እንደማይችል ነው። ስለዚህም ከገዳምና አድባራት መመስረት ጋር ተያይዘው የመጡ ተረኮችን በመተንተን ጥበባዊ ገጽታቸውንና የተረኩን ባለቤቶች ማንነት መመርመር ይቻላልና በዚህ መንገድ ተጉዣለሁ።

### 2.1.2. የቁሳዊ ባህል ጥናት

ቁሳዊ ባህልን ዴቪድ ፕሮውን እንደሚከተለው ይገልጹታል።

> ቁሳዊ ባህል በአንድ በተወሰነ ጊዜ የነበረን ማህበረሰብ እምነት፣ እሴት፣ አመለካከት፣ አስተሳሰብና እውቀትን ከእደ ጥበባቸው አንጻር የሚያጠና ነው። በርግጥ ቁሳዊ ባህል የሚለው ቃል ለቁሶቹ መጠሪያም የሚያገለግል ሊሆን ይችላል። እኔ ግን ቁሳዊ ባህል የሚለውን እንደ ጥናት፣ የሚጠናውን ነገር ደግሞ ቁስ ወይም እደ ጥበብ በሚል እጠራዋለሁ (Prown, 1)።[8]

ከዚህ የምንረዳው ቁሳዊ ባህል የአንድ ማህበረሰብ መገለጫ ከሆነ እደ ጥበብ ተነስቶ የቡድኑን እምነት፣ ስርዓት፣ እውቀት፣ ጥበብ፣ እሴት፣ አመለካከትና አስተሳሰብ የሚያጠና መሆኑን ነው። ቁሳዊ ባህል የሚለው ቃል ለቁሶቹ መጠሪያም ለጥናት መስኩም ሊያገለግል እንደሚችልም ጭምር ነው። ሆኖም ግን ቁሳዊ ባህል የሚለውን ለጥናት ዘርፉ አድርገን ለነገሮቹ መጠሪያ በቀላሉ ቁስ በሚል መጠቀም እንደምንችል የሚያስገነዝበን ነው። ስለዚህ በእኔ ጥናት ውስጥም ሲብራራ ቁሳዊ ባህል የሚለው መጠሪያ እንደ ጥናት መስክነቱ ነው።

---

[8] Material culture is the study through artifacts of the beliefs, values, attitudes, and assumptions of apopular community or society at agiven time. The term Material Culture also frequently used to refer to artifacts themselves, to the body of material available for such study. I shall restrict the term to mean the study and refer to the evidence simply as material or artifacts (Prown,1).

### 2.1.2.1. የቁሳዊ ባህል ዓይነት

የቁሳዊ ባህል ዓይነት ሲነሳ በቀዳሚነት የሚጠቀሰው ዶርሰን በአምስት ዘውግ የከፈላቸው ናቸው፡፡ እነዚህም ሀገረሰባዊ የእጅ ስራ፣ ሀገረሰባዊ ስዕል፣ ሀገረሰባዊ ምህንድስና፣ ሀገረሰብዊ ተውህቦና የምግብ አሰራር የሚባሉት ናቸው (Dorson, 2)፡፡ በእነዚህ ስርም ሌሎች ዝርዝር አይነቶች ይነሳሉ፡፡ በዚህ በቁሳዊ ባህል ስር ከሚጠኑት ጉዳዮች መካከል ለአምልኮት መፈጸሚያ የሚውሉ እቃዎች፣ የማምለኪያ ቤቶችና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው ቁሶች ይጠቀሳሉ፡፡

ቤተ እምነቶችና ሌሎች ተያይዘው የሚነሱ ቁሶች ሲጠኑ ግን እንደማንኛውም ባህላዊ እቃዎች የሚጠኑ አይደሉም፡፡ ምክንያቱም በሃይማኖቱ ዐይን እንዴት ይታያሉ የሚለውም ጭምር መታየት ይገባዋልና፡፡ ቁሶቹ ሲጠኑ መሰረታዊው ጥያቄ ከሃይማኖቱ ወይስ ከፎክሎሩ ተነስተን እንመልከታቸው የሚለው ነው፡፡ Danielson (44) ይሄንን ጉዳይ ሲያብራሩ ሃይማኖታዊ ጉዳይን ለመጥናት የሚነሳ ተመራማሪ የሚያምንበትም ይሁን የማያምንበት ከውስጥ ተነስቶ መሆን እንደሚገባው ያስረዳሉ፡፡ ስለዚህ በቅድሚያ ቁሶቹን ሃይማኖቱ ምን ይላቸዋል? እንዴት ይገለገልባቸዋል? የሚሉትንና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን በመመርመር ወደ ፎክሎራዊ ገጽታቸው መምጣቱ የተሻለ ይሆናል፡፡

### 2.1.2.2. ቁሳዊ ባህልን የማጥናት ተግባርና የአጠናን ስልቱ

የቁሳዊ ባህልን የማጥናት ጠቀሜታን ለማሳየት ቁሳዊ ባህልን የፎክሎር ጉዳይ ምን አደረገው ከሚለው ጥያቄ ብነሳ ግልጽነት ያለው ጠቀሜታ ማስቀመጥ የሚቻል ይመስለኛል፡፡ ለጥያቄው ምላሽ የሚሆነው ሄነሪ ግላሴ ያስቀመጡት ሀሳብ ነው፡፡ ይኸውም የቁሳዊ ባህል ጥናት የፎክሎር መስከኞች ብቻ ሳይሆን የታሪክ፣ የቅርስና የጥበብ አጥኚዎች፣ የመልካምድርና የሥነ ሰብ ተመራማሪዎች፣ የሙዝየም ባለሞያዎች፣ ነገዴዎችና የቁሳዊ ባህል ሰብሳቢዎች የጋራ ጉዳይ ነው፡፡ የጋራቸው ጉዳይ የሆነበት ምክንያትም የሰውን ልጅ በፈጠረው ባህል ውስጥ መረዳት ማስቻሉ ነው (Glassie, 71-72) የሚለው ነው፡፡ ስለዚህ ቁሳዊ ባህል የሰውን ልጅ ማንነት መናገር የሚችል ስለ ሆነ በፎክሎር ይጠናል ማለት ነው፡፡

ዴቪድ ፕሮውን ለዚህ ጉዳይ ምላሽ ሲሰጡ ደግሞ ቁሳዊ ባህልን ማጥናት የሚያስፈልግበት ምክንያት ብለው ዘርዘር ያሉ ጉዳዮችን አስፍረዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ በቀዳሚነት የጠቀሱት

የጥበባዊ እሴት መገለጫ መሆኑን ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ የተፈጥሮ ስጦታና መንፈሳዊ እሴትን የመሳሰሉትን ይጠቀሳሉ። ሌላው ታሪካዊ ድርጊትን የሚያንጸባርቅ መሆኑ ነው (ከቃል የበለጠ የመረጃ ወካይ ያለው ነውና)። በሶስተኛ ደረጃ ያነሱት ባህላዊ ገጽታን የሚያሳይ መሆኑን ነው (Prown, 3)። በዚህ ክፍል ያነሱት ነገር ጠቅለል ሲደረግ የቁሳዊ ባህል ጥናት ጠቀሜታ የአንድ ማህበረሰብ ፖለቲካዊ ርዕዮተ ዓለም፣ የስራ ባህል፣ የአምልኮ ስርዓት ምን እንደሚመስል ለመረዳት የሚያገለግል መሳሪያ እንደሆነ ነው።

በአጠቃላይ ቁሶችን ማጥናት ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት ከዕለት ተዕለት ግልጋሎታቸው ባሻገር ትርጉም ያላቸው፣ የሰዎቹን እሴቶች፣ አመለካከቶችና ፍላጎቶች እንዲሁም የዘመኑን መንፈስና የማህበረሰቡን የህይወት ልምድ የሚያንጸባርቁ መሆናቸው ነው (Jones, 9)። ይሄንን ጉዳይ ግላሲ በምሳሌ አስደግፈው ሲያስረዱ የእርሻ መሳሪያዎችን በማጥናት ስለ አራሾቹ፣ የአደን መሳሪያዎቹን በመመርመር ስለ አዳኞቹ ወይም ደግሞ የእምነት ተቋማትን በመመርመር የአማኞቹን የህይወት አተያይና እሴቶች መረዳት ስለሚያስችል ነው (Glassie, 143) ይላሉ።

የቁሳዊ ባህል ጥናት አስፈላጊነት ከላይ በቀረበው መልኩ ከተነሳ ቁሶች እንዴት ይጠናሉ የሚለው ጉዳይ ቀጥሎ የሚነሳ ይሆናል። ቁሶችን በተቀላጠፈ ሁኔታ ለማጥናት በተለያየ ዘውግ ማዋቀሩ የተሻለ እንደሆነም በምሁራኑ ይገለጻል። አንዱ በአንዱ ውስጥ በሚያደርገው ጣልቃ ገብነት የተነሳ ክፍፍሉን መፍጠር ሌላው አስቸጋሪ ጉዳይ ቢሆንም በሀገረሰባዊ ልምዶችና በሃይማኖታዊ ፎክሎር መካከል የሚፈጠረውን ውስብስብነት ለመቀነስ በተለያዩ ዘውጎች ከፋፍሎ ትንታኔ ለመስጠት መሞከሩ የተሻለ ነው። አስቸጋሪውን ሂደት ለመቀነስ ቁሱ የተሰራበትን መሰረት በማድረግ፣ የአሰራር ጥበብን በመመርኮዝ ወይም አገልግሎቱን ከግምት ውስጥ በማስገባት ዘውግ ፈጥሮ ትንታኔ ለመስጠት መሞከር አንዱ አማራጭ እንደሆነ ይጠቅሱና የተሻለው ግን አገልግሎትን በመመርኮዝ የሚደረገው ክፍፍል እንደሆነ ያስረዳሉ (Prown, 2, Glassie, 252)። ስለዚህ በእኔም ጥናት አገልግሎትን መሰረት በማድረግ ለቁሶቹ ገለጻ ከተደረገ በኋላ ከባህላዊ እሴትነታቸው አንጻር በቁሱና በባለቤቶቹ መካከል ያለውን ዝምድ በማሳየትና ከፍ ሲልም በቁሶቹ አማካይነት የተፈጠረውን ማንነት በመመርመር ትንታኔ ለመስጠት ጥረት ተደርጓል።

የአጠናን ስልትን በተመለከት ፈቃደ (15) ሲገልጹ "እቃውን እራሱን ማጥናት አንድ ዋና ተግባር ሲሆን አሰራሩን ማጥናት ደግሞ ሌላው ነው" እንደሚሉት ሁሉ ከመስሪያ እቃው፣ ከአሰራር

ጥበቡና ተግባሩ ተነስተን የቁሶቹን አንድምታዊ ትርጓሜ ሀገረሰባዊ ጥበብነታቸው ማሳየት እስከሚያስችለን ድረስ መጓዝ እንችላለን፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ቁሶችን ሀገረሰባዊ የሚያሰኛቸው ምንድን ነው የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችል ይሆናል፡፡

ጆርጅና ጆንስ የቁሶችን ሀገረሰባዊነት ሲያብራሩ ቁሶቹን ሀገረሰባዊ የሚያስብላቸው በዓይን የሚታዩና በእጅ የሚዳሰሱ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን የሚሰሩበት ነገር፣ አሠራራቸውና የሚሰጣቸው ስያሜም ጭምር ነው (Georges and Jones, 94) ይላሉ፡፡ ሀገረ ሰባዊነትን ከጥንታዊነት ጋር አያይዘው ዶርሰን ሲያብራሩ ደግሞ አሮጌ የሆነ የእጅ ስራ በሙሉ ሀገረሰባዊ ነው፤ የአሁን ቅርስ ደግሞ ሀገረሰባዊ አይደለም ማለት አይቻልም፡፡ ምክንያቱም ባህላዊ የሚያሰኛቸው እድሜ ሳይሆን የሀገረሰባዊነት ዋጋ ነውና (Dorson, 234)፡፡ ከዚህ የምንረዳው ነገር ባህላዊነት የሚገለጸው ከጥንታዊነት ይልቅ ሀገረሰባዊ በመሆን ነው፡፡ ስለዚህ የቁሳዊ ባህል ሀገረሰባዊነት መገለጫ ከዘመናዊ ኢንደስትሪ በፊት ጀምሮ እስከ አሁን ያለ፣ የማህበረሰቡ የጥበብ ውጤት የሆነ፣ የሚሰራበት መንገድና የመስሪያ እቃው ባህላዊ መሆን፣ የማህበረሰቡ እውቀትና ክህሎት የፈሰሰበት እንዲሁም የቁሱ ከግለሰቡም ሆነ ማህበረሰቡ የእለት ተዕለት ኑሮ ጋር እጅግ የተቆራኘ መሆን ነው፡፡

### 2.1.3. የዝርው ቃላዊ ተረክና ቁሳዊ ባህል ዝምድና

በዚህ ጥናት ተረኮችን ከቁሳዊ ባህል ጋር አያይዞ ማጥናት ያስፈለገበት ዓብይ ምክንያት ተረኮቹ በቁሳዊ ባህሎቹ አማካይነት ተጨባጭ ስለሚሆኑ አንዱን ከሌላው ለያይቶ ለማጥናት መነሳት ጥናቱን ጎደሎ እንዳያደርገው በመስጋት ነው፡፡ ምክንያቱም በፎክሎር ዘውግ ውስጥ አንዱ በአንዱ ውስጥ የመምጣት ነገር ስላለ ለያይቶ መመልከት ይከብዳል፡፡ ሲምስና እስቴፈንስ ይሄንን በዘውግ መከፋፈልን አስቸጋሪነት በምሳሌ የሚገልጹት አንድ የሰርግ ስርዓትን ለማጥናት ብንነሳ ቃላዊ ዜማው አለ፤ እንደ ገና ዜማው እየወረደ ሲጨፈር የዳንስ ጥበብ አለ፤ ስርዓቱን ማድመቂያ ቁሶችም ይኖራሉ፤ እነዚህን ነጣጥሎ ማጥናት ደግሞ ከባድ ነው (Sims and Stephens, 17-18) በማለት ነው፡፡ ዝርው ቃላዊ ተረኩንና ቁሳዊ ባህሉን አዛምዶ ማጥናት የተፈለገበት ዋናው ምክንያትም በዚህ ሂደት የሚፈጠረውን ክፍተት ለማጥበብ ተፈልጎ ነው፡፡

ቃላዊ ፎክሎሩንና ቁሳዊ ባህሉን ስናነጻጽር ቁሶች ቶሎ የሚለወጡ እውነትን አግዝፈውም ይሁን አንኳስሰው የሚነግሩን አይደሉም፡፡ የሚያመለክቱን ነገር ቢኖር ያንኑ ያለውን ነው(Oring, 200)፡፡

ከዚህ የምንገነዘበው ነገር ቁሳዊ ባህልን ከቃላዊ ፎክሎር የሚለየው የተአማኒነታቸው ጉዳይ መሆኑን ነው፡፡ ቁሶች አንዴ ከተሰሩ በኋላ ሰሪዎቻቸው ባይኖሩም እነሱ ባለቤት ሆነው ለዘመናቸው ምስክር ይቆማሉ፡፡ ራሳቸውን ችለው ታሪክ ይሆናሉ፡፡ የእነዚህ ታሪካዊ ቁሶች መጠናት ደግሞ ሰሪውን ማህበረሰብ፣ የማህበረሰቡን አመለካከት፣ ርዕዮተ ዓለም፣ እምነት፣ በጥቅሉ ማንነታቸውንና ምንነታቸውን ለመመርመር ይረዳል፡፡ ምክንያቱም ቁሳዊ ባህሎች ዘመን ተሻጋሪ የሆኑ፣ የሚጨበጡና የሚዳሰሱ፣ ለሌላ ተደራቢ ነገር በውክልና የሚቆሙና ከሚሰሩበት ቁሳቁሶች የተነሳ የጥበብ መገለጫ የሚሆኑ ናቸው፡፡ ስለዚህም የሰው ልጅን ታሪክ ለማጥናት ይመረጣሉ፡፡ የሰውን ልጅ ታሪክ ለማጥናት ብቸኛው መንገድ ቁሳዊ ባህል ነው ማለት ግን አይደለም፤ ቃላዊ ጥበብ አለና፡፡

ቁሳዊ ባህል ከቃላዊው ጥበብ ጋር በጥምረት ካልታየ ደግሞ አንድን ጥናት ምሉዕ አያደርገውም፡፡ አንድ ማህበረሰብ ስለ ራሱ የህይወት ልምድ፣ እሴት፣ ኑሮ በቁሶቹ አማካይነት ሲያወራ ለቁሶቹ ተረክ ፈጥሮላቸው ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ Ian, Woodword የተረክና ቁሳዊ ባህልን ተዛምዶ ሲያስረዱ የቁስ ትረካ የሚባል አለ፡፡ ይኸውም ሰዎች ስለ አኗኗራቸው፣ እሴታቸውና ገጠመኛቸው እንደሚተርኩት ሁሉ ስለ ቁስም የሚተርኩት ነው (Woodword, 152) ይላሉ፡፡ ይህ የሚያሳየን ቁሶቹ ራሳቸው የሚገለጹት በትረካ እንደሆነ ነው፡፡ ለዚህም ነው ቃላዊ ተረኩን ከቁሳዊ ባህሉ ጋር በማገናኘት ለማጥናት የተፈለገው፡፡ ቃላዊ ጥበቡና ቁሶቹ ሲጠኑ መነሻ እንጂ ዋና ግቦች አይደሉም፡፡ ምክንያቱም የጥናት ዓላማ መሆን የሚገባው በሁለቱ የፎክሎር ዘውጎች የማህበረሰቡን ባህልና እምነት መርምሮ ማውጣት ነው፡፡ ይሄንን ጉዳይ ዶርሰን "Folklore and Folk Life" በሚለው መጽሐፋቸው ሲጠቀልሉት "ቃላዊ ጥበብና ቁሳዊ ባህልን የሚያገናኛቸው ድልድይ ባህላዊ የህይወት መስመር ነው" (Dorson, 3) በማለት ነው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ባነሳኋቸው ንድፈ ሀሳቦች አማካይነት ፎክ ቡድኑ ስለሚተርካቸው ተረኮችና ስለሚገለገልባቸው ሃይማኖታዊ ቁሶች እንዲሁም ተረኮቹና ቁሶቹ ስለሚኖራቸው ትዕምርት እንዲሁም ትዕምርቱ ስለሚፈጥረው ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በትንታኔ ክፍል ለማሳየት ሞክሪያለሁ፡፡

## 2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ይህ ንዑስ ርዕስ ከእኔ ጥናት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥናቶች የተቀኙበት ክፍል ነው፡፡ እነዚህም በትምህርት ክፍሉና ከክፍለ ትምህርቱ ውጪ የተሰሩ በሚል በሁለት ንዑሳን ክፍሎች ተደራጅተው ቀርበዋል፡፡

### 2.2.1. በትምህርት ክፍሉ የተሰሩ ጥናቶች

በዚህ ክፍል የቀረቡት ጥናቶች በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የተደረጉ ሆነው በርዕሰ ጉዳይ ከእኔ ጥናት ጋር ተመሳስሎ ያላቸው ናቸው፡፡ በመጀመሪያ የማነሳው ከእኔ ጥናት ጋር በተወሰነ መልኩ ተመሳስሎ ያለውና በ2003 ዓ.ም በሞገስ ጀንበር "ከዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም አመሰራረት ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮችና አምልኳዊ ስርዓቶች" በሚል ርዕሰ ጉዳይ የተጠናውን ነው፡፡ የጥናቱ ዓላማም ከገዳሙ አመሰራረት ጋር ተያይዘው በሚነገሩ ተረኮችና በገዳሙ ውስጥ በሚፈጸሙ አምልኳዊ ስርዓቶች የገዳማውያኑ እምነት ምን እንደሚመስል መመርመርና ይህም እምነት ለገዳማውያኑ ያለውን ፋይዳ ማሳየት ነው፡፡ በዚህም የደሴቱ ተፈጥሯዊ አቀማመጥ የኖህ መርከብ፣ የመስቀልና የመሶበ ወርቅ ቅርጽ ያለው መሆኑ፤ የተሰወረ የመድኃኒዓለም ኃይል አለበት መባሉን፤ በገዳሙ ጠላቶች ላይ ጥቃት የሚያደርስ ለቅዱሳኑ እርዳታ አለ ተብሎ የሚታመን፣ አጽሞች ቅድስናውን የሚያከብሩለት ገዳም ነው የሚል እምነት ያለመሆኑን የሚያሳዩ ተረኮች አሉ፡፡ እነዚህ ተረኮች ገዳማዊ ህይወትን የመትከልና የማጠናከር ተግባር እንዳላቸው ገልጿል፡፡ የአምልኮዊ ስርዓቶቹም ለገዳማውያኑ መንፈሳዊ ድባብን ከማስረጽ በተጨማሪ ገዳማዊ ህይወትን የማጽናት ተግባር እንዳላቸው አሳይቷል፡፡

ከላይ በዝርዝር ከቀረቡት ጉዳዮች መገንዘብ እንደሚቻለው ጥናቱ የተነሳበት ዓላማና ያገኛቸው ግኝቶች ግብ የመቱ ናቸው፡፡ ይሄ ደግሞ የጥናቱን ጠንካራ ጎን የሚያሳየን ነው፡፡ የገዳማዊ ህይወት አጀማመርን ከጣና ሐይቅ ደስያት ገዳማት ጋር በተያያዘ ያቀረበው መረጃም በጣም ጥሩ ነው፡፡ በጥናቱ ታካይ ክፍል የቀረቡት የአባሪ ፎቶዎችና የቃለመጠይቅ ጥያቄዎች ሳይቀሩ በስርዓቱ ዋቢ መደረጋቸው የጥናቱን ጥንካሬ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ከዚህ በተቃራኒ ግን በጥናቱ ላይ የሚስተዋሉ ክፍተቶች አሉ፡፡ የጥናቱ ዳራ ስለ ቃላዊ ተረኩና ቁሳዊ ባህሉ መንደርደሪያ

የሚሆኑ ጉዳዮችን በማንሳት በመስኩ ያለውን ክፍተት በማሳየት የሱን ጥናት አስፈላጊነት ማመልከት ሲኖርበት ስፊውን ገለጻ ያደረገው ስለ ኢትዮጵያ ሥነ ቃል ስብሰባና ጥናት ነው። ይሄ ደግሞ በፊ.ቃደ አዘዘ "የሥነ ቃል መምሪያ" መጽሐፍ ላይ የቀረበውን ሀሳብ በሙሉ አሳጥሮ ማስቀመጥ ይመስላል።

የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎቹ የታተሙ ጽሑፎች፣ ምልከታና ቃለመጠይቅ ናቸው። ስለ ዘዴዎቹ ምንነት፣ ለጥናቱ ተገቢ ስለ መሆናቸው፣ እንዴት እንደሚጠቀማቸው የሚያሳዩ መረጃዎች አላሰፈሩም። በንድፈ ሀሳብ ደረጃም ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብን ለመረጃ መተንተኛነት እጠቀማለሁ ከሚል የዘለለ ንድፈ ሀሳቡ ለትንታኔው ተመራጭ ነው የሚያስብለው አካዳሚያዊ እውቀት አልቀረበበትም። በክለሳ ድርሳኑ አራቱን የፎክሎር ዘውጎች አስተዋውቆ ሰፊውን ገለጻ ሲሰጥ የምናገኘው አንዱን ምዕራፍ በያዘው ሀገረሰባዊ ልማድ ላይ ነው። አንዱ ምዕራፍ የተረኮች ጉዳይ ሆኖ ሳለ ተረኮቹን የሚመለከተው ግን ውስን መረጃ ነው። በጥናቱ ቃላዊ ተረኮቹና ሀገረሰባዊ ልማዶቹ የተገናኙበት መስመርም አልተስተዋለም። በተዛማጅ ጥናቶች ቅኝቱም ከዓላማው ጀምሮ ይዘቱን በአጭሩ ያስቀምጣል እንጂ ዘዴ፣ ደካማና ጠንካራ ጎን፣ የጥናቱ ግብ ምን ይመስላል፣ የውጤቱ አንድምታ ተገልጿል ወይ የሚሉ ነገሮች አልታዩበትም።

የሞገስ ጀንበር የምርምር ስራ ገዳማዊ ተረኮችን በመሰብሰብ በመደረጉ ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ነገር አለ። የእኔ ጥናት ግን ለተረኮቹ በቂ የሆነ የንድፈ ሀሳብ ማዕቀፍ በማስቀመጥ የተሰራ በመሆኑ አካሄዱም ሆነ ግኝቱ የተለየ ነው። በሌላ መልኩ የእሱ ጥናት የትኩረት አቅጣጫው አምልኳዊ ስርዓቶች ናቸው። በእኔ ስራ ከተረኮቹ ጋር ተሰናስለው የቀረቡት ቁሳዊ ባህሎች ናቸው። የዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራት አምልኳዊ ስርዓቶች የእኔ ዋና የትኩረት አቅጣጫ ባለመሆናቸውና በሞገስ ጥናት ቁሳዊ ባህሎች ባለመነሳታቸው እንለያያለን።

በ2003 ዓ.ም በተስፋዬ ተገኘ "የደብረ ነጎድጓድ ሐይቅ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞዓ አንድነት ገዳም አመሠራረትና ቁሳዊ ባሕል ጥናት" በሚል ርዕስ የተደረገው ምርምር ሌላው የዳሰስኩት ጥናት ነው። የጥናቱ አብይ ትኩረት የገዳም አመሰራረት፣ የገዳማውያን የዕለት ተዕለት ህይወት፣ አለባበስና በሰውነት ላይ የሚያደርግ ቁስ ነው። በዚህም የገዳማውያኑ ምግብ ዳቤ፣ የሚለብሱት ቀሚስ፣ የሚያደርጉት ቆብ፣ ለጸሎት የሚጠቀሙበት መቁጠሪያ ሁሉ ተምሳሌታዊ

መሆናቸውን በግኝቱ ለማሳየት ይሞክራል። ጥናቱ እንደ አጠቃላይ ሲታይ የገዳሙን የአመሰራረት ተረኮችን በማንሳት፣ ቁሳዊ ባህላቸውን በመመርመር ተምሳሌታዊ ፍቺ ለመስጠትና ፎክሎራዊነታቸውን በትንታኔ ለማሳየት መነሳቱ ጠንካራ ጎኑ ነው። ሆኖም ግን ጥናቱ የሄደባቸውና የደረሰባቸው ነገሮች ስንመለከት ብዙ ክፍተት አለበት። በመጀመሪያ ጥናቱ ዳራ የለውም። በመግቢያ ሀሳብ ምዕራፎችን ካስተዋወቀ በኋላ በቀጥታ ወደ አነሳሽ ምክንያት ይሄዳል። የጥናቱ ወሰን ደግሞ የዳራውን ሀሳብ የያዘ ይመስላል። ኢትዮጵያ የብዙ አብያተ ክርስቲያናት ሀገር እንደሆነች በሰፊው አስፍሮበታልና። በሥነ ዘዴ ክፍሉ ለመረጃ መሰብሰቢያ ቃለመጠይቅና የምልከታ ዘዴን እንደ ተጠቀመና መረጃው በገላጭ የምርምር ዘዴ የቀረበ መሆኑን ይጠቅሳል። ሆኖም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችና የትንተና ስልቶቹ በስርዓት ያልቀረቡበት ጥናት ነው። ምክንያቱም ዘዴዎቹ ምን አይነቶች እንደሆኑ፣ እንዴት እንደ ተመረጡና ለምን እንደ ተመረጡ ሁሉ የሚገልጽ ምሁራዊ መረጃ የለውም። የፎክሎር ጥናት ሆኖ ሳለ ከመስኩ የተመረጠ የመተንተኛ ንድፈ ሀሳባዊ ዘዴ አልታየበትም። ከዘዴው እንደምንረዳው ትንተናው የትርጎማና የፍካሬ ስልት ሳይኖረው ሙሉ በሙሉ በገለጻ ስልት ብቻ የቀረበ ነው። ይሄ ደግሞ የፎክሎር ጥናት ዓላማ መቀረጽ ብቻ ነው ያስብላል።

የክለሳ ድርሳኑን ሰፊ ክፍል የያዘው የገዳማዊ ህይወት ገለጻ ነው። የቁሳዊ ባህልን ሀሳብም አንድ ላይ ከገዳሙ ጋር አንስቷል። በምን ምክንያት አንድ ላይ እንዳመጣቸው አይታወቅም። መረጃውም በጣም የሳሳ ነው። ተረኮቹን ያየበት ንድፈ ሀሳባዊ መርህ የለም። ጥናቶችን ሲቃኝም ዓላማቸውን ጠቅሶ በጥናቱ የተነሳውን ዝርዝር ሀሳቦች ጨምቆ ከማቅረብ ሌላ ደካማና ጠንካራ ጎናቸው፣ ዘዴያቸው፣ ዓለማቸው ግብ መምታት አለመምታቱን አይገልጽም። በምዕራፍ ሶስት የቀረበው መረጃም ግልጽነት ይጎድለዋል። ለአካባቢው ዳራ ይቅረብ ለትንተና አይታወቅም። ስለ አመሰራረት በሚል ጀምሮ ስለ አካባቢው ያነሳና ከዚያ ወደ ተረኮች ያልፋል። በተረኮቹ ላይ ደግሞ ትንታኔ ሲሰጥ አይስተዋልም። ታሪኩን መዘገብን ዓላማ አድርጎ የተነሳ እስኪ መስል ድረስ ተረኮችን በተከታታይ ያቀርብልናል። የገዳሙን የሥራ ክፍፍልና አይነትን ያነሳል፤ ስለ ስራና ስንፍና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማብራሪያ ያቀርባል። ከጥናቱ ጋር የሚገናኝበት መንገድ ግን አልታየም። በምዕራፍ አራት ያነሳቸው የገዳማውያኑን አመጋገብ፣ አለባበስና በሰውነታቸው ላይ የሚያደርጓቸውን ቁሶች በተመለከተ ስርዓታቸውን ከመዘገብ ያለፈ ተምሳሌታዊ ፍቺ፣ ፋይዳ የሚል ነገር አላነሳም። ለምሳሌ፡- ስለ መቁጠሪያ ያነሳና ጸሎት ሲያደርሱ 12 ጊዜ አልያም 36

ጊዜ እንደሚቆጠር ይገልጻል፡፡ መቁጠሪያ ምንድን ነው፣ እንዴት ተጀመረ፣ ለምን በቁጥር ተለክቶ ይቆጣራል፣ ምሳሌው፣ አንድምታው፣ ከገዳማዊያኑ ጋር ያለው ዘምድና የሚል ጥያቄ ቢነሳ መልስ የለውም፡፡ ስለ ግንዘት ያነሳል ግንዘት በቁሳዊ ባህል ውስጥ እንዴት እንደ ተነሳ ግልጽ አይደለም፡፡ ምክንያቱም የግንዘት ስርዓት በፎክሎር ጥናት ከተነሳ ወይ በልማድ ውስጥ የሚጠና ነው አልያም ደግሞ ክዋኔ ውስጥ የሚነሳ ነው፡፡ የተስፋዬ ጥናት ደግሞ ይሄ አይመለከተውም፡፡ ስለዚህ ለመነኮሳት እንደዚህ አይነት የግንዘት ስርዓት ይደረጋል የሚለው የጸሎተ ፍትሐት ገለጻ ካለቦታው የገባ ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ ፎክሎራዊ ጥናትነቱን ለማየት ይቸግራል፡፡ ነገር ግን መነኮሳቱ በአለባበሳቸው፣ በአመጋገባቸውና በቁሳዊ ባህላቸው ከዓለማውያን የሚለዩበት ስርዓት ተምሳሌታዊ ገጽታ እንዳለው ለማሳየት እንደፈለገ መረዳት አያዳግትም፡፡ በቃለመጠይቅ የተሰበሰቡት መረጃዎች ቃል በቃል በአባሪ ክፍል የቀረቡበት መንገድ ጥሩ ነው፡፡ ምክንያቱም አንደኛው የጥናቱ ዓላማ መሰነድ ስለ ሆነ፤ በቁሳዊ ባህል ውስጥ ግን አንድም በፎቶ የተደገፈ መረጃ አለመኖሩ ጥያቄ የሚያስነሳ ነው፡፡ ምናልባት ፎቶ ያልተፈቀደለት ከሆነ በጥናቱ ያጋጠመው ችግር ላይ መግለጽ ነበረበት፡፡ በአባሪ ክፍል እንኳ ምናገኘው አራት ፎቶ ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ እንደ ቁሳዊ ባህል ጥናትነቱ ክፍተት አለበት፡፡

የተስፋዬ ጥናት የገዳምን አመሰራረት ከቁሳዊ ባህል ጋር አያይዞ ስለሚያጠና የሚያመሳስለን ነገር አለ፡፡ በእሱ ጥናት የአመሰራረት ተረኮች እንደ ተነሱት በእኔም ጥናት ተነስቷል፡፡ ቁሳዊ ባህል በእሱ ጥናት ቦታ እንደ ተሰጠው ሁሉ በእኔም ስራ የሚዳሰስ ሆኗል፡፡ ሆኖም የእሱ ጥናት ሰፊውን ዳሰሳ ያደረገው ከገዳማውያኑ ህይወት ጋር በተያያዘ ሲሆን የእኔ ደግሞ በገዳምና አድባራቱ ተረክና ቁሳዊ ባህል በኩል የደስያቱን ማህበረሰብ እምነትና ማንነት ስለሚመረምር ይለያል፡፡ በሥነ ዘዴ አቅጣጫ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችና የፎክሎር የመተንተኛ ንድፈ ሀሳቦች በሰፊው ተዳስው ተግባራዊ ስለ ተደረጉ፣ ተምሳሌታዊ ጉዳዮች በትርጉማና የፍከራ ስልት ተተንትነው ስለ ቀረቡ ከተስፋዬ ጥናት ይለያል፡፡ በአጠቃላይ ጥናቱ የተጓዘበት መንገድና የደረሰበት ግብም ከተስፋዬ ጥናት የተለየ ነው፡፡

በምህረት ተስፋዬ በ2003 ዓ.ም የተደረገው ጥናት ሌላኛው በተዛማጅ ጽሑፌ የቃኘሁት የምርምር ስራ ነው፡፡ "ከጣና ቂርቆስ የአንድነት ገዳም አመሰራረት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ጥናት" የሚል ርዕስ ይዞ የተነሳ ነው፡፡ ምርምሩ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች በገዳማውያኑ ዘንድ እምነትን በመትከልና በማጠናከር ረገድ ያላቸውን ሚና የማሳየትን

ዓላማ ያነገበ ነው፡፡ የተነሳበትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ መረጃውን በቃለ መጠይቅና በምልከታ ዘዴ ሰብስቧል፡፡ በግኝቱም ተረኮቹና ቁሳዊ ባህሎቹ ገዳማውያንን በበዓታቸው ጸንተው እንዲኖሩ የማድረግና የስፍራውን ህልውና የማስጠበቅ ሚና እንዳላቸው አሳይቷል፡፡

ጥናቱ የገዳማዊ ህይወትን አጀማመር በማስቀኘት በቂ መረጃ ማቅረቡ በመጀመሪያ የሚነሳለት ጠንካራ ጎን ነው፡፡ ለተረኮቹ ያቀረበው ነገር ባይኖርም ቁሳዊ ባህልን ለመተንተን የተጓዘበት መንገድ፣ እያንዳንዱን ቁስ በፎቶ አስደግፎ ማቅረቡ፣ ዓላማው ግብ ይመታ ዘንድ የሚያቀርባቸው ሌሎች መረጃዎች በጣም ጥሩ በመሆናቸው እንደ ጠንካራ ጎን የሚነገርለት ነው፡፡ በአንጻሩ ጥናቱ የተወሰኑ ክፍተቶችም አሉበት፡፡ ከዘዴው ብንነሳ የቃለመጠይቅና የምልከታ ዘዴን እንደሚጠቀም እንጂ ለምን እንደ ተመረጡ፣ እንዴት አገልግሎት ላይ እንደሚውሉ፣ ያላቸው ጠንካራና ደካማ ጎን፣ ክፍተታቸውን ለሞምላት የተደረገን ሂደት የሚገልጽ ነገር የለውም፡፡ የመረጃ አቀባይ የናሙና አመራረጡም በራሱ መንገድ እንጂ በመስኩ የሚነሳውን እውቀት መሰረት ያደረገ አይመስልም፡፡ በአተናተን ዘዴው እንደ ተገለጸው በዋናነት አገልግሎት ላይ የዋለው ንድፈ ሀሳብ የተምሳሌታዊ መስተጋብራዊነት ንድፈ ሀሳብ (Symbolic Intractionalism theory) ነው፡፡ ሆኖም ስለ ንድፈ ሀሳቡ ምንነት፣ አስፈላጊነትና እንዴት እንደሚጠቀምበት አያሳይም፡፡ በተዛማጅ ጥናቶች ቅኝቱ ሂሳዊ ንባብን አናስተውልም፡፡ ተመሳስሎ ያላቸውን ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር በዚህ እንመሳሰላለን፤ በዚህ እንለያያለን ከማለት ሌላ ዓላማን ከግብ ማድረስ፣ ጠንካራና ደካማ ጎን፣ ዘዴ፣ ይዘትና ግኝትን ያገናዘበ ቅኝት አላደረገም፡፡

የእኔ ጥናት ከምህረት ተስፋዬ ስራ ጋር በርዕሰ ጉዳይ ይመሳሰላል፡፡ የጥናት ስፍራችን ግን ይለያያል፡፡ ይሄ ደግሞ የመጀመሪያው የልዩነት በር ከፋች ነው፡፡ ምክንያቱም በቦታ መለያየት ውስጥ ሰፊ ፎክሎራዊ ልዩነት ይፈጠራል፡፡ ምህረት የጣና ቂርቆስ ገዳምን ተረክ ሲያጠና በገዳማውያኑ ላይ ያለውን ተግባር በመፈተሽ ነው፡፡ እኔ አምስቱን የዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራት ሳጠና ከዛይ ማህበረሰብ የማንነት ግንባታ አንጻር ተረኮቹና ቁሳዊ ባህሎቹ የተጫወቱትን ተግባርም በማሳየት ነው፡፡ ምህረት ጥናቱን ከግብ ለማድረስ ይዞት የተነሳው የገዳማውያን ህይወትን አጀማመር በመዳሰስ ነው፡፡ የእኔ ጥናት ደግሞ የዝዋይ ሐይቅ ገዳምና አድባራትን የአመሰራረት ሂደት ከታሪክ ማህደር ማስቃኘትን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ የእኔና የምህረት ስራ ከሌሎቹ ጥናቶች በተለየ ርዕሰ ጉዳያችን ቢመሳሰልም የትኩረት አቅጣጫችን፣

አካሄዳችንና የንደፈ ሀሳብ ማዕቀፋችን በሰፊው ስለሚለያይ በጥናት የዳሰስናቸውና የደረስንባቸው ግኝቶች ይለያያሉ።

እንደ አጠቃላይ በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ተረኮችንና ቁሳዊ ባህልን እንዲሁም ፎክሎራዊ ገጽታን መሰረት አድርገው ከተሰሩት ምርምሮች ጋር የሚያመሳስሉን ነገሮች ቢኖሩም ለማጥናት ከተመረጡ ስፍራዎች መለያየት የተነሳ የምርምር አቅጣጫዎቻችን የተቀነበቡበት መንገድና ግኝታችን የተለያየ ነው። ከዚህ በተጨማሪ የእኔ ስራ እንደ ሌሎቹ አንድ ገዳም ላይ ብቻ የተገደበ አይደለም። በዝዋይ ሐይቅ ውስጥ የሚገኙ አምስቱም ደሴያት ላይ ያሉ ገዳምና አድባራትን የሚመለከት ነው። እንደ ጥናቱ የስፋት መጠንና የመረጃዎች ብዛት የግኝቱም ሁኔታ የተለየ ስለሚሆን ከሌሎቹ ጥናቶች በሰፊው እንድንለያይ ያደርገናል።

### 2.2.2. ከክፍለ ትምህርቱ ውጪ የተሰሩ ጥናቶች

ከኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ውጪ ተሰርተው ከእኔ ጥናት ጋር በተወሰነ መልኩ ተመሳስሎ ያላቸው ጥናቶች በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ተዳሰዋል። በቀዳሚነት የቀረበው በቱማ ናደሞ በ1982 “A History of Zay in the 19th and Early 20th Centuries” በሚል በታሪክ ትምህርት ክፍል ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የተደረገው ጥናት ነው። ጥናቱ በሶስት ምዕራፍ ተደራጅቶ ቀርቧል። ዛይ ከሸዋ መንግስት መመስረት በፊት በሚለው በቀዳሚ ክፍሉ የዛይን ህዝብ አመጣጥ አስመልክቶ ሶስት አይነት ምንጮች እንዳሉ አንስቷል። የመጀመሪያው በመካከለኛው ዘመን አርኝ፣ አቦሩበርና ዘፍት የተባሉ ጎሳዎች በደሴቱ ጠረፎች ይኖሩ እንደ ነበረ የሚያሳይ ነው። በ13ኛውና በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አካባቢ ባልታወቀ ወራሪ ተገፍተው ወደ ሐይቁ ደቡብ ምስራቅ ተጉዘው ወደ ቱሉ ጉዶ፣ ጠዴቻና ፋንዱሮ ደሴያት እንደ ገቡ ይናገራል። ለዛይ ማህበረሰብ መፈጠር እንደ ምክንያት የሚጠቀሰው አንደኛው ምንጭ ይሄ እንደሆነም ያስረዳል።

በሁለተኛነት የቀረበውና እንደ ዋና መረጃነት ያነሳው የኢማም አህመድ ኢብን ኢብራሂም አልጋዚ ወረራን ሸሽተው ታቦታትንና ሌሎችን የአብያተ ክርስቲያነትን ቅርስ ሊያተርፉ ከመንዝ አከባቢ ተነስተው ወደ ደስያቱ የገቡ አማራዎች ናቸው ይላል። መሪያቸውም አዕቀ ስላሴ ይባላል። እነዚህ ጎሳዎች ለተወሰኑ አስርት ዓመታት ሰንጎ በተባለ ቦታ ከተቀመጡ በኋላ ወደ ደስያቱ ሊገቡ እንደ ቻሉ ያትታል። በሶስተኛነት ያነሳው ደግሞ በዝዋይ ሐይቅ ጫፎች የስልጤ

ሙስሊሞች ይኖሩ እንደ ነበረና እነዚህ ጎሳዎች ከኦሮሞ ሕዝብ የመስፋፋት እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ አርሲዎችን ሸሽተው ወደ ደስያቱ እንደ ገቡ በመግለጽ የዛይ ማህበረሰብ መሰረት መሆናቸውን ያስረዳል፡፡ ከእነዚህ ጉዳዮች ጎን ለጎን የዛይን የኢኮኖሚና የፖለቲካ ሁኔታ የተመለከተ ጉዳይም ቀርቧል፡፡ በምዕራፍ ሁለት ክፍሉ ደግሞ የዛይ ማህበረሰብ ከሌሎች አጎራባች ጎሳዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ዳሷል፡፡ በተለይ ደግሞ የንግድ ግንኙነትን በተመለከተ ነው፡፡ በመጨረሻው ምዕራፍ የሸዋ መንግስት መመስረት በዛይ ማህበረሰብ ላይ ያሳረፈውን ተጽዕኖ የተመለከቱ ጉዳዮች አቅርቧል፡፡ በተለይም አጼ ምኒሊክ ማህበረሰቡ ድረስ በመሄድ ያላቸውን ቅርሶች ማየትና ችግራቸውን ለመቅረፍ ጥረት ማድረግን የተመለከተ ነው፡፡

የዛይ ማህበረሰብን በተመለከተ የሚገልጽ ከቃላዊ ትውፊት ውጪ የተደራጀ ጽሑፋዊ መረጃ የሌለ በመሆኑ የቱማ ስራ የታሪክ መሰረት የጣለ ነውና ጥሩ ነው፡፡ ይሄ የጥናቱ ጠንካራ ጎን እንዳለ ሆኖ በጥናቱ ክፍተት የሚነሳው ደግሞ እንደ ጥናት መርህ መሰረት አነሳሽ ምክንያት፣ ዓላማ፣ የምርምር ጥያቄ፣ ጠቀሜታ፣ ወሰን፣ ዘዴ፣ አጠቃሎና ማጠቃለያ የመሳሰሉትን ክፍሎች የሌለው በመሆኑ እንደ አንድ ጥናት ለመመዘን ይከብዳል፡፡ በታሪክ ደረጃ በማህበረሰቡ ዙሪያ ያቀረበው አንዳንድ ጽሑፋዊ መረጃዎችን እየጠቀሰና የደስያቱ ነዋሪዎችን በመጠየቅ ያገኘሁት በማለት የሚያነሳቸው ነገሮች ጥሩ ሆነው ሳለ በእውነት የመስክ ቃለ መጠይቅ አድርጓል ለማለት የማያስደፍር ሁኔታ በጥናቱ ተስተውሏል፡፡ ይኸውም አንድ የዛይ ተወላጅ ሲጠይቅ በመጀመሪያነት የሚያነሳው ነገር የታቦተ ጽዮንን ጉዳይ ነው፡፡ ምክንያቱም ወደዚህ ስፍራ የመጣነው በዮዲት ወራራ ጊዜ ታቦተ ጽዮን ይዘን በመሸሽ ነው ይላሉና፡፡ የቱማ ጥናት ግን ይሄንን አያሳይም፡፡

የቱማ ናደሞን ጥናት ከእኔ ስራ ጋር የሚያመሳስለው ነገር የዛይ ማህበረሰብን ታሪክ ማንሳቱ ነው፡፡ የእኔ ስራ በዝዋይ ሐይቅ የሚገኙ ገዳምና አድባራት ላይ የሚያተኩር ቢሆንም እብያተ ክርስቲያናቱ ሲነሱ የዛይ ህዝብ አብሮ መነሳቱ አይቀርምና የተወሰነ ተመሳስሎ እንዲኖረን ያደርጋል፡፡ በታሪክ ትምህርት ክፍል እንደ መሰራቱ መጠን በተጨማሪ ምንጭነትም የሚያገለግል ነው፡፡ ሆኖም የቱማ ጥናት ዓላማ በቃለ መጠይቅና በጽሑፍ ማስረጃ የተቀመጡትን በማመሳከር የዛይን ህዝብ ታሪክ መጻፍ ሲሆን የእኔ ግን በስፍራው የተነገሩ ተረኮችን ከቁሳዊ መረጃው ጋር በማገናኘት ያላቸውን ማህበራዊ ፋይዳ መመርመርና የፎክሎራዊ ጉዳዮቹን ጥበባዊ ገጽታ ማሳየት ስለ ሆነ በሰፊው ልዩነት እንዲኖረን ያደርጋል፡፡

በቅድስት ስላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ በዘላለም አሰፋ "A Brief History and Activities of Zeway Debre Tsion monastery" በሚል ርዕስ በ2001 ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የተደረገው ጥናት ሌላው ከእኔ ጥናት ጋር የተወሰነ ግኑኝነት ኖሮት የሚዳስስ ስራ ነው። ጥናቱ በሶስት ምዕራፍ ተከፋፍሎ የቀረበ ሲሆን ምእራፍ አንድ መግቢያ፣ ምዕራፍ ሁለት የጥናቱ ዳራ ነው። የመጨረሻው ምዕራፍ የገዳሙን ጥንታዊ ቅርሶች የዳሰሰበት ነው። በጥናቱ የስፍራው አጠቃላይ ገለጻ፣ የገዳሙ ቅርሶች፣ የገዳምና የምንኩስና ሕይወት አጀማመር፣ የደብረ ጽዮን ገዳም አመሰራረትና በገዳሙ ያሉ ቅርሶች ለቱሪዝም ያላቸው ጠቀሜታ የሚሉ ጉዳዮች ተዳሰዋል። የዛይ ማህበረሰብን ወደ ደሴቱ አመጣጥ አስመልክቶ 3 ጊዚያትን ይጠቅሳል። እነዚህም በ842 ዓ.ም በዮዲት ወረራ፣ ከጉራ በ14ኛው ክፍለ ዘመን (1323) እና በ1520 የአህመድ ግረኝ ወራራ ናቸው። የስፋራውን ታሪክ ያብራራበት መንገድ፣ ስለ ንዋየ ቅድሳቱ ያስቀመጠው ገለጻ ጥሩ ነው። በተለየ እንደ መጀመሪያ ዲግሪ ስራ ይዞት የተነሳው ጉዳይና የሄደበትም መንገድ ጥናታዊ ስራውን የሚያስመሰግን ነው።

የዘላለም ጥናት ከላይ የተነሱት ጠንካራ ጎኖች እንዳሉት ሆኖ ሌሎች ክፍተቶችም አሉበት። በመጀመሪያ በገዳሙ ላይ ጥናት ለማድረግ የተነሳበትን ዓላማ አያሳይም። ዘዴ፣ የምርምር ጥያቄና ሌሎች መሰራታዊ የሆኑ የጥናት ክፍሎች የሉትም። የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ገዳሙ ያለውን የውኃ ሀብት በአግባቡ አለመጠቀም፣ በቂ መሬት ቢኖርም ዘመናዊ የአተራረስ ስልት ተግባራዊ አለማድረግ፣ ገዳሙ ከዓሣ ምርት መጠቀም አለመቻል፣ የጤና ችግር መኖሩና እንደ አጠቃላይ ከመሰረተ ልማት አንጻር ያለውን ችግር በማሳወቅ እንዲጎበኙ ማድረግ የሚሉ ናቸው። ከእነዚህ ዝርዝር ጉዳዮች እንደምንረዳው ጥናቱ በሃይማኖቱ ውስጥ ባለ የትምህርት ተቋም የተሰራ ስለ ሆነ ቦታውን በማሳወቅ ያለውን ችግር መቅረፍን ዓላማ ያደረገ ይመስላል። የጥናቱ ጠቀሜታ ብሎ ካስቀመጣቸው ዝርዝሮች ውስጥ እንኳን አንዱ ባነሳ የገዳሙን ችግር በመጠቆም እንዲቀረፍ ማድረግ የሚል ነው። ከባጀት አጥረት አንጻር ብዙ እንዳልሄደ ይገልጻል ሆኖም እስከ የት መሄድ ይችል እንደ ነበረ አያመለክትም። የመረጃዎቹ ትዕምርታዊነትም በጥናቱ አልተመለከተም።

የዘላለም አሰፋን ስራ ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ከዝዋይ ደስያት አንዱ በሆነው በደብረ ጽዮን ገዳም ላይ መስራቱ ነው። ሆኖም የእኔ ምርምር አምስቱም ደስያት ላይ የሚገኙትን ገዳምና አድባራት የሚዳስስ ስለሆነ የተለየ ነው። የጥናቱ ዓላማ ደግሞ የገዳምና አድባራቱን

ታሪክ መዘገብ ሳይሆን በተረኩና በቁሳዊ ባህሉ አማካይነት የተፈጠረውን ፎክሎራዊ ጉዳይ ማሳየትን መሰረት ያደረገ በመሆኑ ከዘላለም ጥናት ይለያል።

በእንዳሻው ወ/ሚካኤል በ2007 “A Study of Ethnolinguistic Attitudes of Zay people; An Investigation of The Language-Ethinicity Relationship Among Zay” በሚል ርዕስ ጉዳይ በሥነ ልሳን ትምህርት ክፍል የተሰራው ሌላው በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር በመጨረሻ የማነሳው የምርምር ስራ ነው። እንዳሻው ዓላማ አድርጎ የተነሳው በስደትና ቋንቋ ቅየራ አውድ ውስጥ የዛይ ቋንቋ ተናጋሪ አሁን ያለውን የጎሳ ሥነ ልሳን ሁኔታ መመርመርን ነው። በምርምሩ የተገኘው ግኝትም የዛይ ማህበረሰብ ከማህበረ ኢኮኖሚ አንጻር ለስደት መዳረጋቸው፣ የዛይ ዘር ሆነው አፋቸውን በሌላ ቋንቋ የሚፈቱ መኖራቸው፣ አብዛኛው ወላጅ ከልጆቹ ጋር የሚግባባው በአማርኛና ኦሮምኛ ቋንቋ መሆኑ፣ ዛዮች ቋንቋውን የሚጠቀሙበት በደስያቱ ውስጥ ሲገናኙ ብቻ መሆኑና ለዛይ ተወላጆቹ የሚሰጠው ትምህርት በኦሮምኛ ቋንቋ መሆኑ የዛይኛ ቋንቋ ወደ ሌላ ቋንቋ እየተቀየረ መሆኑን ያመለክታል የሚል ነው።

ማንኛውም ቋንቋ የአንድ ማህበረሰብ የባህል ተምሳሌት እንደ መሆኑ መጠን ስደቱ ለቋንቋው መቀየር ምክንያት እንደሚሆን ሁሉ የቋንቋው መለወጥ ደግሞ ማንነታቸውን ለመቀየር የሚያስችል መሆኑን ያስረዳል። ይሄ ደግሞ የትውልድ ክፍተት እንዲፈጠር ያደርጋል በሚል መጠናዊ መረጃ ላይ ተመርኩዞ የራሱን ትንታኔ በመስጠት በቋንቋው አማካይነት የዛይ ማህበረሰብ የወደፊት ማንነት ምን ሊሆን እንደሚችል አመላክቷል። በዚህም ወደ ፊት ማህበረሰቡ ሙሉ በሙሉ የኦሮምኛ ተናገሪ አልያም የኦሮምኛና አማርኛ ተናጋሪ ሊሆን እንደሚችል በመተንበይ ከረጅም ጊዜ በኋላ ቋንቋው ወደ ሌላ ቋንቋ ሽግግር ማድረጉ ለባህላቸው፣ ለጎሳቸውና ለማንነታቸው መቀየር ምክንያት ይሆናል የሚል የመደምደሚያ ሀሳብም ማስቀመጥ ችሏል። ጥናቱ በአምስት ምዕራፍ ተደራጅቶ የቀረበ ነው። ምዕራፍ አንድ የጥናቱ መግቢያ፣ ምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳን፣ ምዕራፍ ሶስት ሥነ ዘዴ፣ ምእራፍ አራት ትንተና፣ ምዕራፍ አምስት ማጠቃለያ ነው።

ጥናቱ የአንድን ማህበረሰብ የቀደመ ማንነትና የወደፊቱን ለመተንበይ በቋንቋ ማዕቀፍ ውስጥ ሆነን ማጥናት እንደምንችል ያሳየ የተዋጣለት ስራ ነው። የዛይ ማህበረሰብ የት መጣናት ላይ በቱማ ናደሞ የቀረበውን በማንሳት በዚያ ጥናት ሳይነሳ የቀረውን ከዮዲት ጋር የተገናኘውን

አፈታሪክ ይጨምራል፡፡ ይሄ እንደ ጥናት ተገቢ አካሄድ መሆኑንም እናይበታለን፡፡ በሥነ ዘዴው እንደ ገለጸው አይነታዊና መጠናዊ መረጃን ተጠቅሟል፡፡ መረጃዎቹንም በቃለመጠይቅና በጽሑፍ መጠይቅ ሰብስቧል፡፡ ሆኖም የዘዴዎቹን ለጥናቱ ተገቢ መሆን፣ አካሄዳቸውን የሚያሳይ ምንም አይነት አካዳሚያዊ መረጃ የለውም፡፡ በትንተና ክፍሉም መረጃውን ፈርጅ አሲዞ ከመተንተን ውጪ በትንታኔው መካከል በዚህ ቀን በቃለመጠይቅ ወይም በጽሑፍ መጠይቅ ከእንደዚህ ዓይነት አካል ያገኘሁት ነው የሚል የአተናተን ስልት አይታይበትም፡፡ ይሄ ደግሞ በጥናቱ ላይ በሰፊው የሚስተዋል ክፍተት ነው፡፡ ትኩረት ባለመስጠት በተለምዶ የሚባሉትን እንደ እውነተኛ መረጃ ጥናቱ ላይ አስፍሮትም እናገኛለን፡፡ ለዚህም ገሊላ ካህናተ ሰማይ ቤተክርስቲያን ያለ ሲሆን ከሚከበርበት ቀን መመሳሰል የተነሳ በተለምዶ ገሊላ ተክለ ሃይማኖት ይባላል፡፡ በእንዳሻው የምርምር ስራም ሰፍሮ የምናገኘው ይሄንኑ ነው፡፡

የእንዳሻውን የምርምር ስራ ከእኔ ጥናት ጋር የሚያገናኘው የዛይ ማህበረሰብን የትኩረት አቅጣጫው አድርጎ የማህበረሰቡን ማንነት ለመፈተሽ ሲነሳ የስፍራውን አጠቃላይ ሁኔታ በመግለጹ ነው፡፡ ልዩነታችን ደግሞ የእንዳሻው ስራ ከቋንቋው አንጻር የዛይ ማህበረሰብን የወደፊት የባህል አሻራ ሲያጠና የእኔ ስራ ደግሞ የዛዮች የማንነት አሻራ ያረፈባቸውን ገዳምና አድባራት የሚመረመር ነው፡፡ የማህበረሰቡን ባህላዊ ማንነት ከተረኮቻቸውና ከቁሳዊ ባህላቸው አንጻር በእኔ ስራ የሚነሳ በመሆኑ ሌላው የሚለየን ነገር ነው፡፡ ምክንያቱም የእንዳሻው ምርምር መጠናዊና አይነታዊ መረጃ ላይ ተመርኩዞ ቋንቋውን ማዕቀፍ አድርጎ የወደፊት ማንነታቸውን ሲተነብይ የእኔ ጥናት ደግሞ አይነታዊ መረጃ ላይ ተመስርቶ በእምነት ማዕከላቸው በኩል በተረኮቻቸውና ቁሳዊ ባህላቸው ገንብተው የኖሩትን ማንነት ማሳየት ነው፡፡

በደስታ ፍጹምብርሃኔ በ2009 "Catalogue of some selected Manuscript of Dâbrâ Sâyon Church Ziway Island (Tulu Guddo Island)" በሚል ርዕሰ ጉዳይ በፊሎሎጂ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ደግሪ ማሟያ የተሰራው ሌላው ለክለሳ የተመረጠ የምርምር ስራ ነው፡፡ ይህ የምርምር ስራ የብራና መጻሕፍት ጥንታዊውን እውቀት ለአሁኑ ዘመን በማስተላለፍ እንደ ድልድይ ያገለገሉ መሆናቸውን በመግለጽ የሚጀምር ነው፡፡ ኢትዮጵያ የበርካታ የብራና መጻሕፍት ባለቤት መሆኗንም ይጠቅሳል፡፡ የብራና መጻሕፍቱ በግምት ከ200,000 በላይ ይሆናሉ ብሎ ከመናገር ሌላ በውጪ ቤተ መጻሕፍት እንደሚገኙት ካታሎግ ተሰርቶላቸው ቁጥራቸው እንኳ በትክክል

አለመታወቁን እንደ ችግር ያነሳል፡፡ የብራና መጻሕፍቱ ላይ የተወሰኑ ጥናቶች ከመስተዋላቸው ሌላ ገና የቁጥራቸውን ያህል አለመሰራቱንም ይገልጻል፡፡

የብራና መጻህፍቱ የታሪክ፣ የህግ፣ የሥነ ልሳን፣ የሥነ ጽሑፍ እንዲሁም የሥነ መለኮት ምሁራን ተመራማሪዎች የትኩረት አቅጣጫ እንዲሆኑ ከተፈለገ መጻሕፍቱ የመዝገብ ዝርዝር (Catalogue)ማዘጋጀትና ገለጻ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ጥናቱ ያስገነዝባል፡፡ በ100ሺ. ከሚቆጠሩት የብራና መጻሕፍት 20ሺ. እንኳ ለሚሆኑት የመዝገብ ዝርዝር እንዳልተዘጋጀላቸው ገልጾ አጥኚው በበኩሉ የድርሻውን ለመወጣት ያህል በደብረ ጽዮን ገዳም ካሉት የብራና መጻሕፍት በ12ቱ የገድል የብራና መጻህፍት ላይ የመዝገብ ዝርዝር ማዘጋጀትን ዋና ዓላማ አድርጎ ጥናቱን ሊሰራ እንደቻለ አስቀምጧል፡፡ በዝርዝር ዓላማነት የተነሱት የብራና መጻህፍቱን ባህሪያት፣ የተዘጋጁበት ጊዜ፣ የጸሀፊ ማንነት፣ አይነትና ይዘት፣ መጠንና ጭብጥ እንዲሁም ገድሉ የሚገኝበት ደረጃ የሚሉት ናቸው፡፡ የተነሳውን ዓላማ ከግብ ከማድረስ አኳያ ጥናቱ የተሳካለት ነው፡፡ በተለይ በዝርዝር ዓላማ የቀረቡት ጉዳዮች በእያንዳንዱ የገድል መጽሐፍ ላይ ተንጸባርቀዋል፡፡ የመረጃ መሰብሰብያ ዘዴዎቹ መደበኛ ቃለመጠይቅ፣ መጠናዊ መረጃ የመሰብሰብ ዘዴና የመዛግብት ፍተሻ ናቸው፡፡ ዘዴዎችን ወስኖ የተነሳ ቢሆንም የዘዴዎቹ ምንነት፣ ለምን ተመረጡ፣ እንዴት አገልግሎት ላይ ይውላሉ፣ ስለ ዘዴዎቹ የምሁራን ሀሳብ፣ ያላቸው ጠንካራና ደካማ ጎን ወዘተ. ምንም የተባለ ነገር የለም፡፡ መደበኛ ቃለመጠይቆቹም በአባሪ ክፍል ሰፍረው አንመለከትም፡፡ የምርምር ስራው የተደራጀው በሶስት ምዕራፍ ነው፡፡ ምዕራፍ አንድ የጥናቱ ዳራ ነው፡፡ ምዕራፍ ሁለት ከዝዋይ ደስያት የተወሰዱ የ12 የብራና መጻህፍት ገለጻ ሲሆን ምዕራፍ ሶስት ማጠቃለያ ነው፡፡

ጥናቱ በርከት ላሉት የብራና መጻህፍት በውጪ ሀገር የመዝገብ ዝርዝር እንደ ተዘጋጀላቸው ይናገራል፡፡ ለዚህም ሰፋ ያለ ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ አቅርቧል፡፡ በተዛማጅ ጽሑፉ ያስፈረውን ስንመለከት ግን ከሱ ጋራ አራት ጎደኞቹ በተለያየ ቦታ ለመስራት እንደ ተነሱ ከማሳወቅ ሌላ ከዚህ በፊት በውጪዎቹ ተሰርተዋል ያላቸው ጥናቶች እንዴት እንደ ተሰሩ፣ ከእነሱ የቀሰመውን እውቀት፣ ያየባቸውን ክፍተት አላነሳም፡፡ ደስታ ከብራና መጻህፍት ታሪክንም ሆነ ሃይማኖትን ለማጥናት የተሻሉት የገድል መጻህፍት ስለ ሆኑ የመዝገብ ዝርዝር የማዘጋጀው በ12 የገድል የብራና መጻህፍት ላይ የሚል ዋና ዓላማ አንግቦ ቢነሳም በጥናቱ ላይ የመጽሐፍ ዝርዝር ተዘጋጅቶላቸው የምናገኘው ግን ሌሎቹንም የብራና መጻህፍት ያካተተ ነው፡፡ ለዚህም ማስረጃ

የሚሆነን የገድል መጻህፍቱ ገድለ አቡነ ገሪማ፣ ገድለ አቡነ ሳሙኤልና ገድለ ሐዋሪያት የሚባሉትን ሶስት ብቻ ሲሆን ሌሎቹ ግን ከገድላት ውጪ የሆኑ የሙሴ መጻህፍት ፣ መጽሐፈ ሳሙኤል፣ መጽሐፈ ነገስት፣ አርባዕቱ ወንጌል፣ መጽሐፈ አርጋኖን፣ ርቱዓ ሃይማኖት፣ ምንባበ ዘወርሃ ጾምና ድርሳን ዘከመ ተረክበ መስቀል የሚሉት መጻህፍት ናቸው። ይሄ ሲታይ ዋናው ነገር መጻህፍቱን የመዝገብ ዝርዝር ማዘጋጀት ነው ብንልም እንኳ ይዞት የተነሳውን ዓላማ ያላገናዘበ ነው።

ይህን የምርምር ስራ ከእኔ ስራ ጋር የሚያመሳስለው በዝዋይ ደስያት ከሚገኙት ገዳምና አድባራት አንዱ በሆነው በደብረ ጽዮን ገዳም ላይ መሰራቱና በገዳሙ ሙዝየም የሚገኙ የብራና መጻህፍት የሚዳስስ መሆኑ ነው። ምክንያቱም የእኔም ስራ ከአምስቱ የዝዋይ ደስያት አንዱ የሆነውን የደብረ ጽዮንን ገዳም ታሪክ የሚያጠናና የብራና መጻህፍቱንም ከቁሳዊ ባህል አንጻር የሚመረምር ነውና። ሆኖም የደስታ ጥናት ለ12 መጻህፍት የመዝገብ ዝርዝር ማዘጋጀት ላይ የተገደበ በመሆኑና የእኔ የምርምር ስራ ደግሞ በአንዱ ገዳም ላይ ተወስኖ ሳይሆን በዝዋይ ሐይቅ ላይ ያሉትን የደስያቱን ገዳምና አድባራት የትኩረት አቅጣጫ አድርጎ መጻህፍቱን ፎክሎራዊ ጉዳይና ሌሎችንም ቁሳዊ ባህል የሚዳስስ ስለ ሆነ ይለያል። በደሴቱ የሚነገሩትን ተረኮች ማህበረ ባህላዊ ፋይዳ የሚጨምር በመሆኑም ከደስታ ጥናት በእጅጉ ይለያል።

ከክፍለ ትምህርቱ ውጪ ከተደረጉት ከዚህ በላይ ከቀረቡት ጥናቶች ጋር እንድንለያይ የሚያደርገን የመጀመሪያው ነገር የጥናት መስካችን መለያየት ነው። በጥናቶቹ የዛይ ህዝብ ታሪክና ቋንቋ ተዳሷል። ለጥናታቸውም በመረጃ ምንጭነት ግብዓት ይሆናቸው ዘንድ አልፎ አልፎ ቃላዊ ታሪኩንና ቅርሶቹን ያነሳሉ እንጂ ፎክሎራዊ ጉዳዮቹን በማጥናት ተምሳሌታዊ ገጽታቸውን ለማሳየትና በማህበረሰቡ የማንነት ግንባታ ረገድ ያላቸውን ፋይዳ በመመርመር ላይ አተኩረው የሰሩ አይደሉም። ይሄ ደግሞ የእኔን ጥናት እንዲለይ ያደርጋል።

# ምዕራፍ ሶስት

## የዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራት አጠቃላይ ገለጻ

ይህ ምዕራፍ የዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራትን የተመለከቱ ጉዳዮች የሚቀርቡበት ክፍል ነው። ስለ ደስያቱ አጠቃላይ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ሲባል የመልክዓ ምድራዊ አቀማመጥንና የዛይ ሕዝብን ታሪካዊ አመጣጥ የሚዳስሱ ጉዳዮችን ማንሳት ተገቢ ይሆናል። ስለዚህም ከሐይቁና ደስያቱ ጋር በተያያዘ የሚነሱ ጉዳዮች ከገዳምና አድባራቱ ታሪክ ጋር እንደሚከተለው ተዛንቀው ቀርበዋል።

### 3.1. የደስያቱ መልክዓ ምድራዊ ሁኔታና ስያሜ

የዝዋይ ሐይቅ[9] በስምጥ ሸለቆ ውስጥ ከሚገኙት ሀይቆች አንዱና ትልቁ ነው (ባህሩ፣3)። ከአዲስ አበባ በስተደቡብ 160 ኪ.ሜ ርቀት በአዋሳ መስመር ላይ በዝዋይ ወይም ባቱ ከተማ በስተምስራቅ 5 ኪ.ሜ ገባ ብሎ ይገኛል። በሐይቁ ላይ የሚገኙ የደስያቱ ገዳምና አድባራት በምስራቅ ሸዋና አርሲ ሀገረ ስብከት ስር የሚተዳደሩ ናቸው።[10] አምስቱም ደስያት አንዳንድ ቤተክርስቲያን ያላቸው ናቸው።

የዝዋይ ሐይቅ ከቦራ ተራራ በስተደቡብ፣ ከአሉቶ ተራራ በስተሰሜን፣ ከአሰላ በስተምዕራብና ከዝዋይ ከተማ በስተምስራቅ አቅጣጫ ይገኛል። ሐይቁ የአራት ማዕዘን ቅርጽ ያላው ሆኖ ከሰሜን ወደ ደቡብ 25 ኪ.ሜ፣ ከምስራቅ ወደ ምዕራብ 16 ኪ.ሜ እርዝመት አለው። አጠቃላይ ስፋቱ 434 ስክዌር ኪ.ሜ ጥልቀቱ ደግሞ በአማካይ 4 ሜትር ነው። የዝዋይ ሐይቅ ሁለት

---

[9] ዟይ (ዝዋይ)፡ ያገርና የባሕር ስም ባሩሲ ወረዳ ያለ ባሕር ፣ በውስጡ ካለው ደሴት ጋር ባንድነት ዟይ ይባላል። ዟ ብሎ የተሰጣ፣ የተዘረጋ ከ፭ ደሴት የገጠመ ውሃ ማለት ነው (ደስታ ተክለወልድ፣487)።

[10] ከመካከለኛው የግዛት አከፋፈል የደስያቱ ሕዝቦች ዋግ(ኦጌ) በሚል አገር ስር ተጠቃለው ይጠሩ ነበረ፤ በንጉስ ዓምደ ጽዮን፣ በዘርዓ ያዕቆብና በበዕደ ማርያም ዘመነ ንግስና ጊዜና የኢትዮጵያ መናገሻ ጎንደር በነበረበት ወቅት በማዕከላዊ መንግስት የገቡ ሲሆኑ ከአጼ ኃይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት ጀምሮ ገሊላና ደብረ ሲና በሸዋ ጠቅላይ ግዛት ስር 3ቱ ቀሪ ደስያት ደግሞ በአርሲ ስር ነበሩ (ተስፋዬ፣ 2)።

መጋቢ ወንዞች አሉት፡፡ እነዚህ ገባሮችም ካታርና መቂ ናቸው፡፡ የመቂ ወንዝ ከጉራጌ ከፍተኛ ቦታዎች ተነስቶ በስተሰሜን በኩል ወደ ሐይቁ ሲፈስ ካታር ደግሞ ከአርሲ ከፍተኛ ቦታዎች በመነሳት በስተሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ ወደ ሐይቁ ይገባል፡፡ የሐይቁ የውኃ መጠን በስተደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ ወደ ውጭ እንዲፈስ በማድረግ የሐይቁን የውኃ መጠን ሚዛናዊ የሚያደርገው ወደ 48 ኪ.ሜ ተጉዞ አብያታ ሐይቅ የሚገባው የቡልቡላ ወንዝ ነው (ማህበረ ቅዱሳን ዘጋቢ ምስል ወድምጽ፤ ተስፋዬ፣1-2)፡፡

በዝዋይ ሐይቅ ላይ አምስት ደስያትና በርካታ የአዕዋፍ መስፈሪያ አለቶች ይገኛሉ፡፡ ደስያቱ ያላቸው መጠን የተለያየ ነው፡፡ ይሄንንም ስርግው ሐብለ ስላሴ "አማርኛ የቤተክርስቲያን መዝገበ ቃላት" በሚል መጽሐፋቸው በጋሻና በሄክታር ሲያስቀምጡት ዳንኤል ክብረት ደግሞ በሄክታር ይገልጹታል፡፡ ከደስያቱ ትልቁ ደብረ ጽዮን ነው፡፡ ስፋቱም 10 ጋሻ ወይም 40 ሄክታር ነው፡፡ ደብረ አብረሃምና ጌቴሴማኒ በጋራ 7 ጋሻ ወይም 28 ሄክታር ስፋት አላቸው፡፡ ገሊላና ደብረ ሲናም በጋራ 5 ጋሻ ወይም 20 ሄክታር ይሰፋሉ፡፡ የደስያቱ አማካይ ስፍራ 1953 ሜትር ከፍታ አለው፡፡ በሐይቁ ደቡብ ምዕራብ የሚገኙ ደስያት ገሊላና ደብረ ሲና ሲባሉ በምስራቅ በኩል ያሉት ደግሞ ደብረ ጽዮን፣ አብርሃምና ጌቴሰማኒ በመባል ይታወቃሉ (ዳንኤል፣401፤ስርግው፣236)፡፡ አምስቱም ደስያት የተለያየ ስያሜ አላቸው፡፡

### 3.1.1. የደብረ ጽዮን ደሴት

ከሁሉም ደስያት ትልቁ የደብረ ጽዮን ደሴት ነው፡፡ የሐይቁና የደስያቱ ስያሜ በምን ምክንያት እንደ ተሰጠ ከማህበረሰቡ በቃለመጠይቅ ያገኘሁት መረጃ እንደሚያመለክተው ደሴቱ ደብረ ጽዮን የሚል ስያሜ ያገኘው የጽላተ ሙሴ ማረፊያ ሆኖ ስላገለገለ የጽዮን ማረፊያ ተራራ በማለት ነው፡፡ በሐይቁ ዙሪያ የሚኖሩት ኦሮሞዎች ደግሞ ቱሉ ጉዶ ብለው ይጠሩታል፡፡ ቱሉ ጉዶ ማለት ትልቁ ተራራ እንደ ማለት ነው (ቃለመጠይቅ፣ መምሬ ገብረ መስቀል፣ 02/08/05 ዓ.ም)፡፡

የደብረ ጽዮን ገዳም ከ1973 ዓ.ም በፊት ታቦተ ጽዮን ባረፈችበት 1953 ሜትር ከፍታ ባለው ተራራ ላይ ይገኝ ነበረ፡፡ ከዚህ በኋላ በጥርብ ዲንጋይ በዘመናዊ እቅድ በአራት መዓዘን ተራራው ስር ተሰርቶ ሕዝቡም ገዳሙም ወደታች ወርዷል፡፡ ገዳሙ በ3 ክፍል የተከፈለ ነው፡፡ ደብረ ጽዮን ቤተክርስቲያን ከሌሎቹ የሚለየው አሁንም በገዳም ማዕረግ ያለ መሆኑ ነው፡፡

በተጨማሪም ከሌሎቹ ሐይቁ ላይ ካሉት ደስያት በተለየ መልኩ በተለያዩ አዝማናት ወደ ገዳሙ የመጡ ቅርሶች ይገኙበታል፡፡ በዓለም የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን እንድትታወቅ ያደረገው መጽሐፈ ሄኖክ የሚገኘው እዚህ ደሴት ነው፡፡ በሃይማኖቱ ኢትዮጵያዊ ቁርሎስ በመባል የሚታወቀው የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ የገድል መጽሐፍ የመጀመሪያ ቅጂም እዚህ የተገኘ ነው፡፡ በተለያየ ንድፍ ከብረት የተሰሩ የእጅ መስቀሎች፣ አውድ፣ ጻሕልና ቅዱሳት ስዕላት ይገኛሉ፡፡ በአክሱማዊያኑ ንድፍ የተቀረጸና በንግስተ ነገስታት ዘውዲቱ የተበረከተ የመጾር መስቀል አለ፡፡ ከአንድ ሺ በላይ እድሜ ያስቆጠሩ የብራና መጻሕፍትም ይገኛሉ፡፡ ደሴቱ ላይ አማራርጌና የወይዘሮ ጎሳ የሚባሉ ሕዝቦች በተለያየ ሰፍራ ሰፍረው ይገኙበታል፡፡

### 3.1.2. የደብረ አብርሃም ደሴት

በትልቅነቱ በሁለተኛ ደረጃ የሚጠቀሰው ደሴት ደብረ አብርሃም ነው፡፡ በኦሮምኛ ቋንቋ ጠዴቻ ይባላል፤ ግራራማው ስፍራ ማለት ነው፡፡ ደሲቱ ብዙ ግራር ያለበት ከመሆኑ የተነሳ የተሰጠው ስያሜ ነው፡፡ ቃለመጠይቅ ያደረኩላቸው የደሴቱ አረጋዊያን እንደ ነገሩኝ ከሆነ ደግሞ ደብረ አብርሃምን ከዩዲት ወራራ በመሸሽ ታቦተ ጽዮንን ይዘው የመጡት አክሱማዊያን አይስት ብለውታል፡፡ ይሄንን ስያሜ ሊሰጡት የቻሉበት ምክንያት በንፋስ በሚመራ በረግረግ አማካይነት ወደ ደሴቱ ሲገቡ ፊት ለፊት እያዩ የነበረው የጠዴቻን ደሴት ስለ ሆነና ደሴቱን ሳይስት ስላደረሳቸው ነው፡፡ ከጊዜ በኋላ እይተለመደ ሲመጣ  የአይሱት ደሴት ተብሏል (ቃለመጠይቅ፣ አቶ ታደሰ አሼ፣ በቀን 05/08/05 ዓ.ም)፡፡

ደሴተ አይሱት የአበርሃም መታሰቢያ ቤተክርስቲያን ያለበት ነው፡፡ በደሴቱ በርካታ የብራና መጻሕፍት የነበሩበት ቢሆንም ገሚሱ በስርቆት ሌላው በጥንቃቄ ጉድለት ቤተክርስቲያኑ የሳር በነበረበት ጊዜ ተበላሽቷል፡፡ ቤተክርስቲያኑ በዘመናዊ መልኩ በ2005 ዓ.ም ጥር 19 በአዲስ መልክ ተሰርቶ ተመርቋል፡፡ በአሁኑ ሰዓት 2 ጥንታዊ የብራና መጻህፍትና የተለያየ ቅርጽ ያላቸው መስቀሎች ይገኛሉ፡፡ ደሴቱ ሶስት ተራራ ያለው ሲሆን በአንደኛው ተራራ ስር የደሴቱ ነዋሪዎች በችግር ሰዓት የሸሸጉበት የነበረ አሁን የተደፈነ ዋሻ ይገኛል፡፡ አሁንም ድረስ ከሌሎቹ ደሴት በተለየ በርከት ያለ ሰው የሚኖርበት ደሴት ነው፡፡

### 3.1.3. የጌቴሴማኒ ደሴት

ከደብረ አብርሃምና ደብረ ጽዮን ፊት ለፊት የሚታየው ደሴት ጌቴሴማኒ ይባላል፡፡ ጌቴሴማኒ ከሁሉም ትንሹ ደሴት ነው፡፡ በኦሮምኛ ቋንቋ ደግሞ ፉንዱሮ በመባል ይታወቃል፡፡ ትርጉሙ ፊት ለፊት ማለት ነው፡፡ ለየብስ ቅርብ በመሆኑና ለአርሲ.ዎቹ በቅርበት ስለሚታይ የተሰጠው ስያሜ ነው፡፡ ይህንን ደሴት ስርግው (236) የጥንት ስሙ አይታወቅም ይሉታል፡፡ እኔ ግን ከደሴቱ ነዋሪዎች እንዳገኘሁት የጥንት ስሙ ፋማት ይባላል፡፡ (ቃለመጠይቅ፣ አቶ ጉደታ ሚደግሶ፣ በቀን 07/08/05 ዓ.ም)፡፡ ደሴቱ የዛይ ማህበረሰብ የስብሰባ ማዕከል ስለ ነበረ የዛይ ማህበረሰብ ጠንከር ያለ ችግር ሲያጋጥመው ከሁሉም ደሴት የተወከሉ ሰዎች ተሰብስበው የሚወስኑበት ነው፡፡ አቶ ጉደታ ሚደግሳ እንደ ነገሩኝ በፉንዱሮና በጠዴቻ ደስያት ዘፍት የሚባል ቀዳሚ ጎሳ ነበረ፡፡ አሁን በደሴቱ ላይ የሚገኙት ሕዝቦች ከ20 አባወራ የማይበልጡ ናቸው፡፡ አብዛኛው የደሴቱ ነዋሪ በአጼ ሀይለ ስላሴ ለአርሻ የተሰጣቸውን ቦታ ምክንያት በማድረግ ወደ መቂ ከተማ ተሰደዋል፡፡ ዛሬ ያለው ቤተክርስቲያንም በአጼ ሐይለ ስላሴ ዘመን የታደሰ ነው፡፡ የደሴቱ ነዋሪዎች እንደሚናገሩት ተወላጅ ካህን ደሴቱ ስላልነበረው በደብሩ የነበሩት በርካታ ጽላትም ሆኑ ሌሎች ንዋየ ቅድሳት በንግስ ጊዜ ለአገልግሎት የሚመጡ ካህናት ወስደው እንደ ጨረሷቸው ይናገራሉ፡፡ አሁን ያለው የአርባዕቱ እንስሳ ጽላትም ተሰርቆ ሊወሰድ ሲል አንድ ሰው በማየቱ የአገር ሽማግሌ ተሰብስቦ እንዳስቀረው ይተረካል፡፡ በአሁኑ ሰዓት ከሶስት የማይበልጡ የብራና መጻህፍት ብቻ ይገኙበታል (ቃለመጠይቅ፣ መምሬ ሀይለ ጊዮርጊስ አሴ፣ በቀን 07/08/05 ዓ.ም)፡፡ እነዚህ ከላይ በተከታታይ የቀረቡት ሶስት ደስያት በአርሲ ሀገረ ስብከት ስር ያሉ ሲሆኑ በምስራቅ ሸዋ ስር የሚገኙት ሁለቱ ማለትም ገሊላና ደብረ ሲና ደግሞ ቀጥሎ የሚቀርቡት ናቸው፡፡

### 3.1.4. የገሊላ ደሴት

ገሊላ ካህናተ ሰማይ ከዝዋይ ከተማ ዳርቻ ሶስት ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ በተለምዶ ገሊላ ተክለ ሃይማኖት ተብሎ ይጠራል፡፡ ደሴቱ ከባህር ጠለል በላይ 1744 ሜትር ከፍታ ላይ ይገኛል፡፡ ክብ ጣሪያው በቆርቆሮ በ1965 ዓ.ም ታድሷል፡፡ በዚህ ጊዜ የወርቅ መስቀል የያዙ የአንድ ባህታዊ አጽም ተገኝቷል ተብሎ ይነገራለታል፡፡ በ1998 ዓ.ም እንደገና የመታደስ እድል አገኝቷል፡፡ በአሁኑ ሰዓት ሰው ከማይኖርበት ደሴት አንዱ ነው፡፡ የደሴቱ ነዋሪዎች የነበሩት ከመሬት ጥበት

የተነሳ ከዝዋይ ከተማ በስተደቡብ አቅጣጭ ቦጨሳ በሚባል መንደር ሰፍረው ይገኛሉ፡፡ የደሴቱ ነዋሪዎች ወደ ደሴቱ የሚመጡት ለክብረ በዓልና ዓሣ ለማጥመድ ብቻ ነው፡፡ ቀድሞ ብዙ ሰው ይኖርበት እንደ ነበረ የሚያሳዩ በርከት ያሉ የቤት ፍርስራሾች ይገኛሉ፡፡ በአሁን ሰዓት ከአገልጋዩ መነኩሴ ሌላ በደሴቱ ውስጥ በመኖር የሚታወቁት ወ/ሮ ኩሼ ጎንደር ብቻ ናቸው፡፡ በቅርስ በኩል በርከት ያለ ቁጥር ያላቸው ጽላቶችና ጥቂት የብራና መጻህፍት ይገኙበታል፡፡ ሁሉም ደሴት በልምላሜ ያጌጡ ቢሆንም የገሊላና ደብረ ሲና ግን የበለጠ ነው፡፡

### 3.1.5. የደብረ ሲና ደሴት

ደሴቱ ከባህር ጠላል በላይ 1636 ሜትር ከፍታ ላይ ይገኛል፡፡ ደሴቱ በእጣን ዛፍ፣ ዋርካ፣ ሾላ፣ ቁልቋል፣ ግራርና ቅንጭብ ዛፎች የተሸፈነ ነው፡፡ በ1974 ዓ.ም የቤተክርስቲያኑ የሳር ክዳን በመብረቅ ተቃጥሎ በአቶ ተፈራ መኩሪያ አስተባባሪነት በ1991 ዓ.ም በቆርቆሮ ታድሷል፡፡ በደሴቱ የሚገኘው ቤተክርስቲያን ደብረ ሲና ቅድስት ማርያም ይባላል፡፡ በደሴቱ ምስራቃዊ ዳራቻ የአቡና የሚካኤል ዋሻዎች ይገኛሉ፡፡ እንደ ገሊላ ደሴት በዚህ ደሴትም የሚኖሩ ሕዝቦች ወደ ቦጨሳ አከባቢ ተሰደው ወጥተዋል፡፡ በአሁኑ ሰዓት ከዘበኛው ወጪ ሁለት እናቶች ብቻ የሚኖሩበት ደሴት ነው፡፡ በደብሩ የሚከናወነው አገልግሎት የሚፈጸመው ከዝዋይ የካህናት ማሰልጠኛ ገዳም በሚመላለሱ ካህናት ነው፡፡

የደብረ ሲና ማርያም ቤተክርስቲያንም እንደ ገሊላ ካህናተ ሰማይ በርካታ ጽላቶች ያሉበት ነው፡፡ የነገስታት የለምድ ልብስ፣ የመጾር መስቀልና ሶስት የብራና መጻሕፍት የሚገኙበት ቢሆንም በዚህ ደሴት የሚገኘው የብራና መጽሐፍ ከሌሎቹ የሚለየው በደሴቱ መጻፉን በግልጽ የሚያመለክት መሆኑ ነው፡፡

## 3.2. የደሴቱ የቅርሶች ማዕከልነት

የዝዋይ ሐይቅ በአቀማመጡ ተመራጭነት የተነሳ የነገስታት የወግ ዕቃዎችና የከበሩ ድንጋዮች ማስቀመጫ ከሆኑት ሦስት ሐይቆች ማለትም ከሐይቅ እስጢፋኖስና ጣና ሐይቅ ጋር የሚደመር ነው፡፡ ለዚህም የሚጠቀሰው ነገር በዮዲትና በአህመድ ግራኝ ወረራ ወቅት እያሌ ዕቃዎች ወደ ደስያቱ መግባታቸው ነው፡፡ ዳንኤል ክብረት ይሄንን ጉዳይ ሲገልጹ የዝዋይ ሐይቅ ደስያት ታቦተ ጽዮንን ይዘው የመጡና በተለያየ ጊዜ ወደ አካባቢው የተሰደዱ አበው ይዘዋቸው የገቡትና

እዛው የተዘጋጁ የብዙ መጻህፍት ማዕከል ናቸው። በመላው ዓለም ጠፍቶ የነበረው መጽሐፈ ሄኖክም የተገኘው እዚህ ነው (ዳንኤል፣ 402) ይላሉ።

በ16ኛው ክፍለ ዘመን በአህመድ ኢብን ኢብራሂም ኤልጋዚ ወራራ ምክንያት ወደ ዝዋይ ደስያት በርካታ ጽላቶችና ንዋየ ቅድሳት ገብተው ከጥፋት ሊድኑ እንደቻሉም ይተረካል። ለዚህም እንደ ምክንያት የሚጠቀሰው የአህመድ ግራኝ የጦርነት ታሪክ ጸሐፊ የሆነው የመናዊው አረብ ፋቂህ ፍቱህ አልሀበሽ በተባለው መጽሐፉ እንዳሰፈረው በ1521ዓ.ም አህመድ ግራኝ ከደጋው ጉራጌ ተነስቶ ዝዋይ በደረሰ ጊዜ ታንኳ አሰርቶ ደሴቱን ለመውረር ሀሳብ ቢኖረውም ስንቅ ስላልነበረው እቅዱን ሰርዞ ወደ ሀዲያ ማቅናቱ ነው (ተስፋዬ፣ 39)።

ዳንኤልና ስርግው ይሄንን ጉዳይ ሲገልጹ የዝዋይ ደስያት የነገስታቱ የወግ ዕቃ ማከማቻ ስለ ነበሩ ግራኝ ቦታውን ለመውረር መጥቶ አንድ አሳሽ ቡድን በጀልባ ወደ ደሴቶቹ ላከ። ነገር ግን መነኮሳቱ ብዙዎችን ጠቃሚ ንብረቶች ደብቀዋቸው ስለ ነበረ አሳሾቹ ብዙም ሀብት የለውም ብለው ሪፖርት አድርጉ። እርሱም ወደ ሐዲያ አቀና (ስርግው፣ 238፤ ዳንኤል፣ 402) በማለት ነው። ሁለቱም አገላለጾች የተለያዩ ምክንቶች ቢጠቀሱም አንድ የሚያደርጋቸው ጉዳይ ግን የዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራት የግራኝ ወረራ ያልነካቸው መሆኑ ነው። እኔም በመስክ የመረጃ ስብሰባዬ እንዳረጋገጥኩት ከጥንታዊ ገዳማትና አድባራት የዮዲት ጉዲትና አህመድ ግራኝ ወረራ ካልነካቸው ስፍራዎች መካከል የዝዋይ ደስያት ተጠቃሽ መሆናቸውን ነው። ይህ የሚያመለክተን ደግሞ የደስያቱን የቅርስ ማዕከልነት ነው። ምክንያቱም እንደ ትውፊታዊ መረጃው ከሆነ በሁለቱም የወረራ ዘመን በሽሽት የገባ ቅርስ እንጂ የተወሰደ ነገር የለምና። ልዑል ራስ መኮንን የቁልቢ ገብርኤልን ገዳም እንዲያሰሩ መነሻ የሆናቸው በዝዋይ ያገኙት መጽሐፈ ቀሌምንጦስ እንደሆነም ይተረካል።

> አክሱማዊያን ከዝዋይ ስደት ተመልሰው ታቦታትን ሲቆጥሩ የቁልቢ ገብርኤል ታቦት መረሳቱ ሲታወቅ አባ ሌዊ ታቦቱን ለመውሰድ መጡ። ከ7ቀን ሱባኤ በኋላ ይዘው ሲሄዱ መልአኩ ገብርኤል ተገልጾ ስለ አዘዛቸው ወደ ቁልቢ ቦታ ወስደው ለ130 ዓመታት አገልግለው በንጉሡ ግርማዊ ሥዩም መንግስትም አርፈዋል። ጎንደራዊያን ካህናት በግራኝ ወረራ ወደ ዝዋይ ሲመጡ ስለዚህ ታሪክ የተጻፈ መረጃ አግኝተው መጽሐፈ ቀለሚንጦስ ላይ ጽፈው በደሴተ ዝዋይም አኖሩት። ልዑል ራስ መኮንን ይሄንን ታሪክ አግኝተው ታቦቱን አስመጥተው በ1884ዓ.ም አስተከሉት (ዳንኤል፣ 203-204)።

ይሄንን የዝዋይ ደስያትን የቅርስ ማዕከልነት አስመልክተው ጸሐፊ ትዕዛዝ ገብረ ስላሴ ያስፈሩት ትውፊታዊ ታሪክም የሚከተለውን ይመስላል፡፡

> ዳግማዊ ምኒሊክ ዚይ እንደ ደረሱ ደሴቶቹ ውስጥ የሚገኙትን ንዋየ ቅድሳትን የሚያዩ ቀሳውስትን ወደ ደሴቱ እንዲገቡ አዘው ቀሳውስቱም ብዙ የብራና ጽሑፎችን እንዳገኙ ይታወቃል፡፡ ነገሡም የተገኙ መጻህፍትና ንዋየ ቅድሳት በጥንቃቄ እንዲያዙ ማዘዛቸው የሚነገር ሲሆን አንድ ጥንታዊ የሃይማኖት መጽሐፍና አንድ በቅድስት ድንግል ማርያም ስም የተቀረፀ ጽላት ይዘው ወደ አዲስ አበባ እንደ ተመለሱም ይነገራል (ገብረ ስላሴ፣ 202)፡፡

## 3.3. የገዳምና አድባራቱ መመስረት

የዝዋይ ደስያት ሲነሱ የዛይ ማህበረሰብም አብረው ይነሳሉ፡፡ የደሴቱን ገዳምና አድባራት ከሕዝቡ ነጥሎ ማውራት አይቻልም፡፡ ስለ ዛይ ማህበረሰብ ሲወራ የአብያተ ክርስቲያናቱ ታሪክም አግረ መንገድ ይነገራል፡፡ ስለዚህ የሕዝቦቹን ወደ ደስያቱ መግባት መነሻ በማድረግ የሐይቁን ገዳምና አድባራት ታሪክ አቀርባለሁ፡፡

የደሴቶቹ ነዋሪዎች ራሳቸውን ዛይ ብለው የሚጠሩ ሲሆን በአካባቢው ኦሮሞዎች ደግሞ ላቂ ተብለው ይጠራሉ፡፡ በኦሮምኛ ቋንቋ ላቂ ማለትም ቀዛፊ እንደ ማለት ነው፡፡ ዛይ የሚለው የማህበረሰቡ መጠሪያ ስማቸው የሆነው ከመቼ ጀምሮ እንደሆነ ግን በትክክል አይታወቅም፡፡ ሆኖም ዝዋይ ከሚለው ቃል እንደ መጣ ይነገራል፡፡ ይኸውም በ9ኛው ክፍለ ዘመን ከዮዲት ወራራ ሸሽተው ወደ ደሴቱ የመጡት ስደተኞች አክሱማውያን የአካባቢውን ሙቀትና የደስያቱን ውኃና የመሬት አቀማመጥ ተመልክተው ከሙቀቱ የተነሳ በግዕዝ ቋንቋ ዝ-ዋዕይ-ይህ ቃጠሎ ሲሉት በልምላሜው የተነሳ ደግሞ ዝ-ዋይ ይህ መልካም ስፍራ ብለው ጠርተውታል ይባላል፡፡ ስያሜው ቀስበቀስ የነዋሪዎቹና የአካባቢው ሆኖ ሊቀር ቻለ፡፡ (ቃለመጠይቅ፣ መርጌታ ስምረ ግደይ በቀን10/08/05 ዓ.ም፣ ማህበረ ቅዱሳን ዘጋቢ ምስል ወድምጽ)፡፡ በሌላ መልኩ ዛዮቹ ስለ ራሳቸው ከሚናገሩት አንጻር ዛይ ማለት ሐቀኛ ማለት ነው፡፡ አንድ የዛይ ተወላጅ እኔ ዛይ ነኝ ሲል እውነተኛ ሰው ነኝ ማለቱ ነው (መምሬ ገብረ መስቀል ሂርጳ በቀን 2/08/05 ዓ.ም)፡፡

የዛይ ሕዝብ የአመጣጥ ታሪክ የአንድ ዘመን ክስተት ብቻ እንዳልሆነ ትውፊታዊ መረጃዎቹ ይገልጻሉ፡፡ ለዚህም እንደ ማስረጃ የሚጠቀሰው በዛይ ትውፊት መሰረት በቃል የሚነገረውና በጽሑፍ ሰፍሮ የሚገኘው ነው፡፡ ቃላዊ ትውፊቱ እንደሚለው በዝዋይ ሐይቅ ዙሪያ ጥንታዊ

ሕዝቦች ሰፍረው ይኖሩ ነበር፡፡ ሆኖም ድንገት በተፈጠረው የውኃ ሙላት ሕዝቡ ሕይወቱን ለማትረፍ ተሯሩጦ ያለቀው አልቆ የቀረው የወቅቱን ከፍተኛ ቦታዎች የዛሬዎቹን ደስያት ያዙ የሚል ነው፡፡ ነገር ግን ጊዜው መቼ እንደሆነ በትክክል የሚታወቅ ነገር የለውም (ቃለመጠይቅ፣ አቶ አበጋዝ ኩንቢ፣ በቀን 25/07/05 ዓ.ም)፡፡ በሌላ ቃላዊ ትውፊት የሚነሳው ደግሞ የ9ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ታሪክ ነው፡፡ ይኸውም ከዮዲት "ጉዲት"[11] መነሳት ጋር የሚያያዘው ነው፡፡ ስለዚህ ቀዳሚው የዛይ ሕዝብ ታሪክ እንደ ቃላዊ ትውፊት ማስረጃ ከሆነ ከእነዚህ ሕዝቦች ይጀምራል፡፡ ማህበረ ቅዱሳን ዘጋቢ ምስል ወድምጽ ደግሞ የዛይ ሕዝብ ወደ ደስያቱ የገባው በሶስት የታሪክ አዝማናት እንደሆነ ይዘግባል፡፡ ይኸውም በዮዲት ዘመን፣ በ14ኛው ክፍል ዘመን (በወቅቱ አካባቢውን ያስተዳድሩ የነበሩት የአጼ አምደ ጽዮን የጦር አዝማች ስበሃት ሰዶ አይመለል ደርሰው ሲመለሱ ከእሳቸው ጋር መጥተው እዚያው የቀሩ)ና በግረኝ ወረራ ከመንዝ በሽሽት የመጡ በማለት ነው፡፡

---

[11] ዮዲት ጉዲት በተለያየ ጊዜና በልዩ ልዩ ምክንያቶች ከምድረ ፍልስጤም ተነስተው ወደ አገራችን ከገቡት እስራኤላዊያን እንደሆነች ይታመናል፡፡ ዮዲት በላስታ አከባቢ(ቡግና) ከሚኖሩ ፈላሾች እንደ ተወለደች ሲገመት በ9ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ገደማም ዘመዶቿን አስተባብራ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ላይ የጥፋት ወረራዋን ጀምራለች፡፡ ለዮዲት ጉዲት መነሳት ዋነኛው ምክንያት በትክክል ምን እንደሆነ ባይታወቅም ከጥንት አባቶቿ (አይሁዳዊያን) የዘለቀ ክርስቲያኖችን ጥላቻና ለክርስቲያኑ የአክሱም መንግስት ግብር ለመክፈል አለመፈለግ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል፡፡ በዚህ ለ40 ዓመታት እንደ ቆየ በሚታመነው የጥፋት ዘመቻዋ ዮዲት በኢትየጵያ ቤተክርስቲያን ላይ ከባድ ጉዳት አድርሳለች፡፡ የአክሱም መንግስት ጭራሹን ተዳክሞ ንጉሥ አንበሳ ውድም ወደ መንዝ ሸሽቷል (መንግስቱና አሳምነው፣68)፡፡ በሌላ መልኩ ዮዲት በአባቷ የአክሱም ንጉሥ የውድም አስፈሬ ልጅ ስትሆን በእናቷ በዓድዋ አውራጃ የሐሐይለ ወረዳ ተወላጅ ናት፡፡ በልጅነቷ አባትና እናቷ ስለሞቱባት ዕድሜዋ 15 ሲደርስ በተወለደችበት ሀገር ከሀብታም ተቀጥራ መኖር ስለ አላፈራት አባቱ ሀገር አክሱም ሄጄ ታቦተ ጽዮንን ተማጽኜ እኖራለሁ ብላ ሠርታ የምትኖርበትን ሀብታም ስታፈላልግ እንደ ፀሐይ የምታበራ ቆንጆ ስለ ሆነች ሰርታ ለመኖር የመጣች አትመስለም በሚል ይመልሳታል፡፡ ደጅ ሰላም ብትወድቅም የሚመጸውታት አጣች፡፡ የ22 ዓመት ጎልማሳ አንድ ዲያቆን ሁሌ ለተልእኮ ወደ ቤተክርስቲያን ሲገባ አተኩሮ እያያት በልቡ ተመኛት፡፡ እህል ውሃም ይሰጣት ጀመረ፡፡ ከዚያም ሊገናኛት ጠየቃት የሚመግባት ስላጣች ብቻ የወርቅ ጫማ አጫምቶ ሸልሞ እንዲወስዳት ነገረችው፡፡ እሱም አብርሃ ወአጽብሃ ነገስት ለቤተክርስቲያን ከሰጡት የወርቅ መጋረጃ ቀዶ አዘጋጅቶ ሰጥቶ ወሰዳት፡፡ ካህናቱ የሆነውን ሲያዩ ደንግጠው ሕዝብ ጠርተው ነገሩን ሲያጣሩ በዮዲት ላይ ስለገኙት ዲያቆኑ ያደረገውን ቢያምንም አሳስታው ነው በማልት ሁለት ጡቶቿን በመቁረጥ ከኢትዮጵያ ጠረፍ ጣሏት፡፡ ግብጻዊ ንጉስ ካዳናት በኋላ ሚስት አድርጎ ወሰዳት፡፡ እሷም የአክሱምን ንጉስ አሸንፌህ ካህናቱን ታጠፋልኛለህ ብላ ቃል አስገብታው ስለ ነበረ ምቹ ሁኔታ ስታገኝ የንጉስን ሰራዊት ይዛ ቀይ ባህርን ተሻግራ ቤተክረስቲያናትን አቃጠለች፣ ክርስቲያኖቹን አጠፋች፣ ለ40 ዓመትም በሀገሪቱ ላይ መከራ አጸናች፡፡ የአክሱም ካህናት ግን ቀድመው መምጣቷን ሲሰሙ መጻህፍቶቻቸውን፣ ንዋየ ቅድሳትን፣ ታቦተ ጽዮንን ይዘው ወደ ደቡብ አቅጣጫ ሸሽተው ዝዋይ ደሴት ገብተው ተሸሸጉ (ዘመድኩን፣16-29)፡፡ ከላይ የቀረቡት ሁለቱም ሀሳቦች የተለያየ አካሄድ ቢኖራቸውም መደምደሚያቸው ዮዲት በቤተክርስቲያን ላይ ወረራ ማካሄዷንና አክሱማዊያን ካህናት የተለያዩ ቅርሶችንና ታቦተ ጽዮንን ይዘው ወደ ዝዋይ ደሴት መሻሻቸውን የሚተርኩ ናቸው፡፡

ክርስትናም በዚህ አካባቢ በትክክል መቼ እንደ ተሰበከ የሚገልጽ ምንጭ ባይገኝም ከዮዲት ወረራ ጋር ተያይዞ እናገኛዋለን፡፡ ጽላተ ሙሴ ወደ ዝዋይ ሐይቅ ስትመጣ በርካታ ታቦታትና ቅርሶች አብረው መጥተው ስለ ነበረና ሰላም ሲሰፍን ታቦተ ጽዮን ወደ ስፍራው ብትመለስም እዚያው በቀሩት ጽላቶችና ሕዝቦች አማካይነት ክርስትና ሊስፋፋ እንደቻለም ይገመታል (ቃለመጠይቅ፣ መምሬ መልአኩ ገብረ ማርያም በቀን 01/08/05ዓ.ም)፡፡ ሆኖም የደስያቱ ነዋሪዎች ሙሉ በሙሉ በዚህ ወቅት ወደ ክርስትና ተቀይረው ነበር ለማለት እንደሚከብድ ስርግው ሀብለ ስላሴ የሃይማኖቱ ትውፊታዊ መጽሐፍ ከሆነው ገድለ በጸሎተ ሚካኤል በመምዘዝ ዋቢ አድርገው "በአማርኛ የቤተክርስቲያን መዝገበ ቃላት" በሚለው መጻፋቸው ያስፈሩት ያሳያል፡፡

> ንጉሱም ቅዱሳኑን ከዚህ አስነስተው ወደ አንድ ትልቅ ባህር ስሙ ዝዋይ ወደሚባል ባሕሩ በጥልቀቱና በስፋቱ ትልቅ ወደ ሆነው እንዲያገቡአቸው አዘዘ፡፡ ያለ ታንኳ እዛ ለመግባት አይችሉም፡፡ አረማውያን ሕግና ሥርዓት ከማያቁ ከሚኖሩበት ደሴት አገቡዋቸው፡፡ እነሱም /አረማውያኑ/ የታረደና ያልታረደ የሚበሉ፣ የማይበሉ አራዊትንም የሚበሉ ነበሩ (ስርግው፣236- 238)፡፡[12]

ከላይ የቀረበውን የነዋሪዎቹን ሁኔታ ከግንዛቤ ካስገባን ክርስትና ወደ ደስያቱ የገባው በ14ኛው ምዕት መሆኑ ነው፡፡ ለዚህም እንደ ማስረጃ የሚያቀርቡት ደስያቱ የትምህርት ማዕከል ሆነው ማገልገላቸውንና በ14ኛው ምዕት ማብቂያና በ15ኛው መጀመሪያ አያሌ የሃይማኖት መጻሕፍት መጻፋቸውን ነው፡፡ ታደሰ ታምራት ገድለ አሮንን ዋቢ በማድረግ ይሄንን ጉዳይ ሲያጠናክሩ ከንጉስ ሰይፈ አርድ ጋር በነበራቸው አለመግባበት ፊሊጶስና አኖሪዎስ የተባሉ መነኮስት ወደ ዝዋይ እንደ ተወሰዱና በወቅቱ የነበሩት የደስያቱ ነዋሪዎች እምነት ያልነበራቸው፣ የታረዱም ሆነ የሞቱ እንስሳት ይበሉ እንደነበረ ይገልጻሉ፡፡

> የተለያዩ የገድል መጻህፍት እንደሚያስረዱት ፊሊጶስና አኖሪዮስ የሚባሉ መነኮሳት ወደ ዝዋይ ተወሰዱ፡፡ በደስያቱ ውስጥ ያለው ሕዝብ ከ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አንስቶ መኖር የጀመረ ነው፡፡ ደሴቱ ትልቅ ስፋትና ጥልቀት ያለው ካለ የበላ የማያሻግር ነው፡፡ ሕዝቡም ምንም ዓይነት እምነት የለሽና የሞተ እንስሳም የሚበላ፣ የሚበላውንና የማይበላውን የማይመርጥ ነው፡፡ መነኮሳቱም ይሄንን ከፊሉን ሕዝብ የመቀየርና

---

[12] 'ወአዘዘ ንጉስ ከመ ያፍልስዎ እምህየ ለቅዱስ ወያብእዎ ውስተ ባህር ዐቢይ ዘስሙ ዝዋይ ወባሕሩኒ ዕሙቅ ውእቱ በልቅየ ወርሕቡ፡፡ ወኢይበው እዎ ዘእንበለ ወበል፡፡ ወአብእዎሙ ውስተ ደሴተ ይነብሩ ውስቴቱ አረሚ እለ ኢየአምሩ ሕገ ወሥርዐተ ወይበልው ዘሕሩድ ወዘኢሕሩድ ወይበልዕ በህየኒ ወበዕጓነሂ አራዊተ እለ ኢይበልዑ፡፡'

> የደስያቱን ገዳማት የመመስረት ስራ ቀዳሚ ተግባራቸው ነበር፡፡ ከዚያ ወደ ደቡብና ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ እየተጓዙ ሃይማኖቱን የማስፋፋት ስራ ሰርተዋል (Taddesse, 189)፡፡

ዳንኤል ክብረትም በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከነገስታቱ ጋር በተፈጠረ አለመግባበት በግዞት አባ በጸሎተ ሚካኤል፣ አቡነ ፊሊጶስ፣ አባ አኖሪዎስ[13] እና አባ አሮን የሚባሉ መንፈሳዊ አባቶች ወደ ደስያቱ ተግዘው እንደ ነበር አስፍረዋል (ዳንኤል፣402)፡፡ ይሄንን ጉዳይ በሰፊው አስፍረው የምናገኘው ስርግው ሀብለ ስላሴ ናቸው፡፡ እንደ እሳቸው አገላለጽ ጥንታውያኑ የብራና መጻህፍት የተጻፉትም በዓጼ ዳዊት (1365-1395 ዓ.ም) ዘመነ መንግስት እንደ ነበረና አንዳንዶቹም የዚህን ንጉስ ስም እንደሚጠሩ ነው (ስርግው፣238 )፡፡ ዝዋይ የሚለው መጠሪያም በሥነ ጽሑፍ ሰፍሮ የተገኘው በዚህ ጊዜ እንደ ሆነ ገድለ አቡነ ፊሊጶስን ጠቅሰው አስፍረዋል፡፡

> ዝዋይን በሥነ ጽሑፍ ሰፍሮ የምናገኘው በመጀመሪያ የሸዋ መንግስት(1260-1559) ዘመን ነው፡፡ ይኸውም የቤተክርስቲያን ሰዎች ከዓጼ ዓምደ ጽዮን(1297-1327) ጋር የአባቱን ዕቁባት በማግባቱ ባበቀሉት ጸብ ነው፡፡ ከእነሱ እየተጋዙ ዝዋይ ይገቡ ነበር፡፡ ከእነዚህም አንዱ አቡነ ፊሊጶስ የደብረ ሊባኖስ 3ኛ እጨጌ ነበሩ፡፡ ገድሉ 'ወሰቤሃ አዘዘ ንጉሥ ይሰድዎ ለብጹዓ እምታዐካሁ ወያንብርዎ ማዕከለ ደሴት ዘሀለወት ውስተ ባሕረ ዟይ' (ገጽ 213)፡፡ የዚያን ጊዜ ንጉሡ ብጹዕነቱን ከቤተ መንግስቱ ወስደው በዝዋይ ባሕር መካከል ባለች› ደሴት እንዲያስቀምጡት አዘዘ ይላል (ስርግው፣237)፡፡[14]

ከላይ ትውፊታዊ ጽሑፎችን ዋቢ አድርገው የተገለጹት መረጃዎች የደስያቱን የክርስትና አስተምሮ ወደ 14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ቢወስዱትም ከዛይ ማህበረሰብ በቃል መጠይቅ የተሰበሰቡት መረጃዎች ግን በ842 ዓ.ም ጀምሮ በዝዋይ ደስያት ክርስቲያናዊ ሕይወት እንደ ተጀመረ ያስረዳሉ፡፡ ከጊዜ በኋላ የተዳከመ ቢሆንም በጊዜው የተጠናከረ አገልግሎት መኖሩን ይናገራሉ፡፡ የዓጼ ዳዊትን ስም በግልጽ የሚጠቅስ መጽሐፍ ከገድለ ቅዱሳን ውጪ እንደሌለም መጻህፍቱን የማገላበጥ እድሉ ያላቸው እንደነ መርጌታ ሰምረ ግደይ ያሉት ያስረዳሉ፡፡

---

[13] አባ አኖሪዮስ ተብለው የሚታወቁት ሶስት አበው ናቸው፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ የተጠቀሱት ታላቁ አኖሪዮስ ናቸው፡፡ እኚህም በላይ ወርቁ (26) እንደ ገለጸው በደብረ ሊባኖስ ከጻድቁ ተክለሃይማኖት ጋር የነበሩ፣ ንጉስ አምደ ጽዮንን ሁለት ሚስት ማግባት አልተፈቀደልህም በሚል ከነ አቡነ ፊሊጶስ፣ አባ በጸሎተ ሚካኤልና አባ አሮን ጋር በመሆን የተከራከሩ እንደ ሆኑ ያስረዳል፡፡

[14] ከገድለ አቡነ ፊሊጶስ በተጨማሪ ገድለ አኖሬዎስ ጥቂት ሰፋ ባለ መንገድ ይገልጸዋል፡፡---ወእምዝ ሶበ ነገርዎ ለንጉስ ዘይገብር ቅዱስ ርቱ ወመንክራተ መከረ ይሥድዎ ለቅዱስ ምስለ እለ ተርፉ ደቂቅ እምነዳ ወአብጽሕዎ ውስተ ደሴተ ባሕረ ዝዋይ ወነደግዎ ሐራ በከመ አዘዞሙ ንጉሥ (ገጽ 33)፡፡ ለንጉሱ ቅዱሱ ልዩ ልዩ ምልክቶችና ተአምራት እንደሚፈጽም በነገሩት ጊዜ በትልቁ ባሕረ ዝዋይ ከሚባለው ውስጥ ካለች ደሴት ውስጥ እንዲወስዱት መከረ፡፡ ቅዱሱንም ከተረፉት ደቀ መዛሙርት ጋር ከዳር ባሕረ ዝዋይ ውስጥ አደረሱትና ንጉሡ እንዳዘዛቸው ተውት (ስርግው፣ 237)፡፡

ክርስትና ተዳክሞ የነበረበትን ጊዜ ሲያስረዱ የዮዲትና ግራኝ ወረራ ያልደረሰባቸው፣ ተፈጥሯዊ አቀማመጣቸው ያስከበራቸው የዝዋይ ገዳምና አድባራት በዘመነ መሳፍንት ፈተና እንደ ገጠማቸው ነው፡፡ ከውጭው አካላት ጋር የነበራቸው ግንኙነት ተቋርጦ ስለ ነበረና ከሰሜኑ ክፍል ከመራቂ የተነሳ ያረጁ ካህናት ተተኪ ሳያገኙ በመቅረታቸው በዓመት ወደ ሌላ ሩቅ ስፍራ እየሄዱ ካህናት እያስመጡ እንደሚያስቀድሱበትና በአዘቦት ደግሞ የሀገሬው ሽማግሌዎች እሁድ ጥዋት ጥዋት ቤተክርስቲያን በመክፈት በገል እጣን ያጥኑ ነበረ፡፡ በተለይ ከ17ኛው እስከ 19ኛው ክፍለ ዘመን የምኒሊክ የዝዋይ ዘመቻ ድረስ የክርስትና እምነት እንጂ ጥምቀትና ቁርባን ሳይካሄድላቸው እንደ ኖሩ ይተረካሉ [ቃለመጠይቅ፣ አቶ ስቡህ ገብረ ማርያም፣ (በቀን 02/08/05 ዓ.ም)፤ መምሬ ገብረ መስቀል ሂርጳ፣ (በቀን 02/08/05 ዓ.ም)፤ አቶ ታደሰ አሼ፣ (በቀን 05/08/ 2005 ዓ.ም) መርጌታ ሰምረ ግደይ፣ በቀን 10/08/05 ዓ.ም]፡፡

ጸሐፊ ትዕዛዝ ገብረ ስላሴ ይሄንን ጉዳይ አስመልክተው ሲገልጹ ከደሴቱ ውስጥ ያሉ ሰዎች ክርስቲያኖች ናቸው፡፡ ነገር ግን መምህር አጥተው ጥምቀት ቁርባን ሳያገኙ እየጾሙ ቤተክርስቲያንንም ሲያረጁ እያደሱ በዓመትም በመንፈቅም ከሩቅ አገር ቄስ እያመጡ በመገልገል ፣ታቦታቱንና መጻህፍቱን እየጠበቁ ክርስቲያን ነን እያሉ ይኖሩ ነበር ብለዋል፡፡ በዳግማዊ ምኒሊክ የዝዋይ ዘመቻ ከላይ የተጠቀሰው ችግር ሊቃለል ቻለ፡፡ መጻህፍቱና ሌሎች ንዋየ ቅድሳት በጥንቃቄ እንዲያዙ ተደረገ፡፡ ደብረ ጽዮን ላይ የነበረው የገዳም ስርዓት በአዲስ መልኩ ብዙ መነኮሳትና ቀሳውስትን በመያዝ ተጠናከረ፡፡ የዛይ ሕዝብ ከዝቋላ ወደ ዝዋይ ገዳም በሚላኩት ቀሳውስት አማካይነት የጥምቀትን ስርዓት፣ ስጋ ወደሙን ማግኘት ቻሉ፡፡ ይሄንን ጉዳይ የደብረ አብርሃም ደሴት ነዋሪ የሆኑት አቶ ታደሰ አሼ ሲያስረግጡ "አባቶቻችን እንኳ የተጠመቁት ከእኛ ጋር ነው" በማለት ነው (በቀን 05/08/ 2005 ዓ.ም)፡፡

እነዚህ ከላይ የተነሱትን ቃላዊና ጽሑፋዊ የትውፊት መረጃዎችን የሚያስታርቅልን የገዳማዊ ሕይወት በደስያቱ የመጀመር ጉዳይ ነው፡፡ የክርስትናውን በ14ኛ መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሯል የሚል ሀሳብን የገለጹ አካላትን ስንመለከት የመነኮሳትን ወደ ደሴቱ መጋዝን በምክንያትነት ያነሱበት ነው፡፡ ይሄ ደግሞ የገዳማዊ ህይወት የተጀመረበት እንጂ ክርስትና የተሰበከበት ብሎ ለመደምደም የቃላዊ ተረክ መረጃዎች ይሞግታሉ፡፡ ምናልባት የተለያዩ አባቶች ወደ ደስያቱ በመምጣት ክርስትና በአዲስ መልክ እንዲስፋፋ፣ የምንኩስናና የገዳማዊ ህይወት በደስያቱ እንዲጀመር ምክንያት ሆኖ ይሆናል፡፡ ስለዚህ የ9ኛው ክፍለ ዘመንን የክርስትና አስተምህሮ

ጅማሬ በማድረግ 14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የገዳማዊ ሕይወት መሰረት የተጣለበት መሆኑን በማስረገጥ ይሄንን የሚያጸኑ የተወሰኑ ጉዳዮችን በማንሳት የዚህን ምዕራፍ ሀሳብ እቋጫለሁ።

በደስያቱ ካሉት አብያተ ክርስቲያናት አሁንም በገዳም ደረጃ ያለችው የደብረ ጽዮን ማርያም ናት። ሆኖም ግን መቼ እንደ ተገደመች በትክክል የሚታወቅ ነገር የለም። አንድ ለአዲሱ ቤተክርስቲያን ህንጻ ምረቃ የተጻፈች መጽሔት ላይ እንደ ተገለጸው ከሆነ የገዳም ጅምሬው የአጼ ዘረ ያዕቆብ ዘመነ መንግስት(1436-1468) ነው። ተስፋዬ እንደሚሉት ደግሞ በዚህ ዘመን ነው ብለን መደምደም አንችልም። ምክንያቱም ከዚያ በፊት አባ ሲኖዳን የመሰሉ አባቶች በዚህ ገዳም የምንኩስና ትምህርት ተምረው ወደ ጎጃም ሄደው ደብረ ዕሞና የሚባል ገዳም እስከ መመስረት ደርሰዋልና (ተስፋዬ፣44) ይላሉ። የዝዋይ ገዳም ሐዋሪያዊ ስራውን የጀመረው በእነ አባ ፊሊጶስና አኖሪዎስ በንጉስ አምደ ጽዮን እንደ ሆነና በ14ኛው ክፍለ ዘመን በርካታ መነኮሳት እንደሚኖሩበት የሚናገሩት ታደሰ ታምራት ደግሞ የዝዋይ የደብረ ጽዮን ገዳም የአንድነት ገዳም ሳይሆን ለቦታው ክብር ሲባል ድንግላዊ ቆሞስ የሚሾምበትና ሕጋዊያን የአካባቢው ቀሳውስት የሚያገለግሉባት ሆኖ እንደ ኖረ ይገልጻሉ። ይሄንን ሀሳብ ተስፋዬ ይሞግታሉ። የዝዋይ ገዳም በታሪክ ሂደት ውስጥ በአንድ ወቅት እያደገ በሌላ ጊዜ ቢደክምም ድንግላዊ ቆሞስ ብቻ የሚሾምበት ገዳም እንዳልሆነ ይገልጻሉ። ሰፋ ያለ የመከራከሪያ ሀሳብ ማምጣት ባይችሉም።

የደብረ ጽዮን ገዳም የአንድነት ገዳምም ነበረች ብሎ ለመናገር የሚቻል መረጃ የምናገኘው በንግስተ ነገስታት ዘውዲቱ ዘመነ መንግስት ነው። በፎቶ ማስቀረት ባይፈቀድልኝም በደብር ጽዮን ገዳም ከሚገኘው ሙዚየም ውስጥ ያለው መጽሐፈ ግንዘት መጨረሻ ገጽ ላይ በማህተባቸው ጭምር የተረገጠውን ለማንበብ እንደ ቻልኩት ንግስት ዘውዲቱ ለገዳሙ 150 ገባር የሰው ቁጥር፣ 50 ቀላድ መሬትና ከወንዙ ማዶ የሚቆመውን የቀዳሚት ገበያ ቀረጥ ከሰጡ በኋላ በ1913ዓ.ም እንደ ገና እንደ ገደሙት ይናገራል። ለገዳማዊያኑ ንፍሮ መቀቀያ የሚሆን ትልቅ ብረት ድስት በንግስቲቷ የተበረከተ ተብሎ ዛሬም ድረስ በእቃ ቤት ይገኛል። እነዚህ መረጃዎች የሚያመለክቱን የገዳሙን የቀደመ የንፍሮ ገዳምነት ታሪክ ነው። ገዳሙ በዚህ የታሪክ ሂደት ውስጥ ቢያልፍም አሁን ግን የአንድነት ገዳሙን ማዕረግ አጥቶ ከታሪኩ አንጻር ድንግላዊ ቆሞስ እየተሾመበትና የደሴቱ ቀሳውስት እያገለገሉበት ይገኛል።

በአጠቃላይ በታሪክ ካላቸው ክብር አንጻር የገዳምነት ማዕረግ ይዘው ቢታዩም በአገልግሎት ግን በአሁኑ ወቅት በደስያቱ የሚታየው ከዚህ በተቃራኒ ነው፡፡ ይሄንን እራሴ በምልከታ ያረጋገጥኩት ጉዳይ ነው፡፡ ሆኖም ጥንታዊነታቸውን የሚያሳዩ የተለያዩ ንዋየ ቅድሳት የሚገኙባቸውና ታሪኩን የሚነግሩ የሀገረ ሽማግሌዎች ያሉባቸው ናቸው፡፡ ስለዚህ በስፍራው ተገኝቼ በቃለመጠይቅ ያገኘኋቸውን ተረኮችና በምልከታ ያየኋቸውን ቁሳዊ ባህሎች የተመለከተ ፍካሬያዊ ትንተና በሚቀጥለው ምዕራፍ ለማሳየት ሞክሪያለሁ፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራት ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ትንተና

ይህ ምዕራፍ በቃለመጠይቅ፣ በምልከታና ሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች እንዲሁም በመሰነጃ መሳሪያዎቹ አማካይነት የተሰበሰቡት የቃላዊ ተረክና ቁሳዊ ባህል መረጃዎች በተመረጡት ንድፈ ሀሳቦችና ጽንሰ ሀሳቦች እንዲሁም ሞዴሎች ተፈክረው በገለጻና ትርጎማ ስልት ተተንትነው የቀረቡበት ነው። ይኸውም የዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራትን ታሪክ የሚዘክሩና የሚያትቱ በዘይቤ፣ በምሳሌና በትዕምርት የተሞሉት ተረኮች፣ ለትረካዎቹ ተጨማሪ ግብዓት በመሆን የሚያገለግሉትና የጥባባዊ እሴት መገለጫ፣ የመንፈሳዊ እሴት ነጸብራቅ፣ የታሪካዊ ድርጊት ዘጋቢ፣ ባህላዊ ገጽታን ማሳያና የዘመንን መንፈስ መፈተሻ የሆኑት ቁሳዊ ባህሎች በአንድምታዊ ትንታኔ ተዘጋጅተው የቀረቡበት ክፍል ነው።

### 4.1. ከዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራት የተሰበሰቡ ተረኮች ትንተና

የተረክ አይነትን ባነሳሁበት ክፍል ጃኮቴት የተባለውን ምሁር ጠቅሰው ባስኮም እንዳሰፈሩት ሚትና አፈታሪክ አንዱ በአንዱ ጣልቃ የሚገባ ስለ ሆነ ሚታዊ አፈታሪክ በሚል ይጠሩታል። በዝዋይ ደስያት የሰበሰብኳቸው ቃላዊ ዝርው ተረኮች የዚህ አይነት ሁኔታ ይታይባቸዋል። ለምሳሌ፡- መልአኩ ኡራኤል ጽዋውን ያጠበበት ሐይቅ፣ ወደ ዝዋይ ሐይቅ በረግረግ ላይ ሆነው በንፋስ ሐይል እየተመሩ የአክሱማዊያኑ ታቦተ ጽዮንን ይዘው ወደ ደስያቱ መግባት፣ አራስ ሴት ሳትዘጋው የቀረችው የጉድጓድ ውኃ ሐይቅ መሆን፣ ቀድሞ በመዝሙረኛው ዳዊት ትንቢት የተነገረለት ስፍራ መሆኑ፣ የማይቀደስበት ቁጡው ታቦተ ኢየሱስ መኖሩ፣ ለአክሱም ስረወ መንግስት መመለስና ለአዲስ አበባ ከተማ መመስረት ምክንያት መሆን የሚሉ ሚታዊ ባህሪ ያለባቸው እንዲሁም አፈታሪካዊ የሆኑ ናቸው። ሃይማኖታዊና ዓለማዊ ታሪኮች፣ ልዕለ ተፈጥሯዊና ልዕለ ሰብዓዊ ድርጊቶችና ሁነቶች የቀረቡባቸው ተረኮች ስለ ሆኑ ሚት ስንላቸው አፈታሪክ የሚያሰኝ ባህሪ አላቸው። አፈታሪክ ሲባሉ ደግሞ ወደ ሚት የሚያደላ ባህሪ ይታይባቸዋል። ሚታዊ አፈታሪክ የሚለው የፎክሎር ዘውግ ስለ ተቀደሰ አምልኳዊ ስርዓት፣ ሃይማኖታዊ ትውፊትና የሃይማኖቱ አማኒያን የት መጣነት ገላጻ የሚሰጥ ነው። የደስያቱ ተረኮችም በዚህ መነጽር ሲታዩ ሚታዊ አፈታሪክ ናቸው።

በምዕራፍ ሁለት እንዳነሳሁት ከቃላዊ ዝርው ትረካ የዘውግ ክፍፍል ጋር በተያያዘ ዳን ቤናሞስ የሚሉት በዘውግ ስንከፋፍል ቀያዊ ምደባን መጠቀም ያስፈልጋል ነው። ይህም ማለት የማህበረሰብ የቃል ታሪክ ጥናት ላይ ስናተኩር በማህበሩ አከፋፈልና ስያሜ መጠቀም፣ የእምነት ተቋማትም ሲጠኑ በዚያው ሪጋ መሄድ ነው። ከዝዋይ ደሴያት ገዳምና አድባራት መመስረት ጋር በተያያዘ የተገኙት ቃላዊ ተረኮች የመስኩ ምሁራን ባስቀመጡት የቃላዊ ዝርው ተረክ የዘውግ ምደባ አንጻር ሚታዊ አፈታሪክ ቢሆኑም የቃላዊ ተረኩ ባለቤቶች ወይም ተራኪዎች ስርዓት ባለው ዘውግ ከፋፍለው የሚያስቀምጡበት ሁኔታ አይታይም። ሆኖም ግን ተረኮቹን የሚተርኩት አረጋዊያን አባቶቻችን የነገሩን ታሪክ ነው፣ አፈታሪክ ነው፣ የሰማነው፣ ያየነው፣ ተአምር ነው በሚል የሚተርኳቸው ስለ ሆኑ የአከፋፈሉ ጉዳይ በዚህ መንገድም መታየት ይችላል። ለተረኮቹ ወጥ የሆነ ቀያዊ ዘውግ ናቸው ማለት ግን ይከብዳል። በአንድ መልኩ ሲታዩ ታሪክ ናቸው። ግለሰባዊ እውቀት ላይ የተመሰረቱ ስለ ሆኑ ደግሞ የግለሰባዊ ገጠመኝ ተረኮች ሊባሉ ይችላሉ።

ተረኮቹ ሃይማኖታዊ በመሆናቸው ከዚያ ጎራ ስናያቸው ደግሞ ሌላ ራሱን የቻለ የዘውግ ስያሜ ተሰጥቷቸው እናገኛለን። ይኸውም ትውፊት የሚል ነው። ቤተክርስቲያኒቱ በቃልም ሆነ በቁስ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፈውን ነገር በሙሉ ትውፊት በሚል ስያሜ ትጠራዋለች። ትውፊት[15] በሃይማኖት ውስጥ በቤተክርስተያን በኩል ያለው ስርዓት፣ እምነት፣ ታሪክ፣ ቅርስ ከቀደምት አበው ወደ ተተኪው ትውልድ በቃልም ሆነ በጽሑፍ እንዲሁም በቁስ የሚተላለፍበት ነው። ለዚህም ትልቅ ማስረጃ የሚሆነን በማህበረ ቅዱሳን "ቤተክርስቲያንህን ዕወቅ" በሚለው መጽሐፍ ውስጥ የሰፈረው ነው። ይኸውም "'ሃይማኖት ርትዕት እንተ ሐዋርያት ትውፊት' በማለት ቅዱስ ቄርሎስ እንደ ተናገረው የሐዋርያ ውርስ የሆነች ሃይማኖታችንን የተረከብናትም የምናስረክባትም መንገዱ ትውፊት ነው። ያለበለዚያ የክርስትናው ወንዝ መንገድ ይቆማል" (ማህበረ ቅዱሳን፣ 16)።

ከጥቅሱ ሁለት ዋና ሀሳቦችን መምዘዝ እንችላለን። የመጀመሪያው ከላይ ላነሳሁት ትውፊት ስያሜ ነው አንድም ዘውግ ነው የሚለውን የሚያጠናክርልኝ ሲሆን ሁለተኛው ሀሳብ ደግሞ

---

[15] አወፈየ ካለው የግዕዝ ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉሙም ውርስ ቅብብል ማልት ነው። አንድ ትውልድ ከእርሱ በፊት ከነበሩት ተቀብሎ በተራው ለተተኪው የሚያስተላልፍበት ነው። ዘአወፈየኒ አፈወይኩክ እንዳለ በስርዓተ ቅዳሴ (ቤተክርስቲያንህን ዕወቅ፣ ገጽ 9)።

ትውፊትን ሙሉ በሙሉ የሃይማኖቱ የእምነት ጉዳይ የሚተላለፍበት መንገድ በማድረጉ በዓይነት ለማዋገን ከባድ መሆኑን የምንረዳበት ነው፡፡ ይህ ደግሞ የመስኩ ምሁራን እንደሚሉት ሃይማኖታዊ ፎክሎርን በዘውግ ለመከፋፈል ስንነሳ የእምነት ጣልቃ ገብነት ያስቸግራል፣ የሚለውን የሚያስረግጥልን ይሆናል፡፡ ስለዚህም ጥናቱ የሃይማኖታዊ ፎክሎር መስክ ስለ ሆነ እምነቱን ትቼ ገዳምና አድባራቱ ትውፊታቸውን የሰሩባቸውን ወንዞች በመመርመርና ተምሳሌታዊ መንገዶችን በመለየት የተረኩን ፋይዳ ወደ መምዘዝ አመራለሁ፡፡ ስለዚህ ለተሰበሰቡት ቃላዊ ዝርው ተረኮች ቁርጥ ያለ ዘውጋዊ ትንተና መስጠት ባልችልም፣ የዘውግ ጉዳይ የእኔም ዋና ግብ ስላልሆነ ወሳኝ የሆኑ ጽንሰ ሃሳቦችን በመምዘዝ የጭብጥ ትንታና ለማድረግ ተረኮቹን በይዘት ከፋፍያቸዋለሁ፡፡

ከመስክ የተሰበሰቡት ተረኮች በይዘት ሲከፈሉ የገዳምና አድባራቱን ታሪክ የሚዘክሩ፣ ጥንታዊነታቸውን የሚገልጹ፣ የስፍራውን ቅድስና የሚሰብኩ፣ የነዋሪዎቹን ባህል ከሃይማኖቱ ስርዓት ጋር የሚያዛምዱና ማህበረ ባህሉን ለማስተማር ለመቆጣጠርና ለማጽናት የሚያገለግሉ፣ ለተፈጥሮ ምላሽ የሚሰጡ፣ የቦታውን ክብር ከፍ የሚያደርጉና ሉዓላዊነታቸውን የሚያስከብሩ እንዲሁም ማንነታቸውን የሚገነቡባቸው ሆነው አግኝቻቸዋለሁ፡፡

### 4.1.1. የገዳምና አድባራቱን ጥንታዊነትና ታሪካዊነት የሚዘክሩ ተረኮች

ጥንታዊነት[16] የሚለው ቃል ከቀድሞ ዘመን ጀምሮ ያለ ወይም ደግሞ ከጥንት ጀምሮ የነበረ ለማለት የሚያገለግል ነው፡፡ ታሪካዊነት[17]ደግሞ ድንቅ የሆነ ነገር ወይም ድርጊት የተፈጸመበት፣ በታሪክ የተመዘገበ ክዋኔ የተካሄደበት ለሚለው መጠሪያ ነው፡፡ የተረክ አንዱ ተግባር ደግሞ እንደዚህ አይነት ታሪካዊ ሁነቶችንና ድርጊቶችን መተረክ ነው፡፡ የጥንታዊነትና ታሪካዊነት ጉዳይ ደግሞ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ሰፊ ቦታ የሚሰጠው ነው፡፡ ለዚህም ይመስላል "እኛኮ ጥንትም የነበርን ነን" የሚሉ ንግግሮች በተለያዩ ማህበራዊ አውዶች ውስጥ የሚሰሙት፡፡

---

[16] ኣማርኛ መዝገበ ቃላት፣ ገጽ 560

[17] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 256

ከዝዋይ ደስያት የተሰበሰቡት ቃላዊ ተረኮችም የገዳምና አድባራቱን እንዲሁም አማኒያኑን ጥንታዊነት የሚገልጹ እንዲሁም ታሪካቸውን መዝግበው የሚተርኩ ናቸው፡፡ በምዕራፍ ሶስት ውስጥ እንደገለጽኩት ስርግው ሀብለስላሴ ገድለ አቡነ ፊሊጶስንና ገድለ አባ አኖሪዮስን ዋቢ አድርገው ዝዋይን በሥነ ጽሑፍ ሰፍሮ የምናገኘው በመጀመሪያ የሸዋ መንግስት ዘመን ነው ይላሉ፡፡ ይኸውም የቤተክርስቲያን ሰዎች ከዓጼ ዓምደ ጽዮን ጋር የአባቱን ዕቁባት በማግባቱ ባበቀሉት ጸብ እየተጋዙ ወደ ዝዋይ ይገቡ ነበርና ይሄንን ታሪክ በገድሎቻቸው ውስጥ ተከትቦ እንደምናገኘው ይገልጻሉ፡፡ ከዚህ የምንረዳው የዝዋይ ሐይቅና ደስያትን ታሪክ የምናገኘው ከ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ መሆኑን ነው፡፡ ቃላዊ ተረኮቹ የሚነግሩን ግን ከዚህ የተለየ ታሪክ፣ ሌላ ያልተባለ ጥንትን ነው፡፡

በመጀመሪያ የሚነሳው ተረክ ከታቦተ ጽዮን ጋር በተያያዘ የሚተረከው ነው፡፡ ይኸውም በአባሪ ክፍል በተረክ አንድ ስር የሰፈረው ትረካ ነው፡፡ ተረኩ እንደሚያስረዳን የዝዋይ ገዳምና አድባራት መመስረት መነሻ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደሆነ ነው፡፡ አብዛኞቹ ሥነ ጽሑፋዊ መረጃዎች የዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራት ምስረታ ወደ 14ኛውና 16ኛው ክፍለ ዘመን ይወስዷቸዋል፡፡ ቃላዊ ተረኮቹ ደግሞ ከዚህ በተለየ ጽንፍ የቆሙ ናቸው፡፡ ይሄንንም ከሚከተለው አንቀጽ መረዳት እንችላለን፡፡

> ታቦተ ጽዮን ከዮዲት ጉዲት ወረራ ሸሽታ 40 ዓመት የተቀመጠችው በደብረ ጽዮን ደሴት ላይ ነው፡፡ ይሄ የሆነው በ842 ዓመተ ምህረት ነው፡፡ አንበሳ ውድም እዚሁ በንግስናው ተቀመጠ፡፡ ግዛታቸውንም ወደ አምስቱም ደስያት አስፋፉ፡፡ ከ40 ዓመት በኋላ ታቦተ ጽዮንን ይዘው ሲመለሱ ቦታው ከጠላት ለመሸሸግ ጥሩ ስለ ሆነ ከመጻህፍቱም፣ ከታቦታቱና ሌሎች ቅርሶችም አስቀሩ፡፡ ከሕዝቡም ግመሹ ይቺ የመከራችን ቀን ቦታ ናትና ብለው ተከፍለው ቀሩ፡፡ አንባሰ ውድምም ልጁን አንግሦ ሄደ፡፡ ከዚያ አጼ ምኒሊክ ሀገሪቱን አንድ እስከ አደረጉት ድረስም የተለያዩ ንጉሦች በደስያቱ ነግሠዋል ይባላል (ቃለመጠይቅ፣ መርጌታ ስምረ ግደይ በቀን 10/08/05 ዓ.ም)፡፡

ከዚህ ቃላዊ ተረክ እንደምንረዳው የዛይ ማህበረሰብ ወደ ዝዋይ ደስያት መግባት መነሻ 9ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደ ሆነና የገዳምና አድባራቱም መመስረት ከዚሁ ጊዜ ጋር እንደሚያያዝ ነው፡፡ ማህበረሰቡም ከ9ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እስከ 19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ የራስ ገዝ አስተዳደር በደስያቱ እንደ ነበረ ነው፡፡ ይሄንን መረጃ የምናገኘው ደግሞ በሚተረኩት ተረኮች ነው፡፡ ይሄንን አስመልክቶ ያነጋገርኳቸው ሁሉም የደስያቱ አረጋዊያን አንድ አይነት ምላሽ ያላቸው ናቸው፡፡ ለተጨማሪ ግብዓት አቶ ስቡህ ገብረ ማርያም የተናገሩትን አቀርባለሁ፡፡

> አባቶቻችን ሲነግሩን ዮዲት ጉዲት የተባለች እንዳውም እሳቷ ይሎታል አሉ፤ በዘመኗ በርካታ ቤተክርስቲያናትን አቃጥላለች። ታዲያ የአክሱም ጽዮን ቤተመቅደስ ልታቃጥል ወደዚያ ስትመጣ አክሱማውያኑ ታቦተ ጽዮንን ይዘው ይሸሻሉ። ታቦተ ጽዮንን ይዘው መሸሻቸውን ስታውቅ ማሳደድ ትጀምርላች፤ እነሱ ደግሞ መንዝ ገብተው በተራራማው ስፍራ ይሸሸጋሉ። እሷም ተከትላ መጥታ ጦርነት ትከፍትባቸዋለች። ቦታው ተራራማ ስለ ሆነ አመቺ ሆኖላቸው ለጊዜው ድል ይቀናቻዋል። ሆኖም ግን ሀይሏን አጠናክራ ከተመለሰች ልትጎዳቸው ስለምትችልና ብዙም አስተማማኝ ስላልመሰላቸው ቀን ቀን እየተደበቁ ለሊት ለሊት እየተጓዙ በእግዚአብሔር መሪነት ወደዚህ ስፍራ ይመጣሉ። ወደ ሐይቁ ለመግባት እንደ አሁኑ ጀልባ የለም። በወቅቱ ብዙ ነገር ይዘዋል ታቦታቱና ካህናቱ አሉ። ያው እግዚአብሔር ሲያዘጋጅላቸው ረግረግ ያገኛሉ። ረግረጉ በጣም ትልቅ ነው አንድ ደሴት ያክላል፤ በንፋስ ነው የሚመራው። በረግረጉ አማካይነት በሐይቁ ላይ ተጉዘው መጀመሪያ ያረፉበት ደሴት ደብረ አብርሃም የሚባለው ነው። እዚያ እንዳረፉ ለታቦተ ጽዮን ማረፊያ እግዚአብሔር የፈቀደው ከሆነ ብለው አስቴውን ይሰብቃሉ፣ እሳት አልሰጣቸው ይላል። በመጨረሻ የወይዘሮ ተራራ ሰቀላይ ተብሎ የሚጠራበት ስፍራ አስቴውን ሲሰብቁት ብርሃን ሰጣቸው። ይህ እግዚአብሔር የፈቀደልን ስፍራ ነው ብለው ታቦተ ጽዮንን ይዘው ለ40 ዓመት ተቀመጡ ይባላል (አቶ ስቡህ ገብረ ማርያም በቀን 2/08/05 ዓ.ም)።

ከዚህ ተረክም እንደምንረዳው የገዳምና አድባራቱ መመስረት ምክንያት የታቦተ ጽዮን ወደ ስፍራው መምጣት ነው። ይሄ የሆነው ደግሞ በዮዲት ወረራ ጊዜ ነው። ይሄ ደግሞ የሆነው የልዕለ ተፈጥሮ ረድኤት ኖሮበት እንደሆነ ተረኩ ያስረዳል። ምናልባት ለብዙ ተመራማሪዎች እንቆቅልሽ የሆነው የታቦተ ጽዮን ሀገራችን መኖር ላይም አንዳች የሚፈነጥቀው አንድምታ አለ። ከክብረ ነገስት ትውፊታዊ መረጃ አንጻር ታቦተ ጽዮን በቀዳማዊ ምኒሊክ ዘመን ከእስራኤል መጥታ አክሱም እንደ ተቀመጠች ይነገራል። አክሱም ከገባች ወዲህ ደግሞ የተለያዩ ፖለቲካዊ ሽኩቻዎች ሲፈጠሩ ለዚህች ለዓለማችን ውድ ቅርስ የሆነችው ደህንነት ሲባል ካህናቱ ወደ ተለያየ ስፍራ ይዘዋት እንደ ተሰደዱ ይተረካል።[18] ከእነዚህ ተረኮች መካከል በዝዋይ ደስያት ለ40 ዓመት መሸሸጓን የሚነግረን አንዱ ነው። እነዚህን ሁሉ መረጃዎች የሚነግሩን ቃላዊ ተረኮቹ ናቸው። ስለዚህ ቃላዊ ተረኮች ታሪክን የመዘከር አገልግሎት አላቸው የሚባለው ከዚህ አንጻር ነው።

---

[18] ታቦተ ጽዮን ድጋሚ ወደ ዝዋይ አልተመለሰችም። የአክሱም አባቶች እንደሚገልጹት በዮዲት ወረራ 40 ዘመን በዝዋይ ደስያት፣ በግራኝ ወረራ ወደ ሀምሴን (ጉንዳ ጉንዲ በመባል ወደሚታወቀው ደብረ ገሪዛን ገዳም) እና በአጼ ሱስንዮስ ዘመን በዛሬዋ ኤርትራ በከረን አቅራቢያ 230 ሜትር ከፍታ ባላት ደብረ ሲዳ (ደብረ ሲያት) መሄዷን ይናገራሉ (የማህበረ ቅዱሳን ዘጋቢ ምስል ወድምጽ)።

ቃላዊ ተረኮች በጽሑፍ ያልሰፈረን ታሪክ እንደሚነግሩን ሁሉ በሚተረኩበት ጊዜ በሌላ ጽሑፋዊ ተረኮች የሚደገፉበትና በቁሳዊ ባህል የሚጎሉበት ሁኔታም አለ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ተረኮች ጥንታዊነትንና ታሪካዊነትን የሚዘክሩ ናቸው ብዬ ላነሳሁት ሌላ ግብዓት የሚሆነው በአባሪ ክፍል በተረክ ሁለት የቀረበው ነው፡፡ ተረኩ ከማህበረሰቡ "ዛይ" ብሎ መጠራት ጋር በተያያዘ የሚነገር ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ካነጋገርኳቸው መረጃ አቀባዮቹ መምሬ ባንቲሁን የተናገሩትን ማቅረብ ይቻላል፡፡ ይኸውም "ዝዋይ ሐይቅ የመጣነውና ወደዚህም ደስያት የገባነው በ9ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ቢሆንም ቀድሞ ግን እግዚአብሔር ለዚያች ክፉ ቀን ማምለጫ ብሎ ያዘጋጀልን ስፍራ ነው፡፡ ቀድሞ በልበአምላክ ዳዊት አማካይነት የተነገረ ትንቢት አለ፡፡ ይሄንን ከምን እንደምትረዳው ታውቃለህ የማህበረሰቡ ስያሜ እራሱ ዛይ ከመሆኑ ነው"(መምሬ ባንቲሁን ሀብተ ማርያም በቀን 02/08/05 ዓ.ም)፡፡

የመምሬ ባንቲሁን ንግግር እንደሚያስረዳው ዛይ የሚለው ቃል ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጠቅሶ እናገኘዋለን፡፡ ቃሉን የተናገረው መዝሙረኛው ዳዊት እንደ መሆኑ መጠን ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ከ900 መቶ አመት በፊት የነበረ ነው፡፡ "ዛይ ብሂል ዝኩር እግዚአብሔር፡፡ ዛይ ተዘከር ቃለከ ዘአሰፈውኮ ለገብርከ" (መዝ.118፣ 49)፡፡ የነብዩ ቃል ዛይን በሁለት አንድምታዊ ፍቺ አስቀምጦታል፡፡ አንደኛው የእግዚአብሔር ቃል ሕያው እንደሚያደርግና መጽናኛ እንደሆነ የሚገልጽ ነው፡፡ ሁለተኛው ለዛይ ቃል የተሰጠው ፍቺ ደግሞ ለአገልጋይህ የገባኸውን ቃል አስብ በዚያ ተስፋ ስጥተኸዋልና የሚል ነው፡፡ የመዝሙረኛው ቃል ለዛይ ማህበረሰብ የተነገረነው ብሎ ደፍሮ መናገር ይከብዳል፡፡ ሆኖም ማህበረሰቡ ለእኔ የተነገረ ትንቢት ነው ካለ የምንመዘው ነገር አናጣም፡፡ ለዚህም የሁለተኛውን ለዛይ ቃል የተሰጠውን ፍቺ ስንመለከት "ለአገልጋይህ የገባኸውን ቃል አስብ በዚያ ተስፋ ስጥተኸዋልና" የሚል ነው፡፡ ፈጣሪ ለፍጡራኑ ተስፋ ይሰጣል የሚመስገነው በእነሱ ነውና፤ ያ ተስፋ ደግሞ የማይሻር ነው፡፡ የዛይ ማህበረሰብ ተስፋ የተሰጠው ነው፤ ተስፋው ደግሞ በዛይ ማይ ነው እንበል፡፡ ምክንያቱም እንደ ተረኮቻቸው የቃል ኪዳኑንን ታቦት የያዙ ሕዝቦች ናቸውና፡፡ ጽላተ ሙሴን ይዘው የነበሩ እስራኤላውያን በመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ነገር ተብሎላቸዋል፤ ትንቢትም ተነግሮላቸዋል፡፡ ከጠቢቡ ሰሎሞን በኋላ ግን በግልጽ ከቃል ኪዳኑ ታቦት ጋር ተያይዞ የተነገረ ነገር የለም፡፡ የዛይ ማህበረሰብም እውነት የቃል ኪዳኑን ታቦት ይዞ ከነበረ ስለ እነሱም በትንቢት ተነግሮላቸው ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ አክሱማዊያኑ እግዚአብሔርን በያዙት የቃል ኪዳኑ ታቦት እያመሰገኑ ሲኖሩ አምላካቸው በዮዲት

ወረራ የሚመጣባቸውን አስቀድሞ ያውቅ ስለ ነበረ የሚሸሸጉበትን የዛይ ማይን አዘጋጀላቸው ማለት ነው። ዛይ ቀድመ ልደተ ክርስቶስ በእግዚአብሔር እሪና ታስቦ በልበ አምላክ ዳዊትም ትንቢት ተነግሮለታል ካልንና አክሱማዊያኑን ስደተኞች በመከራቸውም ቀን አምላካቸው አስቧቸው የተስፋውን መሬት የዛይን ሐይቅ አውርሷቸዋል ካልን ሕዝቡ ታሪካዊ፣ ቦታው ጥንታዊ ሆነ። ስለዚህ ተረኮቻቸው ታሪካዊነትንና ጥንታዊነትን የሚዘክሩ ናቸው ማለት ይቻላል።

የስፍራውን ጥንታዊነትና ታሪካዊነት ከሚዘክሩት ተረኮች ጋር ተያይዞ ስለ ተነሳው የታቦተ ጽዮን ጉዳይ ተጨማሪ መረጃ ማከል አስፈላጊ ነው። ጽላተ ሙሴ በናቡከደነጾር ጦርነት ከአለም ላይ እንደ ጠፋ ቢታመንም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ይሄንን ቅርስ እንደ ያዘች ትናገራለች። የተለያዩ የውጪ ምሁራንም የቃል ኪዳኑን ታቦት መሰረት አድርገው የተለያዩ ጥናቶች ሰርተዋል። ከዚህ ውስጥ 10 ዓመት የፈጀውና ጥልቅ ምርምር አድርጎ የታቦተ ጽዮንን በኢትዮጵያ መኖር ያረጋገጠው የግራሃም ሐንኮክ "The Sign and the Seal" የሚለው መጽሐፍ ተጠቃሽ ነው። የጽላተ ሙሴ ጉዳይ የዚህ ጥናታዊ ስራ የትኩረት አቅጣጫ ባይሆንም በተረኮቹ አማካይነት ከተነሳ ዘንዳ በመስክ ከሰበሰብኩት መረጃ የተወሰነ ነገር አክሎ ማለፉ ተገቢ ይሆናል።

የዛይ ማህበረሰብ የተለያዩ ጎሳዎች የፈጠሩት ማህበረሰብ እንደሆነ ይታመናል። በእያንዳንዱ ደሴት ከአምስት በላይ ጎሳ ይጠቀሳል። ከእነዚህ ውስጥ በደብረ ጽዮን ደሴት በቀዳሚነት እንዳረፉ ከሚነገርላቸው መካከል አንዱ የአርኚ ጎሳ ነው (ቃለመጠየቅ፣ መምሬ ባንቲሁን ሀብተ ማርያም፣ በቀን 30/07/05 ዓ.ም)። የዚህን ስያሜ የት መጣነት ስናጠና ተስፋዬ (8) "The Dictionary of Ethiopian Biography" የሚለውን መጽሐፍ ጠቅሰው እንዳስፈሩት አርኚ በንጉስ ዳዊት ዘመነ መንግስት (1011-971 ዓመተ ዓለም) የነበረው የነብዩ ናታን ልጅ እንደሆነና ልጁም ኤሌምያስ እንደሚባል ይጠቅሳል። ኤልምያስ የንጉስ ሰሎሞንን ልጅ ቀዳማዊ ምኒሊክን አጅበው ወደ ኢትዮጵያ ከመጡት አንዱ የነበረና በሊቀ ዲያቆንነት ሲያገለግል እንደ ነበረ ተጽፎ እናገኛለን። ምናልባት አርኚ የሚባለው የዛይ ነገድ ምንጭ ከሊቀ ዲያቆኑ ኤልምያስ ጋር አያይዘን ግምት ማስቀመጥ እንችል ይሆናል። ለዚህ ግምትም ምክንያት የሚሆንን የዛይ ማህበረሰብ ተረክ ነው። አክሱማዊያኑ ስደተኞች በዮዲት ወረራ ጊዜ ታቦተ ጽዮንን ወደ ዝዋይ ሐይቅ ይዘው እንደ መጡና ከ40 ዓመት በኋላ ሲመለሱ ገሚሱ ሕዝብ እንደ ቀረ ከላይ አንስቻለሁ። ከቀሩት መካከል

የአርኘ ጎሳ ይጠቀሳል። ዛሬም የዚህ ነገድ አባላት በዝዋይ ደሴያት ይኖራሉ። መምሬ ባንቲሁን እንደ ነገሩኝ ይሄ ነገድ ከሌላው የዛይ ሕዝብ ተለይቶ የሚታወቅበት በየዓመቱ የአባ ኤዎስጣቴዎስን ዝክር የሚዘክር መሆኑ ነው። ትግራይ ውስጥ ደግሞ የአባ ኤዎስታጣቴዎስ ታላቅ ዓመታዊ ክብረ በዓል እንዳለ ይነገራል።[19] እነዚህ ነገሮች የሚያመለክቱት የዝዋይ ደሴያት ከሚኖሩት ነገዶች መካከል ከአክሱም ፈልሶ የሄደ ጎሳ እንዳለ ነው። የዚህን ነገድ የፍልሰት ጊዜና ይዘው የፈለሱትን ቅርስ ስንመረምርና በዮዲት ወረራ ዘመን ከታቦተ ጽዮን ጋር የተያያዘ ሆኖ እናገኘዋለን። የእነዚህ ተረኮች ድምር ውጤት ተግባር ደግሞ በዝዋይ ሐይቅ ደሴያት ላይ ገዳምና አድባራትን መስርተው የሚኖሩትን ነገዶች ታሪክ የሚዘግቡና ጥንታዊነታቸውን የሚዘክሩ መሆናቸውን ነው። የደሴያቱ ጽላቶች (በአሁኑ ወቅት የማይቀደስበት እንደ ቁጡው ታቦተ ኢየሱስ ያለ የአሪኝ ጎሳ ይዞት የገባው) ከታቦተ ጽዮን ጋር የመጡ በመሆናቸው መቅደሶቻቸው የሆኑትን ገዳምና አድባራቱንም ጥንታዊና ታሪካዊ የሚያስብሉ ናቸው።

ከዘር ሀረጋቸው ጋር በተያያዘ በተለያያ ጊዜ የሚፈጽሙት ባህላዊ ጉዳያቸውና ዝማሪያቸውም ሌላ ተጨማሪ ግብዓት ሆኖ አግቼዋለሁ። በዚሁ ንዑስ ርዕስ ስር አንስቶ ማለፉ ተገቢ ስለሚሆን አቅርቤዋለሁ። በዚህ ጉዳይ ላይ ያነጋገርኳቸው እንደሚሉት “የዛይ ባህል ከሌላው ሕዝብ በእጅጉ ይለያል። በተለያዩ ወቅቶች ለእግዚአብሔር የሚያቀርባቸው ምስጋናዎች እንኳን የተለዩ ናቸው” (ቃለመጠይቅ፣ ቀሲስ ተስፋዬ ነቢ፣ በቀን 09/08/05 ዓ.ም)።

በዛይ ማህበረሰብ ውስጥ ለምን እንደሆነ ባልታወቀ መልኩ የዛይ ማህበረሰብ መዝሙር ሲነሳ ስፊውን ስፍራ ይዞ የምናገኘው የሴቶቹ ምስጋና ነው። ምናልባት ራሳቸውን ከእስራኤል ዘር የሚቆጥሩት እነዚህ የዛይ ነገዶች ባህረ ኤርትራን ሲሻገሩ በቅድሚያ ራሷን ለምስጋና ያዘጋጀችው የሙሴ እህት ማርያም ስለ ነበረች።[20] በዚህም ታቦተ ጽዮንን ይዘው ከዮዲት ጥቃት ሸሽተው

---

[19] በ14ኛው ክፍለ ዘመን በትግራዩ አባ ኤዎስጣቴዎስ (1273-1352) ትምህርት ቤትና በሸዋው የተክለ ሃይማኖት ትምህርት ቤት መካከል ልዩነት ተነስቶ ነበር። ይህም የቀዳሚት ሰንበት ትከበር አትከበር ነው። የተክለ ሃይማኖት ቀዳሚት ሰንበት መከበር የለባትም የብሉይ ኪዳን ተፅዕኖ ነው ሲሉ ኤዎስጣቴዎስና ተከታዮቻቸው ግን ቅዳሜም እንደ እሁድ መከበር አለባት ይሉ ነበር። አባ ኤዎስጣቴዎስ በዚሁ ምክንያት ወደ ሐይቅ ተጉዘው 4 ዓመት ከቆዩ በኋላ ተፈትተው ወደ አርመን አገር እንደ ሄዱና እንዳረፉ ይተረካል። ደቀ መዛሙርቶቻቸው ግን ትምህርቱን እስከ መሀል አገር ሄደው እንዲሰብኩ አዘዋቸው ነበር። የአባ ኤዎስጣቴዎስ ደቀ መዝሙር የነበረው የገብረ ኢየሱስ ተከታይ እና ደቡብ ካመሩት ውስጥ አንዱ እንድርያስ የሚባለው ነበር (Taddesse, 216-219፤ ሉሌ፣72)።

[20] ዘጸ. 16፣21

ወደ ዝዋይ ሐይቅ በረግረግ ተሻግረው ሲገቡ ሴቶቹ ቀድመው ዝማሬውን ጀምረውት ሊሆን ይችላል፡፡ በእስራኤል ዘንድ አብዛኛውን ጊዜ የሚዘፍኑት ሴቶች ነበሩ፡፡ የእግዚአብሔር ታቦት ከአሚናዳብ ቤት ወደ ኢየሩሳሌም ስትመለስ ከሚዘፍኑት መካከል ሰፊውን ሚና የወሰዱት ሴቶቹ ናቸው፡፡ ዳዊት ጎልያድን ድል አድርጎ ሲመለስ በዘፈንና በጭፈራ የተቀበሉትም ሴቶች ናቸው፡፡[21]

የዛይ ማህበረሰብ መዝሙር መቼ እንደ ተጀመረ በግልጽ የሚታወቅ ነገር የለውም፡፡ በዛይኛ የሚቀርብ እንደ መሆኑ መጠን ከዛይ ህዝብ መፈጠር ጋር የሚስተካከል እድሜ እንደሚኖረው መገመት ይቻላል፡፡ በስርዓቱ ላይ ከሚስተዋለው አንጻር ግን ከዚያም የሚዘል ሆኖ ልናገኘው እንችላለን፡፡ ምክንያቱም ዝማሬው የሚቀርበው በሴቶቹ ብቻ መሆኑና ሂደቱ ሲታይ የእስራኤላዊያኑን ባህል፣ የብሉዩን ተረክ የሚጠራ ስለ ሆነ እነሱም የዘር ሀረጋቸውን ከዚያ እንደሚቆጥሩት ሁሉ ተያይዞ የመጣ ነገር ሳይሆን እንዳልቀረ መገመት ይቻላል፡፡

የዘር ሀረጋቸውን እስከ 18 ትውልድ እንደ ደረሰ የሚናገሩት የዛይ ማህበረሰቦች ዘራቸውን ሲቆጥሩ ከእስራኤል ወገን እንደ ሆኑ ለማሳየት "እስራኤል" ብለው ይቆማሉ፡፡ ምናልባትም ክብረ ነገስትን የመሰሉ የትውፊት መጻሕፍትና ሌሎች ቃላዊ ተረኮች እንደሚሉት ቀድሞም ከኢየሩሳሌም ታቦተ ጽዮን ስትመጣ የእስራኤል ወገኖች አብረው እንደ መጡ ይተረካል፡፡ ወደ ዛይ ደስያት በተሰደደችበት ጊዜም እንደዚሁ የአይሁድ ዘር ያላቸው ወገኖች አብረው ሄደው ይሆን የሚለውን ነገር የሚያጭር ነው፡፡ ይሄ እንግዲህ አንዱ ተረክ የሌላውን ትረካ ተአማኒነት ለማጉላት የሚያቀርብም ሊሆን ይችላል፡፡ የዘር ሀረጋቸውን አቆጣጠር ምሳሌውን ለማሳየት ያህል መምሬ ባንቲሁን (በቀን 2/08/05 ዓ.ም) ደብረ ጽዮን ደሴት ላይ በእዮራም ቤት ወደ ኋላ የቆጠሩልኝን መመልከት ይቻላል፡፡

> ሰይፈ ከብሩ የተወለደ ነው፡፡ ብሩ ደግሞ ከማጭኝ → መጭኝ → አሊቦ → ልብሴ → ባህርጣስ → ዳኪዮስ → ወልደ መስቀል → ባንቱ → ኢዮራም → የከናፍር → እናሩ → እጥቁ → እንቁ→ ዘረሰናይ → አዶናይ → እስራኤል

---

[21] 1ኛ ሳሙ.7፣2፤ 1ኛ ሳሙ.18፣6 ዳዊት ፍልስጤማውያንን ከገደለ በኋላ ሰወቹ ወደየቤታቸው በሚመለሱበት ጊዜ፣ ሴቶች ከበሮና መሲንቆ ይዘው እየዘፈኑ፣ እየጨፈሩና እልል እያሉ ንጉሥ ሳኦልን ለመቀበል ከእስራኤል ከተሞች ሁሉ ወጡ፡፡ ሴቶቹም እንዲህ በማለት በመቀባበል ዘፈኑ፤ ሳኦል ሺህ ገደለ ዳዊት ግን እስር ሺህ ገደለ፡፡

ከዘር ቆጠራው እስራኤል ማነው? የሚል ጥያቄ ሊመዘዝ ይችላል። ምክንያቱም እስራኤል ሀገር ናት ወይስ የሰው ስም የሚለው ነገር ይነሳልና። የዘር ሀረጋቸውን በዚህ መልኩ የሚቆጥሩት የደስያቱ ሰዎች እንደ ነገሩኝ "እስራኤል" የሚለው ስያሜ ላይ የሚቆሙት የዘር ግንዳቸውን ለማሳየት ነው። ከታቦተ ጽዮን ጋር በተያያዘ ምንጫችን ወይም መነሻችን እስራኤል ነው፤ በሚል እስራኤል የምትባለውን ሀገር በዘር ሀረግ ውስጥ አምጥተውት ይመስላል። በሰው ልጅ የዘር አቆጣጠር ውስጥ ሀገር የመቁጠር ትውፊት የለምና በተሻለ ሁኔታ ከዘር ሀረጉ ጋር ይናበባል ያልኩትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ የብሉይ ተረክ አነሳለሁ።

> ያዕቆብ ግን ለብቻው ቀረ፤ አንድ ሰውም እስከ ንጋት ድረስ ይታገለው ነበር። እንዳሸነፈውም ባየ ጊዜ የጭኑን ሽሉዳ ያዘው፤ የያዕቆብ የጭኑ ሽሉዳ ሲታገለው ደነዘዘ። እንዲህም አለው። "ሊነጋ ጎህ ቀዷልና ልቀቀኝ።" እርሱም ካልባረከኝ አልለቅህም አለው። "ስምህ ማነው?" እርሱም፣ "ያዕቆብ ነኝ" አለው። አለውም፣ "ከእንግዲህ ወዲህ ስምህ እስራኤል ይባል እንጂ ያዕቆብ አይባል፤ ከእግዚአብሔርና ከሰው ጋር ታግለህ በርትተሃልና" (ዘፍ. 32፣24-29)።

ከላይ ከቀረበው ተረክ እንደምንረዳው እስራኤል የያዕቆብ ስም ሲሆን በእግዚአብሔር የተሰጠው አዲስ ስያሜ ነው። ስለዚህ ዛዮች የሚጠሩት እስራኤል የ12 ነገድ አባት የሆነው ያዕቆብ፣ ኋላም በአሸናፊነቱ እስራኤል የተባለው ነው ልንል እንችላለን። ከልያ ይወለዱ ከራሄል አልያም ከአገልጋዮቻቸው የሚታወቅ ነገር ባይኖርም ማለት ነው። ይሄ ግምታዊ ሀሳብ ነው። ምክንያቱም ዛዮች ከጽላተ ሙሴ ጋር በተያያዘ ከቀዳማዊ ምኒሊክ ጋር ከመጡት ፈላሻዎች የዘር ሀረግ እንዳላቸው ብናምን እንኳን በ18 ትውልድ የዘር ሀረግ ቆጠራ ቅድመ ዓለምና ከክርስቶስ ልደት በኋላ ከ2 ሺህ በላይ ዕድሜ ያለውን የዘር ግንድ ልንደርስበት አንችልም። ሆኖም ግን አንድ ማህበረሰብ ስለ ራሱ የዘር ሀረግ ሲቆጥር በሺዎች የሚቆጠሩት አያት ቅድመ አያቶቹን ሳይጠራ በቅርብ የሚታወሰውን ብቻ አንስቶ የመጨረሻውን የማንነታቸው አሻራ ያረፈበትን ስም ሊጠራ ይችላል። ከዚህ አንጻር የዛዮችን ነገድ ከእስራኤል የዘር ሀረግ የሚያይዘውን ግምታዊ ሀሳብ አንድ ደረጃ ወደ ፊት እንድንደረደር ይረዳናል። ስለዚህ ከእስራኤል ጋር በተያያዘ ተጨማሪ ማሳያ የሚሆነን ደግሞ የዛዮች የምግብ ባህል ነው። በፎክሎራዊ ጉዳይ ውስጥ ምግብ ለማንነት ጥናት ሰፊ ድርሻ አለው።

ከዛይ ማህበረሰብ የዘር ሀረግ ጋር በተያያዘ መረጃ ስሰበስብ ገለጻ ከደረጉልኝ መካከል መርጌታ ስምረ እንደሚሉት "ማህበረሰቡ የሹሉዳ ስጋ አለመብላቱ በራሱ የእስራኤል ደም እንዳለባቸው

የሚያመለክት ነው" (ቃለመጠይቅ፣ መርጌታ ስምረ ግደይ፣ በቀን 10/08/05 ዓ.ም)። በብሉዩ ሃይማኖታዊ ትውፊት ውስጥ የሚበላውና የማይበላው ነገር ተለይቶ ተቀምጧል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ለዛይ ህዝብ የጓሮ ጎመን ስለ ሆነው ዓሣ ማንሳት ይቻላል። ዘሌ.11፣9 "በባህሮችም በወንዞችም ውስጥ ከሚኖሩት ሁሉ ክንፍና ቅርፊት ያላቸውን ትበላላችሁ።---በባህሮችና በወንዞች ውስጥ ክንፍና ቅርፊት የሌላቸው ሁሉ በእናንተ ዘንድ የተጸየፉ ናቸው።" በሚለው ህግ መሰረት በዝዋይ ሐይቅ ውስጥ ቆሮሶ፣ አንባዛ፣ ባርቦ፣ ጃፔ፣ ዱቤና ሚንጪ የሚባሉ የዓሣ ዝርያዎች አሉ። በገበያ ላይ በጣም በሰፊው ተፈላጊነት ያለውና በውድ ዋጋ የሚሸጠው ዓሣ አንባዛ የተባለው ዝርያ ነው። የዛይ ማህበረሰብ ይሄንን የዓሣ ዝርያ ግልፋፊ ስለሌለው ለሽያጭ ያውለዋል እንጂ አይመገበውም። ዋናው ጉዳይ ግን የዛዮች የወርች ስጋ አለመብላት ነው። በሃይማኖታቸው ተከልክሎ ነው እንዳይባል በኦርቶዶክስ ሃይማኖታዊ ዶግማ መሰረት የወርች ስጋ አልተከለከለም ታዲያ ለምን አይበሉም? ከተባለ ቀደም ብዬ ወዳነሳሁት የዘር ሀረግ የሚመልሰን ይሆናል። የያዕቆብ ልጅነቻውን የሚያጠነክርልን ጉዳይ ነው። ምክንያቱም በዘፍጥረት 32፣32"---የእስራኤል ልጆች እስከ ዛሬ ድረስ የወርችን ሹሉዳ አይበሉም፤ የያዕቆብን ጭን ይዞ የወርቹን ሹሉዳ አድንዝዟልና።" የሚለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል የሚያስገነዝበን ነገር ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ባህል መኖሩን ነው። በሃይማኖት ተቋማቸው ውስጥ የተፈቀደውን እስከ ዛሬ ድረስ አለመብላታቸው የመጽሐፍ ቅዱሱ ተረክ እንደሚለው እስከ ዛሬ የወርች ሽሉዳ የማይበሉት የእስራኤል ልጆች ናቸውና ዛዮችም የእስራኤል ልጆች ሆነው ይሆን? የሚስብል ነው።

የምግብን ባህል ለማንሳት የፈለኩት በዛዮች መዝሙር ሴቶቹ ላይ የሚታየው ነገር እስራኤላዊ ትውፊት እንዳላቸው የሚያሳይ ነው ብዬ ላነሳሁት ጉዳይ ያመጣሁት ማዳበሪያ ሀሳብ ነው። ሀሳቡ ሰፋ ያለ የማንነት ጥናት ውስጥ የሚከተን ቢሆንም ለአሁኑ በዚሁ ልዝለለውና ቀደም ብዬ ወደ አነሳሁት የዛዮች መዝሙር እመለሳለሁ። መዝሙሩ በርካታ ይዘት ሊመዘዝለት የሚችል የስፍራውም ሆነ የሕዝቦቹ ታሪካዊነትና ጥንታዊነት ማሳያ ነው። በውኃ ተከልለው በገዳምና አድባራት እንደ መኖራቸው ገዳማውያን፣ እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታይነታቸው ኦርቶዶክሳውያን፣ ታቦተ ጽዮንን ይዘው ከትግራይ እንደ መሰደዳቸው አክሱማውያን የሚያስብላቸውን ጉዳይ ለአምላካቸው ከሚያቀርቡት የምስጋና መዝሙር መምዘዝ እንችላለን።

መስክ የነበርኩበት የጾም ጊዜ ስለ ነበረ የዛይ እናቶች በቤተክርስቲያንና በማህበር ቤት የሚዘምሩትን የማየት እድሉ ገጥሞኛል። ከመዝሙሮቻቸው መካከል በጾመ ማርያም የሚዘምሩት "ያፈታሾት ማይራሜ"ና በሰርግ ወቅት የሚያቀርቡት "ዘወይራ" የተባለው ባህላዊ ጭፈራቸው የሚታወቅ ነው። መዝሙራቸው እስከ 12 የሚደርስ አይነት ያለው ነው። ግጥሞቹ በይዘታቸው ነገረ ሃይማኖትንና አምልኮተ እግዚአብሔርን የሚያስረዱ፣ በራሳቸው ተደርሰው በዜማ በቅብብሎሽ የሚቀርቡ ናቸው። በሰንበተ ክርስቲያን፣ በበዓላት፣ በጾመ ማርያም፣ አብይ ጾም፣ በአዲስ ዘመን መግቢያ፣ ዝናብ በጠፋበት፣ ጎተራ በተሟጠጠበትና ማጀት ባፈረበት ዘመን የሚዘምሩት ነው። የአጀማመር ስርዓቱ፣ የአጨራረስ ሂደቱ፣ የዜማ ስልቱ ከቤተክርስቲያኑ መዝሙር የቀዳው ነገር አለው። ለምሳሌ ሴቶቹ ብቻ በጾም ወቅት የሚያመሰግኑትን ስናይ በየሳምንቱ እሁድ ቤተክርስቲያን እያደሩ ለሊት ላይ ጀምረው እስከ ንጋት የሚያቀርቡት የመዝሙር ስርዓት አላቸው። መዝሙሮቹ መንፈሳዊ ይዘት ያላቸው ናቸው።

በምዕራፍ ሁለት እንዳነሳሁት ተረክ በዝርው ወይም በግጥም ታሪክን የማቅረቢያ መንገድ ነው። ስለዚህ ከመዝሙር ግጥሞቹ የተወሰኑ መስመሮችን እየቀነጨብኩ ለማስረዳት እሞክራለሁ። የዛዮች ዝማሬ በኦርቶዶክስ የአምልኮ ምስጋና ውስጥ ከሚስተዋለው ጋር በሚዛመድ መልኩ መጀመሪያ የእግዚአብሔርን ስም በመጥራት ይጀምርና ከዚያ የድንግል ማርያምን፣ የመላዕክቱን የቅዱሳኑን፣ የታቦታቱን፣ የበዓላቱን ስም በመጥራት የሚቀርብ ነው።

ማረኝ ማረኝ እግዜሮ ማረኝ

ቲት ምረኞ ያመን ጋር ሳኔኞ

ከላይ ባለው ስንኝ እንደምንመለከተው በማንኛውም የማህበረሰቡ ምስጋና ውስጥ በቀዳሚነት የሚነሳው የምስጋናው እፍታ እግዚአብሔር ሆይ ማረኝ፣ ስትምረኝ ደግሞ ያመነ ቤት አድርገኝ የሚለው ነው። የዜማው ስልትና የምስጋናው ስንኝም ሲቀየር የማይለወጠው የተመስጋኞቹ እግዚአብሔርን፣ ከዚያም ድንግል ማርያምን፣ መላዕክቱን እያለ የሚሄደው የስልጣን ተዋረድ ነው። ይሄንንም አመንሆ ሰገድሆ፣ አብሩ መብራቶና ስባተሄ እግዜሮ ስባተሄ በሚሉት የመዝሙር ክፍላቸው ውስጥ መመልከት እንችላለን። የመዝሙሩን ሰፊ ክፍል የያዘው በጥናቱ ዋቢ ክፍል በተረክ አራት ላይ የሚገኝ ሲሆን ከሶስቱም አይነቶች የተቀነጫጨቡ ለምሳሌ የሚሆኑ ስንኞች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

| | |
|---|---|
| እግዜሮ አቦዮ አመንሆ ሰገድሆ | እግዜር ሆይ አመንሁ ሰገድሁልህ |
| ጎይታዬ ወልዲሽ „ „ | ከአለቃው ልጅሽ „ „ |
| ሙኮዮ አቦዮ „ „ | ሚካኤል አባታችን „ „ |
| ገብረመንፈስ አቦዮ „ „ | ገብረ መንፈስ ቅዱስ አባቴ „ „ |
| በላልቻይ ሰንበቻይ „ „ | በዓላትና ሰንበታት „ „ |

"አመንሆ ሰገድሆ" በሚለው የመዝሙር ክፍል ላይ እንደምንመለከተው ፈጣሪ እግዚአብሔር ሆይ አመንኩልህ ሰገድኩልህ በሚል ይጀምርና አለቃችንን የወልድሽ በሚል ደግሞ ድንግል ማርያምን ያስከትላል፡፡ ከዚያም ሙኮዮ፣ ገብርኤሎ፣ ጊዮርጊሶ፣ ገብረ መንፈስ (ሚካኤል፣ ገብርኤል፣ ጊዮርጊስ፣ ገብረመንፈስ ቅዱስ) እያለ መላዕክቱን፣ ጻድቃን ሰማዕታትን ያነሳና፣ በላልቻይ፣ ሰንበቻይ በሚል በዓላትንና ሰንበታትን ወደ ማመስገኑ ይመጣል፡፡

"አብሩ መብራቶ" (መብራታችሁን አብሩ)፣ "ያቦ እግዜሮ ስለቶ ያወልቢ መብራቶ" (እሱ እግዜር ባለበት ቦታ ብርሃን ይሁን) በሚለው የመዝሙር ክፍል ውስጥም የምንመለከተው ከላይ ባየነው ሂደት የሚቀጥል ነው፡፡ ይህ በጧፍ ብርሃን የሚታጀበው የመዝሙር ምስጋና የአብርሃም የስለት ልጅነታቸውን፣ ቀደምትነትታቸውን፣ ገዳማዊነታቸውን፣ የአውስጣጢዖስ በዓል አክባሪነታቸውን ሁሉ የሚያነሳ ነው፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| አብሩ መብራቶ አህ | | ያቦ እግዜሮ ስለቶ | | ያወልቢ መብራቶ |
| „ | „ | „ | የዛኛትን እምነቶ (የጥንት እምነት ነውና) | „ „ |
| „ | „ | „ | የቦስታቶስ (ስለ አውስጣጢዮስ ታቦት -ታቦተ ኢየሱስ) | „ „ |
| „ | „ | „ | የአብርሃምን ስለቶ (የአብርሃም ስለት) | „ „ |

"የዛኛትን፣ የባይራትን እምነቶ" በሚል የእምነቱን ቀደምትነት የሚገለጸው ምስጋና ለአስራት አባታቸው አብርሃም፣ ከትግራይ ለመምጣታቸው መገለጫ ለሆነው ለባስታቶስ በዓላቸው ሁሉ የሚቀርብ ውዳሴ እንደ ሆነ እንመለከታለን፡፡ ይህ እንጉዳይ አንድም የእምነታቸውን ትውፊት የሚያሳይ፣ ታሪካቸውን የሚዘክርና የስፍራውን ቀደምትነትና ቅድስና የሚሰብክ ነው፡፡ የስፍራውን መቀደስ ብቻ ሳይሆን በውስጡ ያሉትን ለምስጋና የተለዩ የቅድስናው አንባ ህዝቦች መሆናቸውንም የሚያስረዳ ነው፡፡ ምክንያትም በክርስትናው ትውፊት ውስጥ ጥንት ምላል

በመባል በዕለተ ሰንበትና በጾም ወቅት ይቀርብ የነበረ ዝማሬ በሌሎች ማህበረሰቦችም የነበረ ነው። አሁን ግን በካሴት መዝሙሮች ተውጦ፣ ትውፊቱን የሚያንፀባርቅ ያለ አይመስልም። በዛይ ግን ኦርቶዶክሳዊ ትውፊቱ እንዳለ ሆኖ ወደ ኋላ ሄዶ የእስራኤላውያንን ዝማሬ የሚያስታውስ ስለ ሆነ ዝማሪያቸው የታሪካዊነታቸውና የጥንታዊነታቸው መገለጫ ነው።

የደስያቱ ማህበረሰቦች በገዳምና አድባራታቸው ገዳማዊያን ናቸው የሚያስብላቸው ሌላው ምክንያት መዘሙራቸው በቤተክርስቲያናቸው ዙሪያ በሚቀርቡ አምልኳዊ ስርዓቶች ውስጥ ብቻ የሚንጸባረቅ ሳይሆን በሌሎች ባህላዊ ጉዳዮችም ላይ የሚስተዋል መሆኑ ነው። ለዚህ ማሳየ የሚሆነን በሰርግ ላይ የሚቀርበው "እግዜር ቤዛኔ" ባህላዊ ጭፈራቸው ነው።

እግዜር ቤይዛኔ አሃደነን በዛዬ - (መድህን እግዚአብሔር በዛይ አስቀመጠን)

ወረዶ ሰናዬ ለሰማየ የአዝማራ ቀናዬ - (ከሰማይ ዝናብን አውርዶ አዝመራውም ቀናልን)

ከላይ የቀረበው የዘፈኑ ግጥም የመጀመሪያ ስንኝ የሚያሳየን በማንኛውም ስርዓት ላይ እግዚአብሔርን በማመስገን የሚጀምሩ መሆናቸውን ነው። የግጥሙ ይዘት ከሰርግ ውዳሴ ጋር በቀጥታ የሚገናኝ ነገር የለውም። አምላካቸው ምድሩን ባርኮ፣ የሰማይ መስኮቶችን ከፍቶ አዝመራን ባይሰጣቸው ለሰርግ ሊበቁ አይችሉም ካልተባለ በስተቀር፤ ሆኖም ግን በዘፈኑ እየጨፈሩ እየተደሰቱም በውስጣቸው ያለው ጸሎት፣ ምስጋናና ቡራኬ እንደሆነ እንረዳለን። ይሄ ደግሞ በገዳማዊያን ስርዓት ባይኖሩም መኖሪያቸው ገዳምና አድባራቱ በመሆናቸው ገዳማውያን ሆነው ይሆን ያስብላል።

የምስጋናው ጸሎት ለራሳቸው ብቻ በመጸለይ የሚቆም አይደለም። በገዳማውያን ተረክ ውስጥ እንደምናውቀው ተጋዳሊያኑ የሚጸልዩት ሌሎችን ያማከለ እንደ ሆነ ሁሉ የዛይ ባህል ምስጋና ምርቃትም ሀገራችን ኢትዮጵያን፣ ጎረቤቶቻቸውን ኦሮሞዎችን፣ ደስያቱን እንዲጠብቅ፣ መንግስትን በዙፋኑ እንዲያኖር፣ ዘመኑን የሰላም እንዲያደርግ የሚያስረግጥ ነው። በተረክ አምስት የቀረበው የዛይ ማህበረሰብ ምርቃት የዚህ መገለጫ ይሆናል።

ኢትዮጵያ ነገየ የሳነን - ኢትዮጵያን ሰላም ያድርግልን

ንጉሴኛይ በአልጋኒያቴን ድርነን- መንግስታችንን በዙፋኑ ያኑርልን

ኦሮሞን በደንበላቴን ድርነን- ከኦሮሞዎቹ ጋር ሰላም ያድርገን

ደሲቴኛይ ነገያ የሳነን- ደሴቶቻችንን የሰላም ያድርግልን

በሃይማኖት ይመጣል ያውለን- በሃይማኖት የሚመጣብንን ያርቅልን

ቡራኪ ስሙር የሳነን - ቡራኬውን ያስምርልን

በምርቃቱ ስንኞች የሰፈረው ነገር እንደሚያመለክተን ከኢትዮጵያ ሀገራችን ጀምሮ፣ ንጉሥን፣ ጎረቤት የሆኑትን አሮሞዎችን፣ ደሴቶቻቸውን እንዲባርክ በተዋረድ የሚጠይቁ ናቸው። ከዚህ በፊት ወደ ስፍራው የመጡት በሃይማኖት ምክንያት በተፈጠረ ጦርነት ነውና የዚያ ስጋት ነጸብራቅ የሆነ "በሃይማኖታችን የሚመጣብንን ያርቅልን" የሚል ተማጽኖም አለበት። የዚህ ምርቃት አጀማመርም፣ አጨራረስም ሆነ በውስጡ የሚነሳው ይዘት ከኦርቶዶክሳዊ ትውፊት ጋር የሚስምር ሆኖ እናገኘዋለን። በኦርቶዶክስ እምነት በቅዳሴው ስርዓት፣ በሰዓታቱና ማህሌቱ ስለ ኢትዮጵያ ሀገር ሰላምና መንግስትን በመንበሩ እንዲያኖር የሚጸለይበት ክፍሎች አሉት። የዛይ ማህበረሰብ ባህል የዚህ ገጽታ ነጸብራቅ ናቸው። የዛይ እናቶች የአንዱን የመዝሙር ዘር ሲጨርሱ በለሆሳስ በየግል የሚደግሙት ጸሎት አላቸው። የጸሎት ማሳረጊያ ሆኖ ከእያንዳንዱ ምስጋና በኋላ አቡነ ዘበሰማያቱ እንደሚታደለው ማለት ነው። በዚህ ሂደት ሀገራቸው ኢትዮጵያን፣ ቤተክርስቲያናቸውን፣ ልጆቻቸውን፣ ቤተሰቦቻቸውን እንዲጠብቅና ጸሎታቸውን እንዲሰማ የሚያቀርቡት ምላል ነው። የመዝሙሩ አዝማች አልቆ ወደ ሌላ አንጓ ሲቀየር ዜማውም አብሮ ይቀየራል። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ትውፊት መሰረት በአቢይ ጾም ከበሮው፣ ጽናጽሉ አገልግሎት አይሰጥም። በዚህ ወቅት የዛይ እናቶች የሚያቀርቡት መዝሙርም እጃቸውን በማመሳቀል፣ በባህላዊ መንገድ የሚያዘጋጁትን ከበሮ ሳይጠቀሙ፣ እጅ ማጨብጨብ ሳይኖር በተሰበረ መንፈስ ነው። የምስጋናው ሁሉ ማሳረጊያ ሆኖ በተለይ ደግሞ ከምግብ በኋላ የሚቀርበው "ስብሃት ለአብ፣ ስብሃት ለወልድ፣ ስብሃት ለመንፈስ ቅዱስ--- ለዘአብልዓነ ዘንተ ህብስተ፣ ወለዘአስተየነ ዘንተ ጽዋዓ እስመ ለዓለም ምህረቱ" (ምስጋና ለአብ፣ ለወልድ፣ ለመንፈስ ቅዱስ ይገባል፤ ይህንን ህብስት ላበላን፣ ይህንንም ጽዋ ላጠጣን ምህረቱ ለዘለዓለም ነውና) የሚለው እንዳለ ሁሉ በዛይ ማህበረሰብ የመዝሙራቸውም ሆነ የምስጋናቸው የመጨረሻ መዝጊያ "ስባተሄ እግዜሮ ስባተሄ ዋበን ደረጉተሄ" የሚለው ነው። ይህም ምስጋና ለአምላክ ይገባል የዕለት ጉርሳችንን ለሰጠን የሚል ነው። ከእነዚህ ዝርዝር ጉዳዮች የምንገነዘበው የትውፊቱን መወራረስ ነው። ከላይ የቀረቡትን ስርዓቶች ጠብቀው መቆየታቸው የታሪካዊነትና ጥንታዊነታቸው መሳያ ነው።

ከዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራት መመስረት ጋር በተያያዘ የተገኙት ተረኮች የገዳምና አድባራቱን ታሪካዊነትና ጥንታዊነት የሚዘክሩት ከላይ በቀረቡት ጉዳዮች ብቻ አይደለም። ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት መመስረት ምክንያት መሆናቸውን በመስበክ ጭምር የቀደምትነት መገለጫቸውን ያጸናሉ። በአባሪ ክፍሉ የቀረበውን ተረክ ሶስትን ለዋቢነት ብንመለከት ከታቦታቱ ጋር በተገናኘ የሚነገሩት ተረኮች የሚያሳዩን ነገር የዝዋይ ደስያት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ስር ላሉ በርካታ አብያተ ክርስቲያናት ማዕከል መሆናቸውን የሚያሳይ ነው።

> በዮዲት ወረራና በግራኝ የጥፋት ዘመቻ ዘመን በርካታ ታቦቶች ወደ ደስያቱ ገብተዋል። ታዲያ ዛሬ በዚህ በአዋሳ መስመር፣ አርሲና አዲስ አበባ ከተማ ላይ የተተከሉት በርካታ አብያተ ክርስቲያን ምንጫቸው የዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራት ናቸው። ለምሳሌ ያህል አባ ኢሳያስ ከዚህ እያወጡ የተከሏቸው የመቂ ሚካኤልና ጊዮርጊስ፣ ሻሸመኔ ማርያም፣ ድሬዳዋ ሚካኤል፣ አሰላ መድኃኒዓለም የሚገኙ ቤተክርስቲያኖች ይጠቀሳሉ። አዲስ አባባ ላይ ምስካየ ህዙናን መድኃኒዓለምን እንዲሁም በቅዱስ ማርቆስ አማካይነት እንደ ተሳለ የሚነገርለት የቁልቢ ገብርኤል በአንድ ባህታዊ አማካይነት ከዝዋይ ደሴት ተወስዶ በአሁን በሚገኝበት ስፍራ ተደብቆ ቆይቶ እንደ ተተከለ ይነገራል (መምሬ ገብረ መስቀል ሂርጳ፣ በቀን 02/08/05 ዓ.ም)።

ቃላዊ ተረኮቹ እንደሚነግሩን ከሆነ የደስያቱ ገዳምና አድባራት ለሀገሪቱ አብያተክርስቲያናት ማዕከል መሆናቸውን ነው። የደብረ ጽዮን ገዳም አስተዳዳሪ የሆኑት አባ ገብረ እግዚአብሔር በተረኩ የተነሳውን ጉዳይ ሲያጠናክሩ "ምን ልበልህ አዲስ አበባ ላይ እንኳን ከተተከሉት ከ20 በላይ የሚሆኑት አብያተ ክርስቲያናት የተመሰረቱት ከነዚሁ ደስያት በወጡ ጽላቶች ነው" ይላሉ። (ቃለመጠይቅ፣ አባ ገብረ እግዚአብሔር አለሙ፣ በቀን 30/07/05 ዓ.ም)። ይሄንን የገዳምና አድባራቱን ለሌሎች መሰረት መሆንና ዛሬም ድረስ በሌሎች ቦታ የሚያገኙ በርካታ ጽላቶች የሚገኙባቸው ደስያት መሆኑን ደግሞ የገሊላ ካህናተ ሰማይና የደብረ ሲና አስተዳዳሪ የሆኑት ቀሲስ ተስፋዬ ነቢ ሲገልጹ "ዛሬም ድረስ በእያንዳንዱ ደሴት በርካታ ጽላቶች ይገኛሉ። በተለይ በሌሎች ቦታ ስማቸው ሲጠራ ብዙም የማንሰማቸው መገኘታቸው ልዩ ያደርጋቸዋል። ለምሳሌ፣ የገላውዲዮስ፣ የቅዱስ ሴባስቲያንና 72ቱ አርድዕት ጽላቶች መጥቀስ ይቻላል" በማለት ነው (ቃለመጠይቅ፣ ቀሲስ ተስፋዬ ነቢ፣ በቀን 09/08/05 ዓ.ም)። ይሄ የሚያሳየን አንድም ማዕከለ ቅርስ መሆናቸውን አንድም ደግሞ ለሌሎች አብያተ ክርስቲያናት መመስረት ምክንያት መሆን መቻላቸውን ነው። ከዚህ ባሻገር ያለው ደግሞ ታሪካዊነታቸውንና ቀደምትነታቸውን የሚነግረን ነው። ይሄንን ሁሉ የሚሉን የደስያቱ ተረኮች ናቸው። ቀደምት ናቸው፤ ታሪካዊ ናቸው ስልም በተረኩ ሪጋ ቆሜ ነው።

በመጨረሻ ለዚህ ንዑስ ርዕስ ማጠናከሪያ አድርጌ የማነሳው ከዓለማዊ ታሪክ የተዛነቁትን ተረኮች ነው፡፡ የእነዚህ ተረኮች ተግባር ከላይ እንዳነሳሁት ሁሉ የቦታውን ታሪካዊነትና ጥንታዊነትን የሚያጠንክሩ ናቸው፡፡ ምክንያቱም አንደኛው የዛግዌ መንግስት በሀገሪቱ የስልጣን ኮርቻ ላይ ተቀምጦ በነበረበት ወቅት የሰሎሞናዊ ስረወ መንግሰት ለ300 ዓመታት በዝዋይ ሐይቅ ደስያት ሲነግስ መቆየቱን የሚያሳይ ነው፡፡ ተረኩ እንደሚለው የሰሎሞን ስርወ መንግስት ሲመለስ ምክንያት የሆነው በዚሁ በዝዋይ ሐይቅ የተወለደው ይኩኖ-አምላክ ነው፡፡ ጻዲቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ታቦተ ጽዮን ጠባቂ እንዳታጣ የሰሎሞን ስርወ መንግስት እንዲመለስ ፍላጎት ነበራቸው፡፡ ሆኖም ግን የሰሎሞን መንግስት የት እንደ ገባ አያውቁም ነበር፡፡ በዚህ ጉዳይ ሲጨነቁ፣ ይኩኖ አምላክ ለትምህርት ከዝዋይ አቡነ ኢየሱስ ሞዓ ገዳም ሲመጣ አግኝተውት የሰሎሞን ስርወ መንግስት የነበረው አክሱማዊ መሆኑን ሲነግራቸው አነገሡት፡፡ ስለዚህ ለክፉ ቀን መሸሸጊያ የሆነቻቸው የዝዋይ ሐይቅ አሳድጋ፤ ዲቁና አስተምራ፣ ይኩኖ አምላክ እንዲነግሥ ስለ ሆነ የሰሎሞን ስረወ መንግስት መላሽ ናት፤ ተረክ ሶስት እንደሚነግረን ከሆነ፡፡ ስለዚህ በታሪክ አንጻር ታሪካዊት፣ የሰሎሞን ስረወ መንግስት እንዲመለስ ምክንያት የሆነች ቀዳማዊት ናት ማለት ነው፡፡ ተረኮቹ ቀደምትነትን በመንገር ጥንታዊነትን የሚተርኩና ታሪካዊነትን የሚሰብኩ ናቸው፤ የተባለውም ከዚህ የተነሳ ነው፡፡

የአፍሪካ መዲናና የሀገራችን ኢትዮጵያ ዋና ከተማ የሆነችው አዲስ አበባ ለመመስረቷም የዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራት የታሪክ ተካፋይ ናቸው፡፡

> አጼ ምኒሊክ አዲስ አበባን ለመቆርቆራቸው ከደስያቱ ገዳምና አድባራት ጋር ተያይዞ የሚነገር ታሪክም አለ፡፡ የዛሬዋ የሀገራችን ኢትዮጵያን ዋና ከተማ አዲስ አበባን ለመመስረትና እንጦጦ ላይ መሰረት ለመጣል የቻሉት በዚህ በዝዋይ ማይ ከተገኘ የትንቢት መጽሐፍ ላይ ተመስርተው ነው ይባላል፡፡ መጽሐፉን ከደስያቱ ያወጣው አንድ መነኩሴ ሀሳቡን አንብቦ ከዚያ ለንጉሱ ወስዶ እንደሰጣቸው ይነገራል፡፡ የእንጦጦ ማርያምና የመልአኩ ራጉኤል ቤተክርስቲያንም የተሰራው በዚሁ መልአኩ ራጉኤል ለአጼ ልብነ ድንግል የነገረው ራእይ ከሰፈረበት ትንሽ የክብረ ነገስት መጽሐፍ ከተገኘው ትንቢት ነው አሉ (መምሬ ገብረ መስቀል ሂርጳ በቀን 2/08/05 ዓ.ም)፡፡

በዝዋይ ደስያት የሰበሰብኳቸው ተረኮች የደስያቱን ገዳምና አድባራት ጥንታዊነትንና ታሪካዊነት የመተረክ ተግባር አላቸው ያልኩት ከላይ ከቀረቡት ተረኮች የተነሳ ነው፡፡ የትረካዎቹ የአተራረክ ስልት ቀድሞ በታሪክ የሚታወቀውን በአዲስና በሌላ ስልት መተረክ፣ የታሪክ ክፍተት ያላቸው የሚመስሉትን በቃል ተረክ ለመሙላት የመሞከር ባህሪ ይታይባቸዋል፡፡ ይሄንን የምንገነዘበው

በንድፊ ሀሳባዊ ዳራዬ እንዳነሳሁት በአራቱ አውዶች ቅንጅት ነው። ባህላዊ አውድን ለመረዳት የሚያስችለን ከማህበረሰቡ እምነትና ስርዓት የተቀዱ ተረኮች ስለ ሆኑ በዚያ መስታወት ውስጥ ስናያቸው ነው። ማህበረሰቡ በጾታ፣ በእድሜና በሙያ የተስማማበት መሆኑንና በግለሰብ ደረጃ ራሳቸውን ከዚያ ታሪክ ተካፋይ አድርገው፣ በተረኩ ውስጥ ራሳቸውን አሳትፈው ስለሚተርኩ ከዚያ የተገኘ ነው። ትርጉም ለመስጠት የበለጠ ያገዘው ደግሞ ንጽጽራዊ አውድ ነው፤ ከሌሎች ተረኮች ጋር ስናደበልቀው የሚፈጠረው የድርጊትና ሁነት ቅንጅት ትርጉሙን ለመፈክር አገልግሏል።

### 4.1.2. የዝዋይ ሐይቅን ገዳምና አድባራት ቅድስና የሚሰብኩ ተረኮች

ከዝዋይ ደሴያት ገዳምና አድባራት መመስረት ጋር በተያያዘ የተገኙትን ተረኮች ስንፈትሽ በዋናነት ከሚነሱት ተግባሮች መካከል ቀዳሚውን ስፍራ ይዞ የምናገኘው የስፍራውን መቀደስና በውስጡ የሚገኙትን ነዋሪዎች መባረክ የሚሰበከው ነው። ምናልባት ቅድስና ራሱ ምንድን ነው? የሚል ጥያቄ በመጀመሪያነት ሊሰነዘር ይችል ይሆናል። አለቃ ኪዳነወልድ ክፍሌ እንደሚተረጉሙት ቅዱስ በቁሙ የተቀደሰ፣ ክቡር፣ ልዩ፣ ምስጉን፣ ንጹህ፣ ምርጥ ማለት ነው። ቅድስና ሲሆን ደግሞ ቅዱስነት፣ ክቡርነት፣ ንጽህና፣ ከበሬታ የሚለውን የሚያመለክት ነው (ኪዳነ ወልድ፣ 784)። ስለዚህ ቅድስናን ለዝዋይ ደሴያት ተረኮች ስንወስድ የገዳምና አድባራቱን ለእግዚአብሔር አገልግሎት መለየት፣ መመረጥና የከበሩ ተራራዎች መባልን እንዲያተርፉ ያስችላቸዋል። የደሴያቱን ማህበረሰቦች የተቀደሱ ሕዝቦች መሰኘትንም ጭምር።

ለአንድ ስፍራ መቀደስ ምክንያት የሚሆነው ነገር በሃይማኖት ውስጥ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው የልዕለ ተፈጥሮ በረከት አደረበት ተብሎ ሲታመን ነው። ይኸውም መላዕክት የባረኩት፣ ቅዱሳን የተወለዱበት፣ የጸለዩበትና ያረፉበት፣ ድንቅ የሆኑ ተዓምራት የተፈጸሙበት፣ ሰማዕታት ዋጋ የከፈሉበት፣ እግዚአብሔር ቃልኪዳን የገባለት ተብሎ የሚታመን ሲሆን ነው። አንድ ስፍራ የተቀደሰ ነው ሲባል አሁን የተጠቀሱትን አይነት ፀጋ አግኝቷል ማለት ነው። ከዚህም የተነሳ የሃይማኖቱ ተከታይ የሃይማኖቱን ዶግማ ለመፈጸም፣ ነፍስን ለማስደሰትና የስጋ በረከትን ለመቀበል በሚል ወደ ስፍራው ይጓዛል። ይሄንን በመዘከር ረገድ ከፍተኛውን ሚና የሚጫወቱት ደግሞ ስለ ስፍራው የሚተረኩት ተረኮች ናቸው። ተረኮች በተለያዩ የመባያ ጉዳዮች የስፍራውን ቅድስና ሊሰብኩ ይችላሉ። ስያሜ፣ ተአምራት፣ የልዕለ ተፈጥሮ ረድኤት፣ የቅዱሳን መኖሪያ

ወዘተ. የመሳሰሉትን በዝዋይ ደስያት ተረኮች ውስጥ ልናገኝ እንችላለን። በዚህ ክፍል ለቅድስና መገለጫ ከሆኑት መካከል የተወሰኑትን እንደሚከተለው አነሳለሁ። ከሥያሜ ጋር የተያያዙት ጉዳዮች ቀዳሚዎቹ ናቸው።

### 4.1.2.1. የስፍራው ሥያሜዎች የፈለቁባቸው ተረኮች

በንድፈ ሀሳባዊ ዳራ እንዳቀረብኩት ተረኮችን ከምንረዳበት አውዶች መካከል አንዱ ንጽጽራዊ አውድ ነው። ከስያሜ ጋር ተያይዘው ሰፋፊ ተረኮች ባይኖሩም የደስያቱን፣ የገዳምና አድባራቱን እንዲሁም የማህበረሰቡን ስያሜ ስንመለከት በሌላ ስፍራ የሚታወቅን ወይም ዓለም አቀፋዊ የሆነ ተረክን የሚጠሩ ናቸው። የቅድስና አደባባዮች ናቸው ተብለው የሚጠሩት የተለያዩ ስፍራዎች የተቀደሱ መሆናቸውን ከሚገልጡባቸው መንገዶች አንዱ ስያሜ ነው። ስያሜ የአንድ ነገር ምንነት የሚገለጽበት ስለ ሆነ ማንነትንም የመሸከም አቅም አለው። የዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራትም ይሄ ሁኔታ ይታይባቸዋል። ከስያሚያቸው ተነስተን ታሪኩን ስንፈትሽ ሌላ የቀደመ ታሪክ፣ በሌላ ስፍራ የተከናወነን ድርጊት የሚጠሩልን ሆነው እናገኛቸዋለን። ይህ ደግሞ የዚያን የከበረ ታሪክ ተቋዳሽ እንዲሆኑ ለማድረግ የተሰጡ ያስመስላቸዋል። ከዚህ የምንረዳው የአንድ ነገር መጠሪያ በተለይም በሃይማኖታዊ ፎክሎር ውስጥ ትልቅ ቦታ እንዳለው ነው። ለዚህም ነው ቴዎድሮስ ገብሬ በበይነ-ዲሲፕሊናዊ የሥነ ጽሑፍ ንባባቸው "ልዕለ ተፈጥሮ ህላዌ በሚገነባቸው ሃይማኖታዊ ተረኮች ውስጥ የሚከወን ስያሜ በአመዛኙ፣ የህላዌው እውቀትና ፍላጎት ማደሪያ፣ የኃይልና ስልጣኑም መከሰቻ ከመሆን አይዘልም ብሎ ማሰብም ይቻላል፤" (ቴዎድሮስ፣106) የሚሉት።

ስም የቀደመ ግብርን ለመግለጽና አዲስ ማንነትንም ለማምጣት የሚያገለግል ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የብሉይም ሆነ የሀዲስ ኪዳን ተረኮች ውስጥ ይሄንን ጉዳይ እናገኛለን። ከብሉይ የአብርሃምን ታሪክ ማንሳት እንችላለን። እግዚአብሔር አብራምን አለው፤ "ከሀገርህ፣ ከዘመዶችህም፣ እኔ ወደ ማሳይህም ምድር ሂድ። ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ፤ እባርካለሁ፣ <u>ስምህንም ከፍ ከፍ አደርጋለሁ፤"</u> (ዘፍ.12፣1-2) (አጽንኦት የራሴ)። አብርሃም በ70 ዓመቱ ከምድረ ካራን ወደ ከነዓን ሲወጣ የተሰጠው ቃል ኪዳን የሌሎች አባት እንደሚሆን ነው። ይሄ ደግሞ በስሙ እንደሚገለጥ ነው፤ ስሙን በማግነን የሚመጣ ለውጥ ነው። የ90 ዓመት የዕድሜ ባለጸጋ ሲሆን የተፈጸመለት ነገርም ይኸው ነው። እንሆ ቃል ኪዳኔን በአንተ መካከል

አጸናለሁ፤ ለብዙ አህዝብም አባት ትሆናለህ። እንግዲህ ስምህ አብራም አይባልም 'አብርሃም' ይባላል እንጂ፤ ለብዙ አህዛብ አባት አድርጌሃለሁና" (ዘፍ.17፣4-5) (አጽንኦት የራሴ)። ከጥቅሱ እንደምንረዳው ለአብርሃም የተገባለት ቃል ኪዳን ሲደርስና የብዙሃን አባት እንደሚሆን ሲገለጽለት በስም ለውጥ ነው። ስለዚህ ስም ከመጠሪያነት ባሻገር ግብርንም ሊገልጽ እንደሚችልና የሰብዕና ለውጥ መገለጫም እንደሆነ እንረዳለን።

በሀዲስ ኪዳንም ይሄ የስምን ሌላ ጽንሰ ሀሳብ እንዲሸከም ማድረግ ነገር ቀጥሎ እናገኘዋለን። ለዚህም ኢየሱስ ክርስቶስ የራሱን ደቀመዛሙርት ሲመለምል ስማቸውን ጭምር እየቀየረ ነበር። ዓሣ አጥማጁ ስምኦን በኢየሱስ ተጠርቶ ግብሩ ወደ ሰው ማጥመድ ሲቀየር ቅዱስ ጴጥሮስ የሚል መጠሪያ ተጨምሮለታል (ሉቃ.5፣10)። አሳዳጅ የነበረው ሳኦል ተሳዳጅ ሲሆን ቅዱስ ጳውሎስ ተብሏል (የሐዋ.9፣1)። በአጠቃላይ ስያሜ ከመጠሪያነት ያለፈ ተግባር እንዳለው እንገነዘባለን። በዝዋይ ሐይቅ ደሴቶች ውስጥ የተሰጡ ስሞችም ስም ለመስጠት ብቻ የተሰጡ ሳይሆኑ ሌላ ተረክ እየጠሩ ተደራቢ ተግባር እንዲኖራቸው የተደረጉ ይመስላሉ።

የደሴቶቹን ስያሜዎች ብቻ በማንሳት ይሄንን ጉዳይ ማስረዳት ይቻላል። ገሊላ ካህናተ ሰማይ፣ ጌቴሴማኒ አርባእቱ እንሳሳ፣ ደብረ ሲና ማርያም፣ ደብረ ጽዮን ማርያምና ደብረ አብርሃም በዝዋይ ሐይቅ ለደሴቶቹና ለገዳምና አድባራቱ የተሰጡ መጠሪያዎች ናቸው። ከገሊላ ካህናተ ሰማይ ብናነሳ ሁለት ስሞች በአንድ ላይ ተጣምረው የፈጠሩት ስም ነው። ሁለቱም የተለያየ ሀሳብ ይዘዋል። በዚህ ዙሪያ የጠየቅኳቸው የደብሩ አስተዳዳሪ እንደሚነገሩት "ገሊላ የሚለው ስያሜ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል ከመስጠት አንጻር የተሰጠው ነው። ካህናተ ሰማይ የደብሩ ጽላት ነው። የእግዚአብሔርን መንበር የሚያጥኑ የሰማያውያን ካህናት ስያሜ ነው" (ቃለመጠይቅ፣ ቀሲስ ተስፋዬ ነቢ፣ በቀን 09/08/05 ዓ.ም)።

ገሊላ[22] የሁለት ነገሮች መጠሪያ ነው። በአንድ በኩል ከሶስቱ የእስራኤል ክፍለ ሀገሮች አንዱ የሆነው ክፍለ ሐገር መጠሪያ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የገሊላ ባሕር መጠሪያ ነው። ኢየሱስ

---

[22] ገሊላ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በነብዩ ኢሳይያስ ምዕራፍ 9፣1 "በመጀመሪያው ዘመን የዛብሎንና የንፍታሌምን ምድር አቀለለ፤ በኋለኛው ዘመን ግን በዮርዳኖስ ማዶ በባህር መንገድ ያለውን የአህዛብን ገሊላ ያከብራል፤" የሚል ትንቢት የተነገረላት በኋለኛው ዘመን ኢየሱስ ያከበራት ቦታ ናት።

ክርስቶስ ብዙ ጊዜ ያስተማረበትና ተአምራት ያደረገበት ነው። የገሊላ ባህር ደግሞ ኢየሱስ የማስተማር ተግባር የተጀመረበትና ዓሣ አጥማጆቹ ደቀመዛሙርት የተጠሩበት ነው። ይሄንን መጠሪያ ከመልክአ ምድሩ አቀማመጥ (የደሴቱ በባህር መከበብ) ጋር ገጠሙኝ በሚመስል መልኩ ለዝዋይ ሐይቅ የአንዱ ደሴት መጠሪያ ሆኖ እናገኘዋለን። ለምን ይሄ ስያሜ ተሰጠ ስንል የምናገኘው ምላሽ የዚያን ታሪካዊ ቦታ ስያሜ በመጠቀም የታሪኩና በረከቱ ተቋዳሽ ማድረግ ነው የሚል ሊሆን ይችላል። ካህናተ ሰማይ በሚለው መጠሪያ የሰማያውያን ካህናት አገልጋዮች ያሉበት ደሴት ነው። በገሊላ መጠሪያነት ደግሞ በክርስትናው አስተምሮ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ኢየሱስ ክርስቶስ ያከበራት ምድር በረከት ያለበት ነው የሚያስብል ነው።

ጌቴሴማኒ አርባዕቱ እንስሳ ደሴትንም ስንመለከት እንደ ገሊላ ካህናተ ሰማይ ተመሳሳይ ነገር ይታይበታል። ጌቴሴማኒ የደሴቱ አጠቃላይ መጠሪያ ነው። አርባዕቱ እንስሳ ደግሞ በደብሩ ጽላት ምክንያት የተሰጠው ስያሜ ነው። ጌቴሴማኒ ኢየሱስ የጸለየበት የጸሎት ስፍራ ነው (ማቴ. 26፣36)። አርባዕቱ እንስሳ ደግሞ የቅድስት ሥላሴን መንበር የሚሸከሙት ኪሩቤልና ሱራፌል ሲኾኑ በገጸ ሰብእ፣ በገጸ አንበሳ፣ በገጸ ላሕምና በገጸ ንስር የሚወክሉ መላእክት ወገን ናቸው። ስለዚህ በስያሜው በኩል ደሴቱ የጸሎት ስፍራ መሆኑንና ሰማያውያን መላዕክት የሚያመሰግኑት አምላክ የሚመሰገንበት ቦታ መሆኑን ለማመልከት የታሰበ ይመስላል።

ደብረ ሲና የተባለ ደሴትም አለ። ደብረ ሲና[23] በመጽሐፍ ቅዱስ ተረክ ውስጥ እንደምናገኘው ሙሴ የእግዚአብሔርን ድምጽ የሰማበት ተራራና የቃል ኪዳኑን ታቦት የተቀበለበት ስፍራ ነው (ዘጸ.3፣1፤ ዘዳ.4፣9-10)። ስለዚህ ደብረ ሲና ሲባል በቀጥታ የሚከሰትልን ነገር ሙሴ ከእግዚአብሔር የተቀበለው የቃል ኪዳኑ ታቦት ነው። ይሄንን ስያሜ መስጠት ለምን አስፈለገ ብለን ብንጠይቅ የምናገኘው ምላሽ የሚከተለውን ነው።

> ደብረ ሲና የተባለው በዮዲት ጉዲት ወራራ ጊዜ ጽላተ ሙሴ፣ ሙሴ በሲና ተራራ ላይ 40 ቀንና ለሊት ጾሞ ያገኛት ጽላት እዚህ ስላረፈች ነው፤ አክሱም ጽዮን ህዳር 21

---

[23] የሲና ተራራ ከግብጽ ሀገር በስተምስራቅና ከእስራኤል በስተደቡብ በሚገኘው የሲና በረሃ ውስጥ የሚገኝ ተራራ ነው። ደግሞም ኮሬብ ይባላል። በዚህ ተራራ መሴ ለአግልግሎት ተጠርቶበታል። የነበልባልና የሐመልማልን ምሥጢራዊ ውህደት ተመልክቶበታል። የእግዚአብሔርን ድምጽ ሰምቶበታል። እስራኤል በሥጋዊም ሆነ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ይተዳደሩበት ዘንድ የተጻፉ ፲ቱ ህግጋት በሁለት የድንጋይ ጽላት ሠሌዳ ላይ በኋላም ከግራር እንጨት የተሠራ ሠሌዳ የተጻፉትን ተቀብሎበታል (ሰሙና ቸሬ፣23-24)።

ትነግሳለች፡፡ ይሄ የሆነውም የሙሴ ጽላት በመሆኗ ምክንያት ህዳር ጽዮን የምትከበረው ከጠላት እጅ የወጣችበት ዕለት ስለ ሆነ ነው፡፡ የኛም ደሴት የታቦተ ጽዮን ማረፊያ ሆኖ ስለ ነበረ ዓመታዊ ንግሱ ህዳር 21 ቀን ነው (ቃለመጠይቅ፣ ቀሲስ ተስፋዬ ነቢ፣ በቀን 09/08/05 ዓ.ም)፡፡

ከላይ የቀረበው ንግግር የሚያስረዳን የደብረ ሲና ስያሜ የተሰጠው ጽላተ ሙሴ ከእግዚአብሔር ዘንድ ለሰዎች የተሰጠችው በደብረ ሲና ተራራ ላይ ስለ ሆነና ያች ጽላትም በዮዲት ወረራ ግዜ በዝዋይ ሐይቅ ከሚገኙ ደስያት በአንዱ አርፋ ስለ ነበረ ነው፡፡ ተረኩን የበለጠ ለማጽናት ጽላተ ሙሴ ለፍልስጥኤማውያን ኃይለ ተአምራቷን፣ ለእስራኤላውያን ደስታን ያሰማችበት፣ የኢትዮጵያን ምድር የረገጠችበት፣ ወደ ዝዋይ ሐይቅ የተሰደደችበትና ተመልሳ አክሱም የገባችበት በሚሉ ተደራራቢ ታሪኮች ህዳር 21 ቀን በአክሱም ትከብራለች፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በዝዋይ ሐይቅም ትከበራለች፡፡ ከዚህ የምንረዳው ነገር ስያሜው በስፍራው የሚነገረውን ቃላዊ ተረክ ማጠናከሪያ መሆኑን ነው፡፡ ምክንያቱም በዝዋይ ደስያት ከሚተረኩት ተረኮች የቀዳሚነቱን ረድፍ የሚይዘው የጽላተ ሙሴ 40 ዘመን በደስያቱ መሸሸግን የሚተርከው ነው፡፡

በዝዋይ ሐይቅ ላይ ከሚገኙት ደስያት ሌላኛው የደብረ ጽዮን ደሴት ነው፡፡ የደሴቱን ታሪክ ከነገሩኝ መካከል [መርጌታ ሰምረ ግዴይ፣ (በቀን 10/8/05 ዓ.ም)፣ መምሬ ገብረ መስቀል ሂርጳ (በቀን 02/08/05 ዓ.ም)ና መምሬ መልአኩ ገብረ ማርያም (በቀን 01/08/05 ዓ.ም)] እንደ ነገሩኝ ከሆነ ታቦተ ጽዮን[24] የአርባ ዓመቱን የስደት ዘመን ገዳም ተገድሞላት የኖረችው በዚህ ደሴት ላይ ስለ ሆነ አክሱማውያኑ ስም ሲያወጡ የጽዮን[25] መሸሸጊያ ናት በሚል ደሴቱን ደብረ ጽዮን ብለውታል ነው፡፡ ስለዚህ ስያሜዎቹ የሚያመለክቱት የዚያ የተቀደሰ ነገር በረከት በዚህ ቦታ ደርሷል፤ ይህም ስፍራ ተባርኳል በሚል የተሰጠ ይመስላል፡፡ አንድም በረከቱ እንዲያድር ከመፈለግም አንጻር የተሰጠ ሊሆን ይችላል፡፡

ስያሜዎች ሲሰጡ ደግሞ እንደ ግብዓት የሚወሰዱት ነገር አለ፡፡ ለምሳሌ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥን ከግንዛቤ አስገብተው ሊሆን ይችላል፡፡ ለዚህም የደብረ አብርሃምን ደሴት ማንሳት

---

[24] ታቦተ ጽዮን - በዳዊት አንባ የነበረች ታቦት፣ ነብሪድ ይሥሐቅ ግን አክሱም መጥታለች ይላል (ደስታ ተክለወልድ፣1250)፡፡

[25] እግዚአብሔር ጽዮንን መርጦአታልና፣ ማደሪያውም ትሆነው ዘንድ ወድዶአታልና፣ ይህች ለዘለዓለም ማረፊያዬ ናት፤ መርጫታለሁና በዚህች አድራለሁ (መዝ.131፣13-14)፡፡

ያስፈልጋል፡፡ በዝዋይ ሐይቅ ውስጥ ከሚገኙ ደስያት ጠዴቻ በሚል በኦሮምኛ ስያሜ የሚጠራው ነው፡፡ ወደዚህ ደሴት በሄድኩበት ጊዜ ደሴቱ ለምን ደብረ አብርሃም እንደ ተባለ ካነጋገርኳቸው መረጃ አቀባዮቹ መካከል የደብረ አብርሃም አገልጋይ በሆኑት በመምሬ አስፋው የቀረበው ንግግር የሚከተለውን ይመስላል፡፡

> ቀድሞ ጽላተ ሙሴን ይዘው ወደዚህ ስፍራ የተሰደዱት ወገኖች እዚህ ደሴት ላይ ለምሳ አርፈው ነበርና የደሴቱን አቀማመጥ ሲያዩ ሶስት ተራራዎች ያሉበት ነው፡፡ ያው ሶስትነት ሲነሳ ስላሴ ይታወሳሉ፡፡ ስላሴ ሲጠራ ደግሞ የአንድነትና ሶስትነት ምስጥሩ የተገለጸለት አብርሃም ይነሳል፡፡ ስለዚህ በዚህ ቦታ የአብርሃምን ጽላት አስቀመጡና ደሴቱን ደብረ አብርሃም አሉት፡፡ ከሶስቱ ተራራዎች ለአንዱ ጉብታ ደግሞ የይሳቅ ዳገት የሚል ስያሜ ሰጥተውታል፡፡ አብርሃም ሲነሳ በሞርያም ተራራ ታዛዥነቱን ያሳየው የአብርሃም ልጅ ይሰሃቅ ይነሳልና (ቃለመጠይቀ፣ መምሬ አስፋው ቱፋ፣ በቀን 6/08/05 ዓ.ም)፡፡

የዛይ ሕዝቦች ለአንድ ነገር መጠሪያ ሲሰጡ የተለያዩ ግብዓቶችን እንደሚጠቀሙ ለደብረ አብርሃም ከመልክዓ ምድራዊ አቀማመጡ ተነስተው መጠሪያውን የሌላ ጽንሰ ሀሳብ ተሸካሚ ካደረጉት መረዳት ይቻላል፡፡ ከላይ ለደብረ አብርሃም ከስፍራው ጋር በተያያዘ የተሰጠውን ስያሜ ለማገናዘብ ይረዳኝ ዘንድ ከመርጌታ አዕምሮና የደሴቱ ተወላጅ ከሆነው ተመስገን ጋር በመሆን በቀን 05/08/05 ዓ.ም ከሰዓት በኋላ እየተዘዋወርኩ ለመቃኘት ሞክሪያለሁ፡፡ በዚህ ሰዓት እንደ ተጨማሪ ግብዓት ያገኘሁት ነገር መምሬ አስፋው ደብረ አብርሃም ላይ ሶስት ተራራ እንዳለና ከሶስቱ ለአንዱ የይስሐቅ ዳገት ስያሜ የተሰጠው አብርሃም ሲነሳ ልጁ አብሮ ስለሚነሳ ነው ከሚለው ሌላ ለይስሐቅ ስያሜ መሰጠት ምክንያት የሚሆንን ነገር ነው፡፡ ይኸውም የይስሐቅ ዳገት ላይ ከግራሩ፣ ከቀጭቡና ሾላ ዛፎች በተጨማሪ የደሴቱ ነዋሪዎች የጤፍ ምርት የሚያስሩበት ሀረግ በጣም በዛ ብሎ ማግኘታችን ነው፡፡ "ይሄ ሀረግ በጣም ነጭ አልሆነም እንጂ በሰሜኑ ክፍል እጸ ሳቤቅ" የሚል መጠሪያ አለው በሚል መርጌታ አዕምሮ በጫወታ መሃል ነገሩኝ፡፡ በዚህ ሰዓት ያስታወስኩት ነገር በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ (ዘፍ.22፣13) አብርሃም በልጁ ተፈትኖ ታማኝነትን ያገኘበት፣ የይስሐቅ ፍጹም ታዛዥነት የታየበት፣ በእግዚአብሔር አዘጋጅነት ቀንዶቹ <u>በዕፀ ሳቤቅ</u> የታሰረ በግ ስለ ተገኘበት ታሪክ የሚተርከው ክፍል ነው (አጽንኦት የራሴ)፡፡ ምናልባትም ይሄንን የይስሐቅ ዳገት የሚለውን ስያሜ የሰጡ ሰዎች መጠሪያው ተጨማሪ ጽንሰ ሀሳብ እንዲሸከም ወይም ሌላ ሃይማኖታዊ ተረክን እንዲጠራ ከመፈለጋቸው ሌላ ስያሜውን

ለመስጠት እንደ ግብዓት የተጠቀሙት ነገር በስፍራው የሚበቅለውን ሀረግ እንደ ዕፀ ሳቤቅ ከመውሰድ የተነሳ ሳይሆን እንደማይቀር የራሴን ግምታዊ ሀሳብ እንድሰጥ አድርጎኛል።

የአንድ ነገር መጠሪያ ከመጠሪያነቱ ባሻገር ተደራቢ ጽንሰ ሀሳብ እንዲሸከም ትልቁን ሚና ከሚጫወቱት መካከል የመልክዓ ምድራዊ ገጽታዎች[26] ይጠቀሳሉ። ከዚሁ ጋር በተያያዘ አንድ የሚነሳው ነገር ታቦተ ጽዮንን ይዘው ወደ ዝዋይ ደሴት የገቡት ስደተኞች ከተፈጥሯዊ አቀማመጡ የተነሳ ይሰጡ የነበረው ስያሜ ምን ያህል ሃይማኖታዊ አንድምታ እንደ ነበረውና በታውንም ክርስትና ከማስነሳት ጋር የተገናዘበ እንደ ሆነ ተረኮቹ ምስክር ናቸው። በደብረ ጽዮን ደሴት በመጀመሪያ ያረፉትና ገዳሙን ሊገድሙ የቻሉት ከባህር ጠለል በላይ 953 ሜትር ከፍታ ባለው የተራራው አናት ላይ ነው። ይሄ ያለ አንዳች ምክንያት እንዳልሆነ መገመት አያዳግትም። ምክንያቱም መልክዓ ምድር ከተፈጥሯዊ ገጽታው ሌላ የማህበረሰቡ ባህል፣ ሃይማኖት ለመጠቆም የሚያስችል ትዕምርትም አለው ብለናልና። በባህላዊ አንድምታ ስናየው ከጠላት እየሸሹ ናቸው። ወደ የብስ ቅርብ የሆኑትን እንደ ደብረ አብርሃምና ጌቴሴማኒ ያሉትን አልፈው መጥተዋል። በዚህም ደሴት ሲያርፉ አናቱ ላይ ነው። ሐይቁን ተከታትሏቸው የሚገባ ጠላት ቢኖር እንኳን ከላይ ሆነው በድንጋይም ቢሆን ለመከላከል ያስችላቸዋል። በባህላዊ ጠላትን የማጥቃት ስልት ጥሩ ምሽግ ይዘዋል። በማጥቃቱ ረገድ ተጠቃሚ ናቸው ልንል እንችላለን።

የትረካዎቹ አንድምታ ግን በዚህ በባህላዊ ጉዳይ ብቻ ተፈትሾ አያበቃም። በሃይማኖታዊ ፎክሎርነቱ ስናየው ደግሞ ሌላ አንድምታ ይዞ የሚመጣና ሌላ ተረክ የሚጠራ ሆኖ እናገኘዋለን። አክሱማውያኑ ከዮዲት ወረራ ለመዳን የተገበሩት በዘፍ.19፣17 ላይ "ወደ ተራራው ሸሽተህ አምልጥ" በሚል ከሰዶምና ገሞራ የእሳት ዲን ሎጥ እንዲድን ከተሰጠው ሃይማኖታዊ መመሪያ ጋር የሚዛመድ ይመስላል። ሙሴ ታቦቷን በተቀበለበት በደብረ ሲና አምሳል በሆነች ተራራ ጽላቷን ከጠላት ሊያተርፉ ተሸሽጉ ይባላልና። ተራራ በብሉዩም ሆነ ሃዲስ ኪዳን ተረኮች ውስጥ የእግዚአብሔር ድንቅ ስራ የተገለጸበት ስፍራ ነውና።

---

[26] መልክዓ ምድራዊ ገጽታዎች የአከባቢውን ተፈጥሯዊ ቀለም ከማሳየት ያለፈ ማህበራዊ/ባህላዊ ገጽታውን ጭምር መጠቆም የሚችል ትዕምርታዊ ፋይዳ ይኖራቸዋል ብሎ ማሰብ ይቻላል (ቴዎድሮስ፣ 115)።

ከላይ ከቀረቡት ተረኮች እንደምንረዳው የስም ለውጥ ትልቅ ፋይዳ እንዳለው ነው፡፡ በስያሜ ብቻ የስፍራውን ቅድስና ለማመልከት የተሰጡትን መጠሪያዎች ተመልክተናልና። ከዚህ ጎን ለጎን ስያሜዎች ሊሰጡ የሚችሉት በሃይማኖቱ ውስጥ ያለውን ስፍራ በራሳቸው አጠገብ ህልው አድርጎ ከመግለጽ፣ አንድም ሥነ ልቦናዊ ፍላጎታቸውንና ሃይማኖታዊ ርዕዮተ ዓለማቸውን በነዚህ ነገሮች ላይ ማሳረፍን ከመሻት አንጻርም ሊሆን እንደሚችል ያስገነዝቡናል፡፡

### 4.1.2.2. በደስያቱ የተለያዩ ገቢረ ተዓምራት መፈጸም

የቤተ-እምልኮዎችን የቅድስና ማዕረግ ከፍ ከሚያደርጉ ነገሮች መካከል አንዱ የገቢረ ተአምራት መፈጸም ነው፡፡ ሙትን ማነሳት፣ የጎበጠን ማቅናት፣ ከአጋንንት ምርኮ ማላቀቅ፣ ከለምጽ ማንጻት፣ ለአይነ ስውር ብርሃን መስጠት፣ መስማት የተሳነውን ማዳን የሚችል ስፍራ የተለየና የተቀደሰ ቦታ ተደርጎ ይቆጣራል፡፡ ምክንያቱም አብዛኞቹ የሃይማኖት ዶግማዊ ተረኮች በመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ በቅዱስ ቁራን እንዲሁም በአይሁዳውያኑ መጽሐፍ ቶራ የሰፈሩት እንደዚህ ዓይነት ትዕይንትን የሚዘክሩ ናቸው፡፡ በዝዋይ ደስያትም እንደ ገቢረ ተአምር የሚተረኩ ተረኮች አሉ፡፡ ከአምስቱ ደስያት በዝዋይ ደብረ ጽዮን ደሴት የሚተረከውን በመጥቀስ መጀመር ይቻላል፡፡ የደብረ ጽዮን ገዳም አስተዳዳሪ የሆኑት አባ ገብረ እግዚአብሔር አለሙ "የዚህን ሐይቅ ውኃ ስታየው ቀዝቃዛ ነው፡፡ ነገር ግን ይሄንን ደሴት ዙሪያውን ብትሄድ ከተራራው ውስጥ ከየአቅጣጫው የሚፈስ ሙቅ ጸበል ታገኛለህ ይሄ እግዚአብሔር ለዚህ በውኃ ለተከለለው ሕዝብ ከበሽታ መፈወሻ የሰጠው መድኃኒት ነው፡፡" በማለት ይናገራሉ (ቃለመጠይቅ፣ በቀን 30/07/2005 ዓ.ም)፡፡ ከዚህ ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው ስፍራው ለሰዎች በሽታ ፈውስን የሚያስገኝ መሆኑን ነው፡፡ ይህ የስፍራው ቅድስና ለደሴቱ ነዋሪዎች ብቻ ሳይሆን ከውጪ እምነው ለሚመጡ ሁሉ ፈውስን የሚሰጥ መሆኑን የዚያው ደሴት ተወላጅ የሆኑትና ለ38 ዓመታት በገዳሙ በክህነት ሲያገለግሉ የኖሩት መምሬ ባንቲሁን ሀብተ ማርያም ይተርካሉ፡፡

> ብዙ ጊዜ በእጅ የያዙት ወርቅ እንደሚባለው ይሆንብናል፡፡ እነዚህ ከተራራው በታች የምታያቸው ጸበሎች ናቸው፡፡ ብጹዕ አቡነ ሉቃስ አስከልለዋቸው ነበረ፡፡ ታዲያ ሕዝቡ ውኃው ወየበ በሚል የታጠረበትን አነሳው፡፡ ሙቅ ውኃ ስለ ሆነ እንደ ገላ መታጠቢያም ይጠቀሙበታል፡፡ ሴቶች ንጹህ ሳይሆኑ መጥተው ይነከሩበታል፡፡ ይገርምሃል የጸበል ክብር የሚያቅ ግን ከሌላ ስፍራ እዚህ ድረስ መጥቶ ፈውስን እያገኘ ይሄዳል፡፡ አሁን ወደ ላይ ስትመጣ የሆነ ከዘራ ይዞ የሚሄድ ሽማግሌ አላየህም፡፡ ሲመጣ በሽክም ነበረ ይሄው ዛሬ ራሱን ችሎ ይሄዳል (ቃለመጠይቅ፣ በቀን 30/07/2005 ዓ.ም)፡፡

በዚህ ምዕራፍ መግቢያ እንዳነሳሁት ቃላዊ ተረኮቹ ከአባቶቻችን የሰማነው፣ የነገሩን ከሚለው ውጪ በአይናችን ያየነው፣ የደረስንበት፣ ተአምር ነው እያሉ የሚተርኩት ነው። መምሬ ባንቲሁን የነገሩኝ የፈውስ ተረኮች ከዚህ ውስጥ ሊመደቡ የሚችሉ ናቸው። እነዚህም ለረጅም ዘመን ኅባጣ ሆነው መሄድ ያቃታቸው በእግራቸው መራመድ መቻል፣ መብላት የተሳናቸው መመገብ፣ የራሳቸውን የምግብ ባህል ሲጨምሩ እንዳውም ዓሣም ተመገቦ ሄደ፤ እያሉ የተረኩልኝ ናቸው። እንደዚህ አይነት ትረካዎች ተግባራቸው ምንድን ነው ብንል አንድ ሰው በዚያ እምነት ውስጥ እንዲሆንና ለዘለቄታው እንዲኖር የሚያደርጉና ምዕመኑ ከስርዓት ሲወጣ ለማስተማሪያነት የሚተረኩ ይመስላሉ። ማህበረሰቡ የተቀደሰ ስፍራ ብሎ ስለሚያምንበት ቦታ ቅድስናውን የሚያጎሉለት፣ የመንፈስ ጥንካሬን እንዲያገኝ የሚነገሩለት፤ ያየሁት፣ የተፈጸመ ተአምር በሚል የሚቀርቡ ትረካዎች መኖራቸውን እንረዳለን።

ከዚሁ ከገቢረ ተአምር ሳንወጣ የስፍራውን ቅድስና የማጉላት ተግባር ካላቸው ተረኮች ቀሲስ ተስፋዬ ነቢ ከተረኩልኝ መካከል አንዱን ማቅረብ ይቻላል። ይኸውም ሐይቁ ውስጥ በመግባት ራሱን ሊያጠፋ ስለ ነበረው ሾፌር የሚተረከው ታሪክ ነው።

> እንደ ድንቅ ስራ ከሚነገረው አንዱ ከአንድ የነዳጅ ቦቴ ሾፌር ጋር የሚያያዝ ነው። ህዳር 23 ለካህናተ ሰማይ በዓል ዋዜማ አባቶች በገሊላ ደሴት ላይ ለምስጋና ቆመዋል። በቀለ ሞላ ሆቴል አርፎ ነዳጁ መጉደሉን የተመለከተው ይሄ የቦቴ ሹፌር ራሴን ማጥፋት አለብኝ በሚል ወደ ሐይቁ ራሱን ሊጥል ወደዚያ ይሄዳል። ሀይቁ ውስጥ ለመግባት ቢሞክርም ሳይሰምጥ ቀርቶ ቀጥታ በውኃው ላይ እየተራመደ ወደ ደሴቱ ይደርሳል። በደሴቱ ዳርቻ ዓሣ አጥማጆች ነበሩና ሰውዬ እንደ መንገድ ዝም ብሎ በውኃ ላይ እየተራመደ ወደ እነሱ ሲመጣ ተደናግጠው ወደ ኋላ ሲሸሹ አትፍሩኝ ሰው ነኝ ብሎ ያናግራቸውና የሆነውን ያጫውታቸዋል። ከዚያም ወደ ቤተክርስቲያኑ ይወስዱታል። በማግስቱ በበዓሉ ላይ ሕዝቡ ፊት ወጥቶ ይሄንን እንዲናገር ይደረጋል። እሱም እግዚአብሔር የፈጸመለትን ድንቅ ተአምር ተናግሮ ይሄዳል። ለዓመቱም ክብረ በዓል ስዕለት ተስሎ እንዳስገባም ይነገራል (ቃለመጠይቅ፣ በቀን 09/09/05 ዓ.ም)።

ተረኩ የቀረበበትን ሂደት ስናይ የድርጊትና ሁነት ትስስርን የሚያሳይ መቼት ያለው ነው። ምክንያቱም ህዳር 24 ካህናተ ሰማይ ይነግሳል። ሐይቅ በመሆኑ በአካባቢው ዓሣ የሚያጠምዱ ሰዎች ሊኖሩ እንደሚችሉም ይታሰባል። ሰውየው በእግር ሐይቁ ላይ እየተራመደ ሲመጣ አጋንንት መስሏቸው እንደ ሸሹትና ከዚያ ሰው መሆኑን አስረድቶ የደረሰበትንና የተደረገለትን ገቢረ ተአምር እንደ ተረከላቸውም ያስረዳል። ተረኩ በክርስትናው ትውፊት ውስጥ ቀድሞ የሚታወቅ ሚታዊ ተረክን የሚጠራ ነው። ይኸውም "በአራተኛው ሌሊትም ጌታችን ኢየሱስ

ባሕሩን እየረገጠ ወደ እነርሱ መጣ፤ ሊያልፋቸውም ይወድ ነበር። በባህር ላይ ሲሄድ ባዩት ጊዜ ምትሀት መስሏቸው ጮኹ። ሁሉም አዩትና ደነገጡ፤ ያንጊዜም ተናገራቸውና አይዟችሁ እኔ ነኝ አትፍሩ አላቸው" (ማር.4፣48-51) የሚለው ነው። በዚህ ሚታዊ ተረክና ከላይ ባነሳሁት ተረክ መካከል መመሳሰሎች ይታያሉ። ሁለቱም ተረኮች በባህር ላይ የሄደን ሰው ታሪክ የሚተረኩ ናቸው። ሁለቱንም የተመለከቱ ሌሎች አካላት ምትሃት መስሏቸው ደንግጠዋል። ተጋዳሊያኑ ለሚደነግጡት አካላት እኔ ነኝ አትደንግጡ ሲሉ ይሰማሉ። በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት በመጽሐፍ ቅዱሳዊው ተረክ ውስጥ ያለው እንደ ፈጣሪ የሚታመን የልዕለ ተፈጥሮ ተግባር ሲሆን በዚህኛው ተረክ ደግሞ ገጸባህሪው አንድ ራሱን ሊያጠፋ ያለ ሰው ነው። የሚትና የአፈታሪክ አይነት አቀራረብ ያላቸው ናቸው። ከፎክሎር አንጻር ስንመለከታቸው ሃይማኖታዊ ተረኮች ምን ያህል ንጽጽራዊ አውድ እንዳለባቸው ማለትም አንዱ ተረክ ሌላውን ተረክ የመጥራት ባህሪ እንዳለባቸው እንረዳለን። በሌላ መልኩ ደግሞ የሚያምኑበትን ተረክ ህልው አድርጎ በመከሰት ወደ ራስ የማምጣት ባህሪ ይስተዋልባቸዋል። ዋናው ተግባራቸው ግን የስፍራውን ቅድስና መግለጽ ነው።

#### 4.1.2.3. የሐይቁ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም መባረክ

የተረኮቹን የቅድስና መልዕክት አንጸባራቂነት የምንመለከተው ከሐይቁ መቀደስ ጋር በተያያዘ ከሚተረከውም ተረክ ነው። ዲያቆን ደጉ ስሜ የነገሩኝን እንደሚከተለው አስፍሬዋለሁ።

> አሁን ይሄንን ውኃ እኛ እየቀዳን እንጠጣዋለን። ማንም ላይ በሽታ አምጥቶ አያውቅም። እኔ እውነቱን ነው የምልህ ይሄንን የሐይቅ ውኃ ስጠጣ ታላቅ ደስታ ይሰማኛል። በቃ ከቧንቧ የምጠጣው ውኃ የማይሰጠኝን እርካታ የማገኝበት ነው። ምክንያቱም ውኃው የተቀደሰ ነው። መልአኩ ቅዱስ ኡራኤል ጌታ በመስቀል ላይ ያፈሰሰውን ደም የቀዳበትን የወርቅ ጽዋ ያጠበው እዚህ ነው ይባላል። እግዚአብሔርን የት ልጠበው ቢለው በዛይ ማይ እጠበው ብሎታልና (ቃለመጠይቅ፣ በቀን 15/08/05 ዓ.ም)።

ከላይ የቀረበው ተረክ ከሀዲስ ኪዳን ሚት ጋር በተያያዘ የሐይቁን መቀደስ የሚሰብክ ነው። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ትውፊት መሰረት የትኛውም ቦታ የሚሰራ ቤተክርስቲያን ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሳለ የፈሰሰውን ደም መልአኩ ኡራኤል በወርቅ ፅዋ ቀድቶ በዓለም ላይ በረጨ ጊዜ ያረፈበት ነው ተብሎ ይታመናል። በዝዋይ ደስያት የሚቀርቡት ትውፊታዊ ተረኮች ደግሞ ደሙን ወደ ዓለም ከረጨ በኋላ ደሙን የቀዳበት ጽዋ የታጠበው

በዝዋይ ማይ እንደ ሆነ ይተርካሉ፡፡ ይህም የደስያቱ ተረኮች ቅድስናን የመስበክ ተግባር አላቸው በሚል ያነሳሁትን ጉዳይ የሚያጠናክር ነው፡፡

### 4.1.2.4. የዝዋይ ደስያት በሃይማኖቱ ተጋዳሊያን መነብኘት

በሃይማኖት ውስጥ የአንድ ስፍራ የቅድስና መለኪያ ተደርጎ የሚወሰደው በእምነቱ ትልቅ ቦታ የሚሰጣቸው ቅዱሳን ወደ ስፍራው መጥተው መባረካቸው፣ መጸለያቸው፣ በዓት ማድረጋቸው እና የተለያዩ ገድልን መፈጸማቸው ነው፡፡ በዝዋይ ደስያት ከሰበሰብኳቸው ተረኮች መረዳት እንደሚቻለው አንዱ ተግባራቸው የተለያዩ ቅዱሳን ወደ ደስያቱ መምጣታቸውን የሚዘክሩ ናቸው፡፡ በዚህ ሐይቅ ተገኝተው ከጸለዩት የሃይማኖቱ ተጋዳሊያን መካከል አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ አንዱ ናቸው፡፡ አባ ገብረ እግዚአብሔር ዓለሙ እንደነገሩኝ ከሆነ "አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ባህሩን እየረገጡ መጥተው ወደዚህ ዋሻ ገቡ ይባላል፡፡ ታዲያ ባህታዊ ገብረ መስቀል በግዞት በመጡ ጊዜ ይኖሩ የነበሩት በዚያ ዋሻ ስለ ነበረ እኔ ምኑን ታስርኩት ተፈታሁ እንጂ አቦዬ ከጸለዩበት ዋሻ የማረፉን እድልን አግቻለሁና" ይሉ ነበር ይባላል (ቃለ መጠይቅ፣ 30/07/05 ዓ.ም)፡፡

የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስን ወደ ደሴቱ መጥቶ መጸለይ ተጨባጭ ያደረጉበት ቁሳዊ ባህል በደብረ ጽዮን ደሴት ተራራ ውስጥ የሚገኘውን ዋሻ ማሳየት ነው፡፡ የተረክን ተአማኒነት ከፍ ከማድረጊያ ስልት አንዱ ቃላዊ ተረኮቹን በቁሳዊ ባህል በማስረገጥ ማቅረብ ነው፡፡ ስለዚህ ዋሻው በተጋዳሊው ስም የአቦ ዋሻ እየተባለ ይጠራል፡፡ በኦርቶዶክሳዊ ትውፊት ውስጥ በትውልድ ግብጻዊ የሆኑት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ አቦዬ ወይም አቦ በሚል በተለምዶ ስለሚጠሩ ስያሜው ከዚህ ጋር የሚዛመድ ይመስላል፡፡ ከሃይማኖቱ ተጋዳሊያን ጋር በተያያዘ የገድል መጽሐፍ የተጻፉላቸውና ወደ ደስያቱ በግዞት የተጋዙ እንዳሉ በምዕራፍ ሶስት አንስቻለሁ፡፡ ይሄንን ጉዳይ በተመለከተ ያነጋገርኳቸው መምሬ ባንቲሁንና ገብረ መስቀል የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> እኛ ያልደረስንባቸው ከነገስታቱ ጋር በሃይማኖት ጉዳይ እየተጋጩ ወደዚህ የሚጋዙ ብዙ እስረኞች ነበሩ ይባላል፡፡ እኛም ከደረስንባቸው አባ በጋር የሚባሉ በአቡነ ቴዎፍሎስ የታሰሩና አባ ገብረስላሴ ተድላን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ከደሴቱ ነዋሪ የሚጠበቀው ወደ ሐይቁ በመሄድ የበላ መቅዘፍ እንዳይለምዱ መጠበቅ ነው፡፡ ከለመዱ ጠፍተው ይወጣሉ ተብሎ ስለሚታሰብ፡፡ (ቃለመጠይቅ፣ በቀን 02/08/05 ዓ.ም)፡፡

ከትረካዎቹ የምንገነዘበው ነገር በሃይማኖታዊ ፎክሎር ውስጥ ምሁራኑ እንደሚሉት ተረኮቹ ሌላ ተረክን የሚጠሩ ንጽጽራዊ አውድ ያላቸው ሆነው እናገኛለን። ለምሳሌ ከነገስታቱ ጋር በሚፈጠር ለግዞት የሚዳረጉት አባቶች ምክንያት ነገሥታቱን ከአንድ በላይ ሚስት ማግባት አይገባችሁም በሚል በሚፈጠር ግጭት ነው። የመጀመሪያ መነሻው ንጉስ ሠይፈ አርዕድ የወንድሙን ሚስት በማግባቱ የተፈጠረ ነው። ይሄንን ታሪክ የሚመስል በሀዲስ ኪዳናዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ተረክ ላይ እናገኛለን። ይኸውም በማቴ. 14፤1 ላይ የሚገኘው ነው። ሄሮድስ የወንድሙን የፊሊጶስን ሚስት ሄሮዲያዳን ሲያገባ ዮሐንስ አትገባህም በማለቱ ወደ እስር ቤት እንደ ተጋዘና በመጨረሻም አንገቱን እንደ ተሰየፈ የሚተርከው ነው። ከዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራት ጋር በተያያዘ የሚተረኩትም ንጉሱ የአባቱን ዕቁባት በማግባቱ የተነሳ ከሃይማኖት መምህራኑ ጋር የተፈጠረ ነው። ስለዚህ ተረኮቹ ቀድሞ ከሚታወቁ ሃይማኖታዊ ትውፊት ውስጥ ከሚገኙ ተረኮች ጋር ይናበባሉ።

የአንድ ስፍራን ቅድስና ከሚያመለክቱበት ነገሮች መካካል ሌላው ጉዳይ በሃይማኖቱ ውስጥ ትልቅ ቦታ የሚሰጣቸውና በማዕረግ ጵጵስና ደረጃ የሚገኙ አካላትና በታሪክ የሚታወቁ ሌሎች ግለሰቦች ከቦታው ክቡርነት አንጻር መጥተው በቦታው ማረፋቸውን፣ መከራ መቀበላቸውን፣ ድንቅ ስራ መስራታቸውን መተረክ ነው። በቅድስናቸው በሃይማኖቱ ውስጥ ከሚታወቁት በ1945 ዓ.ም በግብጽ ጵጵስናን ከተቀበሉ ሰባት አበው መካከል ብጹዕ አቡነ ሉቃስ በደብረ ጽዮን ደሴት መንበረ ጵጵስናቸውን አድርገው ይኖሩ እንደ ነበረ ይተረካል። ከዚህ በተጨማሪ በ1926 ዓ.ም ሲመተ ጵጵስናን በእስክንድርያ ከአራት አበው ጋር የተቀበሉትና ሕዝቡ ለጣሊያን መንግስት እንዳይገዛ አውግዘው በ1929 ዓ.ም መስዋዕትነትን የተቀበሉት አቡነ ጴጥሮስ[27] ከጵጵስና በፊት መምህር ሀይለ ማርያም ይባሉ በነበረበት ጊዜ ዝዋይ ደብረ ጽዮን ገዳምን ያስተዳደሩ እንደ ነበረ ይነገራል። ትረካዎቹን የሚያዳብሩ ቁሳዊ ማስረጃዎች በምዕራፍ አምስት የሚቀርቡ ይሆናል። የተለያዩ ቅዱሳን አበው ወደ ስፍራው ከመምጣታቸው ሌላ የተለያዩ ነገስታት ከስፍራው በረከትን ለመቀበል ሄደው የተመለሱ መኖራቸውም ይተረካል። ከእነዚህ መካከል አጼ ምኒሊክ፣ ንግስተ

---

[27] በ1921 በካይሮ ቅዱስ ማርቆስ ቤተክርስቲያን ውስጥ በአቡነ ዮሐንስ 19ኛ እጅ ጵጵስናን ተቀብለው የተሾሙት፦ 1. አቡነ አብርሃም-- የጎጃምና ጎንደር ጳጳስ፣ 2. አቡነ ይስሐቅ- የትግራይና ሰሜን 3. አቡነ ጴጥሮስ - የወሎና የላስታ 4. አቡነ ሚካኤል የምሥራቅ ኢትዮጵያ ጳጳስ ናቸው። በዚህ ጊዜ ግብጻዊው አቡነ ቄርሎስ በሊቀ ጳጳስነት ማዕረግ ለአራቱ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት የበላይ ሆነው ተሾሙ። አቡነ ጴጥሮስ "ንጉሴ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ኢትዮጵያም የኢትዮጵያውን ናት እንጂ ለፋሽስቶች አትሆንም ብለው በመቃወማቸው በጥይት ተደብድበው ሰማዕት ሆኖዋል (ሉሌ፣ 135-136)።

ነገስታት ዘውዲቱና አጼ ሀይለ ስላሴ ቀዳሚዎቹ ናቸው፡፡ ከተረኩ ጎን ለጎን በጊዜው የቀረቡላቸው መወድስ ቅኔዎች መኖራቸውም ይነገራል፡፡

### 4.1.3. ለመልክዓ ምድራዊ አፈጣጠር ምክንያት የሚሰጡ ተረኮች

ተረኮች በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ልማዳዊ ስርዓቶች ተጠብቀው እንዲዘልቁ የሚያስተምሩ ናቸው፡፡ ምክንያቱም አባቶቻችን በዚህ መንገድ ነው ያለፉት ሲሉ ስርዓታችን፣ ልማዳችን ወይም እምነታችን ይሄ ነው እያሉ ነውና፡፡ ከዚህ ሌላ የሚጠቀሰው የተረኮች ተግባር በአካባቢው ላሉ መልክዓ ምድራዊ አፈጣጠር ምላሽ የሚሰጡ መሆናቸው ነው፡፡ የዛይ ማህበረሰብ ስለ ሐይቁ አፈጣጠር ሆነ በውስጡም ስለሚኖሩት ፍጥረታት በተለይ በየበላ በባህር ሲጓዙ እየገለበጠ ችግር ስለሚፈጥርባቸው ጉማሬ አፈጣጠር የሚተርካቸው ተረኮችም አሉት፡፡ ለማሳያ ያህል በሐይቁ አፈጣጠር ዙሪያ የሚተረከውን ተረክ ማንሳት ይቻላል፡፡ የሐይቁን አፈጣጠር አስመልክቶ በሁሉም ደስያት የሚኖሩ ዛዮችም ሆኑ በአጎራባች ያሉ ኦሮሞዎች የሚተርኩት ተመሳሳይ ነው፡፡ ሁሉም ሲናገሩ የሚሉት ነገር ይሄ እንኳን አፈታሪክ ነው በሚል ዓይነት ንግግር ነው፡፡ ከንግግራቸው የምንረዳው አፈታሪክ እውነት ሊሆን የማይችል ነው፡፡ በምዕራፍ ሁለት ያቀረብኩትና በመስኩ ምሁራን ዘንድ የሚታመንበት ግን አፈታሪክ በእውነት ላይ የሚመሰረት፣ ልማዳዊ የሆኑ ነገሮች የሚጨመሩበት፣ ገጸባህሪያቱ ሰዎች የሆኑና ተአማኒነት አለው የሚል ነው፡፡ የቃላዊ ተረክ በተለያየ ሁነት ውስጥ የመጠናት አስፈላጊነትም እንደዚህ ዓይነት ልዩነቶችን ለማውጣት ነው፡፡ ተረኩ በሚከተለው መልኩ የሚተረክ ነው፡፡

> ስለ ሐይቁ አፈጣጠር የሚነገር አፈታሪክ ነው እንጂ አለ፡፡ በአፈታሪክ እንደሚባለው አባቶቻችን ሲነግሩን ሀይቁ ቀስበቀስ ነው የዛሬውን መልክ የያዘው እንጂ ጥንት እንደዚህ አይደለም ይላሉ፡፡ ለዚህም የመጀመሪያው መሰረቱ እንደ ነገሩን ከሆነ የጉድጎድ ውኃ ነበር፡፡ ተዲያ ከዕለታት በአንድ ቀን አንዲት የልጅ እናት ውኃ ለመቅዳት ወደ ምንጩ ትሄዳለች፡፡ ህጻን ልጇን ቤት አስተኝታው ስለሄደች ከመቸኮሏ የተነሳ ምንጩን ሳትዘጋው ትመለሳለች፡፡ ውኃውም ለሊቱን በሙሉ ሲፈስ አደረና ረባዳውን መሬት አጥለቀለቀው ይባላል፡፡ እንዳውም የዚያን ጊዜ ከውኃ ሸሽተው ወደ ተራራው የወጡት ናቸው ዛሬ ሐይቁ ሲፈጠር ደስያቱ ላይ የቀሩት ይባላል(መምሬ ገብረ መስቀል፣ በቀን 02/08/05)፡፡

ከላይ ከቀረበው አፈታሪክ እንደምንረዳው የዝዋይ ሐይቅ ጥንት እንደነ ያዕቆብ የጉድጓድ ውኃ አፉ በድንጋይ የሚዘጋ ነው (ዘፍ.29)፡፡ የተረክ አንዱ ተግባር ሰዎች ለሚደነቁበት ተፈጥሮ ምላሽ ለመስጠት የሚተርኩት መሆኑ ነው፡፡ ቀድሞ ሕዝቡ በደሴቱ ላይ እንዴት መኖር ጀመረ

ለሚለውም ምላሽ የሚሰጥ ነው። በሐይቁ ውስጥ ያሉት ተራራዎች ዛሬ ደሴት የሆኑት ቀድሞ ለየብቻ የነበሩ ተራራዎች እንደሆኑም ያስገነዝበናል። በሌላ መልኩ ታቦተ ጽዮንን ይዘው ወደ ደሴቱ በ9ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሲገቡ በደሴቱ ላይ የቀደሙ ሕዝቦች ነበሩ የሚለውንም የሚያጠናክር ተረክ ነው።

ከዝዋይ ሐይቅ አፈጣጠር ጋር በተያያዘ የሚነሳው ሌላው "የሲናሩ ቤት ሲሴትብል፤ ገበሩ ማቻ መይነቀሩ፣ የሲናሩ ቤቶች ሲቀልዱ፣ ሲጨፍሩ ውኃ ወሰዳቸው" በሚል የጌቴሴማኒ ደሴት አባቶች የሚናገሩት አባባል ነው። አባባሉ ከምን ጀመረ ብዬ የጠየኳቸው የዚያ ደሴት ተወላጅ የሆኑት ጉደታ ሚደግሶና ደስዮ በዳዳ የሚከተለውን ነግረውኛል።

> ሐይቁ ሲፈጠር እመጫቷ ሴት ሳትዘጋው ቀርታ የፈነዳው ውኃ ቀስበቀስ አካባቢውን እየሞላው መጣ። በዚያን አካባቢ ይኖሩ የነበሩት ሰዎች ከአምስቱ የዛሬዎቹ ደስያት ወደሚቀርባቸው ተራራ ሸሽተው አመለጡ። ጌቴሴማኒ ይቀርባቸው የነበሩት የሲናሩ ቤቶች የሚባሉ ጎሳዎች ግን ገና ነው እንደርሳለን ብለው ሲጨፍሩ፣ ሲጫወቱ ውኃው እንደወሰዳቸው የማህበረሰቡ አባላት ይተርካል። ለዚህም ነው "የሲናሩ ቤት ሲሴትብል፣ ገበሩ ማቻ መይነቀሩ የሚባለው (ቃለመጠይቅ፣ በቀን 07/08/05 ዓ.ም)።

ከትረካው እንደምንረዳው ስለ ሐይቁ አፈጣጠር የሚተርኩት ተመሳሳይ መሆኑንና ከላይ የጌቴሴማኒ አባቶች ከሲናሩ ቤት ጋር በተያያዘ የሚነገር ነገር እንደ ጨመሩበት በዋናው ተረክ ላይ ሌላ የሚታከል ትረካ መኖሩን ነው። ተረካው እንደ ሌሎቹ ተረኮች ሁሉ በንጽጽራዊ አውድ መፈተሽ የሚችል ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ በብሉዩ ታሪክ ውስጥ የምናገኘውን የኖህ ዘመን ሰዎች ታሪክ ጋር በንጽጽር የሚዛመድ ይመስላል። የዝዋይ ማይ የተፈጠረው በእግዚአብሔር ቁጣ ይሁን በምህረቱ አይታወቅ እንጂ በተረኩ ላይ ወደ ተራራ ሸሽተው አምልጠዋል። ወደ ተራራ ሸሽቶ ከሰዶምና ገሞራ የእሳት ዲን እንደ ተረፈው ሎጥ፣ የንፍር ውኃ በምድር ላይ በነበረበት በዚያ ዘመን ወደ መርከብ የገቡት ኖህና ቤተሰቦቹ ድህነትን ሲያገኙ ሲጨፍሩ የነበሩት ሰዎች በንፍር ውኃው እንደ ጠፉ ሁሉ፣ በዛሬው የዝዋይ ሐይቅ አካባቢ የውኃውን መምጣት እያዩ ሲቀልዱ፣ ሲጨፍሩ የነበሩት የሲናሩ ቤቶች ሲጠፉ ወደ ተራራው በጊዜ የተሰበሰቡት ግን ህይወትን ማግኘት ችለዋል። ከማንነት ግንባታ ጋር በተያያዘ ከትረካው እንደምንረዳው የጌቴሴማኒ ደሴት ማህበረሰብ ኖህን በመርከብ ያዳነ፣ በተራራው ሎጥን ያተረፈ እግዚአብሔር እኛንም አድኗል የሚሉ ይመስላል። ምክንያቱም ተረኩ ከሌላ ቀደምት ተረክ ጋር የሚመሳሰል ሀሳብ የዘረፈ ነውና።

ተራራ ተምሳሌት ነው፡፡ በቤተክርስቲያኗ ትውፊት መሰረት ተራራ ቤተክርስቲያን ነው፡፡ ተራራ የአብርሃምና የልጁ ይስሐቅ ታዛዥነት የተገለጸበት (ዘፍ.22)፣ ሙሴ ከእግዚአብሄር ጋር ቃል በቃል የተነጋገረበት፣ የትዕዛዙን ጽላት የተቀበለበት (ዘጸ፣24)፣ ሙሴ ከመቃብር፣ ኤልያስ ከቤሄረ ሄዋንና ሶስቱ ሐዋርያት የተገናኙበት (ማር.9፣1) የምህረት አደባባይ ነው፡፡ ስለዚህ የዚህ ተረክ ተግባር ለመልካአ ምድር አፈጣጠር ምክንያት ምላሽ የሚሰጥ ነው፡፡ ነገር ግን ከዚያም በላይ የሆነ ትርጎማ ልናወጣለት የምንችለው ነው፡፡ እነሱ ሸሽተውበት ለህይወት የበቁባቸው የዛሬዎቹ ገዳምና አድባራት አሻራ ያረፉባቸው ደስያት ቀድሞ ሌላ ተምሳሌት የሚመዘዝላቸው ተራራዎች ነጸብራቅ ናቸውና፡፡

### 4.1.4. የቦታውን ክብር ከፍ የሚያደርጉ ተረኮች

ከደስያቱ የተሰበሰቡት ተረኮች ተግባር ተደርገው ሊነሱ ከሚችሉት ውስጥ የቦታውን ክብር ከፍ የማድረግ ጠቀሜታ ሊመዘዝ ይችላል፡፡ ክብርን በተመለከተ እስከ አሁን ከታሪክ፣ ከጥናታዊነትና ከቅድስና ጋር በተያያዘ ሲነሱ የነበሩት የተረኮቹ ተግባራት በሌላ እይታ የቦታውን ክብርም የሚናገሩ ሆነው ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ የስፍራውን ክብር ከፍ ከሚያደርጉት ተረኮች መካከል አሁንም ድረስ እግዚአብሔር የደሴቱ ነዋሪዎች ሲያጠፉ በድንቅ ተአምራት እንደሚያስተምራቸው የሚያሳዩ ተረኮች ይጠቀሳሉ፡፡ በደብረ ሲና ደብር የተፈጸመ ተብሎ በቀሲስ ተስፋዬ ነቢ የተተረከልኝ በቀዳሚነት ሊነሳ ይችላል፡፡

> በ1960 ዓ.ም አካባቢ ላይ የቤተክርስቲያኑን ነገር ሕዝቡ ዘንግቶት ነበር፡፡ ክዳኑ ሳር በመሆኑ ያፈሳል፡፡ የተለያዩ ንዋየ ቅድሳት እየተበላሹ ነው፡፡ ታዲያ እግዚአብሔር ይቆጣል፡፡ የቁጣውም መገለጫ ከሳማይ እሳት መጥቶ የቤተ ክርስቲያኑን የሳር ክዳኑን ብቻ በልቶ (አቃጥሎ) ተመለሰ፡፡ በዚህን ጊዜ ሕዝቡ እግዚአብሔር እንደ ተቆጣቸው አውቀው እንደ ገና በአዲስ መልኩ በቆርቆሮ ቤቱን ሰርቶታል (ቃለመጠይቅ፣ በቀን 09/08/05 ዓ.ም)፡፡

ከዚህ ትረካ እንደምንገነዘበው የደብረ ሲና ደሴት ነዋሪዎችን ጥፋት ለማሳየት ሌሎች ንዋየ ቅድሳት ሳይነኩ፤ እንዲቀየር የተፈለገው የቤተክርስቲያኑ የሳር ክዳን ብቻ ከሰማይ በመጣ እሳት መበላት የሚተርክ ነው፡፡ ትረካው በቦታው ዛሬም ድረስ ማህበረሰቡ ሲያጠፋ በቀጥታ እንደ ብሉዩ ዘመን እየቀጣ ልጆቹን ከጥፋት የሚመልስ አምላክ አላቸው ብለን ለቦታው የተለየ ዋጋ እንድንሰጠው የሚያደርግ ነው፡፡ በሌላ መልኩ ማህበረሰቡ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ህብረት

በማየት ስፍራውን የሃይማኖቱ ተከታይ እንዲያከብሩ የሚያደርግ ነው። ለውጥ እንዲያደርጉ ሲፈለግ እንኳን ለውጡ የሚመጣው በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ነውና።

ከደስያቱ ገዳምና አድባራት ክብር ጋር በተያያዘ የሚነሳው ሌላው ጉዳይ በተለይ በደብረ ጽዮን የነበረው ገዳማዊ ስርዓት ነው። የደብረ ጽዮን ገዳም ንግስተ ነገስታት ዘውዲቱ የቆረጡለትን ቀላድ መሬትና የገበያ ቀረጥ ከማጣቱ በፊት የንፍሮ ገዳምነት ክብር እንደ ነበረው ይነገራል። በዚህ ጊዜ የተለያዩ የአብነት ትምህርቶች በመኖራቸው ከዚህ ደሴት የሚወጡት ተማሪዎች መጻህፍትን በመጻፍ፣ ሌላ ቦታ ሄደው ሌላ ቤተክርስቲያን የመመስረትና ሌላ ጉባኤ ቤት የመክፈት ስራ ይሰሩ እንደ ነበረ ይነገራል። የደስያቱ ማዕከላዊነት ጎረቤት ሀገሮች ላይ ጽላት በመስጠት ቤተክርስቲያን የማሰራት ብቻ ሳይሆን ቤተክርስቲያን በመትከል ሐዋርያዊ ተልኮን የሚያስፋፉ ደቀ መዛሙርትን እስከ ማፍራት እንደ ደረሱም ይተረካል። ገዳሙ ጥንታዊ ርስቱን ሲያጣ፣ በቦታው የነበሩ ደቀ መዛሙርት ተበትነዋል። ሆኖም ለገዳሙ ክብር ሲባል ከጊዜ በኋላ የገዳሙ የትምህርት ማዕከልነት እንዳይቀር በዝዋይ ከተማ የተከፈተው የዝዋይ ሐመረ ኖህ ካህናት ማስልጠኛ ተቋም ሲጠቀስ እንደሚችል መምሬ ገብረ መስቀል ሂርጳ ይናገራሉ (ቃለመጠይቅ፣ በቀን 02/08/05 ዓ.ም)።

### 4.1.5. የስፍራውን ሉዓላዊነት የሚያስከብሩ ተረኮች

በዝዋይ ደስያት የተሰበሰቡት ተረኮች የስፍራውን ህልውና የማስጠበቅ ተግባርም አላቸው። በደስያቱ ከሚተረኩት ተረኮች መካከል ለዚህ ተግባር ይውላሉ ያልኳቸውን የተወሰኑ ተረኮችን እነሳለሁ። በደብረ አብርሃም ደሴት የደብሩ አስተዳዳሪ የሆኑት መምሬ አስፋውና የደብረ ሲናና ገሊላ ደሴት አድባራት አስተዳዳሪ የሆኑት ቀሲስ ተስፋዬ የተረኩልኝ ናቸው።

> የጣሊያን የወራራ ዘመን ነው አሉ፤ የፖለቲካ እስረኛቸው የሆነ አንድ ስለ ደስያቱ የሚያውቅን ሰው ጣሊያኖቹ ያለውን ሁሉ እንዲነግራቸውና በእሱ በኩል ወደዚህ ደሴት ለመግባት አስበው እንዲነግራቸው ሲጠየቁት ሰውየውም ሚስጢሩን ለመንገር አፉን እንደ ከፈተ ሞተ። ጣሊያኖቹም ይሄንን ሲያዩ በደስያቱ ከባድ ኃይል እንዳለ አስበው ሸሽተው እንደ ተመለሱ ይነገራል (ቃለመጠይቅ፣ መምሬ አስፋው፣ በቀን 6/08/05 ዓ.ም)።

በጣልያን የወረራ ዘመን በርካታ ቤተክርስቲያናት እንደ ወደሙ ታሪክ ያስረዳል። የዛይ ደስያት ገዳምና አድባራት ግን የነካቸው ነገር የለም። ከላይ የቀረበው ለዚህ ግብዓት የሚሆን ተረክ ነው።

እንዲህ አይነት ተረክ ያለፈውን ጊዜ ታሪክ ለመዘገብ የሚያገለግል ቢሆንም በሌላ መንገድ ራስን የማስከበር ሚናም አለው ማለት ይቻላል።

ራስን የማስከበር ሚና ያለባቸው ተረኮች ሕዝቡን የማስተማር ተደራቢ ተግባርም ሊሸከሙ ይችላሉ። ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑን ቀሲስ ተስፋዬ የነገሩኝ ተረክ ነው። "አንድ ዓሣ አጥማጅ ገሊላ ደሴት ውስጥ ዓሣ ለማጥመድ ሄዶ በዚያው በቤተክርስቲያን ውስጥ ሲያልፍ ክብሪት አይቶ እሷን ለማንሳት ዞር ሲል አንገቱ ተጣሞ እንደ ቀረና ከዚያም ለሰዎች ተናግሮና ኢአማኒ ስለ ነበረ ተጠምቆ እንደ ዳነ" ይነገራል። የዚህ ሰውየ ታሪክ ለሰሚው ምን አንድምታ ይኖረዋል ብለን ስንጠይቅ ከቤተክርስቲያን ደጅ ሰባራ ሳንቲም እንኳን ማንሳት ያስቀጣል የሚል ነው። ቤተ አምልኮዎቹ እንዳይዳፈሩ የሚያደርግም ነው። በሌላ መልኩ ተከታይንም የማብዛት ሚና አለው። የደስያቱን ገዳምና አድባራት ሉዓላዊነት ከማስከበር ጋር በተያያዘ የሚነሳው ሌላው ተረክ በአንድ ወቅት ሐይቁ ሰው ማሻገር የጀመረበትን አጋጣሚ ተጠቅመው ጥቃት ለማድረስ ወደ ሐይቁ ገብተው ወዲያው ከሰማይ ዶፍ ወርዶ ወደኋላ እንኳን እንዳይመለሱ ፋታ ሳይሰጣቸው እንዳጠፋቸው የሚተረከው ነው። ስለዚህም ነው ተረኮቹ ሉዓላዊነትን የማስከበር ተግባር አላቸው ሊባል የሚችለው። ይሄንንም የሚያደርጉት ከክፉ የሚጠብቃቸው የልዕለ ተፈጥሮ ረድኤት እንዳለ በማሳየት ነው። የሚቀጥለውን ታሪክ አክሎ ማንሳት ተገቢ ይሆናል።

> የጥምቅት በዓል ዕለት ነው። ገሊላ ካህናተ ሰማይ፣ ደብረ ሲና ማርያምና ቦጨላ ሚካኤል አንድላይ ይወጣሉ። ታዲያ ሕዝቡ ገሊላ ካህናተ ሰማይን ሸኝቶ እስከሚመለስ ድረስ የተወሰነ መንገድ እንድንገፋ ጽላቱን የተሸከሙት አባ ገብረ ህይወት ይነግሩኝና መንቀሳቀስ እንጀምራለን፣ እኔ በወቅቱ በታቦቱ ላይ ጥላ አጥልቼ ነበረ። እንደ ሀምዳ ማርኛ የተባለ ሰው ሞቃት ቢጤ አለበት፣ ሰው ሳይመጣ ታቦቱን ይዛችሁት ለምን ትሄዳላችሁ እያለ ይከተለናል። በመጨረሻ ወደ ጽላቱ አለቅጥ እየተጠጋ አስቸገረን። እንዴት ይሁን እየተጠጋ ነው አልኳቸው። አባ ገብረ ህይወትም ጥላውን ከታቦቱ ላይ አንሳና ጋርድበት ሲሉኝ አንስቼ ከለልኩበት። ካህናተ ሰማይን ሸኝቶ እየተመለሰ ያለው ህዝብ ከኋላ ጮኸ። ለካ ሰውዬው የለበሰው ነጠላ በላው ላይ እየነደደ ነው። ይሄንን ስነግራቸው አባ ጥላውን አንሳ ሲሉኝ አነሳሁ። እንደዚህ ሆኖ ተረፈ እልሃለሁ። ይሄ የደብረ ሲና ማርያም ድንቅ ተአምር ነው (ቃለመጠይቅ፣ በቀን 09/08/05 ዓ.ም)።

በቀሲስ ተስፋዬ የተተረከው ተረክ የተለያዩ ተግባሮች ሊመዘዙለት ይችላሉ። አንዱ ታቦቱ የእግዚአብሔር ሀይል አለበት የሚለውን ሚታዊ ታሪክ የሚያመጣ ነው። ሰውየው ላይ እሳት ያመጣው በታቦቱ ላይ የተጠለለው ጥላ ነውና። ትረካው ቀድሞ በጽላተ ሙሴ ላይ የሚዳፈሩ ሲቀሰፉ እንደ ነበረ የዚያ አምሳይ በሆኑት ላይም አንዳች ነገር የሚያደርግ ይቀስፋል የሚል

ይመስላል። አንድም ስልጣን ከእግዚአብሔር ዘንድ የሆነለትን ካህን በራሱ የፈለገውን ቢያደርግ አትዳፈር በሙሴ ላይ የማይገባ ንግግርን የተናገሩት እህቱና አሮንም በለምጽ ተመተዋለና ከሚለው ጋርም የሚዛመድ ይመስላል። በሌላ መልኩ አትስከር የሚለውን ትዕዛዝም ማስተላለፍ ነው ሊባል ይችላል። ምክንያቱም ሰውየው የተዳፈረው በመጠጣቱ ነውና።

በእነዚህ ተረኮች የአተራረክ ስልት ላይ የሚስተዋለው ሌላው ባህሪ ተራኪዎቹ ራሳቸውን የተረኩ አካል ማድረጋቸው ነው። ከላይ ታቦቱን ለምን ይዛችሁ ሄዳችሁ በሚል ተናግሮ የተቀሰፈው ሰው ታሪክ ላይ ተረኩን የነገሩኝ አባት በወቅቱ ጥላውን ከታቦቱ ላይ አንስተው ወደ ሰውየው ያዞሩት ናቸው። ስለዚህ የተራኪው የታሪክ ባለቤትነት የሚንጸባረቅበት ነው። ተረኮቹ ስህተት የፈጸመውን ሰው ሲያቀርቡ ሰይጣን አሳስቶት በሚል አንድምታ ነው። ለዚህ እንደ ማስረጃ የማነሳው ጽላትን ከደብረ ሲና ማርያም ስለ ሰረቀው ሰውዬ የሚተረከውን ነው።

> በ1989 ዓመተ ምህረት አካባቢ ነው። ለሰውየው ሰይጣን በሰው አምሳል ተገልጦ "በህይወት በደንብ ለመለወጥና የመኪና ባለቤት መሆን አትፈልግም?" ይለዋል። "እፈልጋለሁ ግን በምን መልኩ ብሎ ይጠይቀዋል?" በሰው አምሳል የተገለጠለት ሰይጣንም በደብረ ሲና ገዳም ብዙ ጽላት እንዳለ ይነግረውና ያንን ቢያመጣ ባለመኪና ሁሉ እንደሚያደርገው ቃል ይገባለታል። በወቅቱ የደሴቱ ነዋሪዎችም በቦታ ጥበት የተነሳ ከደሴቱ ተሰደው እዚህ ቦጨሳ ገብተዋል። ዘበኛም አልነበረውም። ያ ሰውም ሌሎች ስድስት ሰዎችን ያስከትልና ከደብረ ሲና ቤተክርስቲያን 7 ጽላቶችን ይሰርቅና በዋሻ ውስጥ ይደብቃል። በሰይጣን ተመስሎ ቃል የገባለት ሰውም ይቀራል። በዚህ መሀከል ግን ቤቱ ውስጥ ትልቅ ተአምር መፈጸም ይጀምራል። ይሄንን አድርጎ ቤቱ በገባበት ዕለት ሚስቱ "ምን ሰርተህ ነው የመጣኸው? አንተ ከቤት ከወጣህ ጀምሮ ወደ ምስራቅ ዞሬ ስተኛ ፊቴን ያቃጥለኛል" ትለዋች፤ እሱም ምንም እንዳል ተፈጠረ ይደብቃታል። ይሄው ህመም ወደ ጡት ማቃጠል ይዞርና ጡቷ ፈንድቶ ሚስቱ ትሞታለች። በሌላ ጊዜም ልጁ በደህና ከልጆች ጋር እየተጫወተ ይሞታል። ከብቶቹን የግጦሽ መሬት ፍለጋ ወደ ሌላ ቦታ ወስዶ ዘመዱ ጋር ያስቀምጣል። በዚህም ድንቅ ስራ ይፈጸማል። የዘመዱ ከብቶች ምንም ሳይነኩ የታቦት ሳራቂው ከብቶች በሙሉ ጅብ ገብቶ እየለየ ይገድልበታል። ይሄ ሁሉ ሲሆን ያጠፋውን ለማንም ለመንገር አልፈለገም። በመጨረሻ አንድ ቀን ጽላቱን የደበቀበት ዋሻ አከባቢ ዛፍ ላይ እንጨት ለመቁረጥ ይወጣና እዛው ላይ መውረድ ያቅተውና ይቀራል። ከዚያ የሀገሩን ሽማግሌዎች አስጠርቶ ከእነዚህ ቁሶች ስር እንደዚህ አድርጊያለሁ። ሂዱና ንገሩልኝ ብሎ የሰራውን ሁሉ ይናገራል። ከዚያ ሽማግሌዎቹ ወደ ካህናቱ ዘንድ በጥዋት ሄደው የሆዳ ጋቢ ያነጥፋሉ። ምን ተፈጸመ ሲባል የሆነውን ይነግሯቸዋል። የዝዋይ የካህናት ማስልጠኛ ውስጥ ካሉት ቀሳውስትን ይወስዱና ጽላቱን ይመልሳሉ። ሰውየው በአርሲ ሌላ ጽላት ከሚሰርቁ ጋርም ይሰራ ነበርና ከአርሲ አካባቢ የተሰረቀው ጽላት ናዝሬት ላይ ይያዛል። እዛ የተያዙት ሰዎች ደግሞ እሱንም ይጠቁሙታል። ከዚያ በህግ ጥላ ስር ይወድቃል፤

አሁን የራሱን ዓለማዊ ፍርድ ተቀብሎ ወጥቷል (ቃለመጠይቅ፣ ቀሲስ ተስፋዬ ነቢ፣ በቀን 09/08/2005 ዓ.ም)።

ከዚህ ተረክ በርከት ያሉ ጉዳዮችን መምዘዝ ይቻላል። የመጀመሪያው ነገር ጽላቶቹ የተለያየ ገቢረ ተአምር እየፈጸሙ መጀመሪያውኑ እንዴት ይማረካሉ? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ለዚህ ጥያቄ ምላሽ የሚሆነው ተራኪው እራሳቸው የተናገሩት ነው። ይኸውም እግዚአብሔር በምዕመናኑ ሲያዝንና አንዳች ገቢረ ተአምርን ለመፈጸም ሲያስብ የሚሉ ምክንያቶች ናቸው። ለዚህም ግብዓት የሚሆነው የቃል ኪዳኑ ታቦት ከእስራኤላውያን ስር ተማርኮ በፍልስጤማውያን እጅ (1ኛሳሙ.4፣1) የገባበት ተረክ ነው። ተረኩ እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ባሳዘኑት ጊዜ በፍልስጤማውያን ድል እንደተነሱና የቃል ኪዳኑ ታቦት እንደ ተማረከ የሚያስረዳ ነው። ፍልስጤማውያንም በተለያየ መቅሰፍት ተቀጥተው በክብር እንደ መለሱት የሚያትት ነው።

በትረካው ውስጥ ከቀረቡት ገጸባህሪያት ንግግርም የምንመዘው ነገር ይኖራል። ይኸውም ጽላት የሰረቀው ሰው ሚስት ባሏ ድርጊቱን ፈጽሞ ወደ ቤቱ የገባ ዕለት የተናገረችው ንግግር ነው። "ለሞኑን ምን ሰርተህ ነው የመጣኸው? ወደ ምስራቅ ዞሬ ስተኛ ፊቴን ያቃጥለኛል" የሚለውን ማየት እንችላለን። በክርስቲያኑ ትውፊት ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ በምስራቅ ይመጣል ተብሎ ይነገራል። ሲመጣ ደግሞ እንደ ቀድሞ በሰው አምሳል ሳይሆን በሚያስፈራ ግርማ፣ ለማስተማር ሳይሆን ለፍርድ ይመጣል የሚል ነገር አለ። ስለዚህም በክርስቲያኑ ትውፊት ሲተኛ ፊትን ወደ ምስራቅ አዙሮ የመተኛት ነገር አለ። ምናልባትም ከእንቅልፍ ሲነሱ ምስራቅን በመሳለም፣ ያቺን የፍርድ ቀን ለማሰብ ሊሆን ይችላል። ታዲያ የሰውየው ሚስት ወደዚህ ዞራ ስትተኛ ፊቷን ያቃጠላት ያ ለፍርድ የሚመጣው አካል በባሏ ሐጢያት እየቀጣት ይሆናል፤ የሚል ግምታዊ ሀሳብም መሰንዘር ያስችላል። ዋናው ነገር ግን ተረኮች አንዳንድ ትውፊታዊ ባህሎችን እንዴት ማንጸባረቅ እንደሚችሉ የምንረዳበት ተረክ መሆኑ ነው። ሌላው ባህል ከሃይማኖት ጋር ተዛንቆ የቀረበበት ሁኔታ እናያለን። ሰውየው እንጨት ላይ ወጥቶ መውረድ ሲያቅተው የአካባቢውን ሽማግሌዎች ጠርቶ ያደረገው ነገር ሄደው ለቄሶች ተናግረው ታቦታቱን እንዲወስዱለት ነው። ሽማግሌዎቹ ለመንገር ሲሄዱ ለሚነገረው አካል ያደረጉት ነገር ይሄ ሆዳ ነው በሚል ጋቢ ደጅ ላይ ማንጠፋቸው ነው። ሆዳ በኦሮሞዎች ባህል ታቡ የሆነ ነገር መፈጸሙን ማመልከት ነው። ስለዚህ በተረኩ ባህላዊ ሰላም የማውረድ ድርጊት እንዴት እንደሚፈጠርም እየተረዳን ነው። በዝዋይ አካባቢ ያሉት ኦሮሞዎች ስለ ሆኑና ድርጊቱም ከደሴቱ ውጪ እየተከናወነ ስለ ሆነ ይሄ

ጉዳይ ሊመጣ ችሏል፡፡ ምናልባትም ተረኩን የነገሩኝ አሁን ከደሴቱ ውጪ እየኖሩ ያሉት የደብረ ሊና ደሴት ተወላጅ የሆኑት ስለ ሆኑ በአዲሱ ባህል ውስጥ እየተዋጡ መሆኑንም የሚያመለክት ነው፡፡ የቋንቋ አጥኚዎች ቋንቋው በኦሮምኛና አማርኛ እየተተካና የዛይኛ ቋንቋ እየሞተ ነው እንደሚሉት ባህሉም በሌላ ባህል እየተተካ ሆኖ ሊሆን ይችላል፡፡ ባህሉ ሃይማኖታዊ ተረክ ውስጥ እንዴት ተዛንቆ እንደሚገባም የሚያመለክት ነው፡፡ ወደ ተረኩ ተግባር ስንመለስ ግን ገዳምና አድባራቱን የሚዳፈር፣ ጽላቶቹን ለመስረቅ የሚያስብ ቢኖር እንደነዚህ ሰዎች ይሆናል፣ የሚል ማስፈራሪያም ያለበት ይመስላል፡፡ ተረኩ ላይ የመጣ አዲስ ለውጥ ደግሞ ቅጣቱ በልዕለ ተፈጥሮ ብቻ ሳይሆን ከዓለማዊ ህግም እንደማያመልጥ የሚነግር ነው፡፡ ምክንያቱም ጽላት ዘራፊው አካል የሆነው እዚህ ያሉትን ጽላቶች ሲያስረክብ፣ ከሌላ ቦታ የተሰረቀው ላይ እጁ በመኖሩና ያ ጽላት ናዝሬት ላይ ሲያዝ አብረው ታቦታቱን ሲያሸሹ የነበሩት ስለ ተያዙ ተጠቂም እሱም አብሮ እስር ቤት እንደገባ ያሳያልና፡፡

## 4.2. በዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራት የተገኙ ቁሳዊ ባህሎች ትንተና

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ስርዓት መሰረት ትውፊት በሁለት ዓይነት የሚታይ ነው፡፡ አንደኛው የሚዳሰሱ የሚባሉት፡- መጻህፍት፣ አልባሳት፣ ገዳማት፣ አድባራት ወዘተ. የሚጠቀሱበት ሲሆን ሁለተኛው የማይዳሰሱት (የሚታዩና የሚሰሙት) ደግሞ ባህሉ፣ ንግግሩ፣ ሥርዓቱና ልማዱ ከአባቶቹ እያየና እየሰማ የሚቀበላቸው ናቸው (ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤልና ቀሲስ ጌታቸው፣37-38)፡፡ የማይዳሰሱ የሚባሉትን በተረክ ክፍል ያነሳሁት ነው፡፡ የሚዳሰሱ የተባሉት ደግሞ በዚህ ክፍል የሚነሱት ቁሳዊ ባህሎች ናቸው፡፡ ቁሳዊ ባህሎች ከፍተኛ ዕሴት ያላቸው የተፈጥሮ ስጦታና የሰዎች የፈጠራ ውጤት ስለ ሆኑ በርካታ ባሕላዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች ይኖራቸዋል፡፡ ይሄንንም ለማሳየት ይቻል ዘንድ አገልግሎታቸውን ምክንያት በማድረግ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ ይህም ሃይማኖታዊ አስተምሮን ለማቆየትና ለማጽናት የሚያገለግሉና ለስርዓተ አምልኮ መፈጸሚያ የሚውሉ በተባሉ ሁለት ክፍሎች ነው፡፡

### 4.2.1. ሃይማኖታዊ አስተምህሮን ለማቆየትና ለማጽናት የሚያገለግሉ ቁሶች

በዝዋይ ደስያት ከሚገኙ ቅርሶች አብዛኞቹ ከአያያዝ ጉድለት የተነሳ በዝናብ፣ በብልና በምስጥ ጉዳት ደርሶባቸው መጥፋታቸውን ቃለመጠይቅ ያደረግሁላቸው የደስያቱ ነዋሪዎች

ገልጸውልኛል። ሆኖም ለማስረጃ የተረፉት ጥቂት ቅርሶች የደስያቱን ታሪካዊነትና ጥንታዊነት የሚያመለክቱ ናቸው። ከእነዚህ መካከል በቀዳሚነት የሚጠቀሱት የብራና መጻህፍቱ ናቸው። ብራና[28] ከተለያዩ የቤት እንስሳት ማለትም ከፈረስ፣ ከበግና የፍየል ቆዳ አስፈላጊው ዝግጅት ተደርጎበት እንደ ወረቀት ለመጻፊያነት የሚያገለግል ሰሌዳ ነው። ከቆዳዎቹ በጣም ተፈላጊው የፍየል ቆዳም እንደ ሆነ ይነገራል። ለሙያው መተዋወቅ የ9ኙ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ መምጣትም እንደ ምክንያትነት ይጠቀሳል። መጻህፍቱ ሃይማኖቱን ለመስተማርና የእምነቱን ስርዓት ለማጽናት የሚያገለግሉ ናቸው። በዝዋይ ደስያትም ጥንታዊ የብራና መጻህፍት እንዳሉ ይነገራል። በዚህ ዙሪያ ያነጋገርኳቸው የደብረ ጽዮን አገልጋይና የሙዚየሙ አስጎብኚ የሆኑት መምሬ መልአኩ ገብረ ማርያም የሚከተለውን ብለዋል።

> እነዚህን መጻህፍት እንደምታየቸው አባቶቻችን አክሱማውያን በዮዲት ጉዲት ዘመነ መንግስት ዮዲት ቤተክርስቲያን ታቃጥል ስለ ነበረ ከዚያ ቃጠሎ ለማትረፍ ሲሉ ይዘዋቸው የመጡት ናቸው። ከ40 ዓመት በኋላ ታቦተ ጽዮንን ይዘው ሲመለሱ ከቅርሱም ከሕዝቡም እዚህ ተከፍሎ ቀረ። ገዳሙ ተራራው ላይ በነበረት ጊዜ እነዚህ ቅርሶች በአንድ ሳጥን ተቆልፎባቸው ይኖሩ ነበረ። ካህናቱ በእረጅና ሲገቱ፣ ተተኪ ጠፋ። የሀገር ሽማግሌዎቹም ከውጪው በገል አጥነው መሄድ እንጂ ውስጡን ከፍተው ስለማያዩ ሳር ቤቱ እያፈሰሰባቸውና ምስጥ እየበላቸው ብዙዎች ተበላሽተዋል። የተረፉትና የተወሰነ ጉዳት የደረሰባቸው በአጼ ሀይለ ስለሴ ጊዜ ተወስደው እንደ ገና ተጠርዘው ተመልሰዋል። እንግዲህ ቅርሶቹ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሲቆጠር 1165 ዓመት ዕድሜ ያላቸው ናቸው። አሁን በሙዚየሙ ውስጥ ከሚገኙት ቅዱሳት መጻህፍት ከ30 በላይ የሚሆኑት ጥንታዊ የብራና መጻህፍት ናቸው (ቃለመጠይቅ፣ በቀን 01/08/05 ዓ.ም)።

ከላይ ከቀረበው ንግግር የምንረዳው ነገር ከ9ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ በርካታ ጥንታዊ የብራና መጻህፍት ወደ ዝዋይ ደስያት እንደ ገቡና አሁንም የተወሰኑት ለታሪክ ምስክርነት እንደሚገኙ ነው። ለዚህ ደግሞ በደብረ ጽዮን ሙዚየም የሚገኘውን ብቻ መመልከቱ በቂ ነው።

---

[28] ብራና "Parchment" የሚለውን ቃል የሚወክል፣ የጥንት ስልጣኔ የሆነና ቀደምት ምስራቃውያን እንደ ጀመሩት የሚነገር ነው። በኢትዮጵያም መቼ እንደ ተጀመረ ባይታወቅም ከእነዚህ ሀገራት ጋር በነበራት የባህልና የንግድ ግንኙነት ሳይገባ እንዳልቀረ ይገመታል (የታምራት ኃይሉ ጥናት፣12-18)። በሌላ በኩል ሊቀ ጉባኤ ፈቃደ ስላሴ ተፈራና ስርግው ሀብለስላሴን ዋቢ በማድረግ የሰፈረው ጽሁፍ እንደሚለው በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተጻፈ ገድለ ሐዋርያት በኢትዮጵያ ብሄራዊ ሙዝየም በመለያ ቁጥር 058 ተመዝግቦ ያለ ሲሆን በብሔራዊ ቤተመጻህፍትና ቤተመዛግብት ደግሞ በ14ኛው ክፍለ ዘመን የተጻፈ አንድ የሐይቅ አርባዕቱ ወንጌል መኖሩ ተረጋግጧል። ከዚህ ተነስቶ ግን ከ13ኛው ክፍለ ዘመን በፊት አልነበሩም ብሎ መጻፍ አዳጋች ነው። ምክንያቱም ከ6ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ወደ ግዕዝ ቋንቋ የተተረጎሙትን መጻህፍት በድንጋይ ላይ መጻፍ ይቸግራልና። ምናልባት ከዚያ በፊት የተጻፉት ብርቅና ድንቅዬ መጻህፍት በአያያዝ ጉድለት አልያም በዮዲትና ግራኝ የወረራ ዘመን ጠፍተው ሊሆን ይችላል (መጣጥፍ፣ በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን ነሐሴ 2002 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ)።



ፎቶ 1. በሙዚየም ውስጥ ከሚገኙት ቅርሶች ሰፊውን ቦታ ይዘው የምናየው የብራና መጻህፍቱ ናቸው።

በዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራት ከሚገኙት የብራና መጻህፍት ስማቸው በተደጋጋሚ ሲጠቀስ የሚሰማው መጽሐፈ ሄኖክና ገድለ ቅዱሳን የተባሉት መጻሕፍት ናቸው። መጽሐፈ ሄኖክ የተደረሰው በዘመነ አበው ሲሆን ሥነ ጽሑፍም የተጀመረው የዚህ መጽሐፍ ደራሲ በሆነው ሄኖክ እንደሆነ የቤተክርስቲያኑ ሊቃውንት ያምናሉ። ይዘቱም ስለ ዓዳምና ሄዋን ዕጸ በለስ መብላት፣ ስለ ቃዔል ልጆች፣ ስለ ኖህ---ወዘተረፈ የሚተርክ ነው። መጽሐፈ ሄኖክ[29] በዓለም ላይ ጠፍቶ በኢትዮጵያ የተገኘና ኢትዮጵያም ለዓለም ያበረከተችው እንደ ሆነ ይተረካል። ይህም የሆነው ደግሞ ከዝዋይ ደስያት ተገኝቶ እንደሆነ የቅርስ አሰባሳቢዎቹ መምሬ መልአኩ ይነገራሉ።

ገድለ ቅዱሳን ደግሞ በአጼ ዳዊት ዘመነ መንግስት እንደተጻፈ የሚነገርለት ሲሆን የ19 ቅዱሳንን ታሪክ ከነትውልድ ስፍራቸው፣ ገዳማቸውና ተጋድሏቸው ከትቦ የያዘ ነው። በታሪካዊ መጻህፍነቱ ሶስት ጊዜ ለጉብኝት ውጪ ደርሶ የተመለሰ ነው ይባላል። በቀዳማዊ አፄ ሐይለ ስላሴ ዘመን ለንደን ሄዶ በአፍሪካ ደረጃ ኢትዮጵያ የታሪክ ሀገር ናት በሚል የወርቅ ሜዳሊያ[30] ማስገኘት የቻለ እንደሆነም መምሬ መልአኩ ይናገራሉ። ገድሉ በቅዱሳን ስዕልና በተለያየ ሀረግ

---

[29] ለረጅም ዘመናት በዓለም ላይ ጠፍቶ በኢትዮጵያ ብቻ የተገኘ ሲሆን ጀምስ ብሩስ የተበላው እስኮትላንዳዊ አሳሽ የአባይን ወንዝ መነሻ ፍለጋ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ሲመለስ ወደ አውሮፓ ስለ ወሰደው ሌሎች አገሮችም አባዝተው ሊጠቀሙበት ችለዋል። (የብራና መጻህፍት ካታሎግ (ቅጽ ፪) ግንቦት 2002 የቅርስና ጥበቃ ባለስልጣን፣ አዲስ አበባ)።

[30] This book of hagiography has won prize of Gold in the black of nations Art Expat at Lagos, in 1972 (Zelalem thesis ).

ያሸበረቀ ነው። የአንዱን ቅዱስ ታሪክ ሲጀምር የተለያየ ሀረግ አለው። ሀረጉን ቀድሞ የቅዱሳኑ ስዕላዊ መግለጫ አለ። ለምሳሌ የአባ ማርቆስ ገድል ሲጀምር "እመ እስራ ወተስኡ ለሰኔ አባ ማርቆስ ዘደብረ ቶርማቅ" የሚል ጽሑፍ በሀረጎቹ መካከል ይነበባል። በመደምደሚያ ክፍሉ የተጻፈበትን ዘመን በመጥቀስ ገድሉን ያነበበ፣ የጻፈው፣ ያስነበበው በረከት እንደሚያገኝ ይገልጻል። ይኸውም "ለዘ አፅሐፎ ለዝንቱ መጽሐፍ ዳዊት ንጉሥ ይጽኀፍ ስሞ እግዚአብሔር ውስተ መጽሐፍ ሕይወት ወለዘፀሐፎ፣ ወለዘአንበቦ፣ ወለዘተረጎሞ፣ ወለዘሰማቃሎ ቃላቲሁ ሀቡረ ይምህረነ፣ ይምህሮሙ እግዚአብሔር በመንግሥተ ሰማያት እስከ ለዓለም ዓለም አሜን"። የሚለው ነው። ይህም የገድላትን የአጻጻፍ ይትባህል የሚያሳይ ይመስላል።

ከዝዋይ ደሴት ጋር በተያያዘ የሚጠቀሱት ቅዱሳት መጻህፍት ከላይ የቀረቡት ብቻ አይደሉም። ለንጉስ ልብነ ድንግል መልአኩ ራጉኤል ተገልጾ ወደ ፊት ኢትዮጵያን በሰላም የሚገዛ ምኒሊክ የሚባል ንጉሥ ይነሳል፣ መቀመጫውንም እንጦጦ ያደርጋል፣ በዚያም ስፍራ የድንግል ማርያምንና የመልአኩ ራጉኤልን ቤተክርስቲያን ያሰራል የሚለው የትንቢት ጽሑፍም በዚህ ይገኝ እንደ ነበረ ይጠቀሳል። ይሄንን ጉዳይ ጸሐፊ ትዕዛዝ ገብረ ስላሴም በመጻፋቸው ጽፈውታል።[31] ስለ ኢትዮጵያ የጥንት ግዛትና የንጉሥ ካሌብን ታሪክ የሚያትተው ገድለ ካሌብና ደብዳቤዎቹ በደብረ ጽዮን ገዳም ይገኛሉ።

> ስለ ኢትዮጵያ የጥንት ግዛቶችና ድንበር የሚዘረዝረው፣ በ525 ዓ.ም የናግራን ክርስቲያኖችን ሲያድን ሲዘምት በታቦተ ጽዮን ፊት ተስሎ እንደ ዘመተና ድል አድርጎ ሲመለስ መንግሥቱን ለልጁ አስረክቦ ወደ ገዳም ገብቶ በምናኔ ስለ ኖረው ገናናው የካሌብ ንጉሥ ታሪክ የሚያትተው ገድለ ካሌብና ንጉሡ ከውጪ መንግስታት ጋር የተጻጻፋቸው ደብዳቤዎችም በዚህ በደብረ ጽዮን ሙዚያም ይገኛሉ (ቃለመጠይቅ፣ መርጌታ ስምረ ግደይ፣ በቀን 10/08/05 ዓ.ም)።

በደሴቱ የሚጠቀሱት መጻህፍት በአብዛኛው በሌላ ስፍራ ጠፍተው የነበሩ ናቸው። ከመጽሐፈ ሄኖክ በተጨማሪም መጽሐፈ ኢየሱስ ክርስቶስ የፀጋ ልጅ (ሦስት ልደት) የተባለው ታሪካዊ መጽሐፍ የተገኘውም በዚሁ በዝዋይ ደሴት ነው።

---

[31] ገብረ ስላሴ፣ ገጽ 97

መጽሐፈ ኢየሱስ ክርስቶስ የፀጋ ልጅ በቦሩ ሜዳ[32] የተደረገውን የሃይማኖት ክርክር ዘግቦ የያዘ መጽሐፍ ነው። ክርስቶስ በተዋህዶ የባሕርይ ልጅ የባሕርይ አምላክ እንደ ሆነ የሚስረዳ ነው። ይህ መጽሐፍ ተፈልጎ የተገኘው በዚህ ገዳም ነው። በወቅቱ በዚህ መጽሐፍ መገኘት ጳጳሱ አቡነ ማቴዎስና እቴጌ ጣይቱ እጅግ በጣም እንደ ተደሰቱ ይነገራል። ምክንያቱም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ለዘመናት በሦስት ልደትና ሁለት ልደት እምነት ተከታዮች ፉክክር ትታመስ ነበረና (ቃለመጠይቅ፣ መምሬ መልአኩ ገብረ ማርያም፣ በቀን 01/08/05 ዓ.ም)።

የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ የገድል መጽሐፍ ከሌሎች ገዳማት በመጥፋቱ በምንጭነት ያገለገለው እናት መጽሐፍ የተገኘው ከእነዚሁ ደስያት እንደ ሆነም ይነገራል።[33] ሆኖም ዛሬ ገድሉ ከአያያዝ ጉድለት ከተበላሹት ወገን የተደመረ ነው።

የብራና መጻህፍቱ ለመንፈሳዊ አገለግሎት የተዘጋጁ ቢሆኑም አሰራራቸው በባህላዊ መንገድ ሀገረሰባዊ እውቀት የፈሰሰባቸው ስለ ሆኑ የፎክሎር የትኩረት አቅጣጫ ናቸው። ብራና መጻህፍቱን በሚመለከት ገለጻ ያደረጉልኝ መምሬ መልአኩ ከነገሩኝ እንደ ተረዳሁት ከእንሰሳቱ የሚገፈፈው ቆዳ ለጽሕፈት እስከሚዘጋጅ ድረስ የሚያልፍበት ሂደት አለው። የስጋው ቅሪት እንዲለቅ መወጠሩ፤ ጸሐይ ካለበት እንዲቆይ መደረጉ፣ በኋላ በመጽሐፉያው መጠን እየተለካ ተቆርጦ በሲር ታስሮ መጠረዙ፤ መስመሮቹ ሹል በሆነ መርፌ ተሰምሮ ለጽህፈት መዘጋጀቱ ሁሉ የሚያሳየን የስራውን የባህላዊ የአሰራር ጥበብ ነው። የቀለም ዝግጁቱም ሆነ የብዕሩ ራሱን የቻለ የአሰራር ስርዓት አለው። ከዚህ የምንረዳው ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ባልነበረበት፣ የጽሑፍ ጥበብ ባልዳበረበት ወቅት በሀገራችን የነበረው የጽህፈት ቢሂል በትውፊታዊ ጥበብ የሚዘጋጅ ሀገረሰባዊ እውቀትና ባህላዊ እሴትነት የሚንጸባረቅበት ሙያ እንደ ሆነ ነው።

የቁሶቹ ጥበባዊነት ይታያል ሲባልም በሀገረሳበዊ መንገድ ተኪዶ የመጣ ውጤት ሲሆን ነው። ሀገረሰባዊ ለማለት ስያሜው፣ አሰራሩ፣ የማህበረሰቡ የጥበብ ውጤት፣ የመስሪያ እቃው ባህላዊ መሆን፣ የማህበረሰቡ እውቀትና ክህሎት የፈሰሰበት መሆኑ ይታያል። የብራና መጻህፍቱም በዚህ ሁኔታ ውስጥ የሚያልፉ ናቸው። አንድ የብራና መጽሐፍ ላይ የቁም ጸሐፊው ሲጽፍ የሚታዩ ሂደቶችም አሉ። እነዚህም የማውጫ ሰንጠረዥ፣ ምዕራፍና ቁጥር መለያ፣ ውበታዊ

---

[32] በ19ኛው መቶ ዘመን ወሎ ክፍለ ሀገር ቦሩ ሜዳ በተደረገው ጉባኤ "ሦስት ልደት" የሚለውን የተሳሳተ እምነት ያስተማሩ የነበሩ ካህናት ተወግዘዋል (ሉሌ፣ 134)።

[33] ማህበረ ቅዱሳን ዘጋቢ ምስል ወድምጽ

መስህብነት ያላቸው ሀረጋትና ስዕላዊ መግለጫዎች ናቸው፡፡ ስዕላትና ሀረጋት የቀረበውን ታሪክ ለማጎላትና ምስል ለመፍጠር የሚቀርቡ ናቸው፡፡



ፎቶ 2 ከደብረ ሲና ማርያም ከተገኙ ሁለት የአርባዕቱ ወንጌል የተወሰዱ ስዕሎች

የሰው ልጅ የረቀቀ አስተሳሰቡንም ሆነ የጠለቀ ስሜቱን ከሚገልጽባቸው መንገዶች መካከል አካላዊና እንደበታዊ ቅላጼን ተከትሎ የሚመጣው የካበተ እውቀት የሚያስፈልገው ስዕል ነው፡፡ ምክንያቱም ስዕል የሰውን ልጅ ህሊናዊ ሀሳብና ቁሳዊ ባህል አበልጽጎ የሚያሳይ የማንነት መገለጫ ነው፡፡ ስዕል በመንፈሳዊው ህይወት ለጸሎት፣ ለስግደት፣ ለአስተብርኮ፣ ወንጌልን ለማስተማር፣ ለስርዓት አምልኮ መፈጸሚያ ያገለግላል፡፡ የፎክሎር ጥናት የትኩረት አቅጣጫ የሚያደርጋቸው ደግሞ ከአገልግሎታቸው ባሻገር በስዕላቱ ላይ የሚታየው የአሳሳል ዘይቤ ነው፡፡ ይኸውም የአሳሳል ጥበቡ ጥንታዊ መሆን፣ ታሪክ ወይም ገላጭ ድርጊቶች ላይ ማተኮር፣ የቀለም ምርጫና ትርጉሙ ምስጢር አዘል መሆን፣ አካባቢያዊ ቁሶችን መጠቀምና የቀለም ምርጫ ሳቢነት በብራናዎቹ ሥዕላትና ሐረጋት ላይ የሚታይ ነው፡፡ ስዕል ባህላዊ የእጅ ስራዎች ላይ ይሳላል ከሚባሉት መካከል ማለትም ሸክላ፣ ብረት፣ ድንጋይ፣ ቆዳ፣ ልብስ ወዘተ. ውስጥ የብራና ስዕልም የቆዳ ላይ በመሆኑ ይጠቀሳል፡፡ ጥንታዊያኑ መጻህፍት ገበታቸው እንጨትና በቆዳ ላይ የሚሳሉ ናቸው፡፡ የማውጫ ገጽ፣ መግቢያ፣ ዋና ክፍልና ራሳቸውን የቻሉ መደምደሚያ ሀሳብ የያዙ ናቸው፡፡ ይሄ ደግሞ ዘመናዊ ጽሑፍ ባልተስፋፋበት ጊዜ በኢትዮጵያ የነበረውን የጽሑፍ ይትበሃል የሚያሳይ ነው፡፡

ምራፍና ቁጥርን ለመለየት የሚጠቀሙባቸው የራሳቸው መንገድ አላቸው፡፡ በተለያዩ የጭረት አይነት ማሳየት ነው፡፡ የቅዱሳኑ ስዕል ሃይማኖታዊ አለባበስ የለበሱ፣ መስቀል የያዙ ናቸው፡፡

ይሄ ደግሞ የሃይማኖቱን አስተምሮ የሚያመልክትና የመንፈሳዊ እሴቱ ነጸብራቅ ነው። በጥንት ዘመን የሚዘጋጁት የቅዱሳን ስዕላት ድንጋይና እንጨት ጠርበው፣ ቆዳ ፍቀው፣ ከአፈር ቀለም በጥብጠው ነበር። በዚህ ዘመን ግን ቴክኖሎጂ ባመጣው መሳሪያ፣ የዘመኑ ሰዓሊያን በሸራ፣ በቆርቆሮ፣ በክርታስና በመሳሰሉት እየተሳሉ ይቀርባሉ። በውጭ ሀገር የአሳሳል ዘይቤ የወረቀት ስዕሎች ሆነው እናገኛለን። የኛዎቹ የጥንት ስዕላት ግን መሳያ ብራናው፣ ማስዋቢያ ቀለሙ፣ መሳያ ሸንበቆው ሁሉ በሀገረሰባዊ እውቀትና ቁሳቁስ የሚዘጋጅ ነው። ፎክሎራዊ የሚያሰኛቸውም ይሄው ነው።



ፎቶ 3 የማውጫ ሰንጠረዥ፣ ምዕራፍና ቁጥር መለያና የሀረግ[34] አጣጣል ማሳያ

ሐረጋት በብራና መጻህፍት ውስጥ በተለያዩ ቅርጽና መጠን ሊሳሉ ይችላሉ። በመክፈቻ ላይ የሚሳሉት በብዛት የሚከሰቱ፣ እንደ ምዕራፍ መክፈቻ የሚያገለግሉና ሲነበቡ ውበት እንዲኖራቸው በሚል በተለያየ ቅርጽ የሚቀርቡ ናቸው። አብዛኛዎቹ ጉንጉን አበቦች ከመላእክት ስዕል ጋር ይሳላሉ። አበባ በተለያዩ ባህል የራሱ አንድምታ እንደ አበባው ቀለም ቢኖረውም ዋና ውክልናው የደስታ መገለጫ ነው። ወንጌል ልብን የሚያስደስት የሕይወት ቃል የሚነገርበትና የመስራች ስለ ሆነ በወንጌላቱ ላይ በሀረግ መልክ የምናገኘው አበባም ያንን የደስታ መግለጫውን ለማጉላት የሚገባ ይመስላል። ሃይማኖታዊ ይዘቱንም የበለጠ ለማጉላት በመስቀል ቅርጽ ሐረጎቹ ሲሰሩ ይስተዋላል። ይህ ሁሉ የሚሆነው ደግሞ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ሳይሆን በባህላዊ የአሳሳል ጥበብ በሀገረሰባዊ እውቀት ነው።

[34] ሐረግ የሚባለው በመጽሐፍ አርዕስት አንዳንድ ጊዜም በሐውልቱና በግሌቱ እንዲሁም በምስማኩ ላይ መጽሐፍ ሲጀመር በልዩ ልዩ ቀለም ተጊጦና ተውቦ የሚታየው ዝምዝም ስዕል ነው (አበባው ይግዛው፣55)።

የቀለሙ አቀባብም ራሱን የቻለ አንድምታዊ ፍቺ ይዞ የሚመጣ ነው። ቀይ ቀለምን የቅዱስነት መገለጫ አድርጎ መውሰድ ስላለ ሲቀመም ንጥረ ነገሮቹን ቀይ አበባና ቀይ አፈርን መጠቀም አለ። ጥቅም ላይ ሲውልም የእግዚአብሔርን፣ የክርስቶስን፣ የማርያምን፣ የቅዱሳንን እና የሰማዕታትን ስም ብቻ ለመጻፍ ሲያገለግል ይስተዋላል። ቀይ የደም መልክን የያዘ ስለ ሆነ የኢየሱስ ክርስቶስን ቤዛነት ለማስታወስ ሲባል የሚደረግም ሊሆን ይችላል። እስከ አሁን በዝዋይ ደሴት ስላሉት የብራና መጻህፍት ያነሳሁት ከተለያዩ ቦታ በስደት የገቡትን ብቻ መሰረት በመድረግ ሳይሆን በደስያቱም የብራና መጻህፍት ይዘጋጁ ስለ ነበረ ነው። በአሁኑ ሰዓት በደሴቱ የብራና መጻህፍት እየተዘጋጁ ባይሆንም ቀድሞ ግን ይዘጋጁ እንደ ነበረ ይነገራል። ለዚህም እንደ ማስረጃ መቅረብ ከሚችሉት ነገሮች መካከል የመጀመሪያው በመምሬ መልአኩ የተነገረኝ "ተፈጸመ ቀለመወርቅ በወርሃ መጋቢት ጸሐፊሁ ገብረ ኪዳን ወምስለ አቡሁ በሀገረ ዝዋይ።" የሚል ሀሳብ የያዘው የብራና ዳዊት ነው። በደብረ ጽዮን ደሴት የመምህር ገብረ ማርያም ደቀመዝሙር የነበሩት ገብረ ኪዳን ዳዊቱን በዚያው በዝዋይ እንዳዘጋጁት ይናገራል። ከአምስቱ ደሴት በየትኛው እንደ ሆነ ለይቶ ባያስቀምጥም። በዚህ የብራና ዳዊት ላይ አንድ ነገር ማንሳት እንችላለን። ይኸውም በብራና መጻህፍት ላይ ስም የመጻፍ ባህል መጀመር ነው። የጥንቶቹ የብራና መጻህፍት ላይ ይሄ ነገር አይስተዋልም። ይሄ የሚሆነው ደግሞ ውዳሴ ከንቱን ከመፍራት የተነሳ ነው። የጻሐፊውንና የተጻፈበት ቦታ ማግኘት ግን ዘመኑንም ለመገመት የሚያስችል ስለ ሆነ ጠቃሚ ነው። ሌላው በዝዋይ ደስያት ውስጥ ብራና መጻህፍት ይዘጋጁ እንደ ነበረ ለማስረጃነት የሚጠቀሰው በደብረ ሲና የተገኘ አርባዕቱ ወንጌል ነው። ወንጌሉ በደብረ ሲና ደሴት መጻፉን በግልጽ የሚጠቅስ ነው። ለዚህም ከብራና መጽሐፉ ያነሳሁትን የሚከተለውን ፎቶ መመልከት ይቻላል።





ፎቶ 4 በደብረ ሲና ደሴት መጻፉን የሚያሳይ የአርባዕቱ ወንጌል ክፍል

የደብረ ጽዮን ሙዚየምን ያስጎበኙኝ መምሬ መልአኩ ገብረ ማርያም እንደሚናገሩት በመምህር ሀይለ ማርያም የኋላው አቡነ ጴጥሮስ የተበረከተው 14ቱ ቅዳሴ ከነምልክቱ የያዘ የብራና መጻህፍም በደብረ ጽዮን ደሴት መገኘት በቃላዊ ተረኩ ለሚቀርበው ግብዓት የሚሆን ነው።

> መምህር ኃይለ ማርያም በ1917 ዓ.ም በዚህ ገዳም አስተዳዳሪ ሆነው መጥተው ነበረ። ማለትም በኋላ አቡነ ጴጥሮስ የሚባሉት በፋሽስት ጣሊያን የተገደሉት አባት ናቸው። አቡነ ጵጥሮስ በዚህ ደሴት እንደ ነበሩ ከሚጠቀሱት ነገሮች አንዱ መቋሚያቸው ነው። ረጅም እንደ ነበሩ በመቋሚያው ብቻ መናገር እንችላለን። ሁለተኛው የቁም ጽሑፍ ችሎታቸው የታየበት የ14ቱ ቅዳሴ ከነምልክቱ የያዘ መጽሐፍ ነው። ይሄ የብራና መጽሐፍም በዚህ ደሴት የተጻፈ ይመስላል። ምክንያቱም መጽሐፉ ውስጥ "ዝንቱ መጽሐፍ ዘመምህር ኃይለ ማርያም ዘወሀባ ለዝዋይ ማርያም እንተ ይእቲ ደብረ ጽዮን በአስርቱ ወበተሰዓቱ ምዕት አስርቱ ወሰባዕቱ አመተ ምህረት ዘሰረቀ ወዘፈሀቀ በስልጣነ ጴጥሮስ ወጳውሎስ ውጉዘ ዘለይኩን" የሚል ቃል እናገኛለንና (ቃለመጠይቅ፣ በቀን 01/08/05 ዓ.ም)።[35]

የብራና መጻህፍቱን በሚመለከት ከላይ ዘርዘር ጉዳዮችን ለማንሳት ሞክሪያለሁ። መጻህፍቱ ሃይማኖታዊ አስተምሮን ለማቆየትና ለማጽናት እንደ ተጻፉም መረዳት አያቅተንም። ከስፍራው ጋር ካላቸው ቁርኝት የተነሳ የዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራትን ጥንታዊነትና የዛይ ማህበረሰብን ታሪካዊነት የሚዘክሩ መሆናቸውንም እንረዳለን። ጥንታዊ የብራና መጻህፍቱ ታሪክን ይዘው ያሉ ስለ ሆነ የቦታውንም ታሪካዊነት ለማሳየት እድል ይኖራቸዋል።

ለታሪካዊነት መገለጫ አንድ ጉዳይ ብቻ ማንሳት በቂ ይመስለኛል። ይኸውም ንግስተ ነገስታት ዘውዲቱ የደብረ ጽዮን ገዳምን ታሪካዊነት ተረድተው ገዳሙን በአዲስ መልኩ በንፍሮ ገዳምነት

---

[35] መምህር ሀይለ ማርያም (አቡነ ጴጥሮስ) ለገዳሙ ያበረከቱት የቅዳሴ መዝገብ ሙሉ በሙሉ በዝዋይ የተጻፈ ነው ብሎ ለመደምደምም የሚከብድ ይመስላል። ምክንያቱም አንደኛ የተጻፈው ቃል ለዝዋይ ደብረ ጽዮን ማበርከታቸውን እንጂ በዚያ ደሴት መጻፋቸውን የሚያመለክት ነገር የለውም። ሁለተኛውና ዋነኛው ነገር ደግሞ መጽሐፉ ላይ ያረፈው ማህተም መምህር ሀይለ ማርያም ዘደብረ መንክራት የሚል ነው። ደብረ መንክራት የሚለው ስም የደብረ ጽዮን ሌላ ስም ነው እንዳንል በቃላዊም ሆነ ጽሁፋዊ ትውፊት ያገኘሁት ነገር የለም። ከዚህ በተለየ የቅዱሱን የህይወት ታሪክ ስፈትሽ ያገኘሁት ደብረ መንክራት በወላይታ ሶዶ የሚገኘው የምሁር ኢየሱስ ገዳም ስም ነው። በሐመር ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ፣ 1996 ዓ.ም፣ 12ኛው ዓመት ቁጥር 2፣ ግንቦት (ሰኔ) ዕትም ገጽ.33 ላይ " 'ዝክረ ቴዎፍሎስ፣ ጴጥሮስ ወሚካኤል' በሚል ርዕስ ስር አቡነ ጴጥሮስ በ1910 ዓ.ም መምህር ኃይለ ማርያም ተብለው በወላይታ ሶዶ በሚገኘው ደብረ መንክራት ምሁር ኢየሱስ ገዳም ተሾሙ። በ1919 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ በመምጣት የመንበረ መንግስት ቅዱስ ማርቆስ መምህርና በቤተ መንግስት የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የንስሃ አባት ሆኑ። የግብጽ ቤተክርስቲያን ከአንድ ሺ ስድስት መቶ ዓመታት በኋላ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በዕውቀት መንፈሳዊ ከእርስዋ ተወልደው በዕቅፏ ውስጥ ባደጉ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት እንድትመራ ፈቃዷን ስትገልጽ ከተመረጡት አባቶች አንዱ በመሆን ግንቦት 18ቀን 1921 ዓ.ም በእስክንድርያው መንበረ ማርቆስ በቤተክርስቲያን መዓረገ ጵጵስናን ተቀበሉ። ከዓመት በኋላም "አቡነ ጴጥሮስ ጳጳስ ዘምሥራቀ ኢትዮጵያ ተላዌ እሡሩ ለአቡነ ኢየሱስ ሞዓ" ተብለው በያኔው መንገዝና ወሎ አገረ ስብከት ተሾሙ፤ ይላል"።

እንደ አደራጁትና መተዳደሪያ እንደ ሰጡት በተረኮቹ ይነገራል። በተመሳሳይ ሁኔታ በብራና መጽሐፍ ተከትቦ ተገኝቷል። ለዚህም በደብረ ጽዮን ሙዚየም ከሚገኙት መጻህፍት በግንዘት መጽሐፍ የመጨረሻ ገጽ ላይ ያሰፈረውን መመልከት ይቻላል።

> ለዝዋይ ማርያም ለገዳሙ መርጃ እንዲሆን ከዛው ከዝዋይ ውስጥ 150 ገባር የሰው ቁጥር፣50 ቀላድ፣ ከባህር ውጪ ደግሞ ከባህሩ ዳር የሚቆመውን የቀዳሚት ገበያ ቀረጥና ዳኝነት ይህንንም ገባሩንም ቀላዱንም፣ ገባያውንም ዳሩ እሳት መሃከሉ ገነት ይሁን ጉልት አድርጌበታለሁ። መስቀል ይዙርበት፣ ጥር 30 ቀን 1913 ዓ.ም ተጽሐፈ ውጉዝ በስልጣነ ጴጥሮስ ወጳውሎስ።[36]

ከዚህ የተነሳ የብራና መጻህፍቱ የጥባባዊ እሴት መግለጫ፣ የመንፈሳዊ እሴት ነጸብራቅ፣ የታሪካዊ ድርጊት ዘጋቢ፣ ባህላዊ ገጽታን ማሳያና የዘመንን መንፈስ መፈተሻ ሆነው ማገልገል እንደሚችሉ እንረዳለን። መጻህፍቱ ከመንፈሳዊነታቸው አንጻር አሁን ያሉበት ሁኔታ ስንመለከት በቅርስነት ከመንብኘት ሌላ በገዳማቱና አድባራቱ ለአምልኮ ስርዓት መፈጸሚያ የሚውሉ አይደሉም። ይሄንን ጉዳይ መምሬ መልአኩ ከሰጡኝ ገለጻ መረዳት እንችላለን። "የቤተ መቅደሱ አገልግሎት በአጼ ሀይለ ስላሴ ዘመን የጽሕፈት መሳሪያ ከአውሮፓ ሲመጣ ከጣናና ከዚህ ከዝዋይ ደሴያት የብራና መጻህፍቱ ተሰብስበው ወደ አማርኛ ተተርጉመው በዘመናዊ መልኩ ተዘጋጅተው የተባዙት ስላሉ አሁን አገልግሎት የሚሰጡት እነዚህ መጻህፍት ናቸው።"

ቁሶች ከአገልግሎት ከፍ ሲሉ በቁሱና በማህበረሰቡ መካከል ያለው ዝምድና በባህሉ እንደሎት እንደ ተገለጸ የማንጸባረቅ ሚና ይኖራቸዋል። አሰራራቸው ከማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ርዕዮት አንጻር ምን ልዩ ሁኔታ እንዳለ የሚያንጸባርቁ ናቸው። የማህበረሰቡን የህይወት ልምድ፣ አመለካከትና ፍላጎትም የሚያሳዩ ናቸው። በደሴያቱ ካየኋቸው ቁሳዊ ባህል መካከል የወንጀለኛ መቅጫ የሆነውን እግረ ሙቅን መመልከት ይቻላል። ምክንያቱም ሃይማኖታዊ አስተምህሮን ለማቆየትና ለማጽናት በመጻህፍቱ ማስተማር ብቻ ሳይሆን ተምሮ አልለወጥ ያለውን በቅጣት እንዲማር ማድረግም ስላለ ማለት ነው። ለዚህ ስራ ከሚያገለግሉ ቁሶች ደግሞ አንዱ እግረ ሙቅ ነው።

---

[36] ለዝንቱ መጽሐፍ ዘወሀበታ በአስርቱ ወበተሰዓቱ ምዕት አስርቱ ወሰለስቱ ዓመተ ምህረት በዘመነ ማቴዎስ ንግስተ ነገስታት ዘውዲቱ ለዝዋይ ማርያም እንተ ይእቲ ማዕከለ ባህር ግርምት ከመይኩና ለሥርየተ ኀጢአት ወመርሐ ለመንግስተ ሰማያት በፀሎተ ለእግዝትነ ማርያም ስዓሊተ ምህረት በኩሉ ጊዜ ወበኩሉ ሰዓት ለዓለም ዓለም አሜን።



ፎቶ 5 የማህበረሰቡ የወንጀለኛ መቅጫ እግረ ሙቅ [37]

እግረ ሙቅ ተመክሮ ከጥፋቱ የማይመለስ ሰው የሚቀጣበት ነው። ስለዚህ የወንጀለኛ መቅጫ እንዲያስረዱኝ ካነጋገርኳቸው መረጃ ሰጪዎቼ መካከል በመምሬ ባንቲሁን ሀብተ ማርያም የተነገረኝ የሚከተለውን ይመስላል።

> ወይዘሮ ተራራ ላይ የሚገኘው የወንጀለኛ መቅጫው ከዲንጋይ የተዘጋጀ ነው። በዚህ ደሴት የአጥቂ ንጉሣዊ አስተዳደር በነበረበት ወቅት ከንጉሱ ጋር የተጣላ፣ ህዝቡን የበደለና ከቤተክርስቲያን ጋር በተያያዘ ችግር የፈጠረ ቂጤ በተባለው የሀገር ሽማግሌዎች ስብሰባ ጥፋተኝነቱ ተመርመሮ ከተረጋገጠ የሚቀጣው በዚያ በዲንጋይ ውስጥ ሁለት እግሮቹን እንዲከት ይደረግና ከሁለት እጆቹ ጋር አንድ ላይ ይታሰራል (ቃለመጠይቅ፣ በቀን በ30/07/05)።

የወንጀለኛ መቅጫው የማህበረሰቡን ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ርዕዮት የሚያንጸባርቅ ነው። ኢኮኖሚያዊ ገጽታው ማህበረሰቡ ለወንጀለኛ መቅጫ ሌላው ዓለም ያዘጋጀውን፣ የሚታመንበትን ነገር ለመፈለግ ሳይደክም በቀላሉ በአካባቢው ተፈጥሮ ከለገሰችው ድንጋይ መቅጫውን ማዘጋጀቱ ነው። የቁሱ ፖለቲካዊ አንድምታ በዋናነት ከንጉሳቸው ጋር የተጋጨ፣ ሕዝቡን የበደለና ቤተ እምነታቸውን ያረከሰ ሰው መቅጫ መሆኑ ነው። ሆኖም ፍርዱ የሚሰጠው በንጉሱ ብቻ ሳይሆን የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንደምንለው አይነት ያሉት የቂጤ ስብሰባ አካል የሆኑ የሀገር ሽማግሌዎች ጉዳዩን አጣርተው ሲፈርዱበት ብቻ የሚከናወን መሆኑ ነው። ይሄ ሂደት ደግሞ የቁሱን ባህላዊ ገጽታ የሚያንጸባርቅ ነው። ባህላዊ

[37] እግረ ሙቅ-እግር ብረት (አማርኛ መዝገበ ቃላት፣367) ከመዝገበ ቃላዊ ፍቺው ተነስተን ለቃሉ አውዳዊ ፍቺ ከሰጠን የእግር ማሰሪያ ካቴና የሚል አንድምታ ሊኖረው ስለሚችል ከድንጋይ የተሰራውን የወንጀለኛ መቅጫ እግረ ሙቅ ቢዬዋለሁ።

ጉዳዮች የሚፈልቁት በማህበራዊ ህይወታቸው ሰዎች ከሚጠቀሙበት ነገር ነው። ማህበረሰቡ በባህላዊ መንገድ ባህሪው እንዲገራ የተፈለገውን ወይፈን በቀንበር እንደሚያቀና ሁሉ ጥፋት ሲፈጽም የተገኘ ዛይም ሕይወቱ እንዲገራ ሲፈለግ በእግረ ሙቁ እንዲቀጣ ይሆናል። በዚህ እልመለስ ያለ ሰው ለእርሻ ያልቀና በሬ ሽያጭ ወይ እርድ እንደሚከተለው ሁሉ በእግረ ሙቁ ተቀጥቶ አልመለስ ያለ ግለሰብም የሚከተለው ወደ ሐይቁ ተወርውሮ መሞት ነው።

የወንጀለኛ መቅጫውን ሃይማኖታዊ ገጽታ ሲታይ አንደኛ ቁሱ አሁንም የሚገኘው ከጥንታዊ ገዳማቸው ስፍራ መሆኑ ነው። ይኸውም በደብረ ጽዮን ገዳም ጥንት ታቦተ ጽዮን አርፋበታለች ከሚባለው ስፍራ ላይ የሚገኝ ነው። በሁለተኛ ደረጃ በገዳማዊ ህይወት ውስጥ በአጋንንት ድል ሆኖ ወደ መጥፎ መንገድ ያመራ መነኩሴ የሚቀጣው በእንደዚህ አይነት መቅጫ እንደሆነ በኢትዮጵያ በተለያዩ ገዳማት የሚስተዋል ነው። የገዳማውያኑ ህግ ምንጭ የሆነው ማር ይሳቅም የሚያዘው ይሄንኑ ነው። ጥፈተኛን የመቅጣት ስርዓት ወደ ሥነ ምግባር ከመመለስና ጥፋትን ከማረም ጎን ለጎን ኀጢአትን ማንጻት ነው።

### 4.2.2. ስርዓተ አምልኮን ለመፈጸም የሚያገለግሉ ቁሶች

ቁሶች ግብራቸውም ስማቸውም ተለውጦ ለመንፈሳዊ አገልግሎት ቢውሉም የሚሰሩበት እቃ፣ አሰራራቸው፣ ህገረሰባዊ መሆናቸው የፎክሎር የትኩረት አቅጣጫ ያደርጋቸዋል። የዝዋይ ገዳምና አድባራት ከብራና መጻህፍቱ በተጨማሪ የተለያዩ ታቦታት ምንጭ፣ ዋሻዎች መገኛ፣ መስቀሎችና ደወሎች እንዲሁም የኦሪት የመሰዊያ ዕቃዎች መገኛ ናቸው። እነዚህ ንዋየ ቅድሳት ራሳቸውን የቻሉ የባህላዊና መንፈሳዊ እሴት መገለጫ ናቸው። የአንድ ሃይማኖታዊ ተቋም ባህላዊ ገጽታ ሲጠና እንደ መስኩ ምሁራን ገለጻ ስያሜውም ሆነ ክፍልፋዩ ከማህበረ ባህሉ ወይም ከሃይማኖቱ መምጣት መቻል አለበት ነው። ስለዚህም በሃይማኖታዊ ፎክሎር ውስጥ ቁሶቹ ለመስራት የሚያልፉበት ሂደት ባህላዊ መሆን የትኩረት አቅጣጫ ቢያደርጋቸውም ለውጡ የሚጀምረው ከስያሜ ነው። በገዳምና አድባራት ውስጥ ያሉ ቁሶች አጠቃላይ መጠሪያ ንዋየ ቅድሳት የሚል ነው። ቁሶቹ መጠሪያውን ለማግኘት የሚያልፉበት ሂደት አለ። በሃይማኖቱ ወደ ቤተክርስቲያን ከገቡ በኋላ በቅበዓ ሜሮን የማክበር ጸሎት ይካሄድና ንዋየ ቅዱሳት የሚል


መጠሪያ ይሰጣቸዋል (ዘፀ.40፤10)::[38] ከዚያ በኋላ ከቅጥሩ ውጪ እንዳይወጡ የተከለከሉ ይሆናሉ። ይሄ ለውጥ እንዲከሰት የሚያደርጉት በቁሶቹ ላይ የሚፈጸሙት ተጨማሪ ስርዓቶች ናቸው።

ንዋይ የሚለው ቃል ከሣር፣ ከእንጨት፣ ከማዕድን፣ ከብረት፣ ከጭቃ፣ ከቁርበት ወዘተ. የሚዘጋጅን ገንዘብ፣ ጥሪት፣ ቅርስ የሚያመለክት ሲሆን ቅድሳት ደግሞ ቅድስና፣ ክብር፣ ንጹህ ፀጋ ያላቸው ለእግዚአብሔር አገልግሎት የተለዩ ማለት ነው (ሚሊዮን፣ 13)። ስለዚህ ንዋየ ቅድሳት ሲባል የተለዩ፣ የተመረጡ፣ የእግዚአብሔር የሆኑ፣ ስርዓተ አምልኮት የሚፈጸምባቸው የቤተክርስቲያን ንብረቶች ማለት ነው። በእነዚህ ቁሶች ላይ የሚነሳው ትልቁ ጥባባዊ ጉዳይ የንዋየ ቅድሳቱ አሰራርና አገልግሎት ተምሳሌታዊ መሆን ነው።

የቁሶቹን አንድምታዊ ትንታኔ ለማቅረብ ከስፍራው መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ መጀመር የተሻለ ይሆናል። በሃይማኖታዊ ተቋም ውስጥ መልክዓ ምድርም ራሱን የቻለ አንድምታ አለው። በዝዋይ ሐይቅ ላይ የዛይ ማህበረሰብ የሃይማኖት ማዕከል የሆኑ አምስት ደሴያት ይገኛሉ። ከቁጥራቸው አንጻር ለሃይማኖቱ መሰረት በሆኑት አምስቱ አዕማደ ምስጢር ሊፈከሩ የሚችሉ ናቸው። "አስቀድሞ እግዚአብሔር መዝሙረኛው ዳዊትን በትንቢት አናግሮ ለእኛ መሸሸጊያ ያስቀመጠው ስፍራ ነው" በሚል እንደሚተርኩት "ከተፈጥሮ አትማሩምን"? የሚል አምላካቸው በምድራዊ አቀማመጡ ምስጢረ ስላሴን፣ ስጋዌን፣ ጥምቀትን፣ ምስጢረ ቁርባንና ትንሳኤ ሙታንን በሕይወታቸው ተርጉመው ከሞት ባሻገር ላለች ህይወት እንዲዘጋጁ በመልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ሊያስተምራቸው ፈልጎ አምስቱን ደሴያት ለስጋዊ ሕይወታቸው መኖሪያ ሰጥቷቸው ይሆን ያስብላልና።

---

[38] በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ለመንፈሳዊ አገልግሎት የሚውሉ ንዋያት ሁሉ የተቀደሱ ናቸው። ምክንያቱም አገልግሎቱ የሚፈጸመው ቅድስና የባህርይ ገንዘቡ ለሆነ ለእግዚአብሔር ነውና። አገልጋዮቹ ቅዱሳን ቦታውም ቅዱስ እንደ ሆነ ሁሉ ንዋያቱም ቅዱሳት ናቸው (ደጀኔ፣ 40)።



ገሊላ ካህናተ ሰማይ ደሴት



ደብረ ጽዮን ደሴት



የደብረ ሲና ማርያም ደሴት



የደብረ አብርሃም ደሴት



የጌቴሴማኒ ደሴት

ፎቶ 6 አምስቱ የዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራት

በምዕራፍ ሶስት እንዳነሳሁት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ስርዓት ሶስት ዓይነት የቤተክርስቲያን ቅርጽ አለ። ቤተ ንጉስ፣ ድርብ ምድርና ጎጆ ቤት ናቸው። በሌላ አነጋገር ሰቀልማ፣ ክብ (ቤተ ንጉስ) እና ፍልፍል (ዋሻ) ይባላሉ። ከዚህ አንጻር የዝዋይ ሐይቅ ገዳምና አድባራት ክብ ናቸው። የደብረ ጽዮን ገዳም ብቻ ወደ አራት ማዕዘን ያዘነብላል። የቤተክርስቲያን ክብነት ምሳሌው ወደ ኋላ የሚወስደን ነው። ለሃዲስ ኪዳን መሰረቱ ብሉይ ኪዳን ነውና ወደ ብሉዩ ትውፊት ስንሄድ የጽላተ ሙሴ ማረፊያ ደብተራ ኦሪት ክብ ናት። በሀዲስ ኪዳንም የመጀመሪያዋ ቤተክርስቲያን የምትባለውና በፊሊጶስዮስ የተሰራችው ክብ እንደ ነበረች የሚገልጹ አሉ። ክብነት የፍጹምነት ምሳሌ እንደ ሆነም ይነገራል። የደብረ ጽዮን ገዳም ሞላላነትም እግዚአብሔር ቤትን እንዲሰራለት የፈቀደለት ሰሎሞን የሰራው ቤተ መቅደስ ምሳሌ ይመስላል። የጉልላታቸው አንድ መሆን የሚያድርባቸው እግዚአብሔርን አንድነት ለማጠየቅ ነው። በዙሪያቸው የሻኩራ መኖር ምሳሌ ቅዱሳን መላዕክት ለሊትና ቀን በቤተክርስቲያን አጸድ ዙሪያ ለመዘመራቸው ምሳሌ ነው።

ቤተክርስቲያን ሲሰራ ሶስት ክፍል እንዲኖረው የሚደረግበትም ምክንያት በሃይማኖቱ አስተምህሮ ሲገለጽ የሲና ተራራን ምሳሌ በማድረግ እንደ ሆነ ነው፡፡ የሲና ተራራ ሶስት ክፍል ሙሴ የወጣባት ጫፍ ክፍል፣ አሮን የወጣባት ግማሽ ክፍልና ሕዝቡ የቆመበት ግርጌው ክፍል እንደ ሆነ ሁሉ የቤተ ክርስቲያን ሶስት ክፍልም ካህናት ብቻ የሚገቡባትና ሥጋና ደሙ የሚፈተትበት ቅድስተ ቅዱሳን (መቅደስ)፣ በንስሐ ራሳቸውን አዘጋጅተው ሥጋና ደሙን የሚቀበሉት የሚቆሙበትና ሌሎች ምዕመናን ሁሉ የሚቆሙበት ቅኔ ማህሌት ነው (ሰሙና ቸሬ፣ 24)፡፡ የበሮቻቸው ሶስት መሆን የገነት ምሳሌ ነው፡፡ ገነትን በሰሜኑ በር አዳም፣ በደቡብ ሔዋን ሲገቡ በምስራቅ በር እግዚአብሔር ይገባበት ነበር፡፡ ምናልባት እነዚህን የቤተ ክርስቲያናትን ምሳሌ ለምን ማንሳት አስፈለገ የሁሉም የሃይማኖቱ አብያተ ክርስቲያናት አስተምህሮ አይደለም ሊባል ይችል ይሆናል፡፡ ምሳሌው የሃይማኖቱ አስተምህሮ ቢሆንም የሀገሪቱ አብዛኛው ክፍል ላይ ያሉ ገዳምና አድባራትን ብንመለከት ከጥንታዊያኑ በስተቀር አዳዲስ የሚሰሩት የተለየ ሁኔታ ይስተዋልባቸዋል፡፡ ምናልባት የፎክሎር የተለዋዋጭነት ባህሪ የወለዳቸው ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ከሃይማኖቱ ስርዓት አንጻር መስቀልኛ ቅርጽ ያላቸው ናቸው የሚል አንድምታ ቢኖርም በአንጻሩ ደግሞ ከስያሜው ጭምር እንደምንሰማው አዲስ የመጣው ቅርጽ ካቴዴራል ይባላል፡፡ ባህሉ የሮማ የካቶሊካዊያን እንደሆነም ይጠቀሳል፡፡ የዝዋይ ደስያት ላይ ግን ከእድሜ ብዛት አርጅተው በአዲስ የተተኩትም አድባራት ቢያንስ ክብነታቸውንና በውስጥ ሶስት ክፍልነታቸውን አላጡም፡፡ ይሄንን የአድባራቱን የጥንታዊነት ቅርጽ ጠብቀው መስራት አስመልክቶ ቃለመጠይቅ ሰጪዎቼ ሲገልጹ "በፊት በሳር የምንሰራው ቤተክርስቲያን ክብ ነው፤ አሁንም ያንን ትውፊታቸውን እንዳያጡ በሚል ነው በዚህ መልክ የምንሰራው" [ቃለመጠይቅ፣ ቀሲስ ተስፋዬ (በቀን 09/08/05 ዓ.ም)፤ መምሬ አስፋው (በቀን 06/08/05 ዓ.ም)] ይላሉ፡፡





ፎቶ 7 ታቦተ ጽዮን አርፋበታለች የሚባለው ቦታና በ2005 ዓ.ም የተመረቀው የደብረ አብርሃም ቤተክርስቲያን

በፎቶ ላይ እንደሚታየው ታቦተ ጽዮን አርፋበታለች ተብሎ የሚነገረው ቦታ በደብረ ጽዮን ተራራ ላይ ከባህር ወለል በላይ 1953 ሜትር ከፍታ ላይ የሚገኝ ነው። ቦታው ላይ በድንጋይ፣ በጭቃና በሳር በተለያየ ጊዜ እየፈረሰ ይሰራ እንደ ነበረ የደሴቱ ነዋሪዎች ይናገራሉ። ሕዝቡ ውኃው ርቆናል በሚል ወደ ሐይቁ አካባቢ ወርዶ ይገኛል። ስፍራው ታቦተ ጽዮን ያረፈችበት ነው ስለሚባል አሁንም ድረስ ተከልሎ ይጠበቃል። በውስጡም የድንግል ማርያም ስዕላዊ መግለጫ አለ። በዘመናዊ የተሰራው የደብረ አብርሃም ቤተክርስቲያን ከጥንት ይትባህል ክብነትን አላጣም። ባህሉ በአሰራር ደረጃ ወደ ቆርቆሮ እንኳን ለመለወጥ ብዙ ጊዜ ፈጅቷበታል። ምክንያቱም የቀድሞው ሕዝቡ ውስጥ የሰረጸውን ለመለወጥ በጣም ከባድ ነበረ። የደብረ አብርሃም ደሴት ነዋሪና የ90 ዓመት የዕድሜ ባለጸጋ የሆኑት ጋሽ ታደሰ አሼ ይሄንን ጉዳይ የገለጹት "ይሄንን ቤተክርስቲያናችንን ወደ ቆርቆሮ የቀየር ነው በብዙ ስቃይ ነው። ምክንያቱም ሕዝቡ ባህላችን ይበላሻል በሚል ስለሚቆጣ ነው (ቃለመጠይቅ፣ በቀን 05/08/05 ዓ.ም)።





ፎቶ 8 ከዝዋይ ደሴት አዱባር ጋር የዛዮች መዋሪያ ቤት ሲነጻጸር

ከላይ የቀረበው የፎቶ መግለጫ ፍጹም ተመሳስሎ አለው በሚል ያቀረብኩት አይደለም፡፡ ሆኖም ማህበረሰቡ ባህላዊውን የቤት አሰራራቸውን ለማስጠበቅ በሚመስል መልኩ የመኖሪያ ቤት አሰራርቸውና ገዳምና አድባራታቸው ተመሳስሎ ይታይበታል፡፡ ምናልባትም በገዳምና አድባራቱ ስፍራ በመኖራቸው ባህሉ ሃይማኖታቸው፣ ሃይማኖታቸውም ባህሉ ሆኖ ሊሆን ይችላል፡፡ በደስያቱ የሚኖሩት ያላቸው ቤትና ወደ ከተማ የተሰደዱት ዛዮች ቤት የተለያየ ነው፡፡ ፎክሎር ይለወጣል እንዲሉ፡፡ የማህበረሰቡ አኗኗር በተቀየረ ቁጥር የሚመጣው ለውጥ ባህላዊም ሃይማኖታዊም መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በደስያቱ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የተሳሉት ስዕሎች ዘመናዊ ቢሆኑም ጥንታዊነትን ለማሳየት በሚመስል መልኩ ኦሪታዊ ታሪክን የሚሰብኩና ከጽላተ ሙሴ ጋር የተገናኙ ታሪኮችን የያዙ ስዕሎች ይበዛሉ፡፡ ከደስያቱ የወጡት ሕዝቦች አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ተስለው የሚገኙት ግን የሀዲስ ኪዳን ተረኮችን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡





ፎቶ 9 በደብረ አየን ገዳምና በቦጨጫ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ ስዕሎች





ፎቶ 10 በደብረ አየን ገዳም የአቡነ በጸሎተ ሚካኤልና ሙሴ ጽላትን ሲረከብ የሚያሳይ ስዕል

በፎቶ 10 ከቀረበው መግለጫ እንደምንረዳው በገዳምና አድባራቱ ውስጥ የሚሳሉት ስዕሎች በተረክ ለሚቀርቡት መረጃዎች ተጨማሪ ግብዓት ሊሆኑ እንደሚችሉ ይታወቃል፡፡ ለዚህም ማሳየ የሚሆነን በተረኮች ክፍል በአጼ ዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግስት ወደ ዝዋይ ደስያት ከተጋዙት ቅዱሳን መካከል አንዱ በጸሎተ ሚካኤል እንደሆኑ ይተረካል፡፡ በደስያቱ ቆይታዬ ወቅት የዚህን ቅዱስ ሰው ስዕል በደብረ ጽዮን ገዳም የውስጥ ግድግዳ ላይ መመልከት ችያለሁ፡፡

በዝዋይ ደስያት የሚተረኩ ተረኮች በቁሳዊ ባህሉም የሚገለጹበት ሁኔታ እንዳለ ነው፡፡ የደስያቱን ፎክሎራዊ ገጽታ የምንመለከተው በገዳምና አድባራት ብቻ ሳይሆን በዋሻዎቹም ጭምር ነው፡፡ ለዚህም የደብረ ጽዮኑን የአቦዬ ዋሻ፣ ከሐይቁ ወጪ የሚገኘውን የሰንጎ ዋሻ፣ የደብረ ሲናውን የአቡ ዋሻ (አቡ ማለት በዛይኛ አባት ነው፤ የአባቶቻችን ዋሻ እንደማለት ነው)፣ እና የሚካኤል ዋሻ (ውስጡ እስከ 7 የአህያ መጫኛ ይረዝማል የሚባልለት)ን ማንሳት ይቻላል፡፡ ከእነዚህ ዋሻዎች ጋር በተያያዘ የሚነገረው ነገር ገዳምና አድባራቱ ከመሰራታቸው በፊት እንደማረፊያና በጣሊያን ወረራ ወቅት እንደ መሸሸጊያ ማገልገላቸው ነው፡፡ በሃይማኖቱ እንደ ተጋዳይ የሚታዩ አካላት በዋሻዎቹ ውስጥ ይጸልዩ እንደ ነበረም ይተረካል፡፡[39]



የደብረ ሲና ሚካኤል ዋሻ



የደብረ አብርሃም ዋሻ



የደብረ ጽዮን የአቦዬ ዋሻ

ፎቶ 11 የዝዋይ ደስያት ውስጥ የሚገኙ ዋሻዎችን ለማሳየት የቀረበ


[39] እኛ አልደረስንበትም፤ ሽማግሌዎች ሲናገሩ እንደ ሰማነው ይሄ ደብረ ጽዮን ያለው የአቦዬ ዋሻ ድሮ መንገድ ነበረው ይባላል፡፡ እንጻውም ከበሮ እየደበደቡ በዚያ ውስጥ ለውስጥ ይሄዱ ነበረ ነው የሚባለው፤ አሁን ግን ተደፍኗል፡፡ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ የጸለዩበት ነው ስለሚባል አባ ገብረ ስላሴ ተድላ እዚህ በሚያስተዳድሩበት ጊዜ እዚያ ውስጥ ነበር የሚኖሩት፡፡ ደብረ ሲና ደሴት ያለው የአቡ ዋሻም ባህታዊያን የሚጸልዩበት ነው፡፡ (መምሬ ባንቲሁን ሀብተ ማርያም፣ በቀን በ02/08/05 ዓ.ም)፡፡

ለስርዓተ አምልኮ መፈጸሚያ ከሚያገለግሉ ንዋየ ቅድሳት መካከል በዝዋይ ደስያት ገዳምና በአድባራት የተገኙት ጥንታዊ መስቀሎች የሚጠቀሱ ናቸው። መስቀል በሃይማኖቱ ውስጥ ብዙ አንድምታ አለው። መስቀል የቀደመ ተግባሩ የወንጀለኞች መቅጫ ነበር። ይህ ሊቀየር የቻለው ኢየሱስ በተመሳቀለ እንጨት ላይ ከተሰቀለ በኋላ ነው። ቁሶች እንዴት በሂደት የተለያዩ ነገሮች መፈጸሚያ እንደሚሆኑም የምንገነዘብበት ነው። ክርስቲያኖቹ መስቀልን የነጻነት ወይም የድል ምልክት አድርገው ይጠቀሙበታል (ኤፌ.2፤15-17)። በመስቀሉ ሰላምን አደረገ የሚለውን አብነት በማድረግ ነው። የመስሪያ ቁሱ እንጨት፣ ወርቅ፣ ብር፣ ነሐስ፣ መዳብና ብረት ናቸው። ይሄንን የወንጀለኛ መቅጫ የነበረ ቁስ ወደ ሕይወት አርማነት እንዲቀየር ያገለገሉ ተምሳሌታዊ ጉዳዮች አሉ።[40]

ከመስቀል ሃይማኖታዊ ምሳሌ እንደምንገነዘበው አንድ ቁስ ከሚሰራባቸው ቁሳቁሶች የተነሳ ተደራቢ ጽንሰ ሀሳብ በመሸከም የተለየ መንፈሳዊ አንድምታ ሊኖረው እንደሚችል ነው። የአንድ ቁሳዊ ባህል ጥበባዊ ገጽታና መንፈሳዊ እሴትነት የሚገለጸውም በዚህ መልኩ ነው። ከዝዋይ ደስያት ጋር በተገናኘ የሚነሱት ጥንታዊ መስቀሎች የሚከተሉትን ይመስላሉ።



በደብረ ጽዮን ሙዚየም የሚገኙ



በደብረ ሲና ደሴት

ፎቶ 12 የደስያቱን ጥንታዊ መስቀሎች የሚያሳዩ

---

[40] ከእንጨት መሰራቱ ጌታችን የተሰቀለበት ስለ ሆነ፣ ከወርቅ መቀረጹ ጌታችን አምላካችን ንጹሃ ባህሪ ስለ ሆነ፣ የብር መስቀል በአስቆሮቱ ይሁዳ አማካይነት ሠላሳ ብር ለመሸጡ ምሳሌ ነው። የነሐስ መስቀል የብሩህነት ምሳሌ ነው። የመዳብ መስቀል የአማናዊ ደሙ ምሳሌ ሲሆን የብረት ደግሞ የተቸነከረበትና ጎኑን የተወጋበት ምሳሌ ነው (ሚሲዮን፤25)።

መስቀሎቹ ለስርዓተ አምልኮ መፈጸሚያ የሚያገለግሉ ከመሆናቸውም በላይ እንደ ተረኮቹ ሁሉ የገዳምና አድባራቱን ጥንታዊነት የሚሰብኩና ታሪካዊነታቸውን የሚያሳዩ ናቸው። ምክንያቱም መስቀሎቹ አክሱማዊያኑ ታቦተ ጽዮንን ይዘው ሲመጡ አብሮ የመጡ ናቸው የሚባሉና የባዕንታይን ንድፍ እንዳላቸው የሚነገርላቸው በመሆናቸው።

ከዘዋይ ደሴያት ገዳምና አድባራት ጥንታዊ ቅርሶች ሳንወጣ የምናገኘው ሌላው ነገር በደብረ ጽዮን ተራራ ላይ የሚገኙትን የድንጋይ ደወሎች ናቸው። እነዚህ የድንጋይ ደወሎችም ታቦተ ጽዮን አርፋበታለች ከሚባልበት ስፍራ ያሉ ናቸው። አንዱ ክብደቱ በጣም ከፍ ያለ በመሆኑ በአሁኑ ሰዓትም እዛው ተራራው ላይ ይገኛል። ሁለቱ በብዙ ሰው ሸክም ገዳሙ አሁን ወዳለበት እንደወረዱ ይተረክላቸዋል። የድንጋይ ደወል በባህላዊ መንግድ ተጠርቦ ለመንፈሳዊ አገልግሎት የሚውል ቢሆንም መንፈሳዊ ይዘትነቱ ያይላል። ድንጋይ በኢየሱስ ይመሰላል (ኢሳ. 28፣16፣ መዝ፣117፣22፣ ኤፌ. 2፣21-22)። አገልግሎት ላይ ማዋል የጀመረው ከዘመነ ኖህ ጀምሮ እንደሆነ ይታመናል። ደወል በአሁን ጊዜም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የሰዓታት፣ የቅዳሴ፣ የማህሌትና የንግስ ሰዓት መድረሱን ለማስገንዘብ ያገለግላል። በቤተክርስቲያኒቷ አስተምህሮም የተለያየ አንድምታ ይሰጠዋል።[41]

ከሃይማኖታዊ አንድምታቸው የምንገነዘበው ነገር አንድ ቁስ ወደ እምነታዊ ጉዳይ ሲመጣ እንዴት ለሃይማኖቱ አስተምህሮ ማንጸባረቂያ እንደሚውልና የመንፈሳዊ እሴት መገለጫ ሊሆን እንደሚችል ነው። አገልግሎቱ የጸሎት ማንቂያ ስለ ሆነም የቅድስና መለኪያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ስለዚህ የድንጋይ ደወሉ ከድምጽ የመስጠት አገልግሎቱ በተደራቢ ሌላ ሃይማኖታዊ አስተምህሮን ይዟል ማለት ነው። የቁሳዊ ባህል ጥናት ዓላማም እንደዚህ ዓይነቱን አገልግሎት በተጨማሪ ያላቸውን አንድምታ መመርመር ነው። የጥንቱ የገዳሙ ደዎሎች ከድንጋይ መሰራታቸው የጥንታዊነታቸው መገለጫ ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም ቁሶችን ከዲንጋይ አለዝቦ የመጠቀም ዘዴ ታሪክ እንደሚነግረን ከሆነ የጥንት ሕዝቦች የስልጣኔ መሰረት ነው። ስለዚህ

---

[41] ደወል የቅዱሳን ነቢያት ምሳሌ ነው። የጌታን መወለድ አስቀድመው በመናገር በተስፋ እንዲጠብቁ አድርገዋልና። በሀዲስ ኪዳኗ ቤተክርስቲያን የሚደወለውም የተለያየ ምስጢር አዘል ተደርጎ ይነገራል። ምዕመናን ለቅዳሴ ለማንቃት የሚደወለው የተጋብኦ ደውል አምስት ጊዜ መሆን የአምስቱ አዕማደ ሚስጥር ምሳሌ ነው። ፍሬ ቅዳሴ ከመጀመሩ በፊት ዲያቆኑ "ባዑ ንኡሰ ክርስቲያን" ሲባል ሶስት ጊዜ መደወሉ የስላሴ ሲሆን እግዚኦታ ላይ አሥራ ሁለት ጊዜ መደወሉ የአስራ ሁለቱ ሐዋርያት በዓለም መዳረስ ምሳሌ ነው (ሚሊዮን፣ 47)።

የዛይ ማህበረሰብም እነዚህን ጥንታዊ ደወሎች ይዞ መገኘቱ አንዱ የጥንታዊነቱ መገለጫ ነው። በሌላ መልኩ ልባዊ እምነቱን በቁሱ አማካይነት ህልው አድርጓል ማለት ነው።

በትንታኔ የቀረቡት ቁሳዊ ባህሎች የዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራትን ጥንታዊነትና ታሪካዊነት ከማሳየታቸው ጎን ለጎን የዛይ የማህበረሰብን ማንነት የሚገነቡና የስፍራውን ጥንታዊነት የሚሰብኩ እንዲሁም ደግሞ ስልጣኒያቸውን የሚያሳዩ ሆነው ተገኝተዋል። ለጥንታዊነታቸው መገለጫ የመስዋዕተ ኦሪት ማቅረቢያ ቁሶችን ይዘው መገኘታቸውንና ለስልጣኒያቸው ማሳያ የእርከን ስራቸውን በተጨማሪነት አንስቼ ትንታኔየን አበቃለሁ። ከነሀስና ብረታ ብረት የተሰሩ የመስዋዕተ ኦሪት ቁሶች በደብረ ጽዮን ገዳም ሙዚየም ውስጥ ይገኛሉ። ከመስዋዕተ ኦሪት ቁሶች ውስጥ ጻህል አንዱ ነው። ይህም እስራኤላውያን ከግብጽ ወደ ከነዓን ባደረጉት ጉዞ የመና መልቀሚያ፣ በኋላ ደግሞ ለመስዋእት ኦሪት የዋለ ነው (ዘጸ.16፣ 31-36)። በገዳምና አድባራቱ የኦሪት መስዋዕት ማቅረቢያ ቁሶች መገኘታቸው ከጽላተ ሙሴ ጋር በተያያዘ ሊመተረከው ተጨማሪ ግብዓት የሚሆን ነው። ምክንያቱም የመስዋዕተ ኦሪት ጉዳይም ከነብያቱ አለቃ ከሙሴ ጋር የሚገናኝ ነውና። ለዛይ ማህበረሰብ የእስራኤል የዘር ሀረግነት ትረካቸውም ተጨማሪ መረጃ ነው።

የማህበረሰቡ ባህላዊ እሴት ውስጥ የስልጣኔያቸው መገለጫ ተደርጎ የሚነሳውና እኔም ሳልጠቅሰው የማላልፈው ነገር የእርከን ስራቸው ነው። ዛሬ በሀገራችን በአዲስ መልክ ገበሬው እየሰለጠነ ያለበትን ነገር የዛይ ማህበረሰብ ከዛሬ አንዷ ሺህ ዓመት በፊት መሬትን ከመሸርሸር ለማዳንና ለእርሻ ስራ ምቹ ለማድረግ ሰርቶ ያለፈው ነገር ምስክር እንደሚሆን የደሴቱ ተወላጅ የሆኑ አቶ ስቡህ ገብረ ማርያም ይነገራሉ (ቃለመጠይቅ፣ በቀን 02/08/05 ዓ.ም)። ከሐይቁ ውስጥ ጀምሮ እስከ ተራራው አናት ላይ በጥበባዊ እውቀት የተሰራው እርከን ባይኖር ኖሮ ደስያቱም በውኃ ተሸርሽረው አልቀው፣ ማንነታቸውም ጠፍቶ ነበር ማለት ይቻላል። ይሄ ስራ አድናቆት የሚቸረው ባህላዊ ጥባባቸው እንደ ሆነ የውጪ አጥኚዎችም ይመሰክራሉ።[42]

---

[42] ፖል ሄንዝ ሀገረሰባዊ እውቀት የፈለሰበት፣ ደስያቱን የሸፈነው የእርከን ስራ ስፍራውን ለእርሻ ምቹ ከማድረጉ በላይ በደስያቱ ላይ ይደርስ የነበረውን የአፈር መሸርሸር ሊያስቀር እንደቻለ ይገልጻሉ (ሄንዝ፣ 80)።

ፎቶ 13 የእርከን ስራውን በጨረፍታ የሚያሳዩ ፎቶዎች

የእርከን ስራ፣ የግድብ ስራ፣ የቤት ግንባታ ስራ፣ የዓሣ ማስገር፣ የደንገል አጨዳ የዛዮችን የመተባበርና አብሮ የመኖር ሕይወት የሚገልጽ ነው። ዛዮች በሽማ ስራም ይታወቃሉ። የደስያቱ የአየር ሁኔታ ሞቃትና ለጥጥ ተክል ተስማሚ ስለ ሆነ በዚህ አጋጣሚ የተጠቀሙ ይመስላል። የሽማ ልብስ እዚያው ደስያቱ ውስጥ እየተቆረጠ በቁምጣና በሽሚዝ መልክ ተሰፍቶ ይለበስ ነበር። በዝዋይ ደስያት ውስጥ ይዘጋጁ ከነበሩት የሸማ ሽራዎች መካከል ቡሉኮ፣ ጋቢ፣ ነጠላ፣ መቀነት፣ ወንደቦና ሌሎችም ይገኙበታል። ወንደቦ ለአርሲ ኦሮሞዎች የሚዘጋጅ ነው።

ፎቶ 14 የዛይ ማህበረሰብን የሽመና ስራ የሚያሳይ

### 4.3. ከዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራት የተገኙ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ተዛምዶ

ተረኮች በቁሳዊ ባህሎች አማካይነት ተጨባጭ ስለሚሆኑ ሁለቱን የፎክሎር ዘውጎች አያይዞ ማጥናት እንደሚያስፈልግ በጥናቱ መነሻ ተገልጿል። በትንታኔ ክፍሉም የተስተዋለው ነገር የዝዋይ ደስያት ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች በተመሳሳይ ሁኔታ የገዳምና አድባራቱን ጥንታዊነትና ታሪካዊነት የሚዘክሩ፣ የስፍራውን ቅድስና የሚሰብኩና የቦታውን ክብር ከፍ የሚያደርጉ መሆናቸውን ነው። ይሄ የተረኮቹና ቁሳዊ ባህሎቹ ተግባር መመሳሰል የሚሰጠው አንድምታ ሁለቱን የፎክሎር ዘውጎች ነጣጥሎ ለማጥናት መነሳት ጥናትን ጎዶሎ እንደሚያደርገው ነው። ምክንያቱም አንዱ የሌላውን ክፍተት የሚሞላ ነውና። ስለዚህ የዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራት ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ተዛምዶ ሁለቱም የጥባባዊ እሴት መግለጫ፣ የመንፈሳዊ እሴት ነጸብራቅ፣ የታሪካዊ ድርጊት ዘጋቢ፣ ባህላዊ ገጽታን ማሳያና የዘመንን መንፈስ መፈተሻ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው። ተረኮቹንና ቁሳዊ ባህሎቹን የሚያገናኙት ድልድዮች ከላይ የተነሱት ዝርዝር ጉዳዮች ቢሆኑም ዋናው የጥምረት መስመራቸው ግን ሁለቱም የፎክሎር ዘውጎች በማንነት ግንባታ ረገድ የሚጫወቱት ሚና ነው። ይሄንን ጉዳይ የሚያሳይ ገለጻ እንደሚከተለው ተዘጋጅቷል።

የፎክሎራዊ ተመራማሪ ዓላማ የፎክሎሩን ጉዳይ መርዳት ብቻ ሳይሆን በጉዳዩ ፎክ ቡድኑን ለመረዳት መጣር ስለ ሆነ የቃላዊ ፎክሎርም ሆነ ቁሳዊ ባህል ማጥናት ዋናው ግብ ሎርን በመተንተን ፎክን መረዳት ነው። ከዚህ አንጻር ተረኮችም ሆኑ ቁሶች ሲጠኑ መጀመሪያ አገልግሎታቸውን ከዚያ ከማህበረሰቡ ጋር ያላቸውን ዝምድና ማሳየት ሲሆን ከዚህ ከፍ ሲል ደግሞ ተረኮቹና ቁሶቹ በማንነት ግንባታ ረገድ የነበራቸውን ሚና ማሳየት ነው። ሁለቱ የፎክሎር ዘውጎች ደግሞ በማንነት ጥናት ረገድ የተቀጣላቸው ናቸው። በዘመናዊያን የተለያዩ የትምህርት ዘርፎች ሲሂቃን ዘንድ የሰው ልጅ ማንነቱን የሚገነባበትን ሁኔታ ለመረዳት በጣም ፈታኝና አዲስ የሆነ ጽንሰ ሀሳብ ተገኝቷል። ይኸውም የተረክ ጥናት ጽንሰ ሀሳብ ነው።[43] ይሄ

---

[43] "... for modern scholarship in various discipline has brought new challenging perspectives to our understanding of human identity construction. These are the perspectives of narrative study" (Brockmeier J. and Donal Carbaugh, 1)

የሚያሳየን በተረኮች በኩል ማንነትን ማጥናት እንደሚቻል ነው። ቁሳዊ ባህልን በተመለከተ ደግሞ ውድወርድ (133) ሲገልጹ "አንድ ማህበረሰብ ቁሶችን ለምንና እንዴት ይጠቀምበታል ብሎ ማንሳት በቁሳዊ ባህሉ አማካይነት የማህበረሰቡን ማንነት መግለጽ፣ ማሳደግና ማጥናት ነው" ይላሉ።

የዛይ ማህበረሰብን የወደፊት ማንነት ለመተንበይ ማንነት በሚገለጥበት ቋንቋቸው በኩል አጥንተው የዛይኛ ቋንቋ በአማርኛና ኦሮምኛ እየተተካ ስለ ሆነ በሞት አፋፍ ላይ ያለ ቋንቋ በሚል የቋንቋው መሞት ደግሞ የባህሉንም ሆነ የማንነት ለውጡን እንደሚያመጣ የሥነ ልሳን ተመራማሪ የሆኑት እንዳሻው ወልደ ሚካኤል እንደሚያስረዱ የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ላይ አንስቻለሁ። የማህበረሰቡ ማንነት ላይ የወደፊት ስጋት ቢኖርም እንኳን የነበረው ማንነታቸው እንዴት ተገንብቷል የሚለውን በሃይማኖታዊ ተረኮቻቸው በኩል ስናጠና እስከ ዛሬ የነበረው ማንነታቸው በእምነት ርዕዮታቸው በኩል ምን እንደሚመስል መገንዘብ እንችላለን። የዛይ ቋንቋ ከግዕዝ በተጫማሪ የትግርኛ፣ የስልጥኛ፣ የጉራግኛ፣ የኦሮምኛና አማርኛ ቋንቋዎች ቅልቅል እንደሆነ ይነገራል። ከዚህ የምንረዳው ደግሞ የዛይ ማህበረሰብ የተለያዩ ነገዶች ተቀላቅሎ የፈጠረው እንደሆነ ነው። ይሄ ከተለያየ ቡድን የተፈጠረ ማህበረሰብ ደግሞ የራሱን አዲስ ማንነት መፍጠሩ የማይቀር ነው። ይሄንን ማድረግ የሚያስችለው የእምነት ርዕዮቱ ነው። ምክንያቱም በባህል በኩል ማንነቱን ለመግለጽ ርዕዮቱን ከሚሰራበት መንገድ አንዱ ሃይማኖታዊ ተረኮቹ ናቸው። ስለዚህ የዛይ ማህበረሰብ በእምነት ርዕዮቱ በኩል ገንብቶት የኖረው አዲስ ማንነት አለ ማለት ነው።

ከገዳምና አድባራቱ መመስረት ጋር ተያይዘው የመጡት ተረኮች የስፍራውን ጥንታዊነት፣ ታሪካዊነትና ቅድስናን የመስበክ ተግባር እንዲሁም እምነትን ለማዝለቅና ታሪኩን ቀጣይ ለማድረግ እንደሚያገለግሉ የታተተላቸው ተረኮች በሙሉ ወደ አንድ ወገን የሚጠቃለሉ ይመስላሉ። ይኸውም የዝዋይ ደሴያት ገዳምና አድባራት ክርስቲያኖች በሃይማኖቱ በኩል ማንነታቸውን የሚያመላክቱ መሆናቸው ነው። የተረኮቹ ተግባር ሲፈተሽ የተራኪው ሁኔታ አብሮ ይታያል። ምክንያቱም እንዴት ተረከው፣ ራሱን ከተረኩ ጋር እንዴት አዛመደ የሚለው ዋና ጉዳይ ነውና። ከዚህ አንጻር ተራኪዎቹ አባቶቻችን እንደ ነገሩን፣ እኛም እንደ ደረስንበት፣ በአይናችን እንዳየነው ብለው መተረካቸው የዛይ ማህበረሰብን የተረኩ ባለቤትነት የሚያሳይ ነው። ስለዚህ ተረኮቹ የስፍራውን ጥንታዊነት፣ ታሪካዊ መሆንና የቅድስና ማዕከልነት ይሰብካሉ ስንል

ታሪካዊው፣ ጥንታዊውና የተቀደሰው የዛይ ሕዝብ እያልን መሆናችንን ልብ ልንል ይገባል። "ስብስ ይቀድስ ለመካን መካን ይቀድስ ለሰብ" ቦታ በሰው ሰው ደግሞ በቦታ ይቀደሳል እንደሚባለው ስለ ደስያቱ ቅድስና ሲተረክ በተዘዋዋሪ ድግሞ ስለ ደስያቱ ነዋሪዎች እየተነገረ ነው።

የዛይ ማህበረሰብ በተረኮቹ እንደ ተገለጠው የአብርሃም ወገንነታቸው፣ የያዕቆብ (እስራኤል) ልጅነታቸው፣ ቀደምት የእምነት ባለቤትነታቸው፣ እግዚአብሔር በመልካሙ ምድር ያኖራቸው የተመረጡ ዘርነታቸው የታየበት ማንነት አላቸው። በተረኮቻቸው የራሳቸውን ማንነት ፈጥረዋል። በተረኮቻቸው አማካይነት ለክርስትና መስፋፋት፣ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ የተለያዩ ቤተክርስቲያናት መመስረት እናት መሆናቸውን አሳይተዋል። የቁሳዊ ባህል ጥናትም የሰውን ልጅ በፈጠረው ባህል ውስጥ መረዳት መቻል ስለ ሆነ በዝዋይ ደስያት የሚገኙት ቁሶችም የደስያቱን ነዋሪዎች ማንነት እንዴት እንደሚገነቡ መረዳት ይቻላል። የእርሻ መሳሪያን በማጥናት ስለ አራሹ ማንነት ማወቅ ከተቻለ፤ የእምነት ተቋማትን ንዋየ ቅድሳት በመመርመር የእምነት ርዕዮታቸውን፣ የህይወት አተያያቸውንና እሴቶቹን መረዳት ይቻላልና። ከገዳምና አድባራቱ ጋር ተያይዘው በመጡ ተረኮች አማካይነት የዛይ ማህበረሰብ እንዴት ማንነቱን እንደገነባ ከላይ የቀረቡት ጉዳዮች ያሳያሉ። በደስያቱ የሚገኙት ቁሳዊ ባህሎችም ይሄንኑ ጉዳይ የሚያጠናክሩ ናቸው። የሁለቱ ተዛምዶ የሚገነጸባረቀውም እዚህ ላይ ነው።

የዛይ ማህበረሰብ ወደ ዝዋይ ሐይቅ ደስያት የገቡት በሀዲስ ኪዳን ዘመን ቢሆንም የጥንተ የኦሪት መስዋያን ይዘው በመገኘታቸው እኛ ቀድሞም አባቶቻችን በህገ ልቦናም ሆነ በህገ ኦሪት እግዚአብሔርን ከሚያመሰግኑት ወገኖች ነን የሚሉ ይመስላል። ለልጆቻቸውም ሆነ በስፍራው ተገኝቶ እነዚህን ቁሶች ለሚመለከት ሰው የሚኖረው አንድምታ ከዚህ የተለየ አይሆንም። ምክንያቱም የመስዋዕትን ታሪክ ስናነሳ ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ከ5400 በፊት አቤልና ቃኤል መስዋዕት ያቀርቡ እንደ ነበረ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል (ዘፍ. 4፣3-5)። ገድለ አዳም ስለ አዳም መስዋዕት ይናገራል። በህገ ልቦና የነበሩት እነ ኖህ፣ አብርሃምም መስዋዕትን ያቀርቡ እንደነበረ በብሉይ ተገልጿል። በሙሴ ዘመን ይህ ስርዓት ተጠናክሮ ቀጥሏል። ስለዚህ እነዚህ ህዝቦች የኦሪት መሰውያን ይዘው መገኘታቸው ከአዳም በትውፊት ሲተላለፍላቸው የነበረውን ስርዓት ሲጠቀሙ የኖሩ የሙሴ ልጆች ናቸው ያስብላቸዋል።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ውስጥ የመሪነቱን ስፍራ እንደሚወስዱ ቁሳዊ ባህላቸው ይናገራል፡፡ "ሙሴ በጸሎት ያገኘውን ታቦት ከዮዲት ጥፋት የታደግን፣ በወንጌላዊ ቅዱስ ሉቃስ የተሳለውን ጽላት ይዘን የነበረን፣ በዓለም ላይ ጠፍቶ የነበረውን መጽሐፈ ሄኖክን ያስገኘን፣ ስለ ግማደ መስቀሉ ማረፊያ የሚተርከውን 'ድርሳን ዘከመ ተረክበ መስቀል' መጽሐፍን የያዝን፣ የመካከለኛው የሥነ ጽሑፍ ዘመን ላይ የነበሩትን የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ የገድል መጽሐፍ ከመጥፋት የታደግንና የቦሩ ሜዳው ታሪካዊ የሃይማኖት ክርክር የተዘገበበትን መዝገብ የያዝን ነን የሚሉ ይመስላል፡፡ በአጠቃላይ የገዳምና አድባራታችን ቁሳዊ ባህሎች ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ህልውና መሰረቶች እንደ ነበርን ምስክሮች ናቸው" የሚሉም ያስመስላቸዋል፡፡ ንዋየ ቅድሳቱ ለሁሉም ነገር ማዕከል፣ መሰረትና ምንጭ ሲሆኑ ያሳያሉና፡፡ ስለዚህ ከተለያየ ማህበረሰብ የተፈጠረ ነው የሚባልለት የዛይ ሕዝብ ከቤተ እምነቱ ጋር ተያይዞ በመጡት ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች እንዴት የራሱን አዲስ ማንነት እንደገነባ መመልከት እንችላለን፡፡ የቁሳዊ ባህል መጠናት ዋና ግብም ከአገልግሎት ባሻገር ያለ ማንነትን ማሳየት ነው የሚባለው ለዚሁ ይመስላል፡፡ በአጠቃላይ በዝዋይ ሐይቅ በሚኖሩ ምዕመናን የሚተረኩት ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች የዛይ ማህበረሰብን የፈጠረ አዲስ የታሪክ ሰንሰለት ገንብቷል፡፡ ከብሉይ ታሪክ የእስራኤል ልጅነታቸውን ያስመሰከረ፤ ኦሪትነተቸውን አውጆ ታቦተ ጽዮንን ያስገኘ፣ በሀዲሱም ለሌሎች ስፍራዎች ማዕከልነታቸውን ያወጀ፤ ታቦታትን (ጽላትን) በመስጠት መሰረት መሆናቸውን የነገረን ነው፡፡ ከቃላዊ ተረኮቹም ሆነ ቁሳዊ ባህሎቹ በመነሳት የዝዋይ ደሴት ገዳምና አድባርት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ማዕከል ነበሩ ማለት ይቻላል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## መደምደሚያ

በዚህ ክፍል የጥናቱ ግብና ከጥናቱ በተገኙ ተጨባጭ መረጃዎች በመነሳት የተሰነዘሩ ጥቆማዎች በአጭሩ ቀርበዋል፡፡

### 5.1. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት ተግባራዊ የሆነው በኦሮሚያ ክልል በምስራቅ ሸዋና አርሲ ዞኖች ውስጥ በሚገኙት የዝዋይ ሐይቅ ገዳምና አድባራት ላይ ነው፡፡ የፎክሎራዊ ጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ በደስያቱ ገዳምና አድባራት መመስረት ምክንያት የተገኙ ቃላዊ ተረኮችንና ቁሳዊ ባህሎችን መመርመር ነው፡፡ በመሆኑም የተረኮችና ቁሳዊ ባህሎችን ምሳሌ፣ ዘይቤና ትዕምርት መርምሮ በማብራራት ፋይዳቸውን ማሳየት የሚል ዓላማን በማንገብ መረጃዎች በቃለ መጠይቅና በምልከታ ዘዴ ከመስክ ተሰብስበዋል፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎችም ከተግባራቸው አንጻር ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ ተረኮቹ የገዳምና አድባራቱን ጥንታዊነትና ታሪካዊነት የመዘከር፣ ቅድስናቸውን የመስበክ፣ ክብራቸውን ከፍ የማድረግ፣ ሉዓላዊነታቸውን የማስከበርና ለመልክዓ ምድራዊ አፈጣጠሩ ምክንያት የመስጠት ሚና ያላቸው ናቸው፡፡ ቁሳዊ ባህሎቹ ደግሞ ሃይማኖታዊ አስተምህሮን ለማቆየትና ለማጽናት እንዲሁም ለስርዓተ አምልኮ መፈጸሚያ ከማገልገላቸው በሻገር የተረኮቹን እውነትነት ለማረጋገጥ በማስረጃነት የሚቆሙ መሆናቸውን ከትንተናው መረዳት ይቻላል፡፡

ከቃላዊ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች የተገኙት መረጃዎች የሚያሳዩት የዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራት የጥባባዊ እሴት መገለጫ፣ የመንፈሳዊ እሴት ነጸብራቅ፣ የታሪካዊ ድርጊት ዘጋቢ፣ ባህላዊ ገጽታን ማሳያና የዘመንን መንፈስ መፈተሻ መሆናቸውን ነው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል፡፡ የሚተረኩት ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ባለቤትነት የዛይ ስለ ሆነ የማህበረሰቡን ማንነት በመፍጠር ረገድም ከፍተኛ ሚና ያላቸው ናቸው፡፡ ጥናቱ ከፎክሎር የምርምር አቅጣጫ አንጻር በዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራት ዙሪያ አንዳች መነሻ ነገር ለማስቀመጥ ተግባራዊ ቢሆንም በስፋራው በሰፊው ሊጠኑና ሊታዩ የሚገባቸው በርካታ ጉዳዮች አሉ፡፡ የዛይ ማህበረሰብ የመስቀልና የሰርግ ስርዓት በተለይ ደግሞ በሴቶቹ የተለየ ቦታ የሚሰጣቸው የዘወይራ ጭፈራና የፈታሾት ማይራሜ መዝሙራቸው ጥልቅ የፎክሎር ምርምርን የሚሹ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በሐይቁ የሚገኙት የተለያየ

# ዋቢ ጽሑፎች

ሉሌ መልአኩ። *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ*፡ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ 1997።

መንግስቱ ጎበዜና አሳምነው ካሳ። *የቤተክርስቲያን ታሪክ (ቁጥር ሁለት)።* አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች፣ 2000።

ሚሊዮን በለጠ። *ንዋየ ቅድሳት።* አዲስ አበባ፣ ባናዊ ማተሚያ ቤት፣ 2005።

ማህበረ ቅዱሳን። "ዝክረ ቴዎፍሎስ፣ ጴጥሮስ ወሚካኤል።" *በሐመር ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ።* 12ኛው ዓመት ቁጥር 2፣ ግንቦት (ሰኔ) ዕትም፣ 1996፣ ገጽ. 33።

---። *ቤተክርስቲያንህን ዕወቅ*፡ አዲስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ድርጅት፣ 1988።

---። *የደቡብ ክዋክብት በዛይ ደስያት*፡ ዘጋቢ ምስል ወድምጽ፣ 2004።

ምህረት ተስፋዬ። "ክጣና ቂርቆስ የአንድነት ገዳም አመሰራረት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተረኮች እና ቁሳዊ ባህሎች ጥናት።" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል (ለአርት ማስተርስ ድግሪ የቀረበ ጥናት)፣ 2003።

ሞገስ ጀንበር። ከዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም አመሰራረት ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች እና አምልኳዊ ስርዓቶች።" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ (ለአርት ማስተርስ ድግሪ የቀረበ ጥናት)፣ 2003።

ሰሙ ምትኩ (ቀሲስ ዶ/ር)ና ቸሬ ለማ (መ/ር)። *የቤተክርስቲያን ታሪክ- ቁጥር ፩።* አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች፣ 2000።

ስርግው ሀብለ ስላሴ። *አማርኛ የቤተክርስቲያን መዝገበ ቃላት።* አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ ብርና ጽሑፎች ማይክሮ ፊልም ድርጅት፣ 1981።

ብርሃኑና ሌሎች፡፡ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ትናንትናና ዛሬ፡፡* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1990፡፡

ባሕሩ ዘውዴ፡፡ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847-1983፡፡* አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ፣ 1999፡፡

ተስፋዬ ኤደቶ፡፡ *የዛይ ሕዝብ ታሪክ፡፡* አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ 2000፡፡

ተስፋዬ ተገኝ፡፡ "የደብረ ነጎድጓድ ሐይቅ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞዓ እንድነት ገዳም አመሠራረትና ቁሳዊ ባሕል ጥናት፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል (ለአርት ማስተርስ ድግሪ የቀረበ ጥናት)፣ 2003፡፡

ታምራት ኃይሉ፡፡ "የብራና መጻህፍት አዘገጃጀት በደቡብ ጎንደር እስቴ ወረዳ፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል (ለአርት ማስተርስ ድግሪ የቀረበ ጥናት)፣ 2000፡፡

ቴዎድሮስ ገብሬ፡፡ *በይነ ዲሲፕሊናዊ የሥነ-ጽሑፍ ንባብ፡፡* አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፡፡ 2001፡፡

አበባው ይግዛው፡፡ *የቁም ጽሕፈት ሙያ፡፡* አዲስ አበባ፣ ዳሸን ማተሚያ ቤት፣ 1999፡፡

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፡፡ *መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፡፡* አዲስ አበባ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1948፡፡

ከንፈ ገብርኤል አልታየ (ሊቀ ካህናት)ና ጌታቸው ደጀኔ (ቀሲስ)፡፡ *ሥርዓተ ቤተክርስቲያን፡፡* (2ኛ ዕትም) አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፣ 1998፡፡

ዘመድኩን በቀለ፡፡ *ቅዱሳን መካናት በኢትዮጵያ ክፍል ፩፡፡* አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት 1992፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፡፡ *አማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡* አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1993፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን። *የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትናንትና ዛሬና ነገ።* አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት፤ 1997።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንና የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር። *መጽሐፍ ቅዱስ።* አዲስ አበባ፤ ማተሚያ ቤት የሌለው፤ 2000።

የዝዋይ ደሴት የጽዮን ማርያም ገዳም ህንጻ አሰሪ ኮሚቴ። *የዝዋይ ደብረ ጽዮን ታሪካዊ አመጣጥና አመሰራረት።* አዲስ አበባ፤ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፤ 1986።

ያለው እንዳወቀ ሙሉ። *የምርምር መሠረታዊ መርሆችና አተገባበር።* አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች፤ 1998።

ዮናስ አድማሱ። "'እስረኛንኩዋ'፤ ሀዲስ አለማየሁና የማህበራዊ ሂስ ሥልታቸው።" የኢትዮጵያ የቋንቋዎችና የሥነ ጽሑፍ መጽሔት፤ ልዩ ዕትም 1፤ ቁ.10፤ 1992፤ ገጽ. 77-120

ደስታ ተክለወልድ። *ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት።* አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፤ 1962።

ደጀኔ ሽፈራው (ቀሲስ)። *ነገረ ቅዱሳን-፩።* አዲስ አበባ፤ ሜጋ ማተሚያ ኃ. የተ. የግ. ማ. 2001።

ዳንኤል ክብረት። *የቤተክርስቲያን መረጃዎች።* አዲስ አበባ፤ ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ፤ 1999።

ገብረ ሥላሴ ወ/አረጋይ (ጸሐፌ ትዕዛዝ)። *ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒሊክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ።* አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ሊሚትድ፤ 1959።

ጎርጎሪዮስ (አባ)። *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ።* አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ፤ 1986።

ፊቃደ አዘዘ። *የሥነ ቃል መመሪያ።* አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የመጻህፍት ማዕከል፤ 1991።

Bal, Mieke. *Narratology Introduction to the Theory of Narrative* (2nd ed). London; University of Tronto press, 1997.

Ballenger, E.W. *Figures of Speech Used in Bible; Explained and Illustrated.* Michigan; Baker Books house Grand Rapids, 1998.

Bascom, William. "Four Functions of Folklore." The Journal of American Folklore; Vol. 67,No.266, Oct-Dec, 1954, pp. 333-349 Jan-Mar,1965, pp. 3-20.

---. "The Forms of Folklore Prose Narratives." *The Journal of American Folklore.* Vol. 78, No. 302,

Belay Worku. "The Life of Abba Anorewos and History." Holy Trinity Theology College (B.Th.thesis), 2001.

Brockmeier Jens. and Donal Carbaugh. *Narrative and Identity.* Amsterdam; John Benjamins Publishing Company, 1984.

Danielson, Larry. "Religious Folklore" In Folk Groups and Folklore Genres; An Introduction. Logan, Utah State University Press, 1986.

Degh, Linda."*Oral Folklore, Oral narratives*" In Folklore and Folk life; RiChard M.

Dorsan (ed) Chicago and London; The University of Chicago Press, 1972.

Desta Fitsumbirhane. "Catalogue of some selected Manuscript of Dâbrâ Sâyon Church Ziway Island (Tulu Guddo Island)." Addis Ababa University: Department of Philology (Masters Thesis), 2009.

Dorson, Richard M. *Folklore and Folk Life*. Chicago and London; The University of Chicago Press, 1972.

---. "Mythology and Folklore." *Annual Review of Anthoropology.* Vol. 2, 1978, pp. 107-126

Endashaw W/Michael. "A Study of Ethnolinguistic Attitudes of Zay People; An Investigation of The Language-Ethinicity Relationship Among Zay." Addis Ababa University: Department of Linguistics (MA thesis), 2007.

Finnegan, Ruth. *Oral Traditions and The Verbal arts.* London and Newyork; Routledge, 1992.

Franzosi, Roberto. "Narrative Analysis." *Annual Review of Sociology;* Vol. 24, 1998, pp. 517-554

Goldstein, Kenneth. *A Guide for Field Workers in Foklore*. Hatboru; published by Gale Research Company, 1964.

Glassie, Henry. *Material Culture.* Blomington; Indiana University Press, 1999.

Georges, A. and Michael, Jones. *Folkloreistics; An Introduction.* Bloomington and Indiana polis; Indiana University Press, 1995.

Henze, Paul Bernard. "Lake Zway and its Island; An Ethiopian Lake where a Unique Christian Culture has Survived Since Medieval Times." *Ethiopian Observer.* XVI, no. 1, 1973.

Jackson, Bruce. *Field Work.* Urbana and Chicago; Illinois University Press, 1987.

Jones, M. Owen (ed). *Putting Folklore to use.* The University of Kentucky; 2000.

Leeming, David. *Myth A Biography of Belief.* New York; Oxford Univeristy Press, 2002.

Oring, Elliott. *Folk Groups and Folklore Genres; An Introduction.* Logan; Utah State University Press, 1986.

Prown, J. David "Mind in Matter; An Introduction to Material Culture Theory and Method." *Winterthur Portfolio.* Vol, 17 No. 1. Spring, 1982. pp. 1-19

Schlereth, J. Thomas. "Understanding the Nine Models of Material Culture interpretation." Online Available at URL;http;// www.btnep.org.

Sergew Habla-sellassie. *The Church of Ethiopia Apanaroma of History and Spritual Life.* Addis Ababa, United printers, 1970.

Sims, Martha C. and Martine Stephens. *Living Folklore; An Introduction to the Study of People and their traditions.* Logan; Utah State Universtiy Press, 2005.

Taddesse Tamrat. *Church and State in Ethiopia 1270-1527.* Oxford; Clarendon Press, 1972.

Tuma Nadamo. "AHistory of Zay in the 19th and Early 20th centuries." Addis Ababa University: Department of History (B.A. thesis), 1982.

Woodword, Ian. *Understanding Material Culture.* London; Sage publication Ltd, 2007.

Zelalem Assefa."A Brief History and Activities of Zeway Debre Tsion monastery." Holy Trinity Theology College (B.Th. thesis), 2001.

# አባሪዎች

## አባሪ አንድ

## ከስፍራው የተሰበሰቡ ተረኮች

### ተረክ አንድ

አባቶቻችን ሲነግሩን ዮዲት ጉዲት የተባለች እንዳውም እሳቷ ይሎታል አሉ፤ በዘመኗ በርካታ ቤተክርስቲያናትን አቃጥላለች። ታዲያ የአክሱም ጽዮን ቤተመቅደስ ልታቃጥል ወደዚያ ስትመጣ አክሱማውያን ታቦተ ጽዮንን ይዘው ይሸሻሉ። እሷም ተቦተ ጽዮንን ማጥፋት ስለምትፈልግ ያገኘች መስሏት 12ቱን ቤተመቅደስ ታቃጥለዋለች። ቤተክርስቲያኑ ከወርቅና ከእንቁ የተሰራ ነው፤ እሳት ሲለኮስበት ሙሉ በሙሉ ቀልጦ ቀረ አሉ። ታቦተ ጽዮንን ይዘው መሸሻቸውን ስታውቅ ማሳደድ ትጀምርላች፤ እነሱ ደግሞ መንዝ ገብተው በተራራማው ስፍራ ይሸሸጋሉ። እሷም ተከትላ መጥታ ጦርነት ትከፍትባቸዋለች፤ ቦታው ተራራማ ስለ ሆነ አመቺ ሆኖላቸው ለጊዜው ድል ይቀናቻዋል። ሆኖም ግን ሀይሏን አጠናክራ ከተመለሰች ልትጎዳቸው ስለምትችልና ብዙም አስተማማኝ ስላልመሰላቸው ቀን ቀን እየተደበቁ ለሊት ለሊት እየተጓዙ በእግዚአብሔር መሪነት ወደዚህ ስፍራ ይመጣሉ። በዚህ በአቡራ በኩል ወደ ዝዋይ ሐይቅ መጡ። መጀመሪያ ያረፉበት ቦታ ከሐይቁ ማዶ ዛሬ ሰንጎ የሚባለው ነው። እዛ ሰንጎ የሚባለው ቦታ ዋሻ ፈልፍለው ለአንድ ዓመት ተቀምጠዋል ይባላል። ወደ ሐይቁ ለመግባት እንደ አሁኑ ጀልባ የለም። በወቅቱ ብዙ ነገር ይዘዋል ታቦታቱና ካህናቱ አሉ። ሕዝቡ ብዙ ነው (ከመንዝ አማራው ተከትሏቸዋል፤ ፈንፈኔ ሲደርሱ ሸዋ ኦሮሞ፣ ጉራጌ ሲደርሱ ደግሞ ጉራጌዎቹ ተቀይጠዋል፤ እዚህ ሲደርሱ የአርሲ ኦሮሞ ነበረ፤ ዙሪያውን ሰፍረው ያሉ ስልጤዎችም ነበሩ፤ ያው ሃይማኖት አልነበራቸውም እንደ አብሃርም ጊዜ ይኖሩ ነበረ፤ በአጠቃላይ አምስት ብሔር ሆኑ) ይሄ ሸክላ ሰሪ፣ ብረት አንጣሪ፣ ሸማ ሰሪ የቀረ የለም፤ መጻህፍቱ አሉ፣ የእህል ዘር

ፋሳው፣ ኑጉ፣ ሰሊጡ፣ ገብሱ ሁሉንም ይዘዋል። በወቅቱ ሕዝቡን የመሩ የነበሩት 3ት ወንድማማቾች ናቸው። ትምዕርተ መስቀል ወደ ጉራጌ ምድር ሄደ። አመሃ ስላሴ እዚያው ሰነጎ ቀረ። አጽቀ ስላሴ በረግረግ ላይ ሆኖ ሁሉንም ነገር ይዞ ወደ ደሴቱ ገባ። ረግረጉ በጣም ትልቅ ነው አንድ ደሴት ያክላል። ድንገት ንፋሱ ረግረጉን ስላስነሳው አመሃ ስላሴ ወንድምዬ እንዴት እኔን ጥለሀኝ ትሄዳለህ ይለዋል። አጽቀ ስላሴ ወንድሜ ይሄ ንፋስ የሚመራው ነውና ምንም ላደርግ አልችልም ብሎት ይለያያሉ። ያው የእግዚአብሔር ሐይል ነው፤ በንፋስ ነው የሚመራው ምንም ሊያደርግ ስላልቻለ ትምህርቴ እዛው እስላም ሆኖ ቀረ። አጽቀ ስላሴ መጀመሪያ ያረፉበት ደሴት ደብረ አብርሃም የሚባለው ነው። እዚያ እንዳረፉ ለታቦተ ጽዮን ማረፊያ እግዚአብሔር የፈቀደው ከሆነ ብለው አስቴውን ይሰብቃሉ፣ እሳት አልሰጣቸው ይላል። እዛው ምሳቸውን በልተው (ምሳ የበሉበት ቦታ ምሳ ናብር የሚባል ነው አሁንም አለ ይታወቃል ) ከዚያ በንፋስ የሚመራው ረግረጋቸው ላይ ሲመለሱ ደብረ ጽዮን ደሴት ቀጭን ደፋር የሚባል ቦት ላይ ያሳርፋቸዋል። በዚያም እግዚአብሔር የፈቀደላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ አስቴውን ሲሰብቁ እሳት አልወጣላቸው አለ። ተራራው ላይ ጉማርጌዎች በነበሩበት ስፍራ ሞከሩት በዚያም እንቢ አላቸው። በመጨረሻ የወይዘሮ ተራራ ስቀላይ ተብሎ የሚጠራበት ስፍራ አስቴውን ሲሰብቁት ብረሃን ሰጣቸው። ይሄ እግዚእብሔር የፈቀደልን ስፍራ ነው ብለው እዚያ ተቀመጡ። ታቦተ ጽዮንም 40 ዓመት የተቀመጠችው እዛ ነው። ይሄ የሆነው በ842 ዓመተ ምህረት ነው። አንበሳ ውድም እዚሁ በንግስናው ተቀመጠ። ግዛታቸውንም ወደ አምስቱም ደስያት አስፋፉ። አንበሳ ወድም ከ40 ዓመት በኋላ ታቦተ ጽዮንን ይዘው ሲመለሱ ቦታው ከጠላት ለመሸሸግ ጥሩ ስለ ሆነ ከመጻህፍቱም፣ ከታቦታቱና ሌሎች ቅርሶችም እንዲሁም ከሕዝበ ግመሹ የሄ የመከራችን ቀን ቦታ ናት ብለው ተከፍለው ቀሩ። አንባሰ ውድምም ልጁን አንገሶ ይሄዳል። ከዚያ አጼ ምኒሊክ ሀገሪቱን አንድ እስከ አደረጉት ድረስም የተለያዩ ንጉሦች በዚህ ደሴት ነግሠዋል ይባላል (መምሬ ገብረ መስቀል ሂርጳ በቀን 2/08/05 ዓ.ም፣ መምሬ አስፋው ቱፋ በቀን 06/08/05 ዓ.ም፣ መርጌታ ሰምረ ግደይ በቀን 10/08/05 ዓ.ም፣ ቀሲስ ተስፋዬ ነቢ በቀን 9/08/05 ዓ.ም፣ አቶ ስቡህ ገብረ ማርያም በቀን 2/08/05 ዓ.ም፣ አቶ ታደሰ አሼ በቀን 5/08/05 ዓ.ም)።

# ተረክ ሁለት

## በደስያቱ ይገኙ ስለ ነበሩና አሁን ያሉ ጽላቶች የሚተረከው

ታቦተ ጽዮን ወደዚህ ደሴት ስትመጣ ከዮዲት ወረራ ሸሽተው ከተለያዩ አቅጣጫዎች የመጡ በርካታ ጽላቶች ናቸው፡፡ እንዳውም ታቦተ ጽዮን ደሴቱ ላይ ሳትደርስ በሌላ አቅጣጫ ቀድሞ የገባው የእዮራም ጎሳዎች ይዘውት የነበሩት ታቦተ ኢየሱስ ነው፡፡ ታቦተ ኢየሱስ ግን አሁንም አለ፡፡ ግን አይቀደስበትም በጣም ቁጡ ነው፡፡ በተከታታይ ሰባት ቄሶች ሞተዋል፡፡ በንጽህና ካልገቡ ምህረት የለውም፡፡ ጥንቃቄ ይፈልጋል፡፡ በዮዲት ወረራና በግራኝ የጥፋት ዘመቻ ዘመን በርካታ ታቦቶች ወደ ደስያቱ በስደት ገብተዋል፡፡ ታዲያ ዛሬ በዚህ በአዋሳ መስመር፣ አርሲና አዲስ አበባ ከተማ ላይ የተተከሉት በርካታ አብያተ ክርስቲያናት ምንጫቸው የዝዋይ ደስያት አብያተ ክርስቲያናት ናቸው፡፡ ለምሳሌ ያህል አባ ኢሳያስ ከዚህ እያወጡ የተከሏቸው የመቂ ሚካኤልና ጊዮርጊስ፣ ሻሸመኔ ማርያም፣ ድሬዳዋ ሚካኤል፣ ቡታጅራ፣ ከንባታ፣ ሃዲያ፣ ጎልጃ፣ ዝዋይ ድጉዳ፣ አዳሚ ቱሉ፣ አሰላ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ይጠቀሳሉ፡፡ አዲስ አባባ ላይ መስካየ ህዙናን መድኃኒዓለም (አጼ ሀይለ ስላሴ ለዓለም መንግስታት የጣሊያንን መንግስትን የግፍ ወረራ አቤት ለማለት ሲሄዱ ሲሉ አቡነ ጴጥሮስ (በጣሊያን የተሰውት አባት) መከረዋቸው ስለት ተስለው የመድኃኒዓለም ጽላት ሲወጣላቸው የደብረ ሊባኖስ እጨጌ የነበሩት ንቡረ ዕድ ገብረ ጊዮርጊስን (ቡኋላ ፓትራሪክ የሆኑት አቡነ ባስሊዮስ) ይዘው መጥተው የወሰዱት እንዲሁም በቅዱስ ማርቆስ አማካይነት እንደ ተሳለ የሚነገርለት የቁልቢ ገብርኤል በአንድ ባህታዊ አማካይነት ከዝዋይ ደሴት ተወስዶ በአሁን በሚገኝበት ስፍራ ተደብቆ ቆይቶ እንደ ተተከለ ይነገራል፡፡ ከዚህ ደሴት በርካታ ታቦቶች ወጥተው አብያተ ክርስቲያናት ተሰርተዋል፡፡ አሁንም በርካታ ታቦታት የሚገኙባቸው ከመሆናቸውም በተጨማሪ በሌላ ቦታ እንኳን እንዳሉ ስማቸውን ሲጠሩ በብዛት የማንሰማቸው ገላውዲዮስ፣ የቅዱስ ሴባስቲያን 72 አርድዕት የተባሉ ታቦታት ከሐይቁ ደስያት በደብረ ሲና ደሴት ይገኛሉ (መምሬ ገብረ መስቀል ሄርጳ በቀን 2/08/05 ዓ.ም፣ ቀሲስ ተስፋዬ ነቢ በቀን 9/08/05 ዓ.ም)፡፡

# ተረክ ሶስት

## ለአክሱም ስረወ መንግስት መመለስ የዝዋይ ደሴያትን ምክንያትነት የሚነግረን ተረክ

ዮዲት ጉዲት ከ40 ዓመት የጥፋት ወረራዋ በኋላ እግዚአብሔር ሰማ፣ በሱ ሐይል ሞተች። ከዚያ አንበሳ ውድም በ882 ዓ.ም ታቦተ ጽዮንን ይዞ ወደ አክሱም ተመለሰ። ዮዲት ጉዲት 12 ቤተ መቅደስ ያለውን አቃጥላው ስለ ነበረ አንበሳ ውድም ሲመለስ 7 መቅደስ ያለውን ቤተክርስተያን አሰራ። አክሱም እንደ ገና ቀና። ከዚያ ምን አደረገ ድሮ ሰላም የሚሰፍነው በጋብቻ ነውና ከዮዲት ዘር የሆነውን መርሃ ተክለ ሃይማኖትን ልጁን አጋባው። የዘር ሀረጋቸው አንድ ነው። የለያያቸው እምነት ነው። ከዚያ የጦር ሚኒስቴር አድርጎ ሾመውና ቀስበቀስ ክርስትና እንዲቀበሉ አደረገ። መርሃ ተክለ ሃይማኖት ንግስና ፈለገ። ከዚያ መፈንቅለ መንግስት አካሄደ (በዘመናዊ ቋንቋ እንደምንለው)። በ912 ዓ.ም ድጋሚ የአክሱም መንግስት ንጉሱ ድል ንዓድ ሸሽቶ ወደዚህ መጣ። አሁን በዓለማዊ ታሪክ በ1500 ዓ.ም የዛግዌ መንግስት እንደ ተመሰረተ ይነገራል። በቤተ ክርስቲያናችን የሚታወቀው ግን በ912 ዓ.ም እንደሆነ ነው። ወደ ዝዋይ የመጡት ታቦተ ጽዮንን ትተው ነው አሁን የእምነት ልዩነት ስለ ሌላቸው ማለት ነው። መርሃ ተክለ ሃይማኖት ዛግዌ ተባለ። ይህም ዙአጉዬ - የግዕዝ ቃል ነው። ያሳደደ ማለት ነው። የአክሱምን መንግስት ያሳደደ ስለ ሆነ ያባረረ ተብሎ ደብረ ብርሃን ላይ ስልጣን ተሰጠው። ከዚያ የዛግዌ መንግስታት ለ300 ዓመታት በዘር መንገስ ጀመሩ። ያው እንደምታውቀው እነ ላሊበላ፣ ናኵቶለአብ የምንላቸው የነገሱበት ነው። የአክሱም መንግስትም እዚህ ገብቶ ቀረ። ከዚያ ብዙ ምሁራን ሲያነቡ መንግስት በአክሱም ይነግስ እንደ ነበረና ስልጣኔው እንደ ነበረ ይታወቃል። ግን የአክሱም መንግስት የት እንደ ሄደ አይታወቅም። ኢትዮጵያን እየገዛ ያለው የዛግዌ መንግስት ነው። ከእነዚህ ምሁራን አንዱ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ናቸው። በጣም ምሁር ናቸው። ለሀገሪቷም ትልቅ ስራ የሰሩ ናቸው። ታዲያ ታሪክ ሲያነቡ "ህግ ይወጽዕ እምጽዮን"፣ መንግስት አክሱም ላይ ይቀባ እንደ ነበረ፣ ታቦተ ጽዮን ደግሞ ያለ መንግስት ትቀመጥ እንዳልነበረ ያነባሉ። ታዲያ የአክሱም መንግስት የት ሄደ የሚል ጥያቄ ይፈጥርባቸዋል። በዚህ ላይ እያለ አጼ ዩኩኖ አምላክ የመጀመሪያ ስሙ ወልደ የሱስ ነው። በዓለማዊ ታሪክ ላይ የአክሱም ተወላጅ ሆኖ ስልጣን እንዳስመለሰ ተጽፎ ይገኛል። የተወለደው ግን እዚህ ደብረ ጽዮን ደሴት እንደ ሆነ ነው የቤተክርስቲያን ታሪክ የሚተርከው። እዚህ ተወልዶ እዚሁ አድጓል። ደብረ ጽዮንን ማዕከል አድርጎ በአምስቱ ደሴት ላይ የአክሱም መንግስት ይነግሳል። በወቅቱ ወደ ስልጣን ሊመጣ የሚችለው የቤተክርስቲያን እውቀት ያለው

ነው፤ ወልደ ኢየሱስ ደግሞ ዲያቆን ነው። ትምህርቱን ሲያዳብር አቡነ ኢየሱስ ሞዓ ወደ መሰረቱት ሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም ይሄዳል። አቡነ ተክለ ሃይማኖት የአቡነ ኢየሱስ ሞዓ ጎደኛ ስለ ነበሩ እዚያ ነበሩ። በእሳቸው ውስጥ ደግሞ የአክሱም መንግስት የትገባ የሚለው ጥያቄ አለ። ከዚያ "ከየት ነው የመጣኸው?" ይሉታል። "ከዝዋይ ደሴት"፣ "መንድን ነው የዝዋይ ደሴት?" ሲሉት ያለውን ታሪክ ይነግራቸዋል። ለካ የአክሱም መንግስት የትገባ የምለው እዛ ሐይቅ ውስጥ ነው ያለው። አሁን ምንድ ነው እሳቸው ታቦተ ጽዮን ጠላት መጥቶ ቢዘርፋት እንኳን ማን ይጠብቃታል የሚለው ስጋትም ውስጣቸው አለ። "ለካ እዚያ ውኃ ውስጥ ነው ያለኸው? እኔ አሁን የስንት ጊዜ የውስጤን ጥያቄ ነው የመለስክልኝ መሰለህ!" ብለው እግዚአብሔርን አመስግነው፤ "በል አሁን እሾምሃለሁ፤ አክሱም ላይ ነው መንግስት መቀመጥ ያለበት፤ የዛግዌ መንግስታት የሚጠብቁት ነገር ምን አለ? በል አሁን አንተን ይኩኖ አምላክ ብዬ አነግስሃለሁ"። ይኩኖ አምላክ እግዚአብሔር ረዳት ይሁንህ ማለት ነው። "አባቶቻችን በድንቅ ስራ ያመጧትን ታቦተ ጽዮንን ጠላት ቢዘርፋት ማን ይጠብቃታል። አንተን አጼ ይኩኖ አምላክ ብዬ አነግስሃለሁ። ለቤተክርስቲያን ስርወ መንግስት እሰጣታለሁ።" ስርወ መንግስት የመሰረቱት እሳቸው ናቸው። "እንደ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ስርወ መንግስት ትከፍላለህ። አክሱም ቤተክርስቲያንን ትጠብቃለህ። ስርዓት ታስመልሳለህ እኔ ሕዝቡን ቀሰቅሳለሁ።" ሐዋሪያ ናቸው ሕዝብ ይከተላቸዋል። ሕዝቡን አሰባሰበው ቀብተው አነገሱት። ከዚያ ወደ ዛግዌ መንግስት ሄደው "እኔ ሁላችሁም እንድትጣሉ አልፈልግም። ሁላችሁም ኢትዮጵያዊያን ናችሁ። ነገር ግን ስርዓቱ እንዲህ አይደለም። የተነሳንበት ምዕራፋችን አክሱም ነው። ታቦተ ጽዮን ያለችው እዚያ ነው" ብለው አሳመኗቸው። የዛግዌ መንግስት አካባቢውን እንዲገዛ የአክሱሙ ደግሞ ኢትዮጵያን እንዲገዛ አስማሟቸው። ከዚያ አጼ ይኩኖ አምላክ ስልጣን ያዘ። ይኩኖ አምላክ መጀመሪያ እንደ ነገሰ ወደዚህ ደሴት መጥቶ በሉ እኔ ንግስና ተቀብያለሁና ተመልሼ ልሄድ ነው። ነገር ግን ውድ ውድ የሆኑት ቅርሶች እዚሁ አምስቱ ደስያት ላይ ተከፍለው ይቀመጡ። ይኖሩበት የነበረውን ደሴት "ደብረ ጽዮን ብያታለሁ፤ የጽዮን መሸሸጊያ ናትና" ብሎ ሄደ። ግማሹ አብሮት ወደ አክሱም ሄደ ከፊሉ ግን ተከፍሎ ቀረ። ቦታው ይሄን ያህል ታሪክ ያለው ነው እልሃለሁ (መርጌታ ሰምረ ግደይ፣ በቀን 10/08/05 ዓ.ም)።

# ተረክ አራት

## የዛይ ሴቶች (እናቶች) በጾም ወቅት የሚዘሙሩት ዝማሬ

| በዛይኛ ቋንቋ | በአማርኛ ቋንቋ አቻ ፍቺ |
|---|---|
| ማረኝ ማረኝ እግዜሮ ማረኝ | እግዚአብሔር ሆይ ማረኝ ማረኝ |
| ቲት ምረኞ ያመን ጋር ሳኔኞ | ስትምረኝ የአመነ ቤት አድርገኝ |
| ማረኝ ማረኝ ዛኛቶ ማረኝ | ማረኝ ማረኝ በነጋታው ማረኝ |
| አቤት ማረኝ (አዝማች) | አቤቱ ማረኝ |
| ሜሪኝ ሜሪኝ አቤት ሜሪኝ | ማሪኝ ማሪኝ አቤት ማሪኝ |
| ሜሪኝ ሜሪኝ እመለስ ስህተቴ ሜሪኝ | ማሪኝ ማሪኝ ከስህተቴ እንድመለስ ማሪኝ |
| ሜሪኝ ሜሪኝ ያይቦሲ የበላ | ማሪኝ ማሪኝ የማይበላ በላለሁና ማሪኝ |
| ሜሪኝ ሜሪኝ አውጂሚ ሜሪኝ | ማሪኝ ማሪኝ ዛሬም ማሪኝ |
| ሜሪኝ ሜሪኝ ጌይሰሜ ሜሪኝ | ማሪኝ ማሪኝ ነገም ማሪኝ |
| ሜሪኝ ሜሪኝ እምነተን አሲሾ ሜሪኝ | ማሪኝ ማሪኝ እምነት አለሽና ማሪኝ |

### አዝማች

| በዛይኛ ቋንቋ | በአማርኛ ቋንቋ አቻ ፍቺ |
|---|---|
| ማረኝ ማረኝ ሰንበቶ ማረኝ | ማረኝ ማረኝ የሰንበት አምላክ ማረኝ |
| ማረኝ ማረኝ ሰማዕቶ ማረኝ | ማረኝ ማረኝ የሰማዕታት አምላክ ማረኝ |
| ማሩኝ ማሩኝ ባዕላላቻይ ማሩኝ | ማሩኝ ማሩኝ በዓላት ማሩኝ |
| ማሩኝ ማሩኝ ተቦቶ ማሩኝ | ማሩኝ ማሩኝ ታቦታት ማሩኝ |
| ማረኝ ማረኝ ኢየሱስ ማረኝ | ማረኝ ማረኝ ኢየሱስ ማረኝ |
| ቲት ምረኞ ያመን ጋር ሳኔኞ | ስትምረኝ የአመነ ቤት አድርገኝ |

| | |
|---|---|
| ማረኝ ማረኝ መጽሐፎ ማረኝ | ማረኝ ማረኝ መጽሐፉ ማረኝ |
| አቤት ማረኝ ወንጌሎ ማረኝ | አቤት ማረኝ ወንጌሉ ማረኝ |
| ማረኝ ማረኝ ሙኮዮ ማረኝ | ማረኝ ማረኝ ሚካኤል ሆይ ማረኝ |
| ማረኝ ማረኝ ገብረመንፈሰ ማረኝ | ማረኝ ማረኝ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ማረኝ |
| ማረኝ ማረኝ ገብሬሎ ማረኝ | ማረኝ ማረኝ ገብርኤል ሆይ ማረኝ |
| ማረኝ ማረኝ ጭርቆሶ ማረኝ | ማረኝ ማረኝ ጭርቆስ ሆይ ማረኝ |
| ማረኝ ማረኝ ጌርጊሶ ማረኝ | ማረኝ ማረኝ ጊዮርጊስ ሆይ ማረኝ |
| ማረኝ ማረኝ ባለወልዶ ማረኝ | ማረኝ ማረኝ ባለወልድ ሆይ ማረኝ |

አቤት አቤት አቤት --- እሜት እሜት እሜት (እስከዚህ ያለው አንድ አይነት ዜማ ነው)

የግል ጸሎት እዚህጋ ይካሄዳል- ሀገራችንን፣ ቤተክርስቲያችንን ጠብቅ የሚል (በለሆሳስ)

| | |
|---|---|
| እግዜሮ አቦዮ *ኡመኖ ሰገድሆ* | እግዜር ሆይ *አመንሁ ሰገድሁልህ* |
| ፈጣሪ ጎይታዮ " " | ፈጣሪ ጌታዬ " " |
| ታማኝ ጎይታዮ " " | ታማኝ ጌታዬ " " |
| ዛኞቶ ቤይራቶ " " | ንጋትም ጥባት " " |
| ዳቺዮ አባቶ " " | የምድር አባት " " |
| ቅላቶ ጥባቶ " " | ጥዋትም ማታ " " |
| ጊስታዬ አዮዬ " " | ንግስቴ እናቴ " " |
| ባይጦኒ ሆዲሾ " " | የማይጫክን ሆድሽ " " |
| ጎይታዬ ወልዲሾ " " | ከአለቃው ልጅሽ " " |
| ያይቦሊን ይበላህ " " | የማይበላ እበላለሁ " " |

| | | | |
|---|---|---|---|
| እመት ለስተቴ | “ ” | ስህተቴን አመንኩ | “ ” |
| ሰብኖሁም ይዳላ | “ ” | ሰው ነኝና እስታለሁ | “ ” |
| አዩ ለምህራቴ | “ ” | የምህረት እናት | “ ” |
| እምነትን አሊሽ | “ ” | እምነት አለሽ | “ ” |
| በላልቻይ (2) | “ ” | በዓለት | “ ” |
| በላላቻይ ሰንበቻይ | “ ” | በዓላትና ሰንበታት | “ ” |
| ሰንበቶ ሰማዕቶ | “ ” | ሰንበታት ሰማዕታት | “ ” |
| ኢየሱስ አቦዮ | “ ” | ኢየሱስ አባቴ | “ ” |
| ታቦቶ ታምሮ | “ ” | የታምር ታቦታት | “ ” |
| ክርስቶስ ጎይታዮ | “ ” | ጌታ ክርስቶስ | “ ” |
| መጽሐፉ ወንጌሉ | “ ” | መጽሐፈ ወንጌሉ | “ ” |
| ሙኮዮ አቦዮ | “ ” | ሚካኤል አባታችን | “ ” |
| ገብረመንፈስ አቦዮ | “ ” | ገብረመንፈስ ቅዱስ አባቴ | “ ” |
| ባህሪ ባላዮ | “ ” | ታላቁ በኣል | “ ” |
| ገብርኤሎ አቦዮ | “ ” | ገብርኤል አባታችን | “ ” |
| ቄርቆሶ አቦዮ | “ ” | ቂርቆስ አባታችን | “ ” |
| አስራ ሖይቲ በዓሎ | “ ” | 12ቱ በዓላት | “ ” |
| ፋኖዮ አቦዬ | “ ” | ፋኑኤል አባቴ | “ ” |
| ጊዮርጊስ አቦዬ | “ ” | ጊዮርጊስ አባቴ | “ ” |
| ባለወልዶ አቦዮ | “ ” | ባለወልድ አባቴ | “ ” |

የማይራም ወልድዮ “ ” የማርያም ልጅ ሆይ “ ”

አቤት (3) እሜት (3) ከዚህ በኋላ በሌላ ዜማ ይቀጥላል

አብሩ መብራቶ አህ ያቦ እግዜሮ ስለቶ ያወልቢ መብራቶ

(መብራፋችሁን አብሩ እሱ እግዜር ባለበት ቦታ ብርሃን ይሁን)

| አብሩ መብራቶ አህ | ያቦ እግዜሮ ስለቶ | ያወልቢ መብራቶ |
|---|---|---|
| “ ” “ ” | እግዜሮ ደቺ (የምድር አምላክ) | “ ” “ ” |
| “ ” “ ” | የዛኛትን እምነቶ (የጥንት እምነት ነውና) | “ ” “ ” |
| “ ” “ ” | የማይራምን (የእመቤት ስለት) | “ ” “ ” |
| “ ” “ ” | የባይራትን እምነቶ (የጥንት የጥዋቱ) | “ ” “ ” |
| “ ” “ ” | የቅላትን እምነቶ (ከፍታ ላይ ያለው እምነት) | “ ” “ ” |
| “ ” “ ” | ያዶራታን እምነቶ (የአደራ እምነት) | “ ” “ ” |
| “ ” “ ” | የጥባትን እምነቶ (የመሰረት እምነት) | “ ” “ ” |
| “ ” “ ” | የጦሬታይ እምነቶ (የኔ ቻይ) | “ ” “ ” |
| “ ” “ ” | ይዱን የባል (የአመት በዓል) | “ ” “ ” |
| “ ” “ ” | የገዳሚን እምነቶ (የገዳማዊያን እምነት) | “ ” “ ” |
| “ ” “ ” | የሱባኤን እምነቶ (የሱባኤ እምነትን) | “ ” “ ” |
| “ ” “ ” | ያንፋንለፎን (የእናቶችን እምነት) | “ ” “ ” |
| “ ” “ ” | የአብረሃምን ስለቶ (የአብርሃም ስለት) | “ ” “ ” |
| “ ” “ ” | የቦስታቶስ (ስለ አውስጣጢዮስ ታቦት -ታቦተ ኢየሱስ) | “ ” “ ” |
| “ ” “ ” | አርባዕቱ እንስሳ | “ ” “ ” |

“ ” ” የኪዳን ምህረት እምነቶ “ ” “ ”

“ ” ” የመድኃኒዓለም ስልቶ “ ” “ ”

“ ” ” የዮሐንስን እምነቶ “ ” “ ”

“ ” ” የሰንበትን እምነቶ “ ” “ ”

“ ” ” የታቦትን እምነቶ “ ” “ ”

“ ” ” የባላልቻ እምነቶ (የበዓላት) “ ” “ ”

“ ” ” የመጽሐፍን እምነቶ “ ” “ ”

“ ” ” ኢየሱስን እምነቶ “ ” “ ”

“ ” ” የወንጌልን እምነቶ “ ” “ ”

“ ” ” የክርስቶስ እምነቶ “ ” “ ”

“ ” ” የገብረመንፈስ እምነቶ “ ” “ ”

“ ” ” የስላሴን እምነቶ “ ” “ ”

“ ” ” የጭርቆስ ስለቶ “ ” “ ”

“ ” ” የገብርኤል ስለቶ “ ” “ ”

“ ” ” የ12ን እምነቶ “ ” “ ”

“ ” ” ጎርጊስን እምነቶ “ ” “ ”

“ ” ” የባለወልድን እምነቶ “ ” “ ”

አቤት (3) - እሜት (3)

የግል ጸሎት እዚህ ጋር አለ

ስባተሄ እግዜሮ ስባተሄ -ዋበን ደረጉተሄ (2)

(ምስጋና ለአምላክ- ስጠኝ የዕለት ጉርስ)

| | | | |
|---|---|---|---|
| ስባተሄ | እግዜሮ | ስባተሄ | ዋበን ደረጉተሄ |
| " | ተፈናይ (የቤቴ ጉበን) | " | " " |
| " | ኢርኮዋይ (መደገፊዬ) | " | አልሃንባተሄ (ክብር አለህ) |
| " | ዳዮዋይ (ከለላዬ) | " | ያሌኘይ ተሃተቴ (ያለኝ አንተ ነህ) |
| " | አይጠኖ (የማይጨክን) | " | ያግባህ ስባተሄ (ምስጋና ይግባህ) |
| ስባተሼ | እናቴ | " | ውብሽኝ ዳረጉተሄ(የዕለት ጉርስ ስጭኝ) |
| " | አይጠኖ (የማትጨክኚ) | " | ያግባሽ ስባተሼ |
| " | ኢርኮዋይ (መደገፊዬ) | " | ያግባሽ ስባተሼ |
| " | አብድያ (ጠበቂዬ) | " | ያግባሽ ስባተሼ |
| ስብተሄ | ባለወልዶ | " | ያግባህ ስበተሄ |
| አቤት (3) | | | እሜት (3) |

የግል ጸሎት (ኢትዮጵያን ጠብቅ፣ መንግስትን በመንበሩ አኑር፣ እረኛን በብረሃ ጠብቀው፣ ልጆቻችንን ጠብቅልን፣ ይቅር በለን፣ ቃላችንን አስምርልን፣ ልጆቻችንን በያሉበት ጠብቅልን)

(ከዋኝ ሴቶች - ኦብሴ ቢጢሉ፣ በሾ ዱሬሳ፣ ሂኮ አምዶ፣ ሀዊ ዳቢ፣ ዱሬቲ ቁፋ፣ ሸንዶ ገብሮ፣ ብርዝነሽ ከፈኒ)

# ተረክ አምስት

*በዛይ ማህበረሰብ በአንጋፋ ቤት የሚቀርብ ምርቃት*

| | | |
|---|---|---|
| ኢትዮጵያ ነገየ የሳነን | - | ኢትዮጵያን ሰላም ያድርግልን |
| ኦሮሞን በደንበላቴን ድርነን | - | ከኦሮሞዎቹም ጋር ሰላም ያድርገን |
| ንፉሴኛይ በአልጋኒያቴን ድርነን | - | መንግስታችንን በዙፋኑ ያኑርልን |
| ደሲቴኛይ ነገያ የሳነን | - | ደሴቶቻችንን ሰላም ያድርግልን |

ሁሉምኒ ቢስደቺኒ የበሱሁም ያጦብጤይ -ሁሉንም በሀገሩ እንደ ተጨበጠ በሶ ያድርገው

| | | |
|---|---|---|
| ያይትናክ ደብር የሳነን | - | ለመጥፎ የማይተሳሰብ ያድርገን |
| እግዜር ጎይታይ ሀድ የሳነን | - | ጌታ አምለክ አንድ ያድርገን |
| በሃይማኖት ይመጣል ያውለን | - | በሃይማኖት የሚመጣብንን ያርቅልን |
| ሃይማኖተኛ ይነካብና ያውለን | - | ሃይማኖትን ከሚነካብን ይሰውረን |
| በደቺ ያወጣል ያሀተርነን | - | ከስደት ይጠብቀን |
| እርብ ወጥማት ያሀተርነን | - | ረሃብና ጥምን ያርቅልን |
| ቡራኪ ስሙር የሳነን | - | ቡራኪውን ያስምርልን |
| አሚን! | - | አሜን! |

(አቶ ስቡህ ገብረ ማርያም - በቀን 2/08/05 ዓ.ም)

# አባሪ ሁለት

## ለመረጃ ሰጪዎች የቀረቡ ጥያቄዎች

### አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

### በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

### የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

ዝዋይ ደስያት ገደምና አድባራትን ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎችን በማጥናት የትውፊቶቹን ፋይዳና ትዕምርታዊነት ማሳየትን ዓላማ አድርጌ ለምሰራው ጥናቱ ግብዓትን ለማግኘት ለመረጃ አቀባዮቹ የሚቀርቡ መደበኛ ቃላዊ ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ማሳሰቢያ፡- ቀጥሎ ለሚቀርቡት ጥያቄዎች እርስዎ የሚሰጡት ምላሽ ለጥናቱ መሳካት ትልቅ አስተዋጽኦ አለው፡፡ ስለዚህ ለጥያቄዎቹ ተገቢውን ምላሽ በመስጠት እንዲተባበሩኝ ስጠይቅ በታላቅ ትህትና ነው፡፡ እርስዎም ምላሽ ለመስጠት ፍቃደኛ በመሆኗ ከወዲሁ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

ክፍል አንድ፡- ገዳምና አድባራቱ በደስያቱ ከመመስረታቸው በፊት ስለ ሐይቁና አከባቢው <u>የሚነገሩ ተረኮችን ለመፈተሽ የሚቀርቡ ጥያቄዎች</u>

1. ስለ ሐይቁና ደስያቱ አፈጣጠር የሚነገረው ነገር ምንድን ነው?
2. በጥንት ጊዜ በተለያየ ጊዜ ወደ ደስያት የገቡት ጎሳዎች እነማና ናቸው?
3. እነዚህ ጎሳዎች በምን ምክንያት ወደዚህ ስፍራ ሊመጡ ቻሉ?
4. ወደ ደስያቱ የገቡበትን መንገድ ቢጠቅሱልኝ? (ከመጓጓዣ ጋር በተያያዘ)
5. ታቦተ ጽዮን ወደ ስፍራው ከመምጣቷ በፊት በቦታው የነበረው ሁኔታ ምን ይመስላል?

ክፍል ሁለት፡- <u>ከስያሜ አሰጣጥ ጋር በተያያዘ መረጃ ለመሰብሰብ የሚጠየቁ ጥያቄዎች</u>

6. የሐይቁና የደስያቱ ስያሜና በምን በምን ምክንያት እንደተሰጠ ቢነግሩኝ?
7. ለሐይቁ ዝዋይ የሚለው ስያሜ ከመሰጠቱ በፊት ሌላ ስያሜ ይኖር ይሆን?
8. ከከተማው ስያሜው ጋርስ እንዴት አንድ አይነት ሊሆን ቻለ? ለከተማው መቆርቆር ሐይቁ

   ወይስ ለሐይቁ ከተማው ምክንያት ሆነ?

9. "Haroo Dambal (ሀሮ ደንበል)" የሚለው የኦሮምኛ ቋንቋ ስያሜ ለሐይቁ እንዴት ተሰጠ?

10. ለየደስያቱ በኦሮምኛ ቋንቋ የተሰጡት ስያሜዎች ከሐይማኖታዊ ስያሜ የቀደሙ ናቸው? ወይስ ከቀርብ ጊዜ ወዲህ የታዩ ናቸው?

ክፍል ሶስት፡- ገዳምና አድባራቱ በደስያቱ ከመመስረታቸው ጋር በተያያዘ እና በጊዜ ሂደት የተፈጠሩ ክስተቶችን አስመልክቶ የሚተረኩትን ተረኮች ለመሰብሰብ የሚቀርቡ <u>ጥያቄዎች</u>

11. በእያንዳንዱ ደሴት የገኙ የነበሩና አሁን የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ስንት ናቸው?

12. በአንድ ቤተክርስቲያን ምን ያህል ጽላቶች ይገኛሉ? በጥንቱ እና በአሁኑ ጊዜ የቁጥር መበላለጥ ካለ በምን ምክንት የመጣ ነው?

13. ከታቦተ ጽዮን ወደዚህ ስፍራ መምጣት ጋር ስለሚነገረው ታሪክ የሚያውቅትን ቢነግሩኝ? (ዓ.ምቱ መቼ ነው? ወደ ደስያቱ በምን መልኩ ገቡ? ገዳምና አድባራት ሊታነጹ የቻሉበት ሂደት ምን ይመስላል?)

14. በዐፄ ዓምደ ጽዮን (1307-1337) እና በንጉስ ሰይፈ አርዕድ (1337-1365) ዘመን ነገስታቱን በመቃወማቸው ወደዚህ ስፍራ በግዞት ስለ ገቡት አባቶች የሚያውቁትን ነገር ቢነግሩኝ?

15. ገዳማዊ ህይወት በእነዚህ በግዞት ወደ ደሴቶቹ በመጡት አባቶች ወይስ ታቦተ ጽዮን ይዘው በመጡት የተጀመረ ነው? ከዚሁ ጋር በተያያዘ ክርስትና ወደ ደሴቱ ገባ ብለን ልንናገር የምንችለበት ጊዜ መቼ ነው? እንዴት?

16. ለዝዋይ ሐይቅ ገዳማት መመስረት በዋናነት የሚጠቀሱ ቅዱሳን አባቶች ይኖሩ ይሆን? (ለምሳሌ፣ የደብረ ዳሞን ገዳም ስናነሳ አባ አረጋዊን እንደምንጠቅሰው ሁሉ)

17. የዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራት በሌሎች ስፍራ ለተመሰረቱ አብያተ ክርስቲያናት እንደ መክንያት ይጠቀሳሉ፡፡ ከምን የተነሳ ነው? (ከቁሉቢ ገብርኤል ጋር የሚያያዘው ጉዳይስ?)

18. በደስያቱ ላይ ያሉት ገዳመት ያላቸው የአሰራር የታሪክ ቅደም ተከተልን እና በሁሉም ደስያት ላይ ቤተክርስቲያን ሊሰራ የቻለበትን ምክንያት ቢነግሩኝ? በአመሰራረት ሂደቱ የተከናወኑ ዋና ዋና ድርጊቶች ምንድናቸው? በእነማን አማካይነት?

19. ታቦተ ጽዮን ወደ ቀደመ ስፍራዋ ከተመለሰች ቡኋላ ሌሎች ጽላቶች እንዴት መጡ? ዘመኑስ መቼ ነው? በእነማን አማካይነት?

20. የደስያቱ አብያተ ክርስቲያናት የገዳምነት ማዕረግ ያገኙት መቼ ነው? በወቅቱ ስለ ነበረው የአገልጋዮች ቁጥር፣ የመተዳደሪያ ንብረትና ገዳማዊ ስርዓት ቢነግሩኝ?

21. ስፍራው ለገዳምነት የተመረጠበት ዋና ምክንያት ምንድን ነው? በታሪክ ሂደት ያጋጠመው ነገር ካለ አያይዘው ቢያነሱልኝ

22. ከደስያቱ መካከል ትልቁ ደሴትና ለትልቅነቱ ማሳያነት የሚጠቀሰው ነገር ምንድን ነው?

23. በገዳምና አድባራቱ መካከል ያለው የግንኙነት ሁኔታ ምን ይመስላል?

24. የገዳምና አድባራቱ የአስተዳደር መዋቅር ምን ይመስላል? የመነኮሳቱ ሱታፌስ?

25. በገዳምና አድባራቱ ውስጥ ይሰጥ የነበረው የትምህርት ዓይነት ዘርዝረው ቢነግሩኝ?

26. በእነዚህ ገዳምና አድባራት የሚሰጠውን ትምህርት ተምረው፣ ምንኩስና ተቀብለው ይሄንን ስርዓት በሌሎች ስፍራ ለማስረጽ የተጓዙ ካሉ ቢጠቅሱልኝ?

27. ገዳምና አድባራቱ በደስያቱ መመስረታቸው ለአካባቢው እና ለሀገሪቱ ያበረከቱት እንዲሁም እያበረከቱ ያሉት አስተዋጽኦ ምንድን ነው?

28. የገዳምና አድባረቱ ይዞታ አሁን ካላቸው እና ቀድሞ ከነበራቸው ጋር በማነጻጸር ቢነግሩኝ? በአሁኑ ሰዓት ያላቸው የገቢ ምንጭስ ምን ይመስላል?

29. ይሄንን ታሪካዊ ስፍራ ለማስተዋወቅ አሁን በየገዳምና አድባረቱ እየተሰራ ያለው ነገር ምን ይመስላል?

30. በደስያቱ ላይ በቅድሚያ የመኖር ዕድሉን ያገኘው የማህበረሰብ ጎሳ ማነው?

31. አሁን በደስያቱ ስለሚኖሩት እና ቀድሞ በደስያቱ ይኖሩ በነበሩት ሕዝቦች መካከል በንጽጽር ሲታይ ያለውን ልዩነት ቢነግሩኝ?

32. በማህበረሰቡ ባህል እና ሐይማኖት መካከል ያለው ግንኙነትስ ምን ይመስላል?

33. የዛይ ማህበረሰብ ወደ ደስያቱ የመጡበት ጊዜ እና የመጡበትን ምክንያት ቢገልጹልኝ?

34. የዛይ ማህበረሰብ ሀረግ አቆጣጠር ከየትኛው ጎሳ ይጀምራል? ማህበረሰቡ ከሌሎች ጎሳዎች ጋር የነበራቸውን ቢነግሩኝ? አሁን በደስያቱ የሚገኙት ከየትኛው ጎሳ የሚመደቡ ናቸው?

35. ከደስያቱ ወደ ሌሎች አጎራባች ህብረተሰቦች ለምን ሊሰደዱ ቻሉ? የሄንን ስደት እንዴት ማስቆም ይቻላል? መሰደዳቸው ለታሪካዊ ስፍራው የሚኖረው አሉታ ምንድን ነው?

ክፍል አራት፡- <u>ስለ ስፍራው ቅድስና የሚያትቱ ተረኮችን በተመለከተ የሚጠየቁ ጥያቄዎች</u>

36. በዚህ ስፍራ በተለያየ ጊዜ ተፈጸሙ ስለሚባሉት ድንቅ ተዓምራት ቢነግሩኝ?

37. የምንኩስና ህይወት በገዳማቱ ተጀምሮ የነበረበት ጊዜ መቼ ነው? የምንኩስና ስርዓቱን ከሌሎች የሚለየው ምንድን ነው? የተለያዩ አካላት በዚህ ስፍራ በምንኩስና ለመኖር ምክንያት የሚያደርጉት ነገርስ ምንድን ነው?

38. በደብረ ጽዮን ስለሚገኘው ፍል ውሃ የሚያውቅትን ነገር ቢገልጹልኝ?

39. በስውር እንዳለ ስለሚነገረው ታቦተ ኢየሱስ የሚያውቁትን ታሪክ ቢነግሩኝ?

40. በደስያቱ የሚከበሩት ታላላቅ በዓላት መቼ መቼ ናቸው? በምን ምክንያት ይከበራል?

ክፍል አምስት፡- በደስያቱ ገዳምና አድባራት ስለሚገኙ ቅርሶች መረጃ ለመሰብሰብ የሚያግዙ <u>ጥያቄዎች</u>

41. ብዙ ጊዜ የደስያቱ ገዳማት የሀገራችን አብያተመዛግባት ናቸው፤ እየተባለ ሲነገር ይሰማል። ይሄ እንዴት ነው?

42. ይሄንን ስፍራ ከሌሎች ቦታዎች ልዩ ሆኖ እንዲጠራ ያደርገዋል የሚሉትን ቅርስ ቢጠቅሱልኝ?

43. ከጥንታዊ የብራና መጽሐፍቱ አብዛኞቹ የአጼ ዳዊትን ስም እንደያዙ ይነገራል። ለምን ይሆን? ቅርሶቹ በምን ምክንያት እዚህ ሊገኙ ቻሉ?

44. በተለያዩ ነገስታት ለገዳማቱ የተበረከቱ ቅርሶች አሉ? ካሉ ስጦታዎቹን በዝርዝር ቢነግሩኝ?

45. ከቅርሶቹ መካከል አሁን አገልግሎት የሚሰጡ ካሉ ቢጠቅሱልኝና አገልግሎቱን ቢነግሩኝ?

46. የብራና መጽሐፍቱ በዚህ ስፍራም ይዘጋጁ ነበር? ወይስ ሁሉም ከሌላ ስፍራ የመጡ ናቸው? በዚህ ስፍራ የሚዘጋጁ ከነበሩ የአሰራር ሂደቱ ምን ይመስል ነበር?

47. የዓጼ ዘድንግል የልጅ ልጅ የሆነችው አጋያ ወደዚህ ስፍራ በመጣች ሰዓት መጽሐፍ ወዳድ ስለሆነ አንቷ አንድ መጽሐፍ አውጥታ ልካለት እንደነበረ ይነገራል። የትኛው መጽሐፍ ነው?

48. በገዳምና አድባራቱ ያሉት ጥንታዊ ቅርሶች ያላቸው የቱሪስት መስህብነት ምን ይመስላል?

49. ጥንታዊ ቅርሶቹ ድሮ ከነበረው ይዘታቸው አንጻር አሁን ያሉበት ሁኔታ እንዴት ይገለጻል? (ከመጥፋትም ሆነ ከመበላሸት ጋር በተያያዘ)

50. ጥንታዊ ቅርሶቹን በአይነትና በአገልግሎት ብንፈርጃቸው እንዴት ይገለጻሉ? (ንዋየ ቅድሳት፣ ቅዱሳን መጽሐፍት፣ የነገስታት የወግ ዕቃዎች ወዘተ.)

51. የብራና መጽሐፍት የተሰሩበትን የቆዳ ዓይነት እና የተጻፉበትን ቀለማት ቢገልጹልኝ?

52. በስፍራው ካሉት ቅርሶች በባህልና ቱሪዝም ቢሮ የተመዘገቡት ምን ያህሎቹ ናቸው? ከዚህ በፊት በቅርሶቹ አመካይነት ለስፍራው የተደረገ ማበረታቻ ካለ ቢገልጹልኝ?

53. ገዳምና አድባራቱ ስለ ታነጹበት ቅርጽ እና ስለ መስሪያ ጥሬ ዕቃዎች ቢነግሩኝ?

*ስለ ትብብርዎ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፤ እግዚአብሔር ይስጥልኝ !*

*ፍጹም ኩራባቸው*

## ቁሳዊ ባህሎችን የመሰነጃ ቅጽ ናሙና

| ተ.ቁ. | የቁሱ መጠሪያ | የቁሱ ዓይነት | ብዛት | አገልግሎት | የሚሰራበት ጥሬ ዕቃ | የባለሙያ ማንነት | የአሰራር ሂደት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | | | | | | | |

# አባሪ ሶስት

## የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር መግለጫ

| ተ.ቁ. | ሙሉ ስም | ዕድሜ | ጾታ | የትምህርት ደረጃ | ሐይማኖት | የትውልድ ስፍራ | ሞያ | ርዕሰ ጉዳይ | ቃለ መጠይቁን የሰጡበት ቀን | መረጃው የተሰበሰበበት ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ አበጋዝ ኩንቢ | 75 | ወ | - | ኦርቶዶክስ | ገሊላ | ግብርና የዓሣ አምራች | ስለ ደብረ ሲናና ገሊላ ደስያት ታሪክ | 25/07/05 | ዝዋይ ከተ |
| 2 | አቶ ነገዎ ማርኖ | 60 | ወ | - | ኦርቶዶክስ | ገሊላ | ግብርና የዓሣ አምራች | ስለ ደብረ ሲናና ገሊላ ደስያት ታሪክ | 25/07/05 | ዝዋይ ከተ |
| 3 | አባ ገዳ አብዱርሃማን ዳቀቢ | 31 | ወ | - | ወቄፌታ | አዳሚ ቱሉ | አባ ገዳ | ስለ ሐይቁና ህዝቦቹ | 26/07/05 | ዝዋይ ከተ |
| 4 | አቶ ገዳ መርፌቶ | 54 | ወ | - | ሙስሊም | ባቱ | ገበሬ | ስለ ሐይቁና ህዝቦቹ | 26/07/05 | ዝዋይ ከ |
| 5 | አቶ ገመዳ አቱሎ | 60 | ወ | - | ሙስሊም | ባቱ | ገበሬ | ስለ ሐይቁና ህዝቦቹ | 26/07/05 | ዝዋይ ከ |
| 6 | አቶ ሰፈዎ ነገዎ | 38 | ወ | ዲግሪ | ሙስሊም | ባቱ | የወረዳ ባህልና ቱሪዝም ሀላፊ | ስለ ሐይቁና ደስያቱ የቱሪስት መዳረሻነት | 26/07/05 | ዝዋይ ከ |
| 7 | አቶ ከዲር አቢቲ | 25 | ወ | ዲግሪ | ሙስሊም | ዝዋይ ዱግዳ | ባህል ቱሪዝም ሰራተኛ | ስለ ሐይቁና ደስያቱ የቱሪስት መዳረሻነት | 26/07/05 | ዝዋይ ከ |
| 8 | አቶ እሼቱ ጉተማ | 27 | ወ | ድግሪ | ኦርቶዶክስ | ኢተያ | ባህል ቱሪዝም ሰራተኛ | ስለ ሐይቁና ደስያቱ የቱሪስት መዳረሻነት | 26/07/05 | ዝዋይ ከ |
| 9 | ሊቀ ካህናት ጸጋዬ ቡኪ | 50 | ወ | 9ኛ ክፍል | ኦርቶዶክስ | ገሊላ ደሴት | የአዳሚ ቱሉ ስራ አስኪያጅ | ስለ ገሊላና ደብረ ሲና ደስያት ታሪክና ቅርስ | 27/07/05 | ዝዋይ ከ |
| 10 | መምሬ ባንቲሁን ሀብተ ማርያም | 76 | ወ | - | ኦርቶዶክስ | ደብረ ጽዮን | የደብሩ አገልጋይ | በደስያቱ ስለሚነገሩ ተረኮችና ስለ ቅርሶች | በ30/07/05 በ02/08/05 | ደብረ ጽ ደሴት |
| 11 | አባ ገብረእግዚአብሔር አለሙ | 38 | ወ | - | ኦርቶዶክስ | ላስታ | የደብረ ጽዮን አስተዳዳሪ | ስለ ደብረ ጽዮን ገዳም ታሪክና ቅርሶች | 30/07/05 | ደብረ ጽ ደሴት |

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 12 | ወ/ሮ ብርዝነሽ ከፊኒ | 65 | ሴ | - | " " | ደብረ ጽዮን | የቤት እመቤት | በሐይማኖቱ ውስጥ ሴቶቹ ስላላቸው ባህል | 01/08/05 | ደብረ ጽዮን ደሴት |
| 13 | አቶ ነገዎ ሾጎሮ | 70 | ወ | - | " " | ደብረ ጽዮን | ሽመና | ከሐይማኖቱ ጋር በትስስር ስለሚፈጸሙ ባህሎች | 01/08/05 | ደብረ ጽዮን ደሴት |
| 14 | አቶ ቡኔ ሀምዳ | 85 | ወ | - | " " | " | ገብርና | ከሐይማኖቱ ጋር በትስስር ስለሚፈጸሙ ባህሎች | 01/08/05 | " |
| 15 | አቶ ስሜ ካዮ | 63 | ወ | - | " " | " | ሽመናና ግብርና | ከሐይማኖቱ ጋር በትስስር ስለሚፈጸሙ ባህሎች | 01/08/05 | " |
| 16 | መምሬ መልአኩ ገብረ ማርያም | 75 | ወ | - | " " | " | ክህነት | በደብረ ጽዮን ቅርስና የደስያቱ ታሪክ | 01/08/05 | " |
| 17 | መምሬ ገብረ መስቀል ሂርጳ | 69 | ወ | - | " " | " | ክህነት | ስለ ደስያቱ ገዳምና አድባራቱ አጠቃላይ ታሪክ | 02/08/05 | " |
| 18 | እማሆይ ወለተ ሰንበት | - | ሴ | - | " " | ደብረ ሲና | መነኩሲት | ስለ ዛይ ህዝብ መዝሙር | 02/08/05 | " |
| 19 | ወ/ሮ በሾ ዱሬሳ | 50 | ሴ | - | " " | ደብረ ጽዮን | የቤት እመቤት | ስለ ዛይ ህዝብ መዝሙር | 02/08/05 | " |
| 20 | ወ/ሮ ሂኮ አምዳ | 45 | ሴ | - | " " | " | የቤት እመቤት | ስለ ዛይ ህዝብ መዝሙር | 02/08/05 | " |
| 21 | ወ/ሮ ሃዊ ዳቢ | - | ሴ | - | " " | " | የቤት እመቤት | ስለ ዛይ ህዝብ መዝሙር | 02/08/05 | " |
| 22 | ወ/ሮ ዱሬቲ ቁፋ | 40 | ሴ | - | " " | " | የቤት እመቤት | ስለ ዛይ ህዝብ መዝሙር | 02/08/05 | " |
| 23 | ወ/ሮ ሸንዴ ገብሮ | - | ሴ | - | " " | " | የቤት እመቤት | ስለ ዛይ ህዝብ መዝሙር | 02/08/05 | " |
| 24 | እማሆይ ወለተ ሚካኤል | - | ሴ | - | " " | | መነኩሲት | ስለ ዛይ ህዝብ መዝሙር | 02/08/05 | " |
| 25 | አቶ ገብሩ ጊዮርጊሶ | 70 | ወ | - | " " | " | ዓሣና ግብርና | የቤተክርስቲያን ጅማሮ | 02/08/05 | " |
| 26 | አቶ ኩረቱ ወዮ | 80 | ወ | - | " " | " | ዓሣ አምራችና ግብርና | ስለ ገዳምና አድባራቱ የአመሰራረት ታሪክ | 02/08/05 | " |
| 27 | ዷጋጋ አምዳ | 62 | ወ | - | " " | " | ግበርና | ስለ ገዳምና አድባራቱ የአመሰራረት ታሪክ | 02/08/05 | " |
| 28 | ብሪቱ ቱፋ | - | ሴ | | " " | | የቤት እመቤት | ስለ ቤተክርስቲያኑ የአመሰራረት ታሪክ | 02/08/05 | " |
| 29 | አቶ ስቡህ ገብረ ማርያም | 91 | ወ | - | " " | " | ግብርና ሽመና | አጠቃላይ ታሪክና ቅርስ | 02/08/05 | ደብረ ጽዮን |
| 30 | አቶ ታደሰ አሼ | 90 | ወ | - | " " | ጠዴቻ | ግብርና | ስለ ገዳምና አድባራቱ | 05/08/05 | ደብረ |

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | አጠቃላይ ታሪክና ቅርስ | | አብርሃም |
| 31 | አቶ ከፈኒ. እጀራ | 60 | ወ | - | " " | ጠዴቻ | ግብርና | የደብረ አብርሃም ታሪክ | 05/08/05 | " |
| 32 | አቶ ዳቢ. ኢደኦ | 70 | ወ | - | " " | ጠዴቻ | ግብርና | የደብረ አብርሃም ታሪክ | 05/08/05 | " |
| 33 | አቶ ቁፋ በዳሳ | 65 | ወ | - | " " | ጠዴቻ | ግብርና ሽመና | የደብረ አብርሃም ታሪክ | 05/08/05 | " |
| 34 | አቶ ኩርጂ ዳቢ. | 55 | ወ | - | " " | ጠዴቻ | ዓሣና ግብርና | የደብረ አብርሃም ታሪክ | 05/08/05 | " |
| 35 | መምሬ አስፋው ቱፋ | 50 | ወ | - | " " | ጠዴቻ | ዓሣና ግብርና እና ክህነት | ስለ ገዳምና አድባራቱ ታሪክና ገቢረ ተአምር | 06/08/05 | " |
| 36 | መምሬ ኪዳነ ማርያም ደጋጋ | 45 | ወ | - | " " | ጠዴቻ | ዓሣና ግብርና እና ክህነት | ስለ ገዳምና አድባራቱ ታሪክና ገቢረ ተአምር | 06/08/05 | " |
| 37 | አቶ ጉደታ ሚደግሶ | 60 | ወ | - | " " | ጌቴሴ ማኒ. | ዓሣና ገብርና | ስለ ጌቴሴማኒ. ደብር ታሪክና ቅርስ | 07/08/05 | ፉንድሮ |
| 38 | አቶ ደስዮ በዳዳ | 50 | ወ | - | " " | ጌቴሴ ማኒ. | ዓሣና ገብርና | ስለ ጌቴሴማኒ. ደብር ታሪክና ቅርስ | 07/08/05 | ፉንድሮ |
| 39 | መምሬ ሀይለ ጊዮርጊስ አሴ | 47 | ወ | - | " " | ጌቴሴ ማኒ. | ክህነት፣ ዓሣና ገብርና | ስለ አርበዕቱ እንስሳ ቤተክርስቲያንና ቅርስ | 07/08/05 | ፉንድሮ |
| 40 | አባ አስራት | 77 | ወ | - | " " | መራ ቤቱ | ክህነት | ስለ አርበዕቱ እንስሳ ቤተክርስቲያን አመሰራረት | 07/08/05 | ፉንድሮ |
| 41 | ቀሲስ ተስፋዬ ነቢ. | 50 | ወ | - | " " | ደብረ ሲና | የሲና፣ ገሊላና ቦጨሳ ሀላፊ | ስለ ገሊላና ደብረ ሲና ታሪክና ቅርስ | 09/08/05 | ቦጨሳ |
| 42 | መርጌታ ሰምረ ግደይ | 30 | ወ | 11ኛ | " " | ማየጨ ው | መርጌታ | የደስያቱ ታሪክና መጻፍ ቅዱሳዊ አስተምሮ | 10/08/05 | ዝዋይ |
| 43 | ኩሼ ጎንደር | 72 | ሴ | - | " " | ጽዮን | መነኩሲት | ስለ ገሊላ ደሴት ደብር | 11/08/05 | ገሊላ ደሴት |
| 44 | አብረሃም ገብረስላሴ | 65 | ወ | - | " " | - | | ስለ ገሊላ ደሴት ደብር | 11/08/05 | ገሊላ ደሴት |
| 45 | አቶ ቱራ ነቢ. | 35 | ወ | - | " " | ሲና | ዓሣ አምራች | የደብረ ሲና ቅርሶች | 14/08/05 | ደብረ ሲና |
| 46 | ወ/ሮ ዳንሴ ቁብሳ | - | ሴ | - | " " | መቂ | የቤት እመቤት | ስለ ደስያቱ ታረክና ባህል | 13/08/05 | ደብረ ሲና |
| 47 | ወ/ሮ አዩ ኩሼ | - | ሴ | - | " " | መቂ | የቤት እመቤት | ስለ ደስያቱ ታረክና ባህል | 13/08/05 | ደብረ ሲና |
| 48 | ወልደ ጊዮርጊስ ፋሮ | 98 | ወ | - | " " | ጽዮን | ክህነት | የቤተክርስቲያን ጅማሮ | 14/08/05 | ደብረ ጽዮን |

➢ መረጃው የተሰበሰበው በቴፕ ሪከርደር፣ በፎቶና ቪዲዮ ካሜራ እንዲሁም ማስታወሻ ደብተር ነው፡፡

# አባሪ አራት

## ከስፍራው የተወሰዱ ፎቶዎች በጥቂቱ



እጥኚው ወደ ዝዋይ ሐይቅ ደሴያት በተለያየ ጊዜ ያደረገውን ጉዞ የሚያሳዩ



የዝዋይ ሐይቅን፣ ደሴያቱን፣ ቤተክርስቲያናቸውንና የአዕዋፍት አለቶችን በመጠኑ የሚያሳዩ




የደሴያቱን ነዋሪዎች  መጓጓዣና የሚኖሩበት ቤት እንዲሁም ምግባቸው የሆኑትን የዓሣ ዝርያዎች የሚያሳዩ





የገዳምና አድባራቱን ቅርሶች የሆኑ መጽሐፍትና አትሮናስ

የድንጋይ ደውል





ከገዳሙ በንግስት ዘውዲቱ የተበረከተ

በደብረ ጽዮን ደሴት የሚገኙ የፍል ውኃ የጸበል ስፍራዎች








አጥኚው በቃለመጠይቅ ከመረጃ ሰጪዎች ጋር በተለያዩ ሁኔታዎችና ስፍራዎች





አጥኚው በመስክ የዝዋይ ሐይቅ ደሴያትን ታሪካዊ ቦታ ሲጎበኝና ቅርሶችን ሲመለከት የሚያሳዩ





ንፌሳዊያን ተጓዦች በጉዞ ላይና በደሴቱ ሲያርፉ ያለውን ሁኔታ የሚያሳይ የውጪ ዜጎች በጉብኝት ላይ





አስተርዮ ማርያም ክብረ በዓል በዝዋይ ሐይቅ ደብረ ጽዮን ደሴት






በዝዋይ ሐይቅ ዳር እየተሰሩ ያሉ መዝናኛዎች፣ በደብረ ጽዮን የጎብኚ ማረፊያና የደሴያቱን እደጥበብ የሚያበረታታ ማህበር

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ADDIS ABABA UNIVERSITY

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮ ሚዩኒኬሽን
የአማርኛ ቋንቋ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር
ክፍለ ትምህርት

Humanities, Lang. Studies, Journalism & Com
Department of Amharic Lang. Lite. & Folklore

☎ +251-11-123-98-00 Ext. 127
+251-11-123-97-02
✉ 1176

E-mail: dtell@ils.aau.edu.et

http://www.aau.edu.et/index.php/ethiopian-languages-and-literature

---

ቀን፦ 27/05/05 ዓ.ም

## ለሚመለከተው ሁሉ

ጉዳዩ፦ ትብብር ይመለከታል

የክፍለ ትምህርታችን የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር ተማሪ የሆኑት አቶ ፍጹም ሃይለብቻው ባላቸ "የዝዋይ ሐይቅ ገዳማት የአመሠራረት ታሪካቸ እና የቁሳዊ ባህላቸ ጥናት" በሚል ርዕስ የኤም.ኤ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፍ በማዘጋጀት ላይ ይገኛሉ፡፡ ስለዚህ ጥናታቸውን አጠናቀው ለማቅረብ የሚያስችላቸውን አስፈላጊውን መረጃ እንዲያገኙ እንድትተባበሯቸው እየጠየቅን ለሚደረግላቸው ትብብር በቅድሚያ እናመሰግናለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ዶ/ር ደረጀ ገብሬ
የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር
ትምህርት ክፍል ሊቀመንበር

ቁጥር 8533/5046/2003
Ref. No.

13-6 ቀን ፳፻2 ዓ/ም

Date ________ 200______

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
# መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት
# Ethiopian Orthodox Tewahedo Church
# PATRIARCHATE HEAD OFFICE

ለምሥራቅ ሸዋ ሀገረ ስብከት
ናዝሬት
ለአርሲ ሀገረ ስብከት
አሰላ

አቶ ፍጹም ኩራባቸው ባልቻ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የዶክተር ትምህርት ክፍል ድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር ተማሪ ሲሆኑ ለመመረቂያ ጽሑፍ ዝግጅት እንዲረዳቸው በዝዋይ ደሴት ባሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ገዳማት ዙሪያ ጥናትና ምርምር ለማድረግ እንዲችሉ የትብብር ደብዳቤ እንዲጻፍላቸው ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በተጻፈ ደብዳቤ ጠይቀዋል።

ስለዚህ በ2000 ዓ/ም ስለ ቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ በተመለከተ ከልዩ ጽ/ቤት የተላለፈው መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ አመልካቹ ለጥናትና ምርምር በሚመጡበት ወቅት በአናንት በኩል ትብብር እንዲደረግላቸው እናሳስባለን።

"ሰላመ እግዚአብሔር ከሁላችን ጋር ይሁን"

ግልባጭ፡
ለብፁዕ ዋና ሥራ አስኪያጅ
ለብፁዕ ዓቃቤ መንበረ ፓትርያርክ ልዩ ጽ/ቤት
ለቅ/ጥ/ጥ/ም/ት/ቤት መጻሕፍት ወመዛግብት
ለአቶ ፍጹም ኩራባቸው ባልቻ
አዲስ አበባ

አባ ፊልጶስ የጠቅላይ ቤተ ክህነት
ዋና ሥራ አስኪያጅ የኢሉባቦርና የጋምቤላ
ሀ/ስብከት ሊቀ ጳጳስ
Abba Philipos G/M of the EOTC
Archbishop of Illubabor & Gambella Dioceses


የመልእክት ሣጥን ቁጥር ፩ሺ፪፻፹፫
P.O. Box 1283
TEL. 011 155 00 98
011 155 00 99
አዲስ አበባ
ADDIS ABABA
FAX 57-45-14

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የምሥራቅ ሸዋ ሀገረ ስብከት
Ethiopian Orthodox Tewahedo Church
Eastern Shoa Diocese Office

ቁጥር 1117/2005
ፖ.ሣ.ቁጥር 271
ስልክ ቁጥር 022 111 26 57
16/7 ቀን 2005 ዓ/ም

ለአዳሚ ቱሉ ወረዳ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት

ዝዋይ፤

አቶ ፍጹም ኩራባቸው ባልቻ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፎክሎር ትምህርት ክፍል ድህረ ምረቃ መርሐ ግብር ተማሪ ሲሆኑ ለመመረቂያ ጽሑፍ ዝግጅት እንዲረዳቸው በዝዋይ ደሴት ባሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ገዳማት ዙሪያ ጥናትና ምርምር ለማድረግ እንዲችሉ የትብብር ደብዳቤ እንዲጻፍላቸው ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በተጻፈ ደብዳቤ ጠይቀዋል።

ስለዚህ በ2000 ዓ.ም ስለቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ በተመለከተ ከልዩ ጽ/ቤት የተላለፈው መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ አመልካቹ ለጥናትና ምርምር በሚመጡበት ወቅት በእናንተ በኩል ትብብር እንዲደረግላቸው እናሳስባለን በማለት ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት በቁጥር 2533/5092/2005 በ13/06/2005 የተጻፈ ደብዳቤ ደርሶናል። ስለሆነም ከላይ በተላለፈው መመሪያ መሠረት አመልካቹ በዝዋይ ደሴት ባሉ ገዳማት ዙሪያ ጥናትና ምርምር ማካሄድ እንዲችሉ ትብብር ይደረግላቸው ዘንድ እናስታውቃለን።

ከመንፈሳዊ ሰላምታ ጋር//

መጋቤ ጥበብ ሙሉጌታ ቸርነት
የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ
M/T/ Mulugeta Cherinet
Manager of the Diocese

ግልባጭ

ለአቶ ፍጹም ኩራባቸው
ዝዋይ፤

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የአርሲ ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት
Ethiopian Orthodox Tewahido Church
Arsi Diocese Secretariat

ቍጥር 747/2005
Ref. No.

19 -ሰኔ ቀን 2005 ዓ.ም

Date ____________200______

ለቱሉ ጉዶ ደ/ጽ/ቅ/ ማርያም ገዳም ጽ/ቤት

ለጠደቻ አብርሃም ሰ/ጉ/ጽ/ቤት

ለፉንድሮ አርባእቱ እንስሳ ሰ/ጉ/ጽ/ቤት

አቶ ፍጹም ኩራባቸው ባልቻ በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ የዶክትሬት ትምህርት ክፍል ድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር ተማሪ መሆናቸውን በመጥቀስ ከላይ በተጠቀሱት በሶስቱ ደሴቶች ገዳማት ምርምር ለማድረግ እንዲችሉ በእኛ በኩል ትብብር እንዲደረግላቸው ከመንበረ ፓትርያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት በቁጥር 8533/5092/2005 በተጻፈ ደብዳቤ አሳስበውናል።

ስለዚህ ከላይ ሥማቸው የተጠቀሰው ግለሰብ በዝዋይ ደሴት ባሉት ገዳም ምርምር እንዲያደርጉ የተፈቀደላቸው በመሆኑ ተገቢውን ትብብር ታደርጉላቸው ዘንድ እናስታውቃለን።

ከመንፈሳዊ ሰላምታ ጋር

...ክ ገነት አዳነ በርሔ
የአርሲ ሀ/ስብከት ዋና
ሥራ አስኪያጅ
Melake Genet Adane Berhe
...al Manager

ግልባጭ

ለአቶ ፍጹም ኩራባቸው

ባሉበት

ስልክ ቁጥር
Tel. No. 022 331 17 04
022 331 17 05
022 331 10 36
የመልእክት ሣጥን ቁጥር 51
P.O. Box 51
ፋክስ 022 331 76 13
አርሲ
Arsi

# መግለጫ

ይህ የአርት ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፍ በየትኛውም ስፍራ ያልቀረበ የእኔ ወጥ ስራ ነው፡፡ ለጥናቱ በምንጭነት የተጠቀምኩባቸው መረጃዎች በተገቢ ሁኔታ መጠቀሳቸውን አረጋግጣለሁ፡፡

ፍጹም ኩራባቸው

ስም

ፊርማ

የማስረከቢያ ጊዜ፡- ታህሣስ/ 2006 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሙዩኒኬሽን ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የድህረ ምረቃ ትምህርት መርሃ ግብር

ታህሣስ፣ 2006 ዓ.ም

አዲስ አበባ